# ምህዳራዊ አስተሳሰብ ለዘላቂ ሃገራዊ መፍትሔ

ደስታ መብራቱ

የካቲት 2013

*በነፃ የተሰራጨ*

# ምህዳራዊ አስተሳሰብ ለዘላቂ ሃገራዊ መፍትሔ

ደስታ መብራቱ

የካቲት 2013

*© ደሰታ መብራቱ የካቲት 2013 ዓ.ም.*

*አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ*

*የደራሲው መብት በህግ የተጠበቀ ነው*

*All rights reserved*

የመጀመሪያው ህትመት: የካቲት 2013 ዓ.ም.

የሽፋን ገጽ ቅንብር: ዳግማዊ ደሰታ መብራቱ

*የዚህ የመጀመሪያ ዕትም 1500 መጽሃፍ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት፣ ቤተ መጻህፍት እና የሚዲያ አካላት በነጻ የሚሰጥ ሲሆን ከደራሲው የተጻፈ ፍቃድ ሳያገኙ መጽሃፉን በህትመትም ሆነ በዲጂታል መልኩ አባዝቶ ለሽያጭ ማቅረብ በህግ ያስጠይቃል።*

*ለተጨማሪ መረጃ እና ተግባቦት: Dmebratu57@gmail.com*

## *ምስጋና*

ለዚህ መጽሃፍ መጻነስ ዋነኛው መነሻ ከሐምሌ 2012 እስከ ጥቅምት 2013 በአዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ ባወጧኋቸው ጽሁፎች ላይ የተሰጡ አስተያየቶች ናቸው። ስለዚህም፣ የአዲስ አድማስ ጋዜጣ አዘጋጆችን እና አስተያየት የሰጡኝን ወገኖች ሁሉ በቅድሚያ አመሰግናለሁ። ከዚህ በመቀጠል፣ የመጽሐፉን ረቂቅ በማንበብ ጠቃሚ አስተያየት ለሰጡኝ ለአቶ በቀለ ባይሳ፣ አቶ ብርሐነ መዋ፣ ዶ/ር ጉልላት ከበደ፣ ዶ/ር ሰለሞን አበበ፣ ፕሮፌሰር ጌታቸው እንግዳ፣ አቶ ማሞ ደስታ እና አቶ ሙሉጌታ አምሐ ጥልቅ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። እንዲሁም፣ በጋዜጣ የወጡትንም ሆነ የዚህን መጽሃፍ ረቂቅ በማረም እና መጽሃፉ በተጻፈበት ወቅት አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠት ከፍተኛውን አስተዋጽኦ ያበረከተችውን ባለቤቴን ወይዘሮ መቅደስ ቦጋለን፣ ክብረት ይስጥልኝ እላለሁ። በመጨረሻም፣ የመጽሐፉን ሽፋን ያቀናበረውን እና ከመጽሐፉ ተደራሲያን ዋነኛው የሆነው የወጣቱ ትውልድ አካል የሆነውን ልጄን አቶ ዳግማዊ ደስታ መብራቱን አመሰግናለሁ።

## *መታሰቢያነቱ*

በአማርኛ የመጀመሪያዬ የሆነው ይህ መጽሃፍ፣
መልካምነትን፣ ዕውቀት መሻትን፣ ጥረትን፣ እና ጽናትን ላወረሱኝ ለአባቴ
***ለአቶ መብራቱ በላይ እና ለእናቴ ለእማሆይ ፅጌ ማርያም (ዘነበች) በየነ***
መታሰቢያ ይሁንልኝ።

# *ለቅምሻ*

የ1960ዎቹ ትውልድ እምነት እና ጽናት ዋነኛው ምንጭ በወቅቱ የነበረውን ድህነት፣ ኋላቀርነት፣ ጭቆና እና አድልዎ ‘ለምን’ ብሎ መጠየቁ እና ሁኔታውን ለመቀየር ቆርጦ መነሳቱ ነበር። ከዚህ ጋር ተያይዞ በየትኛውም ወገን ለተከፈለው መስዋእትነት ታላቅ ክብር አለኝ። ገጽ ነ

በምህዳራዊ አስተሳሰብ መሰረት አንድ ምህዳር ማለት የየራሳቸው ህልው ነባራዊነት ያላቸው የተለያዩ ቁሳዊ ነገሮች እና ባህርያት (attributes) የተደራጁበት የግንኙነት ስብስብ ነው። የምህዳራዊ ትንተናም ዋነኛው መለያው አንድን ውስብስብ ምህዳር በጥቅልነቱ ለመረዳት የሚያስችሉ መሰረታዊ ጥያቄዎችን መጠየቁ ነው። ገጽ ነ7

ባሁኑ ሰዓት አብዛኛው የፖለቲካ ንግግሮቻችን (discourses) ከሚዛናዊነት ይልቅ ስሜታዊነት፣ ከሩቅ አላሚነት ይልቅ ቅርብ አዳሪነት፣ ከአካታችነት ይልቅ አግላይነት ጎልቶ ይታይባቸዋል። ይህም፣ ሃገሪቱን ከዕለት ወደ ዕለት ወደ ተባባሰ ቀውስ እየከታት ይገኛል። ገጽ 22

ከሃገራዊው እውነታ ያልተጣጣሙ ጭፍን የአስተሳሰብ እመርታዎች፣ ለረጂም ዘመናት ተንሰራፍቶ የኖረው ባላባታዊ የፖለቲካ ባህል ቅሪቶች፣ እና ውስብስብ ለሆነው የሃገሪቱ የፖለቲካ ችግር የተቀነበቡ እና ቀላል የሆኑ (simplistic) መፍትሔዎች ለመሻት እና ለማራመድ የተደረጉ ጥረቶች የኢትዮጵያ የፖለቲካ ህመሞች ዋነኛ አእምሮአዊ ምንጮች፤ ናቸው። ገጽ 23

የሃገረ መንግሥት ምስረታ ፈተናችን ዋነኛው አስኳል በሁለት ልዩ ታሪካዊ ወቅቶች ከተራመዱ የአሃዳዊነት ሥርዓቶች ጋር በተያያዘ የተፈጠሩ የማንነት ቀውሶች (Identity crisis) ናቸው። ገጽ 45

የወንዳዊነት አስተሳሰብ ጎልቶ በሚታይበት የሃገራችን ፖለቲካ ውስጥ ያለውን ውስብስብ ችግር ለመፍታት በሚደረገው ጥረት የፖለቲካችንን ሴታዊነት ባህርይ ማጠናከር ይኖርብናል። ገጽ 62

በምህዳራዊ አስተሳሰብ መሰረት፣ በማናቸውም ህብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ ተቃራኒ ተረኮችን ወደ ዐይነታዊ የለውጥ ተረክ ማምጣት ያንን ማህበረሰብ በዘላቂነት ወደፊት ለማሻገር ቁልፍ እና አይነተኛ እርምጃ ነው። ገጽ 76

ሃገራችን ኢትዮጵያ ያለፉት ሶስት የኢንዱስትሪ አብዮቶች በተሳታፊነት ሳይሆን በበዩ ተመልካችነት አሳልፋለች። ከዚህ የበዩ ተመልካችነት እንድትወጣ ከተፈለገ፣ የሚወጡ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች፣ የአራተኛውን የኢንዱስትሪ አብዮት ፈተናዎችን በሚቀንስ እና እድሎቹን በሚያሰፋ መልኩ ሊቀረጹ እና ሊተገበሩ ይገባል። ገጽ 93

## *የይዘት ማውጫ*


ወፍ በረር ምልከታ 1
መቅድም 4
መግቢያ
1. አካባቢ፣ ሳይንስ እና ምህዳራዊ አስተሳሰብ 9
1.1 ሰው እና የተፈጥሮ ምህዳር 9
1.2 ቀውሶች እንደ ዕውቅት ምንጮች 11
1.3 የፍልስፍናው ሽግግር 13
1.4 የምህዳራዊ አስተሳሰብ መሰረቶች 16
1.5 ምህዳራዊ አስተሳሰብ እና ሃገር በቀል ዕውቀት 19

2. ፖለቲካችን በምህዳራዊ ዕይታ 24
2.1 የፖለቲካችን ዋነኛ ህመሞች 26
2.2 የምህዳራዊ አስተሳሰብ ዓበይት መርሆዎች 29

3. መዋቅራዊ ችግሮቻችን ከምህዳራዊ እይታ አኳያ 36
3.1 የፖለቲካችን መዋቅራዊ ችግሮች 36
3 2 ዳሩን መሃል የማድረግ ፖለቲካ 40

4. ማንነት እና የዳያስፖራው ፖለቲካ 47
4.1 የማንነት ቀውስ እና የኢትዮጵያ ፖለቲካ 47
4.2 ዳያስፖራው እና የኢትዮጵያ ፖለቲካ 53

5. ሴታዊነት፣ ለኢትዮጵያ ፖለቲካ ጤናማነት 61
5.1 ሴታዊነት እና የኢትዮጵያ ፖለቲካ 61
5.2 ኢትዮጵያ ብዙ ሙፈሪያቶች ያስፈልጓታል 66

6. ተረኮች እና ብሔራዊ መግባባት 72
6.1 ከተዓብዮ ወደ ዓይነታዊ የለውጥ ተረክ ለመሻገር 73
6.2 ችግሩን ከሥሩ ለመንቀል፣ መዋቅራዊ ምንጩን ማድረቅ 79
6.3 ለብሔራዊ መግባባት ውይይት ውጤታማነት 84

7. አካታች እና ዘላቂ ልማት 92
7.1 አጠቃላይ የዘላቂ ልማት ፈተናዎች 93
7.2 ብሔራዊ የልማት ፈተናዎቻችን እና መፍትሔዎቻቸው 97
7.3 የዘላቂ ልማት ዕድሎቻችን 101
ማጠቃለያ 109
ተጨማሪ ንባቦች 111

# *ወፍ-በረር ምልከታ*

በደራሲው የተሟላ ህይወት (fulfilling life) እሳቤ መደነቅ የጀመርኩት ከጥቂት ዓመታት በፊት በርካታ ጥቅማጥቅሞች የታጨቁበትን፣ በተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም የያዘዉንና ሊያገኝ ይችል የነበረዉን ከፍተኛ የኃላፊነት ቦታ በቃኝ ብሎ ለመሰናበት የመልቀቂያ ደብዳቤ ማስገባቱን ሲነግረኝ ነበር። ጤናውን የተጠራጠርን ያኔ በናይሮቢ በተለያዩ የመንግስታቱ ድርጅት ተቋማት ዉስጥ የምንሰራ ኢትዮጵያዊያንና ሌሎች ጓደኞቹ ጥቂት አልነበርንም። ከቁሳዊ ስኬት ባሻገር ብዙ ዋጋ ያላቸዉ፣ ለወጣበት ህብረተሰብ ወረታ መመለስን ታሳቢ ያደረጉና ቀጣይ በሆነ አኳኋን ለመጭዉ ትዉልድ የረዥም ጉዞ ስንቅ የሚሆኑ የብዙ ህልሞች ባለቤት እንደሆነ ያስተዋልነው ናይሮቢን ከለቀቀ በኋላ የሚሰራቸዉን ስራዎች ስናይ ነው ። ይህ መፅሀፍ ከነዚህ ህልሞች አንዱ መሰለኝ። ከህልሞቹ አንዱን በማሳካቱም ዉጭ ሃገር የተወለደችዉና ያደገቺው ልጇ ዲቦራ ነፍሷን ሐሴት ሲሞላት እንደምትለው ደራሲዉን “እሰይ የኛ ነበዝ” ልለው ወደድሁ።

ከተለመደው ወጣ ያለ ጭብጥ ይዞ መነሳቱ የመፅሀፉ አንዱ ፋና ወጊ ገፅታው ይመስለኛል። የተወሳሰቡና ሙያዊ የሆኑ የምህዳራዊ አስተሳሰብ አላባዊያንና ተግባራዊ አንድምታቸዉን በሃገራዊ ሁነቶች መመንዘሩና ቀላልና ጣፋጭ በሆነ አቀራረብ መቀመሩ ደራሲዉ ብዙ ትጋትን የጠየቁ ሰፊ ማብሰልሰልንና መብሰልሰልን ያካተቱ ረዣዥም የሃሳብና የምጥ ሌሊቶች እንደነበሩት ይጠቁማል። ከሁሉ በላይ የምህዳራዊ አስተሳሰብ የተጠየቅ ስልትን ከወቅታዊ ሁኔታ ጋር አሰናስሎ ዛሬም ላልተገታው ማህበረሰባዊ ዉድቀታችን መፍትሄ ይሆናሉ ያላቸዉን ሃሳቦች ስፋት ላለው የሃገራችን ህዝብ ተደራሽ አድርጎ ማቅረቡ ደራሲዉን ከበርካታዎቹ ዓይናአፋር ልሂቃቻችን ለየት አድርጎ ያቆመዋል። ይህ ምህዳራዊ አስተሳሰብን ከሃገራዊ ማዕቀፍና ጭብጥ ጋር ያዋደደበት እና የልፋቱ ትሩፋት የሆነው መፅሀፍ፣ ውይይቶችን የሚያጭር እና ለሃገራችን መቀጠል ሲባል ተረኮቻችንን እና ዕሴቶቻችን የተዋቀሩባቸውን ጡቦች እንደገና እንድንነበሯቸው የሚያበረታታ፣ ለተግባቦትና ለመግባባት ጥቂት የማዕዘን ድንጋዮችን የሚያቀብል ድርሳን ያደርገዋል ብዬ አስባለሁ። በእነዚህ ላይ የታነፁ የአመለካከት ሽግግሮች ዕዉን ቢሆኑ፣ ያለውን እንካችሁ በማለቱ ከሚሆነው በላይ በአማርኛ የበኩር ልጇ ባለውና በእኔ ዕይታ እጅግ ተነባቢና ጠቃሚ በሆነው መፅሀፉ ጥልቅ እፎይታ የሚሰማዉ ይመስለኛል።

ደራሲው በቅንፍ ዉስጥ በእንግሊዝ አፍ ያመላከታቸው አንዳንድ ጉዳዮች ለተጨማሪ ንባብ መንደርደሪያ የሚሆኑ ቁልፎች (key words) ማስቀመጥን መነሻ ያደረጉ ሳይሆኑ አይቀርም ። እነዚህን በመጠቀም፣ ደራሲዉ በተለይ ሊደርስ የፈለገው አዲሱ ትውልድ ያለማመንታት ተጨማሪ ንባብ በማድረግ፣ በምህዳራዊ አስተሳሰብ ለመራቀቅ፣ የሃገሩን ዉጣዉረዶች በአዲስ መነፅር ለማየትና ለመተንተን አዲስ የምናብ ፍኖት የቀደደ ይመስለኛል - መፅሀፉ።

***ዶ/ር ሰለሞን አበበ***፣ የተባበሩት መንግስታት አቶሚክ ኢነርጂ ተቋም

ሁሉም አንዳቅሙ የሃገሩ ጉዳይ ያሳስበዋል ተብሎ ቢገመት ከዕውነተኛነት ብዙም አይራቅም። ሃገራዊ ችግርን ስናብሰለስል፣ ስሜትና ምኞታችን ትንታኔያችንን እና አቋማችንን ይጫኑታል። ከዚህ ተነስተን የምንደርስበት ውሳኔም ካለንበት አዙሪት አላወጣንም። ፕሮፌሰር ደስታ ሙብራቱ ይህን በመገንዘብ ነው ከስሜታዊነት ወጥተን፣ ምኞታችንንም ምክንያታዊ አድርገን እንድናስተውል የሚመክረን። በግሉ በሚያደርጋቸው ውይይቶችና በጽሁፍ በሚያቀርባቸው ሃሳቦች የሚጠቀምበትን ሳይንሳዊ ዘዴ ሊያካፍለን ይህችን 'ምህዳራዊ አስተሳሰብ ለዘላቂ ሃገራዊ መፍትሔ' የምትል መጽሐፍ አቅርቦልናል።

በመጽሐፉ ውስጥ የምህዳራዊ አስተሳሰብን ታሪካዊ አመጣጥና ምንነት ለአብዛኛው አንባቢ ሊገባ በሚችል መልኩ አቅርቦታል። ይህ ሳይንሳዊ የውስብስብ ችግሮች መፍቻ ዘዴ ለተለያዩ የህይወት ዘርፎች የሚያገለግል በመሆኑ፣ ለህበረተሰብና ለሃገራዊ ፖለቲካ ችግሮቻችን መፍቻም ሊሆን እንደሚችል በምሳሌዎች አስደግፎ ያሳየናል። በሳይንሳዊ ሙያው ያካበተውን ዕውቀት፣ በማስተማር ሙያው የተጠቀመበትን ዘዴ፡ በግል ህይወቱ የሚተገብረውን አስተዋይነት በዚህ መጽሃፍ ውስጥ በሚገባ አንጸባርቋል፡፡ የቃላት አጠቃቀሙ ግልጽነት እንዲኖረው አስፈላጊ በሆነው ቦታ ሁሉ ለመግለጽ የሚያስቸግሩ የእንግሊዝኛ ቃላትን የአማርኛ ትርጉም እንዲያገኙ አድርጓል፡፡ በመሆኑም፣ ያልተለመዱ ሳይንሳዊ ቃላት ተብራርተው እናገኛለን፡፡ መጽሃፉ ለንባብ ብቻ ሳይሆን ለመማሪያም ሰለሆነ በያንዳንዱ ምዕራፍ ማጠቃለያ ላይ ዋና ዋና ነጥቦቹ ባጭሩ ቀርበዋል፡፡

በመሆኑም፣ በተለይም ወጣቶች፣ ፖለቲከኞች፣ የፖለቲካ ተንታኞች፣ እና በማንኛውም የስልጣንና የሃላፊነት ደረጃ ላይ ያሉ ግለሰቦች ከመጽሐፉ በርካታ ቁምነገሮችን እንደሚያገኙ እገምታለሁ፡፡ በተለይ ሃገራችን ባሁኑ ጊዜ ያለችበትን የተወሳሰበ ሁኔታ አቅጣጫ ማስያዝ ሃላፊነቱ ለተጣለባቸው ወገኖች ሁሌ ከስሜትና ከምኞት በመራቅ እና ምህዳራዊ አስተሳሰብን በመጠቀም መፍትሄ እንዲያገኙ የፕሮፌሰር ደስታ መብራቱ መጽሐፍ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

***አቶ ብርሐነ መዋ፣*** *ሜሪላንድ፣ አሜሪካ*

እውቁ የኢኮኖሚክስ ባለሙያ ዶ/ር እሸቱ ጮሌ በ1984 ባቀረበው አንድ ጥናታዊ ጽሁፍ፣ ሃገሪቱ ሌላ መልካም የለውጥ አጋጣሚ ላይ እንደምትገኝ አውስቶ ይህንን የለውጥ ዕድል ማበላሸት በታሪክ ታላቅ ተወቃሽ እንደሚያደርገን አስጠንቅቆ ነበር። ከሰላሳ ዓመታት በኋላ በሌላ የለውጥ አጋጣሚ ላይ ከተመሳሳይ ሃገራዊ ጥያቄዎች ጋር ተፋጠን እንገኛለን። ፕሮፌሰር ደስታ፣ በምህዳራዊ አስተሳሰብ በመቃኘት ውስብስብ ችግሮቻችንን በአግባቡ መረዳት እና ወደ ዘላቂ መፍትሔ ማምራት እንደምንችል በዚህ መጽሐፍ አሳማኝ በሆነ መንገድ አቅርቦልናል። በዚህ ረገድ መጽሐፉ፣ ፊት ለፊታችን የተድቀኑብንን ፈተናዎች ለመሻገር ከሚኖረው አበርክቶት ባሻገር ለመጪው ትውልድም ታላቅ ትምህርታዊ ፋይዳ ይኖረዋል።

***ዶ/ር ጉልላት ከበደ፣*** *ኒው ሰኩል፣ አሜሪካ*

ይህ መጽሐፍ እጅግ በጣም የሚያሳስበንን የወቅቱን የሃገራችንን ጉዳይ እስከአሁን ድረስ ሲቀርቡ ከነበሩት ፖለቲካዊ አቀራረቦች ወጣ ባለ ሁኔታ አዲስ፣ ሁለንተናዊና ሳይንሳዊ በሆነ የአመለካከት ስልት (ምሕዳራዊ አስተሳሰብ) ትንታኔ የሚያቀርብ ነው። በመጽሐፉ የቀረቡት ትንታኔዎች የሃገራችንን የወቅቱን የፖለቲካ ቀውስ እና የኢኮኖሚ ችግሮች ከምሕዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ በመተንተን የመፍትሔ አቅጣጫዎችንና ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች ያሳያሉ። የመፍትሔ አቅጣጫዎቹ የተሳሳቱ አመለካከቶችን በአሳማኝና ሐቀኛ ምክንያቶች በመሞገትና ገንቢና አካታች የሆኑትን በማሳየት የቀረቡ ስለሆኑ ብዙዎችን ሊያግባቡ ይችላሉ የሚል ዕምነት አለኝ። በመሆኑም ሁሉም የአገራችን የፖለቲካ ተዋናዮችና መጪው ጊዜ የሚያሳስባቸው ወገኖች ሁሉ መጽሐፉን እንዲያነቡትና ተገቢውን ትምህርት ወስደው ለሃገራችን የሰላምና የዴሞክራሲያዊ ሽግግር አስፈላጊ ለሆነው ለብሔራዊ መግባባት ጥረት እንዲጠቀሙበት ለማሳሰብ እወዳለሁ። ፕ/ር ደስታ ይህን ከቀውስ መውጫ አዲስ አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን አዲስ የአማርኛ ቃሎችን ጭምር ስለሰጡን ሊመሰገኑ ይገባል።

***አቶ በቀለ ባይሳ፣*** *የምክር ሥራ ባለሙያ፣ አዲስ አበባ*

አገራችን በአንድ ገጹ እንደ መልካም ኣጋጣሚ በሌላው ደግሞ በስጋት የሚታይ የለዉጥ ማዕበል ዉስጥ ባለችበት በአሁኑ ወቅት ፕሮፌሰር ደስታ ይህን ወቅቱን የጠበቀ መጽሃፍ ለአንባቢው አበርክተዋል። መጽሃፉ ለየት ያለ ትንተናና ኣቀራረብ ያለዉና ላለንበት ኣገራዊ ችግር ጠቃሚ የመፍታሔ ሃሳቦች ያዘለ ቢሆንም “…. ትንተናዎቹም ሆነ የመፍትሔ ሃሳቦቹ ከአመላካችነት የዘለለ ድርሻ እንዳይሰጣቸው ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፤ በመሆኑም በመጽሃፉ ዉስጥ የቀረቡትን ሃሳቦች ይበልጥ መፈተሽ እና ተለዋዋጭ ከሆነው ሀገራው እና ዓለም ኣቀፋዊ እውነታ ጋር ኣዛምዶ መተንተን ከሁሉም ወገን የሚጠበቅ ድርሻ ይሆናል” ይለናል ፕ/ር ደስታ በተለመደው ሙያዊ ትህትናው።

***አቶ ሙሉጌታ አምሀ፣*** *ቪየና፣ ኦስትሪያ*

## *መቅድም*

የዚህን መጽሐፍ ርዕስ የሚመለከቱ ፖለቲከኞች እና የፖለቲካ ተንታኞች በቀዳሚነት የደራሲውን ማንነት ለማወቅ እንደሚፈልጉ እገምታለሁ፡፡ የሙያ ማንነቴን በተመለከተ የዘመናችን በይነ-መረብ ያለብዙ ድካም በቂ መረጃ እንደሚሰጣቸው አምናለሁ። የፖለቲካ 'የጀርባ ታሪኬን' በሚመለከት ግን ብዙ እንዳይቸገሩ ስለራሴ በጥቂቱ ልግለጽ፡፡ የልጅነት ዘመኔ አስተሳሰብ የተቃኘው በአብዛኛው ባካባቢዬ ከምታዘባቸው ማህበራዊ ጭቆናዎች እና በተለያየ ወቅት ከአባቴ ከአቶ መብራቱ በላይ ጋር በማደርጋቸው ጭውውቶች ላይ የተመሰረቱ ነበሩ። ያም ሆኖ፣ በተማሪው እንቅስቃሴ ውስጥ ከአጫፋሪነት የዘለለ ድርሻ አልነበረኝም። በ1966 ዓም በወቅቱ ስሙ ናዝሬት በአሁኑ ስሙ አዳማ በሚገኘው የአፄ ገላውዴዎስ ትምህርት ቤት የ12ኛ ክፍል ተማሪ ነበርኩ። ይህንን ተከትሎ የመጣው የእድገት በህብረት የዕውቀት እና የሥራ ዘመቻ በወቅቱ የነበረኝን የፖለቲካ አመለካካትም ሆነ አጠቃላይ የህይወት እይታ በመሰረታዊ መልኩ የቀየረ ሁነት ነበረ። ከአስራ ሰባት እስከ ሃያ አንድ ዓመት እድሜዬ ድረስ፣ ከወጣት እና የሰራተኛ ማህበር መሪነት እስከ ቀበሌ ሊቀመንበርነት እና የክፍለ ሃገር የፖለቲካ ሃላፊነት የደረሰ ንቁ የፖለቲካ ተሳትፎ ነበረኝ። በነዚሁ ዓመታት ውስጥ፣ በቀዳሚነት በኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ (ኢህአፓ) ተባባሪነት ሶስት ጊዜ እና በኋላም በማርክሳዊ ሌኒናዊ ሪቮሉዩሽናዊ ድርጅት (ማሌሪድ) አባልነት ሁለት ጊዜ በአስራ አራት የተለያዩ እስር ቤቶች ቆይታ አድርጌአለሁ። በመጨረሻም፣ የአስር ዓመት እስራት ተፈርዶብኝ በ1975 ህዳር ወር 'በምህረት' እስከተፈታሁበት ጊዜ ድረስ በወህኒ ቤት ታስሬአለሁ። በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የነበረኝ ንቁ እና ቀጥተኛ ተሳትፎ በዚሁ አብቅቷል ማለት ይቻላል።

ከላይ በተጠቀሰው መሰረት፣ እኔም አንዳንድ የአሁኑ ዘመን ፖለቲከኞች እና ተንታኞች ሊወቅሱት የሚዳዱት የዚያ ትውልድ አባል ነኝ። የዚያ ትውልድ እምነት እና ጽናት ዋነኛው ምንጭ በወቅቱ የነበረውን ድህነት፣ ኋላቀርነት፣ ጭቆና እና አድልዎ 'ለምን' ብሎ መጠየቁ እና ሁኔታውን ለመቀየር ቆርጦ መነሳቱ ነበር። ከዚህ ጋር ተያይዞ በየትኛውም ወገን ለተከፈለው መስዋእትነት ታላቅ ክብር አለኝ። በዚያው መጠን ግን፣ የየራሳችንን ፖለቲካ መሪዎች የሚገባውን ያህል 'ለምን' ብለን አለመጠየቃችን ብዙ ዋጋ እንዳስከፈለን ይሰማኛል። ምንም እንኳን ሁሉም እስራቶቼ ይህንኑ ጥያቄ ከማንሳቴ ጋር የተያያዙ ቢሆንም፣ የዚያ ትውልድ አባል የሆን ሁላችንም በበቂ ሁኔታ ባለመጠየቃችን ለተከተለው ቀውስ የየድርሻችንን ኃላፊነት ልንወስድ ይገባል። ከአስር ዓመታት የፖለቲካ እና የእስር ህይወት በኋላ፣ በ1966 ወዳቆምኩት ትምህርት በመመለስ የኬሚካል፣ ኢንዱስትሪ እና አካባቢ ምህንድስናን በማጥናት ላለፉት ሰላሳ ሁለት ዓመታት ለተለያዩ ድርጅቶች፣ ዓለም አቀፍ ተቋማት እና ዩኒቨርሲቲዎች ሰሰራ ቆይቻለሁ።

እንደመታደል ሆኖ፣ የሙያ ህይወቴም በዘመናችን ገኖ ያለው ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት (globalization) በምድራችን የተፈጥሮ ሚዛን ላይ የሚያስከትለውን መዛባት 'ለምን' ብሎ በመመርመር፣ ሁሉንም አካታች የሆነ ዘላቂ ልማት ለማምጣት የሚያስችሉ መፍትሔዎችን ማፈላለግ ላይ የሚያተኩር ሆኗል። በዚህ ሂደትም ውስጥ፣ ውስብስብ ችግሮችን ባግባቡ ለመረዳት እና መፍትሔ ለመሻት ምህዳራዊ አስተሳሰብ (systems thinking) ያለውን አበይት አስተዋጽኦ ለመገንዘብ እና ለመረዳት ችያለሁ።

ዛሬ በሃገራችን ያለውን የፖለቲካ ምስቅልቅል ስንመለከት፣በቀዳሚነት በማናቸውም ወገን ለሚወሰዱ የፖለቲካ አቋሞች እና እርምጃዎች 'ለምን' የሚለውን ጥያቄ አንስቶ ከመመርመር ይልቅ አብዛኞቻችን አንድን የፖለቲካ አመለካከት በጅምላ እና በጭፍንነት መደገፍ ይታይብናል። ጥቂቶች የሚጠይቁ ቢኖሩም፣ አብዛኞቹ ውስብስብ የሆነውን የፖለቲካ መስተጋብር ወደ ጥቂት የአመክንዮ ሰበዞች የማቀናነስ አዝማሚያ (simplification) ይታይባቸዋል። እንዲህ አይነቱ አዝማሚያዎች በተለይም ወጣቱን በስሜታዊነት በማነሳሳት አስፈላጊ ወዳልሆነ የእልቂት አዙሪት ሲመሩት ይታያሉ። ባለፉት ሰላሳ ዓመታት ምንም ዓይነት ቀጥተኛ ተሳትፎ ባይኖረኝም፣ 'ለምን' የሚለውን ጥያቄ ባገኘሁት የተናጠል አጋጣሚ ሁሉ እንደ ዜጋ ማንሳቴ አልቀረም።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሃገራችን እየበረታ የመጣው የፖለቲካ ምስቅልቅል እያሳሰበኝ በመምጣቱ፣ በዋና ዋና ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ ምሁራዊ ሃሳቦችን በአዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ እንዳጋራ አድርጎኛል። እነኝህን ጽሁፎች የተከታታሉ እና በጽሁፎቹ ላይ ተመርኩዞ በጥቂት ሚዲያዎች የቀረቡትን ውይይቶች ያዳመጡ ኢትዮጵያውያን፣ ጽሁፎቹ በመጽሀፍ መልክ ተደራጅተው እና ዳብረው ቢቀርቡ አመለካከቱ በይበልጥ ለህዝብ፣ በተለይም ለወጣቱ ትውልድ ተደራሽ እንዲሆን ያደርገዋል የሚል ሃሳብ ሰንዝረዋል። ይህንን መሰረት በማድረግ የምህዳራዊ አስተሳሰብ ታሪካዊ አመጣጥ እና ዋና ዋና እሳቤዎቹን በማቅረብ እና ቀደም ሲል በጋዜጣ የወጡትን ጽሁፎች ይበልጥ በማብራራት በመጽሀፍ መልክ ተደራጅቶ ቀርቧል።

በዚህ መጽሃፍ ውስጥ የተካተቱ ሃሳቦች በወጣትነት ዘመኔ በነበረኝ የፖለቲካ እይታ እና በንልማሳነት ከኖርኩበት የአካዳሚ እና ዓለም አቀፍ የስራ መስክ በተቀሰሙ የሙያ ልምዶች የተቃኙ በመሆናቸው የራሳቸው ውሱንነት እንደሚኖራቸው እገምታለሁ። ይህ ውሱንነት እንዳለ ሆኖ፣ በተለይ ወቅቱ ለሚጠይቀው የብሔራዊ መግባባት ውይይት የራሱን ድርሻ ያበረክታል የሚል እምነት አለኝ። ከዚህ በተጨማሪም፣ ወጣቱን ትውልድ ዘመኑን ከሚመጥን የዕውቀት መስክ ጋር በመጠኑ በማስተዋወቅ የምክንያታዊ ጠያቂነት (critical thinking) ባህልን እንዲያዳብር ያግዛል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

# *መግቢያ*

*ዘመናዊው ፖለቲካ በኢትዮጵያ መቀንቀን ከጀመረበት ከ1950ዎቹ ጀምሮ፣ ሃገራችን ኢትዮጵያ እና ህዝቦቿ በበርካታ የፖለቲካ ውጣ ውረድ ውስጥ አልፈዋል። ባለፉት ስልሳ ዓመታት የተፈጠሩ የተለያዩ የፖለቲካ ሁነቶች እና የለውጥ አጋጣሚዎች የተሻለ የፖለቲካ ሥርዓት ለመፍጠር ከማስቻል ይልቅ ለበርካታ የሀገሪቱ ዜጎች መሞት እና መፈናቀል ምክንያት ሆነው አልፈዋል። ባለፉት ጥቂት የሽግግር ዓመታትም፣ ይህ አሳዛኝ ሁኔታ ተባብሶ ሃገሪቱን ለበለጠ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ቀውስ አጋልጧታል። ውስብስብ የሆነውን ሃገራዊ የፖለቲካ ህመሞቻችንን ባንድ አቅጣጫ በተቀነበበ ትንተና ለመረዳት እና ቀላል መፍትሔ ለመሻት የሚደረገው ጥረትም ችግሩን በይበልጥ እያወሳሰበው በመሄድ ላይ ይገኛል። በነዚህ ሂደት ውስጥ የጉዳቱ ከፍተኛ ገፈት ቀማሽ የነበረው በየዘመኑ የነበረው ወጣት ትውልድ ሲሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ህጻናት እና ሴቶችም የቀውሱ ቀጥተኛ ተጠቂ እየሆኑ መጥተዋል። የአጠቃላይ ህብረተሰቡም የዕለት ተዕለት ኑሮ ከድጡ ወደማጡ እንዲያሽቆለቁል አድርጎታል።*

*በሃያኛው ክፍለ ዘመን የታየው እጅግ ፈጣን የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ እና ኢንዱስትሪ እድገት በቢሊዮን ለሚቆጠሩ የዓለም ህዝቦች ከድህነት መላቀቅ መሰረት መሆኑ እሙን ነው። በሌላ በኩል ግን ይኸው እድገት ለበርካታ ውስብስብ ኢኮኖሚያዊ፣ አካባቢያዊ፣ ማህበራዊ፣ እና ፖለቲካዊ ፈተናዎች ምንጭ ሊሆን ችሏል። ይህም፣ በርካታ የዓለማችንን ህዝብ ወደከፋ ድህነት ከመግፋት አንስቶ ለዓለማችን ከፍተኛ ስጋት የሆነውን የተፈጥሮ ሚዛን መዛባት እና የምድራችን ሙቀት መጨመርን ያካትታል። ከዚህ ጎን ለጎን፣ የዓለማችን ህዝብ ብዛት በብዙ እጥፍ መጨመር ፈተናውን ይበልጥ እያወሳሰበው ነው። እነኚህን ፈተናዎች በልዩ ልዩ የሳይንስ መስኮች በተደረጉ ምርምሮች ለመረዳት እና ለመፍታት ጥረት ቢደረግም ችግሮቹ ይበልጥ እየተባባሱ እና እየተወሳሰቡ ከመሄድ ሊገቱ አልቻሉም።*

*ምህዳራዊ አስተሳሰብ (systems thinking) እንዲህ አይነት ውስብስብ ችግሮችን በአግባቡ ለመረዳት እና መፍትሄ ለመሻት ከ1950ዎቹ ጀምሮ እየዳበረ የመጣ የልዕለ-ዘርፍ (transdisciplinary) ሳይንስ ነው። እንደ ልዕለ-ዘርፍ ሳይንስነቱ የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ሳይንስ ተብሎ ቢጠቀስም፣ ምህዳራዊ አስተሳሰብ ለማንኛውም ሰው በተፈጥሮ ከሚሰጥ ክህሎት ጋር በጥብቅ የተሳሰረ በመሆኑ ሁላችንም ልናዳብረው የምንችለው አስተሳሰብ ነው። ለዚህም ማረጋገጫው፣ ምንም ዓይነት ዘመናዊ ትምህርት ሳይኖራቸው እዚሁ በሃገራችን በተለያየ ወቅት ከበርካታ ማህበረሰቦች መሃል ወጥተው የነበሩ እና ውስብስብ ማህበራዊ እና አስተዳደራዊ ችግሮችን ሲፈቱ የኖሩ አስተዋይ ሰዎች መኖራቸው ነው። የዚህን አስተሳሰብ መሰረታዊ ይዘት ለመረዳት እንዲረዳ፣ የምህዳራዊ አስተሳሰብ መሰረታዊ መነሻዎች እና መርሆዎች በመጽሐፉ የመጀመሪያው ክፍል ቀርበዋል። ይኸው ክፍል፣ ምህዳራዊ አስተሳሰብ ከሃገር በቀል እውቀቶች ጋር ያለውን ትስስርም ያሳያል።*

በመጽሐፉ ሁለተኛው ክፍል፣ ላለፉት ስልሳ ዓመታት በሀገራችን ሰፍኖ የቆየውን እና በአሁኑ ወቅትም ያለውን የፖለቲካ ህመም እና ምስቅልቅል ዋነኛ መሰረታዊ የአመለካከት ችግሮች ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ ለማመላከት ተሞክሯል። በተጨማሪም፣ ዛሬ ያሉብንን ዋና ዋና የፖለቲካ መሰረታዊ ህመሞች እና መዋቅራዊ ችግሮቻችን ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ በመተንተን እነኚህን ችግሮች ከምንጫቸው ለማድረቅ የሚያስፈልጉንን ዐበይት የአመለካከት ሽግግሮች በማያያዝ ቀርቧል።

ከዚህ ቀደም በጋዜጣ ላይ የወጡት ጽሁፎቼ በዋነኝነት ያተኮሩት የሃገሪቱን ዋነኛ የፖለቲካ ጥያቄዎች ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ በመተንተን ለፖለቲካ መሪዎች እና ተንታኞች ጠቋሚ ሃሳቦችን ማቅረብ ላይ ነበር። ሌላው፣ ከፖለቲካዊው ፈተናችን ጋር በጥብቅ የተሳሰረው እና ምናልባትም ለሃገሪቱ ዘላቂ ሰላም እና ለህዝቡም ሁለንተናዊ ደህንነት (Wellbeing) ከፍተኛ ፈተና የሆነው አብይ ጉዳይ በሃገሪቱ ተንሰራፍቶ የሚገኘው የኢኮኖሚ ኋላ ቀርነት እና ድህነት ነው። ይህ ሁኔታ እጅግ በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ከመጣው የህዝብ ቁጥር እድገት እና ስራ አጥ ወጣት ቁጥር ጋር ተዳምሮ ዘላቂ ልማት ለማምጣት የሚደረገውን ጥረት እጅግ ፈታኝ አድርጎታል።

በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን እየገነነ የሚመጣው የዲጂታል ኢኮኖሚ ተጽእኖም በማደግ ላይ ያሉ ሃገሮችን የልማት ጥረት ይበልጥ ፈታኝ እንዲሚያደርገው ይጠበቃል። ያም ሆኖ ግን፣ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በማደግ ላይ ያሉ ሃገሮች ሃገራዊውን የተፈጥሮ እና የሰው ሃብት ከዓለም አቀፋዊ እድሎች ጋር በብልሃት እና በእውቀት የሚያስተሳስሩ ፖሊሲዎች መተግበር እስከቻሉ ድረስ አካታች እና ዘላቂ ወደሆነ የኢኮኖሚ ልማት ለመስፈንጠር (leapfrog) የሚያስችል እድል ይኖራቸዋል። በዚህ መጽሐፍ ሶስተኛው ክፍል፣ የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የኢኮኖሚ ልማት አቅጣጫዎች የሚወስኑትን አበይት ገፊ ምክንያቶች (drivers) በመተንተን እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በማደግ ላይ ያሉ ሃገሮች በሚያወጧቸው የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ትኩረት ሊሰጧቸው የሚገቡ አበይት ነጥቦችን ያመላክታል።

ምንም እንኳን ይህ መጽሀፍ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ተደራሽ እንዲሆን ቢፈለግም በአበይትነት የተጻፈው ግን ለወቅቱ የሃገራችን ፖለቲካ ተዋናዮች እና ለሃገራችን ወጣቶች መሆኑን ለመግለጽ እፈልጋለሁ። የዚህ ዋነኛው ምክንያት፣ የፖለቲካ ተዋናዮቻችን በአብዛኛው ወደ ኋላ (rear-view mirror) እየተመለከቱ ሃገር ለመምራት ከመሞከር ይልቅ ወደፊት ለመመልከት የሚያስችላቸው ግንዛቤ መስጠት እና ወጣቱን ትውልድ በህብረተሰባችን ውስጥ ተንሰራፍተው ካሉ የተዛቡ አመለካከቶች ማላቀቅ ወሳኝ በመሆኑ ነው። ከዚህ በተጨማሪ፣ የወጣቱ ትውልድ በምህዳራዊ አስተሳሰብ መታነጽ ሃገራችን በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ለሚያጋጥሟት የኢኮኖሚ፤ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊ እና ፖለቲካዊ ፈተናዎች የሚኖራትን ዝግጁነት የሚወስን እንደሚሆን በማመን ነው።

ለዚህም እንዲረዳ፣ በያንዳንዱ ክፍል መዝጊያ ላይ የየክፍሉን ቁልፍ ሃሳቦች ባጭሩ ለማቅረብ ተሞክሯል። እነኚህን ቁልፍ ሃሳቦች በቅድሚያ ማንበብ፣ አንባቢዎች የመጽሃፉን ዋነኛ ጭብጦች እንዲገነዘቡ እና ዝርዝር ሃሳቦቹንም በደንብ ለመረዳት እንዲችሉ ያግዛል ተብሎ ይታመናል። በተጨማሪም፣ የመጽሀፉ የመጀመሪያ እትም ለፖለቲከኞቻችን እና ለወጣቱ ትውልድ ተደራሽነቱን ለሚያረጋግጡ ተቋማት፣ ሚዲያ እና የማህበረሰብ አንቂዎች በነጻ እንዲዳረስ ይደረጋል። በመጨረሻም፣ በዚህ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱት የምህዳራዊ አስተሳሰብ መርሆዎች በማናቸውም የህይወት እና ሙያ ዘርፍ ተግባራዊ የሚደረጉ በመሆናቸው፣ አንባቢዎች እነኚህን መርሆዎች ለግልም ሆነ ለሙያ ህይወታቸው እንዲጠቀሙባቸው ይመከራሉ።

# 1. አካባቢ፣ ሳይንስ እና ምህዳራዊ አስተሳሰብ

## 1.1 ሰው እና የተፈጥሮ ምህዳር

የሰው ልጅ በቀደምት አናኗሩ፣ እንደማንኛውም በምድራችን እንደሚገኙ ፍጡራን ህልውናው ባካባቢው በነበረው የተፈጥሮ ምህዳር ሙሉ ቁጥጥር ስር እንደነበር ታሪክ እና ሳይንስ ያረጋገጠው ጉዳይ ነው። ያም ሆኖ፣ የሰው ልጅ አካባቢውን ለማወቅ እና ለመረዳት ያለውን ልዩ ጉጉት (curiosity) መሰረት በማድረግ በህይወቱ ውስጥ ያሉ አበይት ተፈጥሮአዊ ኡደቶችን (natural cycles) ለመረዳት ሲታትር ቆይቷል። በዚህም ጥረቱ፣ ባካባቢው የሚገኙትን የተፈጥሮ ሃብቶች ለህይወቱ ቀጣይነት በሚጠቅም መልኩ ከመገልገል ባሻገር በአጥናፈ-ሰማይ (the universe) ውስጥ የሚገኙትን ዋና ዋና የኃይል እና ኡደት ምንጮችን ለመገንዘብ ሙከራ አድርጓል። ይህንን መነሻ በማድረግም፣ ፀሐይን እና በዙሪያዋ የሚገኙ ፕላኔቶችን በመለየት ከነርሱ ጋር የነበረውን ግንኙነት በተለያየ መልኩ ለራሱ እንደሚጠቅም ኡድርጎ ለመቃኘት ሞክሯል። በዓለማችን ቀደምት ከሆኑት ሥርወ-መንግሥታት መካከል፣ የአዝቴክ፣ የማያ፣ የፈርኦን እና የአክሱም ሥርወ-መንግሥታት ትተውልን ያለፉት የሥነ ህንጻ ቅሪቶች ይህንኑ የሚያመላክቱ ናቸው። በዚህ ሂደት ውስጥ፣ የሰው ልጅ ስለአካባቢው እና ምድራችን ስለምትገኝበት አጥናፈ-ሰማይ ያለውን ዕውቀት ለማዳበር በመቻሉ ራሱን ከሌሎች ፍጡራን በበለጠ ከተፈጥሮ አካባቢው ሊያገኝ የሚችለውን ተጠቃሚነት ሊያጎለብት ችሏል።

የዘመናዊው ሳይንስ ዋነኛው መሰረት ከተጣለበት ከአስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛው አጋማሽ ጀምሮ ያለው ዘመን በሰው ልጅ የዕውቀት አድማስ ውስጥ እጅግ ከፍተኛ የዐይነት ለውጥ የታየበት ዘመን ነው። ይህም፣ ቀደም ሲል በልዩ ልዩ የፍልስፍና እና እምነት ዘርፎች ላይ የተመሰረተው የሰው ልጅ ዕውቀት በተለያዩ የሳይንስ መስኮች በመደርጀት ይበልጥ ጥልቀት እና ግዝፈት እያገኘ እንዲመጣ አስችሏል። በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ የተፈጥሮ አካባቢያችን፣ ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ከመስጠት ባሻገር የዕውቀቶቻችን ሁሉ ዋነኛ ምንጭ በመሆን አገልግሏል። በመሆኑም፣ ከዝቅተኛው የቴክኖሎጂ ውጤቶቻችን እስከ ከፍተኛው የዘመናችን ሰው-ሰራሽ ብልህነት (arficial intelligence) ድረስ ያሉ የቴክኖሎጂ ዕውቀቶች በሙሉ ተፈጥሮን በማጥናት እና በማስመሰል (mimcry) ላይ የተመረኮዙ ናቸው። ይህንን፣ በሰው ልጅ የእውቀት አድማስ እና በተፈጥሮ አካባቢው መካከል ያለውን ጥብቅ ቁርኝት አለመረዳት የሰው ልጆችን በተለያዩ ወቅቶች ለተከሰቱ የመታበይ (hubris) ፈተናዎች እንዲጋለጥ አድረገውታል። ይህም፣ ራስን ወደ ፈጣሪነት የማስጠጋት እና የተፈጥሮ አካባቢውን ምህዳራዊ መረጋጋት እና ዘላቂነት ከግምት ውስጥ አለማስገባት አስከትሏል። እንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች በታሪክ ውስጥ ቀደምት የሚባሉት ሥልጣኔዎች እንዲንኮታኮቱ ካደረጓቸው አበይት ምክንያቶች አንዱ መሆኑን በከባቢያዊ አርኪኦሎጂ (Environmental archaeology) መስክ የተከናወኑ ጥናቶች አመላክተዋል።

ሃያኛው ክፍለ ዘመን፣ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ እድገት የተመዘገበበት ዘመን መሆኑ ግልጽ ነው። በዚያው መጠን ግን፣ በአጠቃላይ የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ዘመን አንስቶ በተፈጥሮ አካባቢያችን ላይ ከታየው ከባቢያዊ ለውጥ የገዘፈ ተጽዕኖ በምድራችን ምህዳር ላይ ባለፉት ሁለት መቶ ዓመታት አስከትሏል። በዚህም የተነሳ፣ ዓለማችንን በመሰረታዊነት ሊቀይራት ወደሚችል ፍጹም የሰው ልጅ ጭፍን የበላይነት ዘመን (the Anthopocene age) እንደገባን የሚያሳዩ በርካታ ሳይንሳዊ መረጃዎች በመውጣት ላይ ይገኛሉ። ይህ ሁኔታ በዚሁ ከቀጠለ፣ የዓለማችን ከባቢያዊ መዛባት ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅም እንደፍጡር መቀጠል (existential) ፈተና ውስጥ ሊገባ እንደሚችል ይገመታል።

ባለፈው አንድ ዐመት ውስጥ የተከሰተው የኮሮና ቫይረስ እና በዓለማችን ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ህይወት ላይ ያስከተለው ቀውስ ሊከተል ስለሚችለው ጥፋት ጥሩ የማንቂያ ደወል ሊሆን ይችላል። ይህንን በይበልጥ ለመረዳት፣ በቅርቡ የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም ያወጣውን የዚህን ዓመት የሰዎች ልማት ሪፖርት (Human Development Report 2020) መመልከት ጠቃሚ ይሆናል። በሃያኛው ክፍለ ዘመን የታየው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በተፈጥሮ ከባቢያችን ላይ ካስከተለው ጎጂ ተጽዕኖዎች ባሻገር፣ በቢሊዮን የሚቆጠሩ የዓለማችን ህዝቦችን የስራ እና የመኖር ዋስትና አሳጥቷል። ይህም፣ በመላው ዓለም ዙርያ የፖለቲካ አለመረጋጋቶችን እና ህዝባዊ ተቃውሞዎችን አስከትሏል። በዚህም የተነሳ፣ ዛሬ በዓለማችን ገኖ ያለው ኢዘላቂ (unsustainable) የዕድገት እና ልማት አቅጣጫ በመሰረታዊነት ካልተቀየረ በመጪዎቹ ዓስርተ ዓመታት የሀገሮች እና ህዝቦች ፈተና ይበልጥ እየተጠናከረ እንደሚሄድ ይገመታል።

## 1.2 ቀውሶች እንደ ዕውቀት ጫሪዎች

ታዋቂው የሳይንስ ፍልስፍና ምሁር ቶማስ ኩን (Thomas Kuhn) እንዳለው፣ ባንድ ዘመን ባለ ዕውቀት ሊተነተኑ እና ሊፈቱ የማይችሉ ተደራራቢ እና ውስብስብ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ቀውሶች መከሰት የሚያመላክቱት አዲስ እና ዓይነታዊ ለውጥ ሊያስከትሉ የሚያስችሉ ሳይንሳዊ አስተሳሰቦች አስፈላጊነትን ነው። ለብዙ ሺህ ዓመታት፣ የሰው ልጅ በተፈጥሮ አካባቢው ላይ የሚያደርሳቸው ተጽእኖዎች ባንድ አካባቢ የተወሰኑ እና በተፈጥሮአዊው የማዋሃድ አቅም (assimilation capacity) ውስጥ የሚስተናገድ ነበር። ከሃያኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ጀምሮ የታየው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በምድራችን የተፈጥሮ ሚዛን መዛባት ላይ ያስከተለው ተጽእኖ መጠነ ሰፊ በመሆኑ እና ከምድራችን የማዋሃድ አቅም በላይ በመሆኑ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለው ፈተና ደቅኗል። ይህን ተከትሎ የተከሰተው የዓለማችን ሙቀት መጨመር በዓለም ዙሪያ የሚከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎችን በቁጥርም ሆነ በጉዳት መጠናቸው በከፍተኛ ደረጃ እንዲያድጉ አድርጓቸዋል።

ባለፉት ጥቂት ዓስርተ ዓመታት በሃገራችን በኢትዮጵያ የተከሰቱት እና በብዙ መቶ ሺህ ለሚቆጠር የሃገራችን ህዝብ ሞት እና መፈናቀል ምክንያት የሆኑት የድርቅ እና ጎርፍ አደጋዎች የዚሁ ዓለም አቀፋዊ ፈተና አካል ናቸው። ኮሮናን ጨምሮ ባለፉት ሃያ ዓመታት ውስጥ የተከሰቱ አስር የወረርሽኝ በሽታዎችም በዓለም ዙሪያ ከተከናወኑ የተፈጥሮ ደን መውደም እና የብዝሃ ህይወት መመናመን ጋር በጥብቅ የተያያዙ መሆናቸውን የሚያመላክቱ ሳይንሳዊ መረጃዎች አሉ።

ከሃያኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ጀምሮ የታየው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ያስከተለው ሌላው ዐቢይ መዛባት ሃገሮች፣ በተለይም በማደግ ላይ ያሉ ሃገሮች፣ በኢኮኖሚያቸው ላይ ያላቸውን ሉዓላዊነት የሚያሳጣው ሉላዊነት (globalization) ነው። ይህ የኢኮኖሚ ሥርዓት ባራመዳቸው የተዛቡ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች የተነሳ ባለፉት ሃምሳ እና ስልሳ ዐመታት ውስጥ በሃገሮች ውስጥ እና በሃገሮች መካከል ከፍተኛ የሃብት ልዩነት በመፍጠር ዕልፍ ዓዕላፋትን ለከፋ ድህነት እና የኑሮ ጉስቁልና ዳርጓል። እንደ አውሮፓ አቆጣጠር (እ.አ.አ.) በ2016 ኦክስፋም የተባለው ድርጅት ባወጣው ረፖርት መሰረት፣ በ 2015 (እ.አ.አ.) በዓለም ውስጥ የነበሩት 62 ሃብታሞች የነበራቸው የሃብት መጠን በዝቅተኛ ኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ 3.6 ቢሊዮን ሰዎች ከነበራቸው አጠቃላይ ሃብት ጋር ተመጣጣኝ ነበር። ባለፉት ተከታታይ ዓመታት ይህ የሃብት መጠን ክፍተት በከፍተኛ መጠን እየጨመረ መሄዱን የሚያመላክቱ መረጃዎች በመውጣት ላይ ይገኛሉ።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ፣ ባላፉት አስር ተከታታይ ዓመታት በመንግስትም ሆነ በአንዳንድ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት የሚወጡ መረጃዎች እንዳመላከቱት ሃገራችን ኢትዮጵያ በአፍሪካ ደረጃ ከፍተኛ የሚባል የኢኮኖሚ ዕድገት አስመዝግባለች። በሌላ በኩል ግን፣ የህዝቦች ሁለንተናዊ ደህንነት[1] (wellbeing) ይበልጥ እያሽቆለቆለ እና የሃብት ክፍፍል ክፍተቱም እየሰፋ መሄዱን የሚያመለክቱ በርካታ መረጃዎች አሉ። እንዲህ ዓይነቱ የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ኢፍትሃዊነት በዓለም ዙሪያ ከፍተኛ ለሆነ ማህበራዊ ቀውስ እና የህዝቦች ተቃውሞ እንቅስቃሴ መነሻ በመሆን ላይ ይገኛል። ካፒታል በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የተሰኘውን ድንቅ የምርምር መጽሐፍ እ.ኤ.አ. በ2014 የጻፈው ኢኮኖሚስቱ ቶማስ ፒኬቲ አበክሮ እንዳስገነዘበው፣ ባሁኑ ሰዓት የበላይነትን ይዞ የሚገኘው ሉላዊ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ሥርዓት ለዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ዋነኛ መሰረት ከሆኑት የማህበራዊ ፍትህ እሴቶች ጋር በእጅጉ የሚጋጭ በመሆኑ ሊታከም እንደሚገባው ያመላክታል።

በአጠቃላይ፣ ባለፉት ጥቂት ዓስርተ ዓመታት ዓለማችን ከዚህ በፊት ታይቶ ወደ ማይታወቅ ውስብስብ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ ከባቢያዊ፣ እና ፖለቲካዊ አጣብቂኝ ውስጥ በመግባት ላይ ትገኛለች። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እጅግ ፈጣን በሆነ ሁኔታ በኢኮኖሚ ሥርዓቱም ላይ ሆነ በዕለት ተዕለት ኑሮአችን ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ በማድረግ ላይ የሚገኘው የመረጃ ቴክኖሎጂ እና ዲጂታይዜሽንም ያለንበትን ሁኔታ ውስብስብነት ይበልጥ እያጠናከረው እንደሚሄድ ይገመታል። እነኚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ቀውሶች ተጠናክረው መውጣት ከጀመሩበት ከ1950ዎቹ ጀምሮ በተለያዩ የሳይንስ መስኮች ሰፊ ጥናት ሲደረግባቸው ቆይቷል። ነገር ግን፣ የችግሮቹ ውስብስብነት በአንድ የሳይንስ ዘርፍ የተቀነበበ ትንተና (reductionism) መረዳትም ሆነ መሰረታዊ መፍትሔ ማግኘት እንዳይቻል አድርጎታል። የሳይንሱ ማህበረሰብ የእንዲህ ዓይነቱን አቀራረብ ውስንነት ይበልጥ እየተገነዘበ ሲመጣ፣ ከ1960ዎቹ ጀምሮ የውስንነቶቹን ዋነኛ ምንጮች ለመረዳት እና ለፈተናዎቹ የሚመጥን ሳይንሳዊ ያተናተን ዘዴዎችን ወደማፈላለጉ አምርቷል። ይህም፣ የሳይንሳዊ አስተሳሰቦችን የፍልስፍና መሰረቶች እንደገና በጥልቀት እንዲመረምር አስገድዶታል።

[1] ሁለንተናዊ ደህንነት (wellbeing) የሰዎችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊ እና ፖለቲካዊ ደህንነት በተቀናጀ ሁኔታ የሚዳስስ የልማት ፅንሰ-ሃሳብ ነው።

## 1.3 ፍልስፍናዊ መነሻዎች

በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ፣ እውነትን ፍለጋ (search for truth) የእውቀት ምንጭ እና የፍልስፍናዎች ሁሉ መሰረት መሆኑ ይነገራል። ይኸው የእውነት ፍለጋ ያልተገደበ ጉጉት (unbounded curiosity) የሳይንስ ፍልስፍናም መሰረት ሆኖ ዘልቋል። ከላይ የተዘረዘሩት ተደራራቢ ቀውሶች እየተጠናከሩ እና ይበልጥ ውስብስብ እየሆኑ መምጣት የሳይንሱ ማህበረሰብ መሰረታዊ የፍልስፍና ጥያቄዎችን እንዲያነሳ አስገድደውታል። በዚህ ሂደት ውስጥ በርካታ መሰረታዊ ጥያቄዎች የተነሱ ቢሆንም፣ ከዚህ መጽሐፍ ጋር በተያያዘ የተወስኑትን ባጭሩ እንመለከታለን። ከዚህ ውስጥ ቀዳሚው በእውነት አመክንዮ (logic of truth) ዙሪያ የተነሳው ጥያቄ ነበር። በዚህ ረገድ ወደ ኋላ ያለውን ጥንታዊ ታሪክ መለስ ብለን ስንመለከት የምዕራባውያንን እና የምስራቁን ዓለም አመክንዮ ታሪክ እናገኛለን፡፡ ይህም፣ በሁለትዮሽ እውነት (bivalent truth) እና በሁለገብ እውነት (multivalent truth) አመክንዮ ላይ ለተመሰረቱ የሁለት አለሞች ፍልስፍና መሰረት ሆኖ ዘልቋል። ምንም እንኳን የሳይንስ ዋነኛው ዓላማ እውነታዎችን ወይም እውነትን መፈለግ መሆኑ በሁሉም የሳይንስ ልሂቃን ቢነገርም እውነት ምንድን ነው ለሚለው ጥያቄ በሚሰጠው መልስ ላይ ለዘመናት የዘለቀ ልዩነት ነበረ። በምዕራባውያኑ የፍልስፍስና መርሆዎች መሰረት ማንኛውንም ዕውነታ በጥልቀት ለመረዳት ሁል ጊዜ በጥቁር እና በነጭ እውነታ ላይ በተመሰረተ የሁለትዮሽ አመክንዮ መተንተን እንደሚገባ ያምናል። በዚህ ፍልስፍና መሠረት፣ በነዚህ እውነታዎች መካካል ያለውን አእምሮአዊ መስመር በተሻለ ግልጽ አድርገህ ባወጣህ መጠን አእምሮህም ይበልጥ አመክንዮአዊ፣ ሳይንስህም ትክክለኛ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል ግን፣ በተለይ በምስራቁ ዓለም ፍልስፍና የተቃኘው የሁለገብ እውነታ፣ የገሃዱ ዓለም እውነታ ባብዛኛው በግራጫነት የሚታወቅ ሲሆን ጥቁር እና ነጭ ዕውነት የግራጫውን ዓለም ጊዜያዊ እና ተሸጋጋሪ እውነታ (transient state) የሚያመላክት ነው ይላል። በዚህም መሰረት ሁለገብ አመክንዮ ሁሉም ሳይንሳዊ እውነቶች ግራጫ ናቸው ሲል የሁለትዮሽ አመክንዮ ግን በአንድ በኩል ሳይንሳዊ ዕውነቶች ግራጫ አለመሆናቸውን አበክሮ እየገለጸ በሌላ በኩል የበለጠ መረጃዎች በተገኙ መጠን ተቀባይነታቸውን የሚያጡ ጊዜያዊ እውነቶች ናቸው ይላል።

በሁለትዮሽ እና ሁለገብ እውነታ አራማጆች መካከል የነበረው ክርክር እና ፉክክር ለረጅም ዘመን የሁለትዮሽ እውነታ የሳይንሱን ዓለም በበላይነት ይዞ እንዲቆይ አድርጎታል። ሆኖም ግን፣ ከሁለገብ ዕውነታ ጋር የተያያዙ እንደ ኳንተም ፊዚክስ[2] ጽንሰ ሃሳብ ያሉ ሳይንሳዊ አስተሳሰቦች በሃያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ ላይ ከመውጣታቸው ጋር

[2] የኳንተም ፊዚክስ መሰረታዊ ጽንሰ ሃሳብ፣ ማንኛውም በአጽናፈ ሰማይ ውስጥ ያለ ነገር በተመሳሳይ ጊዜ የጥቃቅን ቁስነት (particle) እና የሞገድነት (wave) ተፈጥሮ አለው ብሎ ያምናል። ይህም፣ ለረጂም ዘመናት በጥቃቅን ቁስ ወይንም ሞገድ አስተሳሰብ ላይ ተመርኩዞ የነበረውን የፊዚክስ አስተምህሮ ከመሰረቱ ቀይሮታል።

ተያይዞ ይህ ፉክክር ወደ አዲስ ደረጃ እየተሸጋገረ መጥቷል። የሁለገብ ዕውነት አመክንዮ፣ በተለይም ከሃያኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ጀምሮ በፈጣን ሁኔታ ላደገው የመረጃ እና ተግባቦት (information and communication) ቴክኖሎጂ መሰረት ለሆነው ተወራራሽ አመክንዮ (Fuzzy logic) መነሻ በመሆንም አገልግሏል[3]። ሳይንሳዊ እውቀታችን በከፊል እና ግራጫ እውነታዎች ላይ የተመሠረተ መሆኑን እውቅና መስጠቱ ውስብስብ እየሆኑ የመጡትን የዓለማችንን ስርዓቶች ለመረዳት እና ከዚህ ጋር ተያይዘው የመጡትን በርካታ ችግሮች መፍትሔ ለመሻት ቁልፍ እርምጃ ነው። ይህ ደግሞ በባህሪያቸው እጅግ ውስብስብ እየሆኑ የመጡትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ቀውሶችን ለመረዳት ለሚደረገው ጥረት ዋነኛ መሰረት ሊሆን ችሏል።

በሌላ በኩል፣ የምዕራባዊው ሳይንስ ዋነኛ መለያ የሆነው የተቀነበበ ትንተና ተፈጥሮን የራሱ ህልው የሂደት መርህ እንዳለው ፍጡር (organism) ሳይሆን እንደ አንድ ታላቅ ማሺን ሊጠና እና ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል አካል አድርጎ ይወስዳል። ይህ አመለካከት ለረጂም ጊዜ በሳይንሱም ሆነ በጠቅላላው ዘመናዊ አስተሳሰብ ውስጥ ታላቅ ተጽእኖ ያለው የአመለካከት ዘይቤ (metaphor) ሆኖ ዘልቋል። ይህ አቀራረብ፣ በተለይ በተፈጥሮ ሳይንስ መስክ ለተገኘው ሰፊ የዕውቀት ጥልቀት ከፍተኛውን አስተዋጽኦ አድርጓል፤ ወደፊትም እንደሚያደርግ ይጠበቃል። በሌላ በኩል ግን፣ ከሃያኛው ክፍለዘመን መጀመሪያ አንስቶ አንድ ተገዳዳሪ የሆነ የተፈጥሮ ምህዳርን በማያቋርጥ፣ ተለዋዋጭ እና ተወራራሽ መስተጋብራዊ ምሉዕነቱ የሚመለከት ንዑስ የሳይንሳዊ አመለካከት ዘርፍ ብቅ ማለት ጀመረ። ይህ አመለካከት፣ ከአንድ ወጥ እና ብቸኛ (deterministic) አካሄድ ይልቅ የማያቋርጥ ፈጠራን፣ ከቁስ ይልቅ ሂደትን፣ ከክፋዮች ይልቅ ምሉዖችን ያነላል። የሰውን እና የተፈጥሮ ንፍቀ ክበብን አንድ ላይ ከማገናኘቱም በላይ ገሃዱን ዓለም እንደማያቋርጥ የኃይል እና የቁስ ፍሰት መስተጋብር አድርጎ ያሳያል። በዚህም ሁለንተናዊ እይታ (holistic view) ተብሎ ለሚጠራው መሠረት ጥሏል።

በሁለንተናዊ አስተሳሰብ (holistic thinking) መሠረት፣ ማናቸውም ምሉእነት ያለው ቁስ ሆነ ሕይወት የተመሰረተው የራሳቸው ምሉዕነት ባላቸው ክፋዮች ቅንጅታዊ አደረጃጀት ነው። የሁለንተናዊው አመለካከት ቀዳሚው አቀንቃኝ የነበረው ጃን ስሙትስ (Jan Smuts) እንዳለው የ 'ምሉዕነት' ባሕርይ በሁሉም ቦታ የምናገኘው እና በአጽናፈ ሰማይ (universe) ውስጥ ለሚታየው ማንኛቸውም ተፈጥሯዊ ዝግመተ ለውጥ መነሻ ነው። ስለዚህም፣ ምሉእዎች ሰው ሰራሽ የአስተሳሰብ ግንባታዎች ሳይሆኑ በአጽናፈ-ሰማይ ውስጥ የሚገኘውን እውን ነባር ያመለክታሉ። ለምሳሌም፣ አንድን እጽ ወይም እንስሳ ብንወስድ፣ የዚህ እጽ ወይም እንስሳ ምሉዕ ባህርይ ከክፋዮቹ ተደማሪነት ባሻገር በክፋዮቹ መካከል ባለው መስተጋብራዊ ግንኙነት የሚወሰን ይሆናል። በዚያው መጠን ደግሞ፣

[3] አንዳንድ ጥናቶች፣ የቻይና እና የህንድ ባለሙያዎች በኮምፒዩተር ሶፍትዌር ቴክኖሎጂ ዘርፍ ያላቸውን የበላይነት ከዚሁ በምሥራቁ ዓለም በሰፊው ካለው የሁለገብ ዕውነት አመክንዮ ቅኝት ጋር ያያይዙታል።

ይኸው ምሉዕ እጽ ወይም እንስሳ ከአካባቢው ጋር የሚኖረው መስተጋብራዊ ግንኙነት በውስጡ ያሉት ክፋዮች የሚኖራቸውን የቅርጽ እና የተግባር ባህርይ ይወስናል።

በዚህ መልኩ፣ በምሉዕ እና በክፋዮች መካከል የሚከናወነው የማያቋርጥ መስተጋብር የአጠቃላዩ አጽናፈ-ሰማይ መሰረት በመሆን ያገለግላል። በሁለንተናዊ አስተሳሰብ መሰረት፣ የተቀነበበ ትንተና (reductionist analysis) ባጠቃላዩ የሁለንተናዊ እይታ ማዕቀፍ ውስጥ ስለ አንድ ውስን ክፋይ ጠለቅ ያለ ዕውቀት ለማመንጨት የራሱ ጠቀሜታ እንዳለው ይገነዘባል። ውስብስብ የሆኑ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ እና ከባቢያዊ ምህዳሮችን ባግባቡ ለመረዳት ግን ይህ አመለካከት በሁለንተናዊ አስተሳሰብ መቃኘት ይኖርበታል።

## 1.4 የምህዳራዊ አስተሳሰብ መሰረቶች

ምህዳራዊ አስተሳሰብ (Systems thinking) ከዚህ በላይ በተጠቀሱት አማራጭ የፍልስፍና እና የዓለም እይታ (world view) ላይ በመመስረት ከ1960ዎቹ ጀምሮ እየዳበረ የመጣ የሳይንስ መስክ ነው። መነሻ ነጥቡም፣ በተቀነበበ ትንተና ላይ የተመረኮዘው ምዕራባዊው ሳይንስ ለሰው ልጆች ህይወት መሻሻል ያደረገውን እና ወደፊትም ሊያደርግ የሚችለውን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ተገንዝቦ ለድክመቶቹ ምንጭ የሆኑትን የፍልስፍና እና የአተናተን መሰረቶች መመርመር እና መፈተሽ ነው። በዚህም፣ ከተለያዩ የሳይንስ መስኮች የተገኙትን ዕውቀቶች በተለየ የዕውቀት አደረጃጀት በማስተሳሰር ጎጂ የሆኑ የሁለተኛ ደረጃ ተጽእኖዎቻቸውን (second-degree effect) ለመቀነስ የሚያስችል ሁኔታን ሊፈጥር ችሏል። ለዚህም የሚጠቀምበት የአጠናን ዘዴ የልዕለ-ዘርፍ (transdisciplinary) የአጠናን ዘዴ[4] ተብሎ ይታወቃል። በዚህ ሂደትም የተነሳ፣ ባለፉት ጥቂት ዓስርተ ዓመታት፣ ምህዳራዊ አስተሳሰብ በተለያዩ የተፈጥሮ እና ማህበራዊ ሳይንስ መስኮች የየራሱን ልዩ ገጽታ በመያዝ በመተግበር ላይ ይገኛል። ከዚህም ውስጥ አንደኛው ምሳሌ፣ አምስተኛው ዘርፍ (The fifth discipline) ተብሎ የሚጠቀሰው እና በድርጅታዊ ሥራ አመራር ዘርፍ ሰፊ ተቀባይነት ያገኘው የምህዳራዊ አስተሳሰብ ትግበራ ነው።

የዘመናዊው ሳይንስ ዋንኛው መሰረት የሆነው የእንቅስቃሴ ሳይንስ (mechanics) የተወሰኑ ኣይነት ግንኙነቶች ከሌሎች የበለጠ አስፈላጊ እንደሆኑ በመገመት ውስብስብ ምህዳሮችን ወደ ቀላል ክፍልፋዮች በመቀነስ ላይ በመመርኮዝ የሚከናወን የጥናት ሥርዓት ነው፡፡ ይህም፣ በተደራጀ ቀላልነት (organized simplicity) ላይ የተመረኮዙ መፍትሔዎችን ይሰጣል። የዚሁ ተቀጽላ የሆነው በስታቲስቲክሳዊ ዘፈቀዳዊነት (statistical randomness) ላይ የተመረኮዘው አተናተን፣ አንድ ምህዳር ውስብስብ ቢሆንም በበቂ ሁኔታ ተገማች የሆነ ዘፈቀዳዊነት እስካለው ድረስ በስታቲስቲክሳዊ የአጠናን ዘዴ ሊተነተን ይችላል ይላል። ይህም፣ በዓለማችን ለሚገኙ በጣም ጥቂት ለሆኑ ያልተደራጀ ውስብስብነት (unorganized complexity) ላላቸው ክስተቶች የሚሰራበት ሁኔታ እንዲኖር አስችሏል።

ነገር ግን፣ አብዛኛው ገሃዱ ዓለም፣ የተደራጀ ውስብስነት (organized complexity) ባላቸው ምህዳሮች የተሞላ በመሆኑ በተደራጀ ቀላልነት ላይም ሆነ ባልተደራጀ ውስብስብነት ላይ የተመረኮዙ መፍትሔዎች በሙሉ ጊዜያዊ (tentative) እና ያልተሟሉ ይሆናሉ። ከላይ የተጠቀሰው የተቀነበበ ትንተና፣ እንደ ሂሳብ፣ ፊዚክስ፣ እና ኬሚስትሪ በመሳሰሉ የሳይንስ መስኮች አንጻራዊ ውጤታማነት ያሳየ ሲሆን ውስብስብነት ጥልቅ ተፈጥሮአዊ (inherent) ባህሪያቸው ለሆኑት እንደ ሥነሕይወት እና ማህበራዊ

[4] ይህ ዓይነቱ የአጠናን ዘዴ በተለይ በምህንድስናው ዘርፍ አስቀድሞ የተተገበረ እና ከፍተኛ ውጤትም ያስገኘ ነው። ለምሳሌም ያህል ባለፉት ጥቂት ዓስርተ ዓመታት ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡትን የዘረ መልዕ ምህንድስና (Genetic engineering)፣ የሥነህይወት ቴክኖሎጂ (Bio technology) እና የናኖ ቴክኖሎጂን (Nano Technology) መጥቀስ ይቻላል።

ሳይንሶች ውስጥ ውጤታማነታቸው ዝቅተኛ ሊሆን ችሏል። ይህንን የምሉዕነት እና ውስብስብነት ዕውነታ፣ ካብዛኛዎቹ ሳይንቲስቶች በተሻለ የሥነ ጥበብ ሰዎች[5] እንደሚረዷቸው እና በሥራዎቻቸውም ለማሳየት እንደሚሞክሩ የሚያሳዩ መረጃዎች አሉ።

ከዚህ በታች ያለው ምስል አንድ፣ ከላይ የተጠቀሱት የምህዳራዊ ውስብስብነት ዓይነቶች በገሃዱ ዓለም ውስጥ ያላቸውን ድርሻ በስዕላዊ መግለጫ የሚያመላክት ነው። በዚሁ መሰረት፣ የመጀመሪያው ከፍል እና በገሃዱ ዓለም በጣም አነስተኛውን ድርሻ የሚወስደው የተደራጀ ቀላልነት በተቀነበበ ተንተና (reductionist analysis) ሊጠና የሚችለውን የቁሳዊውን ዓለም ይወክላል። ይህም ባብዛኛው ፊዚክስ እና ኬሚስትሪ በመሰሉት የሳይንስ ዘርፍ የሚሸፈን ነው።

ምስል ፡ ምህዳራዊ ውስብስብነት




[5] በእኔ እይታ ከሃገራችን የሥነ ጥበብ ሰዎች ታላቁ የሥነ ጽሁፍ ሰው አቦ ፀጋየ ገብረ መድህን፣ ባለቅኔው ሙሉጌታ ተስፋዬ እና ገጣሚ ነቢይ መኮንን እዚህ ውስጥ የሚካተቱ ይመስለኛል።

ከዚያ ቀጥሎ ያለው፣ በስታቲስትክሳዊ ትንተና (statistical analysis) የሚሸፈነው እና በበቂ ሁኔታ ተገማች ዘፈቀደነት (randomness) ያለው ያልተደራጀው ውስብስብነት (unorganized complexity) የዓለማችን ክፍል ነው። ለምሳሌም ያህል፣ ያንድን ወረርሽኝ በሽታ ባህርይ እና የመሰራጨት አቅጣጫ ለማጥናት የሚካሄድ ጥናት በዚህኛው የዓለማችን ክስተት ውስጥ የሚካተት ይሆናል። አብዛኛው የዓለማችን ኩነት እና ክስተት ግን የሚገኘው የተደራጀ ውስብስነት (organized complexity) ተብሎ በሚታወቀው ክፍል ውስጥ ሲሆን ይህም አብዛኛዎቹን ማህበራዊ፣ ከባቢያዊ፣ እና ፖለቲካዊ ምህዳሮች ያካትታል። እስካሁን ድረስ በአብዛኛው እነኚህን ምህዳሮች በተለመዱት የተቀነበበ እና ስታቲስቲካዊ ትንተና ለመረዳት እና ከእነርሱም ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት የተደረጉ ጥረቶች ችግሮቹን ይበልጥ እየተወሳሰቡ እንዲሄዱ አድርገዋቸዋል። ስለሆነም ነው፣ በዚህ ዘርፍ ውስጥ የሚገኙ ምህዳሮችን ባግባቡ ለመረዳት የሚቻለው በምህዳራዊ ትንተና ብቻ ነው የሚባለው።

በምህዳራዊ አስተሳሰብ መሰረት አንድ ምህዳር ማለት የየራሳቸው ህልው ነባራዊነት ያሏቸው የተለያዩ ቁሳዊ ነገሮች እና ባህርያት (attributes) የተደራጁበት የግንኙነት ስብስብ ነው። የምህዳራዊ ትንተናም ዋነኛው መለያው አንድን ውስብስብ ምህዳር በጥቅልነቱ ለመረዳት የሚያስችሉ መሰረታዊ ጥያቄዎችን መጠየቁ ነው። ከነዚህም ዋነኛው፣ በጊዜ ሂደት የሚከሰቱ መሰረታዊ መዋቅራዊ ግንኙነቶች (underlying structural relationships) እና የባህሪ ዘይቤዎች (patterns of behavior) ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች ናቸው። በዚህ ላይ በመመርኮዝም፣ በምህዳሩ መስተጋብር ውስጥ ሊያጋጥሙ የሚችሉ መዘግየቶች (potential delays)፣ አዎንታዊ እና አሉታዊ ግብረመልሶች (positive and negative feedbacks) እና ያልተጠበቁ መዘዞቻቸው (consequences) ላይ ያተኩራል፡፡ ለዚህም እንዲረዳው፣ በተለያዩ የሳይንስ መስኮች በተለይም በተፈጥሮ የሳይንስ መስክ የተረጋገጡ አጠቃላይ ሳይንሳዊ መርሆዎችን በማቀናጀት ይጠቀማል።

## 1.5 ምህዳራዊ አስተሳሰብ እና ሃገር በቀል ዕውቀት

በተለያዩ ጥናቶች እንደተረጋገጠው፣ ህጻናት አብዛኛውን የገሃዱን ዓለም የመጀመሪያ ዕውቀቶቻቸውን የሚያዳብሩት በቅድሚያ የምሉዕ ምህዳሩን ስሜት ተወራራሽ በሆነ አመክንዮ (transductive logic) በመገንዘብ ነው። ይህ ባብዛኛው ህጻናቶች ላይ የሚታይ አመክንዮ፣ ከአጠቃላይ ወደ ተናጠል (deductive) ወይንም ከተናጠል ወደ አጠቃላይ (inductive) ከሚሄደው አመክንዮ በተለየ አንድን ተናጠል ሁኔታ ከሌላ ተናጠል ሁኔታ ጋር በቀጥታ የሚያገናኙበት መንገድ ነው። ይህም፣ ሁሉም የሰው ፍጡር የሁለንተናዊ አስተሳሰብ ክህሎት በተፈጥሮ የተሰጠው መሆኑን ያሳያል። እንዳለመታደል ሆኖ፣ አብዛኛዎቻችን በተቀነበበ ትንተና ላይ በተመረኮዘው የምዕራባዊያን የትምህርት ሥርዓት ሳጥን ውስጥ ባለፍንበት መጠን ይህንን ተፈጥሮአዊ የሁለንተናዊ አስተሳሰብ ክህሎታችንን እያቀጨጭነው እና እያጠፋነው እንሄዳለን። ከዚህም የተነሳ፣ በተለምዶ እንደሚባለው እና በተግባርም እንደሚታየው፣ ባንድ የሳይንስ ዘርፍ በጣም ጥልቅ የሆነ ዕውቀት ባለቤት የሆነ ሳይንቲስት፣ በአብዛኛው ከዚያ የሙያ ዘርፍ ውጭ ባሉ ዘርፎች ከፍተኛ ለሆነ የዕውቀት ድህነት የተጋለጠ ይሆናል።

ከዚህ በተቃራኒው፣ ለምንም ዓይነት ዘመናዊ ትምህርት ሳይጋለጡ በተፈጥሮ የተሰጣቸውን የሁለንተናዊ አስተሳሰብ ክህሎት በህይወት ልምዶቻቸው በማዳበር እጅግ ከፍተኛ የሆነ አስተዋይነታቸውን ያስመሰከሩ የማህበረሰብ አዋቂዎች በሁሉም የህብረተሰብ ታሪክ ውስጥ እንደነበሩ እና አሁንም እንዳሉ ይታወቃል። እነኚህ የማህበረሰብ አዋቂዎች፣ ሃገራችንን ጨምሮ፣ ለበርካታ የዓለማችን ማህበረሰቦች ለዘመናት አብሮ የመኖር እና ከተፈጥሮ አካባቢያቸውም ጋር በሚዛናዊነት ለመዝለቅ ዋነኛ የዕውቀት መሰረቶች በመሆን አገልግለዋል። ሃገር በቀል ዕውቀት በመባል የሚታወቀው የዕውቀት ዘርፍ እነኚህ የማህበረሰብ አዋቂዎች ያመነጯቸው እና በዘመናት ሂደት ውስጥ በማህበራዊ ይሁንታ እና ቅብብሎሽ እየዳበረ ለመጣው የዕውቀት ዘርፍ ዋነኛ ማከማቻ (repository) ነው።

እዚህ ላይ፣ በሀገር በቀል እውቀቶች እና በማህበራዊ ልማዶች መካከል ያለውን የይዘት ልዩነት መረዳት ተገቢ ይሆናል። በርካታ ሰዎች፣ በአንዳንድ ሁኔታ ጎጂ የሆኑ ማህበራዊ ልማዶችን (rituals) በዘመናት ሂደት ከዳበሩ እና የማህበራዊ እሴቶች ቋት ከሆኑት ሃገር በቀል እውቀቶች ጋር በማምታታት የዚህን የዕውቀት ዘርፍ አስተዋጽኦ ሲያጣጥሉ ይሰማል። የዚህ ዕውቀት ዘርፍ ዋነኛው የትንተና መሰረቱ ተፈጥሮአዊው የሁለንተናዊ አመለካከት ክህሎት በመሆኑ በጣም በሚያስገርም ሁኔታ በሃያኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ እየዳበረ ከመጣው ምህዳራዊ ሳይንስ ጋር በአብዛኛው የተጣጣመ ሆኖ ይገኛል። ለምሳሌም ያህል፣ በምህዳራዊ አስተሳሰብ መሰረት፣ መተካካት (succession) የማናቸውም ምህዳር ዘላቂነት ዋነኛው ማረጋገጫ መርህ ነው። በመሆኑም፣ በማናቸውም ተፈጥሮአዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ምህዳሮች ላይ ይሰራል።

ይህ የመተካካት መርህ በሀገር በቀል እውቀቶች ውስጥ ሁነኛ ስፍራ እንዳለው በርካታ ማሳያዎችን ማቅረብ ይቻላል። ከእነዚህም ውስጥ አንዱ፣ አብዛኞቹ ሃገር በቀል የአስተዳደር ሥርዓቶች እጅግ በልጽገዋል ከሚባሉ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓቶች ባልተናነሰ መልኩ የመተካካት መርህን የሚከተሉ ሆነው መገኘታቸው ነው[6]። እነኚህ የመተካካት ሂደቶች፣ በዘመናት ሂደት የዳበሩ የውይይት እና የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓቶችን መሰረት በማድረግ እና የተለያዩ ትውልዶችን አስተዋጽኦ ግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወኑ ናቸው።

ይህ የዕውቀት ዘርፍ ለየማህበረሰቦቹ ቀጣይነት ካበረከተው ቁልፍ ድርሻ ባሻገር ለተለያዩ የምዕራባዊው ሳይንሶች በርካታ ጠቃሚ መነሻዎች እንደሰጠ ይታመናል። ለምሳሌም ያህል፣ በሃገር በቀል ዕውቀት ተጠብቀው የቆዩት መድሃኒትነት ያላቸው አጽዋት እና ባህላዊ ህክምናዎች የዘመናዊው ህክምና ሳይንስ ዋነኛ መንሻ እንደነበሩ እና አሁንም እንደሆኑ ይታወቃል። ከዚህ በተጨማሪም፣ ዛሬ የምዕራባዊው ዲሞክራሲ አዲስ ግኝት ተደርጎ የምንሰበከው የሶስትዮሽ መንግስታዊ አስተዳደር ሥርዓት ኢትዮጵያን ጨምሮ በበርካታ ሃገር በቀል የህዝብ አስተዳደር ሥርዓቶች ውስጥ የነበሩ እና አሁንም ያሉ መሆናቸውን የሚያረጋግጡ በርካታ መረጃዎች እንዳሉ ማቅረብ ይቻላል። ይህንን በይበልጥ ለመረዳት፣ በኢትዮጵያ የሃገር በቀል ዕውቀቶች ጥናት ተቋም[7] የተካሄዱ በርካታ ጥናት ውጤቶችን መመልከት ይጠቅማል።

አሳዛኙ ከስተት፣ ምዕራባዊው ሳይንስ እና ትምህርት ለረጅም ዘመናት የዚህን የዕውቀት ዘርፍ ታላቅ ጠቀሜታ እና አስተዋጽኦ ማሳነስ ብቻ ሳይሆን ስልታዊ (systematic) በሆነ መልኩ እንዲቀጭጭ እና እንዲጠፋ ከፍተኛ ስራ ተሰርቷል። የሃገራችን የትምህርት ሥርዓትም ሆነ የዚህ ውጤት የሆንነው ምሁራን በአብዛኛው የዚህ ስልታዊ ጥቃት ሰለባ በመሆናችን ለሃገር በቀል ዕውቀት የምንሰጠው ትኩረት አነስተኛ ሊሆን ችሏል። ይህም ሲባል፣ ሃገር በቀል እውቀቶች የሚጎሏቸው እና ሊስተካከሉ የሚገባቸው አካሄዶች የሏቸውም ማለት አይደለም።

ባለፉት ጥቂት ዓስርተ ዓመታት በዓለማችን ዙሪያ እየተጠናከረ ከመጣው ተደራራቢ ቀውሶች ጋር በተያያዘ ለሃገር በቀል ዕውቀቶች የሚሰጠው እውቅና ይበልጥ እየተጠናከረ በመምጣት ላይ ይገኛል። ለዚህም በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስ እና የባህል ድርጅት (UNESCO) በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡት የኮንሶ ማህበረሰብ የአካባቢ ጥበቃ እና ልማት እና የኦሮሞ የገዳ ሥርዓት ጥሩ ማሳያ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ፣ በርካታ የሃገር በቀል ዕውቀት መርሆዎች በሳይንሱ ዓለም በሚካሄዱ ጥናቶች ውስጥ እየተካተቱ በመምጣት ላይ ይገኛሉ። ከነዚህ ውስጥ፣ በበርካታ አፍሪካ

[6] በገዳ ሥርዓት ውስጥ ያለው በየስምንት ዓመቱ የሚካሄደው የሥልጣን ሽግግር ለዚህ አንድ አቢይ ምሳሌ ነው።

[7] ይህ ተቋም፣ የበርካታ ብሔረሰቦችን የአስተዳደር እና የዳኝነት ሥርዓቶች በዝርዝር በማጥናት ለህትመት አብቅቷል።

ሃገራት በሚገኙ ማህበረሰቦች በስፋት የሚተገበረው የኡቡንቱ (Ubuntu) ጽንስ ሃሳብ አንደኛው ነው።

የኡቡንቱ አስተሳሰብ በጥቅሉ 'እኔ እኔን የሆንኩት ባንተ እና በእናንተ ነው' ይላል። ይህ አባባል የአንዱ ህልውና በሁሉም ላይ እና የሁሉም ዘላቂነት ደግሞ ባንዱ ላይ ያለውን የህልውና ተደጋጋፊነት (interdependence) ያመላክታል። ኡካማ (Ukama) የሚባለው አስተሳሰብ ሌላው ከዚሁ ጋር የተያያዘ ጽንስ ሃሳብ ሲሆን ይህ አስተሳሰብ በቀደመው ፣ በአሁኑ እና በመጪው ትውልድ መካከል የማይነጣጠል አንድነትን ያቀፈ ከመሆኑም በላይ የሰው ልጅ ከተፈጥሮአዊው (biophysical)) ዓለም ጋር ያለውን ቁርኝት ያሰምርበታል። እነኚህ ሁለት አስተሳሰቦች፣ ከሁለንተናዊው አስተሳሰብ ጋር በቅርብ የተዛመዱ ከመሆናቸዎም በላይ በሰው እና የተፈጥሮ አካባቢ ሁለንተናዊ ደህንነት (Wellbeing) መካከል ያለውን ጥብቅ ትስስር ያሳያሉ። በአጠቃላይ፣ በዘመናዊው ሳይንስ እና ሃገር በቀል ዕውቀቶች መካከል የሚፈጠር ስልታዊ ቅንጅት ዛሬ ለተጋፈጥናቸው በርካታ ውስብስብ ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ለማመንጨት ጠቃሚ አስተዋጽኦ ሊያደርግ እንደሚያስችል ይታመናል።

## የክፍል አንድ ቁልፍ ሐሳቦች

i. የተፈጥሮ አካባቢያችን፣ ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳዊ ግብዓቶችን ከመስጠት ባሻገር የዕውቀቶቻችን ሁሉ ዋነኛ ምንጭ በመሆን አገልግሏል። በመሆኑም፣ ከዝቅተኛው የቴክኖሎጂ ውጤቶቻችን እስከ ከፍተኛው የዘመናችን ሰው-ሰራሽ ብልህነት (arficial intelligence) ድረስ ያሉ የቴክኖሎጂ ዕውቀቶች በሙሉ ተፈጥሮን በማጥናት እና በማስመሰል (mimcry) ላይ የተመረኮዙ ናቸው።

ii. ከሃያኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ጀምሮ የታየው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት በምድራችን የተፈጥሮ ሚዛን መዛባት ላይ ያስከተለው ተጽእኖ መጠነ ሰፊ በመሆኑ እና ከምድራችን የማዋሃድ አቅም በላይ በመሆኑ ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያለው ፈተና ደቅኗል። ከዚህ በተጨማሪም፣ ሃገሮች፣ በተለይም በማደግ ላይ ያሉ ሃገሮች፣ በኢኮኖሚያቸው ላይ ያላቸውን ሉዓላዊነት የሚያሳጣው ሉላዊነት (globalization) ባራመዳቸው የተዛቡ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች የተነሳ ባለፉት ሃምሳ እና ስልሳ ዓመታት ውስጥ በሃገሮች ውስጥ እና በሃገሮች መካከል ከፍተኛ የሃብት ልዩነት በመፍጠር ዕልፍ ዓዕላፋትን ለከፋ ድህነት እና የኑሮ ጉስቁልና ዳርጓል።

iii. በዚህም የተነሳ፣ ዓለማችንን ወይ ሊያጠፋት ወይንም በመሰረታዊነት ሊቀይራት ወደሚችል ፍጹም የሰው ልጅ ጭፍን የበላይነት ዘመን (the Anthopocene age) እንደገባን የሚያሳዩ በርካታ ሳይንሳዊ መረጃዎች በመውጣት ላይ ይገኛሉ። ይህ ሁኔታ በዚሁ ከቀጠለ፣ የዓለማችን ከባቢያዊ ሁኔታ መዛባት ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅም እንደፍጡር መቀጠል (existential) ፈተና ውስጥ ሊገባ እንደሚችል ይገመታል።

iv. እነኚህ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ችግሮች ተጠናክረው መውጣት ከጀመሩበት ከ1950ዎቹ ጀምሮ በተለያዩ የሳይንስ መስኮች ሰፊ ጥናት ሲደረግባቸው ቆይቷል። ነገር ግን፣ የችግሮቹ ውስብስብነት በአንድ የሳይንስ ዘርፍ የተቀነበበ ትንተና (reductionism) መረዳትም ሆነ መሰረታዊ መፍትሔ ማግኘት እንዳይቻል አድርጎታል። ይህም፣ ከ1960ዎቹ ጀምሮ እየዳበረ ለመጣው ምህዳራዊ አስተሳሰብ (systems thinking) መሰረት ሊሆን ችሏል።

v. ምንም እንኳን የሳይንስ ዋነኛው ዓላማ እውነታዎችን ወይም እውነትን መፈለግ መሆኑ በሁሉም የሳይንስ ልሂቃን ቢነገርም እውነት ምንድን ነው ለሚለው ጥያቄ በሚሰጠው መልስ ላይ ለዘመናት የዘለቀ ልዩነት ነበረ። ይህም፣ በሁለትዮሽ እውነት (bivalent truth) እና በሁለገብ እውነት (multivalent truth) አመካኝዮ ላይ ለተመሰረቱ የሁለት ዓለሞች ፍልስፍና መሰረት ሆኖ ዘልቋል።

vi. የምዕራባዊው ሳይንስ ዋነኛ መለያ የሆነው የተቀነበበ ትንተና ተፈጥሮን የራሱ ህልው የሂደት መርህ እንዳለው ፍጡር (organism) ሳይሆን እንደ አንድ ታላቅ ማሺን ሊጠና እና ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል አካል አድርጎ ይወስዳል። በሌላ በኩል ግን፣ በሁለንተናዊ አስተሳሰብ (holistic thinking) መሠረት፣ ማናቸውም ምሉዕነት ያለው ቁስ ሆነ ሕይወት የተመሰረተው የራሳቸው ምሉዕነት ባላቸው ክፋዮች ቅንጅታዊ አደረጃጀት ነው ይላል።

vii. የምህዳራዊ አስተሳሰብ የፍልስፍና መሰረቶች፣ ሁለትዮሽ ዕውነትን የሁለገብ ዕውነት ጊዜያዊ መገለጫዎች፣ የተቀነበበ አስተሳሰብን የሁለንተናዊ አስተሳሰብ ደጋፊ አካል አድርጎ በመቀበል ላይ የተመረኮዙ ናቸው። በዚህም መሰረት፣ አብዛኛው ገሃዱ ዓለም፣ የተደራጀ ውስብስነት (organized complexity) ባላቸው ምህዳሮች የተሞላ በመሆኑ በተደራጀ ቀላልነት (organized simplicity) ላይ የተመረኮዘ የተቀነበቡ መፍትሔዎችም ሆኑ ባልተደራጀ ውስብስብነት (unorganized complexity) ላይ የተመረኮዙ ስታቲስቲካዊ መፍትሔዎች በሙሉ ጊዜያዊ (tentative) እና ያልተሟሉ ይሆናሉ ብሎ ያምናል።

viii. በምህዳራዊ አስተሳሰብ መሰረት አንድ ምህዳር ማለት የየራሳቸው ህልው ባህርያት ያሏቸው የተለያዩ ቁሳዊ ነገሮች እና ባህርያት (attributes) የተደራጁበት የግንኙነት ስብስብ ነው። የምህዳራዊ ትንተናም ዋነኛው መለያው አንድን ውስብስብ ምህዳር በጥቅልነቱ ለመረዳት የሚያስችሉ መሰረታዊ ጥያቄዎችን መጠየቁ ነው። ከነዚህም ዋነኛው፣ በጊዜ ሂደት የሚከሰቱ መሰረታዊ መዋቅራዊ ግንኙነቶች (underlying structural relationships) እና የባህሪ ዘይቤዎች (patterns of behavior) ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች ናቸው።

ix. በተለያዩ ጥናቶች እንደተረጋገጠው፣ ህጻናት አብዛኛውን የገሃዱን ዓለም የመጀመሪያ ዕውቀቶቻቸውን የሚያዳብሩት በቅድሚያ የምሉዕ ምህዳሩን ስሜት ተወራራሽ በሆነ አመክንዮ (transductive logic) በመገንዘብ ነው። ይህም፣ ሁሉም የሰው ፍጡር የሁለንተናዊ አስተሳሰብ ክህሎት በተፈጥሮ የተሰጠው መሆኑን ያሳያል። በመሆኑም፣ ለምንም ዓይነት ዘመናዊ ትምህርት

ሳይጋለጡ በተፈጥሮ የተሰጣቸውን የሁለንተናዊ አስተሳሰብ ክህሎት በህይወት ልምዶቻቸው በማዳበር እጅግ ከፍተኛ የሆነ አስተዋይነታቸውን ያስመሰከሩ የማህበረሰብ አዋቂዎች በሁሉም የህብረተሰብ ታሪክ ውስጥ እንደነበሩ እና አሁንም እንዳሉ ይታወቃል።

x. ሃገር በቀል ዕውቀት በመባል የሚታወቀው የዕውቀት ዘርፍ እነኚህ የማህበረሰብ አዋቂዎች ያመነጯቸው እና በዘመናት ሂደት ውስጥ በማህበራዊ ይሁንታ እና ቅብብሎሽ እየዳበረ ለመጣው የዕውቀት ዘርፍ ዋነኛ ማከማቻዎች (repositories) ናቸው። የዚህ ዕውቀት ዘርፍ ዋነኛው የትንተና መሰረቱ ተፈጥሮአዊው የሁለንተናዊ አመለካከት ክህሎት በመሆኑ በጣም በሚያስገርም ሁኔታ በሃያኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ እየዳበረ ከመጣው ምህዳራዊ ሳይንስ ጋር በአብዛኛው የተጣጣመ ሆኖ ይገኛል።

xi. ባለፉት ጥቂት ዓስርተ ዓመታት በዓለማችን ዙሪያ እየተጠናከረ ከመጣው ተደራራቢ ቀውሶች እና ከምህዳራዊ አስተሳሰብ እየበለጸገ መምጣት ጋር በተያያዘ ለሃገር በቀል ዕውቀቶች የሚሰጠው እውቅና ይበልጥ እየተጠናከረ በመምጣት ላይ ይገኛል። ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ በዘመናዊው ሳይንስ እና ሃገር በቀል ዕውቀቶች መካከል የሚፈጠር ስልታዊ ቅንጅት ዛሬ ለተጋፈጥናቸው በርካታ ውስብስብ ችግሮች ዛላቂ መፍትሔ ለማመንጨት እንደሚያስችል ይታመናል።

## 2. ፖለቲካችን በምህዳራዊ ዕይታ

በክፍል አንድ ውስጥ፣ በተቀነበበ ትንተና ላይ የተመረኮዙት አብዛኞቹ የሳይንስ መስኮች ዛሬ በዓለም ዙሪያ እየተጠናከሩ የመጡትን ውስብስብ የማህበራዊ፣ አካባቢያዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮችን በጥልቀት ለመረዳትም ሆነ መፍትሔ ለመሻት ያለባቸውን ጽንሰ ሃሳባዊ እና የትንተና ዘዴ ውሱንነት ለማሳየት ተሞክሯል። ይህም፣ ከ1960ዎቹ ጀምሮ እየበለጸገ ለመጣው ምህዳራዊ አስተሳሰብ ዋነኛ መሰረት እንደሆነው እና የምህዳራዊ አስተሳሰብ የፍልስፍና እና የሳይንስ መሰረቶችንም በመጠኑ ዳሥናል። ባላፉት ዓመታት ውስጥ በርካታ ምሁራን በኢትዮጵያ የፖለቲካ ችግሮች እና መፍትሔዎቻቸው ላይ የተለያዩ ጽሁፎች እና ትንተናዎች አቅርበዋል። አብዛኞቹ ትንተናዎች የችግሮቹ ዋነኛ መነሻ የአመለካከት መሆኑን የሚያመላክቱ ቢሆንም የህመሙን ምንጮች ካንድ ወይንም ከሌላ የፖለቲካ ድርጅት ከዚያም ከፍ ሲል ከአንድ ወይንም ከሌላ ትውልድ ጋር ሲያያይዙት ይስተዋላሉ። በዚህ ፀሃፊ እምነት ይህ የሆነበት ዋነኛ ምክንያት አብዛኞቹ ከሰለጠኑበት የሙያ መስክ ወይንም የፖለቲካ አመለካከት ጋር በተያያዘ ከሚከተሉት የተቀነበበ ትንተና (reductionist analysis) ነው። በተለያየ ጥናት እንደተረጋገጠው ከፍተኛ ውስብስብነት ላላቸው ችግሮች እንዲህ አይነቱን ትንተና መጠቀም ከፊል እውነታን ከማሳወቅ ባሻገር መሰረታዊ መፍትሔዎችን የማመላከት ውሱንነት ይኖረዋል። እንዲህ ዐይነቱን የትንተና ውሱንነት መሻገር የሚቻለው በምህዳራዊ አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ትንተና በማካሄድ ብቻ ይሆናል።

ምህዳራዊ አስተሳሰብ ለትንተና ከሚጠቀምባቸው ተምሳሌታዊ የተፈጥሮ ክስተቶች አንደኛው በምስል ሁለት የሚታየው የበረዶ ቋጥኝ[8] (Iceberg) ምስል ነው። በውቅያኖስ ውስጥ የሚገኙ የበረዶ ቋጥኞች አብዛኛው አካላቸው በውሃው ተሸፍኖ ከውሃው ጠለል በላይ የሚታየው አካላቸው እጅግ በጣም አነስተኛው ነው። ይህንን እውነታ ባለማስተዋል፣ በርካታ የባህር ልምዳቸው አነስተኛ በሆኑ ካፒቴኖች የሚመሩ መርከቦች እና በአካላዊ ታላቅነታቸውን ሊይደፈሩም ተብለው የታመኑ መርከቦች ፍጻሜአቸው አሳዛኝ ሆኗል። ለዚህም እንደማሳያ፣ በዘመኑ ታላቅ የተባለችውን የታይታኒክ[9] አሳዛኝ ፍጻሜ ያስታውሷል። በሃገሮች ታሪክ ውስጥም፣ ታላቅነታቸውን ከላይ ላይ በሚታዩ ሁነቶች ላይ የገነቡ የፖለቲካ ድርጅቶች እና አምባገነን መንግስታትም በተመሳሳይ ሁኔታ ሲወድቁ እና ሲከስሙ ታይተዋል።

---

[8] የበረዶ ቋጥኝ (Iceberg) ከዓለማችን ሰሜናዊ እና ደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ከሚገኘው የበረዶ ግግር እየተገመሰ በመውጣት በውቅያኖስ ውስጥ የሚንሳፈፍ ከአነስተኛ ጉብታ አስከ ከፍተኛ ጋራ የሚያክል መጠን ያለው የበረዶ አካል ነው።

[9] ታያታኒክ (Titanic) እ.ኤ.አ. በ1911 በእንግሊዝ ሃገር የተሰራ በወቅቱ የዓለም ግዙፍ የመጓጓዣ መርከብ ሲሆን እ.ኤ.አ. በ1912 በሽዎች የሚቆጠሩ ተሳፋሪዎችን በመያዝ የመጀመሪያውን ጉዞ ወደ አሜሪካ ሃገር ባደረገበት ወቅት፣ ግዙፍነቱን ከባህር ወለል በታች ከከለለ የበረዶ ቋጥኝ ጋር በመላተም ሊሰጥም ችሏል።

የዚህ ተምሳሌታዊ ምስል ዋነኛው ትኩረት ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ አንድን የፖለቲካ ምህዳር የመተንተኛ መንገድ ለማሳየት ነው።




ምስል 2፡ የፖለቲካ ምህዳር የበረዶ ቋጥኝ (Iceburg)

አንድን የፖለቲካ ምህዳር በምህዳራዊ ትንተና መነጽር ስንመለከት አራት አበይት ክፍሎች እናገኛለን። የመጀመሪያው ከማንኛውም ሰው የዕለት ተዕለት ህይወት ጋር በቀጥታ ወይንም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የተያያዙ እና በቀላሉ ሊታዩ የሚችሉ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ሁነቶች ናቸው። ባንድ ወቅት እና አካባቢ የሚከሰት የተፈጥሮ ድርቅ፣ የኑሮ ወድነት፣ የወንጀል መስፋፋት፣ እና የፀጥታ መደፍረስ ለዚህ ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ። በአንድ የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ እንዲህ ዓይነት ሁነቶች በተደጋጋሚ በሚከሰቱበት ወቅት ጥልቅ የሆነ የአመለካከት እና መዋቅራዊ ህመምን የሚያመላክቱ ሂደቶችን ይፈጥራሉ። ሁነቶችም ሆኑ ሂደቶች በአብዛኛው በግልጽ የሚታዩ እና ለስሜታዊ ምላሽ የሚያነሳሱ ናቸው። ያንድን የፖለቲካ ምህዳር መሰረታዊ ህመሞች ለመረዳት ግን ሥልታዊ በሆነ መንገድ የሁነቶችን እና ሂደቶችን ጤናማነት ወይንም ታማሚነት የሚወስኑትን እና ጥልቀት ያላቸውን መዋቅራዊ እና ያስተሳሰብ ምንጮችን መመርመር ያሻል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት በሃገራችን ገንነው የሚታዩ የፖለቲካ ውይይቶች እና መጣጥፎች በአብዛኛው የሚያተኩሩት የተናጠል ሁነቶችን እና ሂደቶችን በመተንተን እና የግልም ሆነ የድርጅት አቋምን ማንጸባረቅ ላይ ሆነው ይታያሉ። ይህም በመሆኑ፣ ባሁኑ ሰዓት አብዛኛው የፖለቲካ ንግግሮቻችን (discourses) ከሚዛናዊነት ይልቅ ስሜታዊነት፣ ከሩቅ አላሚነት ይልቅ ቅርብ አዳሪነት፣ ከአካታችነት ይልቅ አግላይነት ጎልቶ ይታይባቸዋል። ይህም፣ ሃገሪቱን ከዕለት ወደ ዕለት ወደ ተባባሰ ቀውስ እየከተታት ይገኛል።

ሃገራችን አሁን በምትገኝበት ወሳኝ የፖለቲካ ምዕራፍ በእጅጉ የሚያስፈልገን በየቦታው እየተከሰቱ ላሉት አሳዛኝ የህዝቦች ግጭት እና መፈናቀል ሁነቶች እና ሂደቶች ዋነኛ ምንጭ የሆኑትን መዋቅራዊ ችግሮች፣ ለነኚህ መዋቅራዊ ችግሮች መነሻ የሆኑትን የአስተሳሰብ ምንጮችን መረዳት እና ለዚህም የሚመጥን አካታች እና ፋና-ወጊ መፍትሔዎች መሻት ነው። ይህም እንዲሳካ፣ እያንዳንዱ የፖለቲካ ተዋናይ ያሉትን አስተሳሰቦች እና እምነቶች ከምህዳራዊ አስተሳሰብ መርሆዎች አኳያ ሊመረምራቸው እና ሊፈትሻቸው ይገባል።

## *2.1 የህመሞቻችን ምንጮች*[10]

የሃገራችንን የፖለቲካ ችግሮች በመሰረታዊ ሁኔታ ለመፍታት የመጀመሪያው እርምጃ የበሽታው ዋነኛ ምንጮች የሆኑ የአመለካከት እና የዕምነት መሰረታዊ እሴቶችን (values) መመርመር ያስፈልጋል። እነኚህ እሴቶች፣ በሀገሪቱ ውስጥ ለረጅም ዘመን ተንሰራፍተው ከቆዩት የአስተዳደር፣ የዕምነት፣ የትምህርት፣ የባህል እና የልማድ ሥርዓት ጋር በጥብቅ የተሳሰሩ ናቸው። የበርካታ ብሔረሰቦች ሃገር የሆነችው ሃገራችን ኢትዮጵያ፣ የብዙ ጠቃሚ እና ድንቅ እሴቶች ባለቤት እንደሆነች ይታመናል። እንዳለመታደል ሆኖ፣ የሃገራችን ዘመናዊ ፖለቲካ፣ ጠቃሚ በሆኑ ዕሴቶቻችን ላይ ከመገንባት ይልቅ ጎጂ በሆኑ ውርሶቻችን ተተብትቦ ይገኛል። ለዚህ እንደ ዋነኛ ምክንያት ሊጠቀሱ የሚችሉ በርካታ አባባሽ ሁኔታዎች ቢኖሩም፣ ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ የችግሮቹ ዋነኛ አእምሮአዊ ምንጮች የሚከተሉት ሶስት አበይት ፈተናዎች ናቸው።

***ጭፍን እመርታዎች፡*** የኢትዮጵያ ዘመናዊ ፖለቲካ ከዘመናዊው የትምህርት ሥርዓት መጀመር ጋር በጥብቅ የተሳሰረ መሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ነው። በዘመናዊው የትምህርት ሥርዓታችን ውስጥ ያለው አንዱ መሰረታዊ ችግር የትምህርት ይዘቱንም ሆነ አሰጣጡን ከሃገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ እና ሃገር በቀል እውቀት ክምችት ጋር ለማጣጣም እና ለማዋሃድ የተደረገው ጥረት ውሱን መሆኑ ነው። ይህም በመሆኑ የሃገሪቱ የተማረ የሰው ሃይል የሃገሪቱን የልማት ችግሮች ለመፍታት ካለው የእውቀት አቅም ውሱንነት ባሻገር ባብዛኛው ጭፍን የሆነ የድንበር ተሻጋሪ ዘመናዊነት አምላኪ ሊሆን ችሏል። ይህ መሰረታዊ ህመም በዘመናዊው የፖለቲካ አስተሳሰባችንም ላይ በተናጠከረ ሁኔታ ታይቷል። በመሆኑም፣ ከ1950ዎቹ ጀምሮ ከሃገራዊ እውነታ እና ተጨባጭ የህዝብ ፍላጎት ጋር የማይጣጣሙ የፖለቲካ አስተሳሰቦች እና የማህበረሰብ እድገት ሞዴሎችን በጅምላ እና በጭፍን ተቀብሎ ማህበራዊ መሰረቱን ግምት ውስጥ ሳያስገቡ ለማራመድ እና ለመተግበር መሞከር የፖለቲካችን ዋነኛው መለያ ሊሆን ችሏል። እንዲህ ዓይነቱ አመለካከትም፣ ከ1960ዎቹ ጀምሮ በሃገራችን ለተፈጠሩት የፖለቲካ ምስቅልቅሎች ታላቁን ድርሻ እንዳበረከተ ይታመናል።

[10] የዚህ ክፍል አብዛኛው፣ ሐምሌ ፲፩ ቀን 2012 በወጣው አዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ ታትሟል።

ይህ ህመም በአሁኑ ወቅትም አብዛኛዎቹ የሃገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች በሚያራምዷቸው የፖለቲካ ፕሮግራሞች እና ፖሊሲዎች ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ሲያሳድር ይስተዋላል። ከተለያዩ ሃገሮች ማህበረሰባዊ ተመክሮ እና የእውቀት ክምችት መማር እና ጠቃሚውን መርጦ መውሰድ አስፈላጊ መሆኑ አጠራጣሪ አይደለም። ነገር ግን ይህንን እውቀት ከሃገራዊው እውነታ እና የእውቀት መሰረት ጋር ማጣጣም እና ማዋደድ ዘላቂ እና አስተማማኝ የሆነ እድገት ለማምጣት እጅግ በጣም ወሳኝነት ያለው መሆኑን ባለፉት ሰባ ዓመታት ከፍተኛ እድገት ካስመዘገቡ ሃገራት ልምድ መረዳት ይቻላል"። ከዚህ የጭፍን እመርታ ህመም መላቀቃችን የሃገራችን ፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ እድገት መስመርን ለማቃናት ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል።

***ባላባታዊ የፖለቲካ ቅሪቶች፡*** ዘመናዊው ፖለቲካ ምናልባትም ካንድ ምዕተ ዓመት ያልዘለለ እድሜ ያለው ቢሆንም፣ ሃገሪቱ ካላት የረጅም ዘመን ታሪክ ጋር በተያያዘ ስር የሰደዱ ከባቢያዊ የፖለቲካ ባህሎች እንዳሏት አይካድም። ከነዚህም ውስጥ፣ ለሃገሪቱ የወደፊት እድገት ጠቃሚ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ በርካታ አስተዳደራዊ ሥርዓቶች እና ልማዶች የመኖራቸውን ያክል ለዘመናት ተንሰራፍቶ የኖረ ባላባታዊ የፖሊቲካ ባህልም ነበረ። የሚያሳዝነው ነገር፣ የዘመናዊው ፖለቲካ አራማጅ ሆኖ የተነሳው የ1960ዎቹ (የእኔ) ትውልድ በሃገሪቱ ከነበሩት የዘመናት ሃገራዊ የአስተዳደር እና የፖለቲካ ልምዶች ጠቃሚውን ከመውሰድ ይልቅ በሚያስገርም ደረጃ የባላባታዊው የፖለቲካ ባህል እስረኛ መሆኑ ነው። ይህም በመሆኑ፣ አብዛኞቹ አንጋፋ የፖለቲካ ድርጅቶች በተሟላ ነፃነት ላይ ከተመረኮዘ ፖለቲካዊ አካሄድ ይልቅ ፖለቲካዊ ጭሰኝነትን (political serfdom) የሚያራምድ የፖለቲካ ሂደት ሲተገብሩ ኖረዋል።

እስከ ዛሬም ድረስ በፖለቲካችን ውስጥ ስር ሰዶ የሚታየው የመጠፋፋት ፖለቲካ የዚሁ ባላባታዊ ፖለቲካ ቅሪት ውጤት መሆኑ አያጠያይቅም። ባለፉት ሃምሳ እና ስልሳ ዓመታት ውስጥ እንዲህ አይነቱን ፖለቲካዊ ጭሰኝነት አንቀበልም ብለው የተነሱ በርካታ ወጣቶች በየራሳቸው ድርጅቶች መቀጠፋቸውም የፖለቲካችን አንዱ አሳዛኝ ገጽታ ነው[12]። በአሁኑ ወቅት ከዚህ ባላባታዊ የፖለቲካ ቅሪት ነፃ የሆኑ ወጣት ፖለቲከኞች እና የህብረተሰብ መሪዎች በአንዳንድ ድርጅቶች አካባቢ ብቅ ያሉ ቢሆንም በተመሳሳይ ፈተና እንዳይጠለፉ ከፍተኛ ሲጋት አለ። ስለሆነም፣ ሁሉም የፖለቲካ እና የማህበረሰብ መሪዎች በተለይም ወጣት ፖለቲከኞቻችን ከእንደዚህ ዓይነቱ በሽታ ራሳቸውን ለማንጻት መጣር ይኖርባቸዋል።

[11] በዚህ ረገድ፣ ጃፓን እና ቻይናን ጨምሮ ከ1950ዎቹ ወዲህ ከፍተኛ እድገት ያስመዘገቡት የሩቅ ምስራቅ ሃገሮች ይጠቀሳሉ።

[12] ይህ ጉዳይ፣ አብዛኞቹ በኢትዮጵያ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ሁነኛ ስፍራ የነበራቸው ድርጅቶች ንስሃ ሊገቡበት የሚገባ ነው።

***የተቀነበበ ትንተና፡*** በዚህ ክፍል መግቢያ ላይ ለማሳየት እንደተሞከረው፣ ያንድን ፖለቲካ ምህዳር መሰረታዊ ችግሮች ባግባቡ ለመረዳት እና ዓይነታዊ ለውጥ ለማምጣት ከሁነት እና ሂደቶች ባሻገር ጠልቆ በመመልከት መሰረታዊ የሆኑ መዋቅራዊ ምንጮችን እና የአመለካከት ሞዴሎችን መመርመር ያሻል። እንዲህ ዓይነት አተናተን በተለይም ሁነቶች እጅግ ፈጣን በሆነ ሁኔታ በሚፈጠሩበት እና ሂደቶችም በሚቀያየሩበት የሽግግር ወቅት እጅግ አስፈላጊ ይሆናል። ባላፉት ጥቂት ዓመታት የሚወጡ የፖለቲካ ትንተናዎች እና ጥናቶች ባብዛኛው በተናጠል ሁነቶች እና ሂደቶች ላይ በሚያተኩር የተቀነበበ ትንተና ላይ የተመረኮዙ በመሆናቸው የፖለቲካውን ግለት ከማፋፋም ያለፈ አስተዋጽኦ ሊያረጉ አልቻሉም። በመሆኑም በተቀነበበ ትንተና ላይ ተመስርቶ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ችግሮች ለመተንተን የተደረጉት ጥረቶች ምሉእነት የጎደላቸው ከመሆናቸውም ባሻገር ብዙዎቹ እጅግ ተቃራኒ የሆኑ ማጠቃለያዎች እና አቋሞች እንዲወስዱ አድርጓቸዋል። በዚህ ረገድ የሃገሪቱ ምሁራን እና የሚዲያ ሰዎች ባንድ አቅጣጫ የተቀነበበ ትንተና (linear thinking) ላይ የተመረኮዘ ፖለቲካዊ ትንተናዎች ከመስጠት መታረም እና ዙሪያ መለስ እይታ ሊሰጥ በሚችለው ሁለንተናዊ አስተሳሰብ ለመታነጽ ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል።

በጥቅሉ፣ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን አበይት ህመሞች እና ሌሎችንም በጥልቀት ፈትሾ መድሃኒት መሻት የሀገሪቱን ፖለቲካ ወደበሰለ እና የተረጋጋ የፖለቲካ ስርዓት ለማሸጋገር የመጀመሪያው አስፈላጊ እርምጃ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሂደት ለፖለቲካ መሪዎች ብቻ የሚተው ሳይሆን ሁሉም ባለድርሻ አካላት በእውቀት እና አስተውሎት ላይ ለተመረኮዘ ውይይት እና መግባባት የየበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ይህንንም ዘመኑ በሚጠይቀው እውቀት ላይ ተመርኩዞ ለማካሄድ በምህዳራዊ አስተሳሰብ መመራት ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ ይታመናል። በሚቀጥለው ክፍል ለዚህ ሂደት ከሚያግዙ መሰረታዊ የምህዳራዊ አስተሳሰብ መርሆዎች ዋና ዋናዎቹን እንመለከታለን።

## 2.2 የምህዳራዊ አስተሳሰብ ዓበይት መርሆዎች[13]

ቀደም ባለው ክፍል፣ ምህዳራዊ አስተሳሰብ የሃገራችንን የፖለቲካ ህመሞች በአግባቡ ለመረዳት የሚኖረውን አስተዋጽኦ በመግለጽ በዚሁ እይታ ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ዋነኛ የፖለቲካ ህመሞቻችንን ለማመላከት ተሞክሯል። በዚህ ክፍል ከምህዳራዊ አስተሳሰብ መርሆዎች መካከል ለሃገራችን የፖሊቲካ ህመሞች ፈውስ ለማግኘት ይረዳሉ ከሚባሉት አበይቶቹን እንዳስሳለን። እነኚህ መርሆዎች በማንኛውም የተፈጥሮ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ እና ፖለቲካዊ ምህዳሮች ላይ ሊተገበሩ የሚችሉ መሰረታዊ መርሆዎች በመሆናቸው አንባቢዎች በግልም ሆነ በሙያ ህይወታቸው ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ።

***ክፋይነት እና ምሉእነት፡*** በምህዳራዊ አስተሳሰብ መሰረት፣ ማንኛውም ምህዳር በአንድ ተመሳሳይ ወቅት በራሱ ምሉእ (whole) ሆኖ የሚቆም ሲሆን በተመሳሳይ ወቅት የሌላ ከፍ ያለ ምህዳር ደግሞ ክፋይ አካል (part) ነው። በዚህ መሰረት ክፋዮች የማንኛውም ምሉዕነት መሰረቶች ሲሆኑ እነኚህ ምሉዕነቶች ግን ከክፋዮቹ ተደማሪነት በላይ የሆነ ልዕልና ይኖራቸዋል። በተጨማሪም፣ በአንድ ምህዳር ውስጥ በሚኖሩ ክፋዮች መካከል የሚኖረው የማያቋርጥ መስተጋብር በአጠቃላይ በምሉዕ ውስጥ ለሚኖረው መሰረታዊ ለውጥ ዋነኛው ምንጭ ስለሆነ በክፋዮቹ መካከል ያለውን መስተጋብር በጥልቀት መረዳት፣ ምሉዕ ምህዳሩን በአግባቡ ለመረዳት እና ለመምራት ቁልፍ ጉዳይ ነው።

ይህንን በምሳሌ ለማስረዳት፣ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያሉ አባላት እያንዳንዳቸው ራሳቸውን የቻሉ ምሉእ ሰው ሲሆኑ፣ ቤተሰብ የተባለው ከፍ ያለ ምሉእ ምህዳር ደግሞ ክፋይ ናቸው። ነገር ግን፣ ቤተሰብ በደፈናው የሰዎች ስብስብ ሳይሆን በያንዳንዱ የቤተሰብ አባል መካከል በሚኖረው መስተጋብር እና መተሳሰር የሚገለጽ ምህዳር ነው። ስለሆነም አንድን ቤተሰብ በአግባቡ ለማስተዳደር፣ እያንዳንዱን የቤተሰብ አባል እንደምሉእ ሰውነቱ መረዳት እና በሁሉም የቤተሰብ አባላት መካከል የሚኖረውን መስተጋብር በአግባቡ መገንዘብ እና መያዝ ይጠይቃል። በተመሳሳይ፣ ቤተሰቦች ወደ ማህበረሰብ፣ ማህበረሰቦች ወደ ብሔረሰብ፣ ብሔረሰቦች ደግሞ ከሁሉም ከፍ ያለ ልዕልና ወዳለው ሃገረሰብ ያድጋሉ ማለት ነው። በክፋይነት እና ምሉዕነት መርህ መሰረት፣ እንደኢትዮጵያ ባሉ የበርካታ ብሔረሰቦች ሃገር ውስጥ አካታች እና ውጤታማ የሆነ ሥርዓተ-መንግስት ለመገንባት የእያንዳንዱን ብሔረሰብ ምሉእነት ከሀገራዊው ልዕልና ጋር የሚያጣጥም የፖለቲካ ሥርዓት መገንባት የግድ ይሆናል።

[13] የዚህ ክፍል አብዛኛው፣ ሐምሌ 18 ቀን 2012 በወጣው አዲስ አድማስ ጋዜጣ የተነበበ ነው።

***አንፃራዊ ዕውነት፡*** በዚህ መርህ መሰረት፣ ሁሉም ምህዳሮች ቀጣይ በሆነ የለውጥ ሂደት ውስጥ ስለሆኑ ሁሉም እውነቶች አንጻራዊ ከመሆናቸውም በላይ አንድ እውነታ (reality) ከአንድ በላይ በሆኑ (multivalent) እውነቶች ሊገለጽ ይችላል። በዚህም የተነሳ፣ አብዛኛው ገሃዱ ዓለም በግራጫው ማእቀፍ (grey-zone) ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ጥቁር ወይም ነጭ እውነታ ቅጽበታዊ የሽግግር ሁነት (Transient state) መገለጫ ብቻ ነው። በሳይንሱ ዓለምም ያለው እውነት በአብዛኛው አንጻራዊ ሲሆን፣ ፍጹም እውነት የሚገኘው በሂሳባዊው ቀመር (mathematical models) ውስጥ ብቻ ነው። ይህ ዕውነታ፣ በተለይም እጅግ ተለዋዋጭ በሆነ የፖለቲካ ምህዳር ላይ ገኖ የሚታይ ባህርይ በመሆኑ ይህንን መገንዘብ የአንድን የፖለቲካ ማህበረሰብ ጤናማነት ሊወስኑ ከሚችሉ ዓበይት ጉዳዮች ዋነኛው ነው።

የሃገራችን ፖለቲካ አንዱ ልዩ መገለጫ፣ አብዛኞቹ ፖለቲከኞቻችን ሌላው ወገን አለኝ የሚለውን እውነት ለማዳመጥ ዝግጁ አለመሆን ብቻ ሳይሆን የራሳቸውን ‘እውነት’ በሌላው ላይ በጉልበት ለመጫን በሚሄዱበት ርቀትም ነው። እንዲህ አይነቱ አመለካከት ከ1960ዎቹ ጀምሮ እሰከ አሁን ድረስ ከፍተኛ ዋጋ ሲያስከፍለን ቆይቷል። ከዚህ በሽታ ለመላቀቅ ብዙዎቹ ፖለቲከኞቻችን በከፍተኛ ደረጃ ከተጠናወታቸው ‘የእኔ ብቻ እውነት’ ከሚለው አመለካከት ተላቀው የሌላውንም ወገን ‘እውነት’ ለመስማት ዝግጁ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ይህንንም በማድረግ፣ አንድን ጉዳይ ከተለያየ አቅጣጫ በመመልከት እና በመረዳት ለእውነታው በይበልጥ የሚቀርብ መግባቢያ ሃሳብ ላይ መድረስ እና ለፖለቲካ ችግሮቻችን ተስማሚ የሆኑ መፍትሔዎችን ማመንጨት ይቻላል።

***ብዝሃነት እና ምህዳራዊ መረጋጋት (stability)፡*** በዚህ መርህ መሰረት፣ ብዝሃነት (diversity) የማንኛውም ምህዳር የመረጋጋት እና የዘላቂነት ዋነኛ መነሻ ምንጭ ነው። ይህም ማለት፣ በማንኛውም ምህዳር ውስጥ የሚኖረው ብዝሃነት ወደ ተሻለ ሥርዓት ለመሻገር የሚያስችል መወራረስ እና መዳቀል ከማሳለጡም በላይ ምህዳራዊ መረጋጋትን እና ሚዛናዊነትን ለማረጋገጥ ያግዛል። ከዚህ በተቃራኒው፣ በአንድ ወጥነት (monocultural) ላይ የተመረኮዘ ምህዳር ለመውደቅ (crash) እና ከዚህም ከከፋ ለመጥፋት (extinction) አደጋ የተጋለጠ ይሆናል። ከዚህ አኳያ፣ በሃገራችን የሚገኘው የሥነምህዳር፣ የቋንቋ፣ የባህል፣ እና የሃይማኖት ብዝሃነት ለሃገሪቱ ቀጣይ እና ዘላቂ እድገት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው መሰረት ሊሆን እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል። ይህ ግን ሊሆን የሚችለው የነኚህን ብዝሃነት ጠቀሜታ ባግባቡ ተረድቶ የእርስ በርስ ተደጋጋፊነታቸውን እና ተወራራሽነታቸውን በሚያጠናክር ህገ መንግስታዊ ሥርዓት ሲደገፉ ብቻ ነው። ከዚህ በተቃራኒው፣ በአሃዳዊነት ወይንም  አሁን ባንዳንድ የክልል ፖለቲካ አራማጆች እንደሚታየው ‘ራስን በራስ ማስተዳደር’ በሚል ሽፋን ‘አንድ ወጥነትን’ ለመፍጠር የሚደረገው ጥረት ያንኑ ማህበረሰብ በከፍተኛ ደረጃ ሊጎዳው እና ከከፋም ሊያጠፋው እንድሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል።

***ትብብር እና ፉክክር፡*** በዚህ መርህ መሰረት፣ የማንኛውም ምህዳር ውጤታማነት እና ዘላቂነት የሚወሰነው በክፋዮቹ መካከል ለሚኖረው ትብብር እና ፉክክር በሚኖረው አያያዝ ውጤታማነት ይሆናል። በክፋዮቹ አካላት መካከል የሚኖረው ትብብር የምህዳሩን አሰራር ውጤታማነት እና መረጋጋት (efficiency and stability) የሚወስን መሰረታዊ ጉዳይ ሲሆን በነኚሁ ክፋዮች መካከል የሚኖረው ፉክክር እና ውድድር ደግሞ ለምህዳሩ ቀጣይ እድገት አስፈላጊ ለሆነው ፈጠራ (innovation) ዋነኛ መሰረት ነው።

በዚህ መሰረት፣ በአንድ ሃገር ውስጥ የሚኖረው የፖለቲካ ምህዳር ጤናማነት የሚወሰነው በፓርቲዎች መካከል ሊኖር በሚገባው የመተባበሪያ ማእቀፍ ጥንካሬ እና በመወዳደሪያ ሜዳው አካታችነት ይሆናል። የአንድ ሃገር ህገመንግስት የፓርቲዎችን የመተባበሪያ ማዕቀፍ የሚወስን ዋነኛ መሰረት ሲሆን በማናቸውም ሁኔታ ዘላለማዊ ምሉዕነት ሊኖረው አይችልም። በመሆኑም በሁሉም ወገኖች ተሳትፎ እና ቅቡልነት ባለው አካሄድ በቀጣይነት መዳበር ይኖርበታል። ይህንን ሂደት በመወዳደሪያነት ለህዝብ ድምጽ መቅረብ ከሚገባቸው የፓርቲ ፕሮግራሞች እና ፖሊሲዎች መለየትም እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። የሃገራችን የፖለቲካ ምስቅልቅል አንደኛው ምንጭ ይህንን ሃገራዊ የመተባበሪያ ማዕቀፍ ከፓርቲዎች የመወዳደርያ ፕሮግራም ጋር ከማደበላለቅ የሚመነጭ ነው።

***መዘርዝራዊ እና መስተጋብራዊ ውስብስብነት፡*** በዚህ መርህ መሰረት፣ በአንድ ምህዳር ውስጥ ባለ መዘርዝራዊ (detailed) እና በመስተጋብራዊ (dynamic) ውስብስብነት መካከል ሊኖር የሚችለውን ግንኙነት እና ልዩነት መረዳት አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታል። ይህም ማለት፣ ለአንድ ውስብስብ ሁኔታ ሁለንተናዊ መፍትሔ ለማግኘት ከተናጠል ሁነቶች (events) እና ድግግሞሽ (patterns) ባሻገር በመመልከት መዋቅራዊ ምንጮችን በጥልቀት መመርመር እና መፍታት የግድ ይላል። በተናጠል ሁነቶች ላይ ተመርኩዞ ሃገራዊ መፍትሔ ለመሻት የሚደረጉ ጥረቶች መውጫ ወደሌለው መዘርዝራዊ ውስብስብነት ይከታል። ከዚህ ይልቅ፣ የአመለካከት እና መዋቅራዊ ችግሮችን በመመርመር በርካታ ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችሉ ልዩ ቋጠሮዎችን (dynamic knots) መፍታት ይቻላል።

በዚህ ሂደት ውስጥ፣ አንድን ውስብስብ ሁኔታ ለመፍታት ካንድ በላይ የመፍትሔ መንገዶች ሊኖሩ እንደሚችሉ መገንዘብ ይገባል። እስከአሁን ድረስ ለኢትዮጵያ የፖለቲካ ችግሮች የሚጠቆሙ መፍትሄዎች በአብዛኛው ወይ በአንድ ከፍል ወገናዊነት ላይ የተመረኮዙ ምሉዕነት የጎደላቸው ይሆናሉ አለዚያም ሁሉንም ዝርዝር ጥያቄዎች በአንድ ጊዜ ለመመለስ በሚያደርጉት ጥረት መያዣ መጨበጫው የጠፋበት የመፍትሄ ሃሳብ ሆነው ይገኛሉ። በአንዳንድ ሁኔታም፣ መፍትሔ ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው የሚወሰዱ እርምጃዎች ችግሩን ይበልጥ ሲያወሳስቡት ይታያል።

***ተመክሮአዊ መማማር*** *(adaptive learning)*፡ በዚህ መርህ መሰረት፣ ውጤታማ ተመክሮአዊ የመማማር ስርአት ያለው ምህዳር ያልተቋረጠ እና ቀጣይነት ያለው ሽግግር ለማረጋገጥ ከፍተኛ አቅም ይኖረዋል። ይህም ማለት፣ ጠቃሚ መረጃዎችን በስርዓት የሚያደራጅ፣ የሚያጠራቅም እና ካንድ ትውልድ ወደ ሌላው ትውልድ የሚያሸጋግር ምህዳር ላልተቋረጠ እና ቀጣይ ለሆነ ሽግግር ጥሩ መሰረት ይኖረዋል። እዚህ ላይ፣ ማንኛውም አይነት የፖለቲካ ምህዳር፣ የመጠኑ መብዛት እና ማነስ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የራሱ የሆነ መልካም እና ጎጂ ጎኖች ሊኖሩት እንደሚችሉ መረዳት ያስፈልጋል። እንዳለመታደል ሆኖ፣ የዘመናዊ ፖለቲካ ታሪካችን በአብዛኛው የነበረውን ከመሰረቱ አፍርሶ እንደ አዲስ የመጀመር በሽታ የተጠናወተው ነው።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ ሃገር በቀል የእውቀት ስርአቶች በትውልድ የዳበሩ ጠቃሚ መረጃዎች በማከማቸት እና ለቀጣይ ትውልድ በማሸጋገር ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። ነገር ግን፣ የሃገራችን የፖለቲካ ባህል ሃገር በቀል እውቀቶችንም ሆነ ጠቃሚ የፖለቲካ ተመክሮዎችን ባግባቡ አድራጅቶ በመጠቀምም ሆነ ለተተኪው ትውልድ በማስተላለፉ ረገድ ከፍተኛ ድክመት ያለበት ነው። ይህንን ችግር ለማስወገድ፣ አንጋፋ ፖለቲከኞቻችን ካለፈው ትውልድ በጎም ሆነ ክፉ ተመክሮዎች ልንማር የሚገባንን በቅንነት በማስተማር፤ ወጣት የፖለቲካ መሪዎቻችንም በበጎው ተመክሮ ላይ ለመገንባት እና ጎጂ ታሪካችንን ላለመድገም ብርቱ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

በአጠቃላይ፣ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት መርሆዎች በተቀናጀ መልኩ ከተተገበሩ፣ ቀደም ሲል የተጠቀሱትን መሰረታዊ የፖለቲካ ህመሞቻችንን በማከም የወደፊቱን የሃገራችንን የፖለቲካ ምህዳር በጤናማ መሰረት ላይ ለመገንባት ያግዛሉ ተብሎ ይታመናል። ለዚህም ተግባራዊነት፣ የፖለቲካ መሪዎች፣ ምሁራን፣ አንቂዎች እና ተንታኞች ጥልቀት እና ብስለት በሚጎድላቸው አመለካከቶች ላይ ተመርኩዞ ህዝብን፣ በተለይም ወጣቱን ትውልድ ስሜታዊ ለሆነ እንቅስቃሴ ከማነሳሳት ሊቆጠቡ ይገባል።

## የከፍል ሁለት ቁልፍ ሃሳቦች

i. ምህዳራዊ አስተሳሰብ ለትንተና ከሚጠቀምባቸው ተምሳሌታዊ የተፈጥሮ ክስተቶች አንደኛው የበረዶ ቋጥኝ (Iceberg) ተምሳሌታዊ ትንታኔ ነው። አብዛኛዎቹ በውቅያኖስ ውስጥ የሚገኙ የበረዶ ቋጥኞች አብዛኛው አካላቸው በውሃው ተሸፍኖ ከውሃው ጠለል በላይ የሚታየው አካላቸው እጅግ በጣም አነስተኛው ነው። በዚህም የተነሳ፣ በርካታ የባህር ልምዳቸው አነስተኛ በሆኑ ካፒቴኖች የሚመሩ እና በአካላዊ ታላቅነታቸው አይደፈሩም ተብለው የታመኑ መርከቦች ፍጻሜአቸው አሳዛኝ ሆኗል።

ii. አንድን የፖለቲካ ምህዳር በምህዳራዊ ትንተና መነጽር ስንመለከት አራት አበይት ክፍሎች እናገኛለን። የመጀመሪያው ከማንኛውም ሰው የዕለት ተዕለት ህይወት ጋር በቀጥታ ወይንም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የተያያዙ እና በቀላሉ ሊታዩ የሚችሉ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ሁነቶች (events) ናቸው። ሁነቶችም ሆኑ

ሂደቶች (patterns) በአብዛኛው በግልጽ የሚታዩ እና ለስሜታዊ (emotive) ምላሽ የሚያነሳሱ ናቸው።

iii. ያንድን የፖለቲካ ምህዳር መስረታዊ ህመሞች ለመረዳት እና መፍትሔ ለመሻት ግን ሥልታዊ በሆነ መንገድ የሁነቶችን እና ሂደቶችን ጤናማነትንም ሆነ ታማሚነት የሚወስኑትን መዋቅራዊ (structural) እና አእምሮአዊ ምንጮችን (mental models) መመርመር ያሻል።

iv. ባለፉት ጥቂት ዓመታት በሃገራችን ገነው የሚታዩ የፖለቲካ ውይይቶች እና መጣጥፎች በአብዛኛው የሚያተኩሩት የተናጠል ሁነቶችን እና ሂደቶችን በመተንተን እና በዚህም ላይ ተመርኩዘው ጥቅል የፖለቲካ አቋምን ማንጸባረቅ ላይ ሆነው ይታያሉ። እንዲህ አይነቱ የፖለቲካ ነጥብ የማስቆጠሪያ አካሄድ በብሔራዊ መግባባት ላይ የተመሰረተ እና የተረጋጋ ሃገራዊ የፖለቲካ ሥርዓት ባለበት ሁኔታ ውስጥ ጠቃሚ እና የፖለቲካውም አካሄድ ዋነኛ መገለጫ ሊሆን ይችላል። ዴሞክራሲያዊው ሥርዓት ባልደረጀበት ሁኔታ ግን ጽንፍ ለያዘ ንትርክ ከማጋለጡ ባሻገር፣ ለተባባሰ የፖለቲካ ቀውስ ሊያጋልጥ ይችላል።

v. ለኢትዮጵያ የፖለቲካ ህመሞች ዋነኛ ምንጭ ከሆኑት አእምሮአዊ ምንጮች ቀዳሚዎቹ፤ ከሃገራዊው እውነታ ያልተጣጣሙ ጭፍን የአስተሳሰብ እመርታዎች፣ ለረጂም ዘመናት በሃገሪቱ ተንሰራፍቶ የኖረው ባላባታዊ የፖለቲካ ባህል፣ እና ውስብስብ ለሆነው የሃገሪቱ የፖለቲካ ችግር ቀላል የሆነ የፖለቲካ መፍትሔዎች ለመሻት እና ለማራመድ የተደረጉ ጥረቶች ናቸው። የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ፣ ፖለቲካችንን ከመነሻው የተሳሳተ ቅርጽ ሲያስይዟቸው፣ የኋለኛው ችግሮች ይበልጥ አየተወሳሰቡ እንዲሄዱ አድርጓቸዋል።

vi. ከ1950ዎቹ ጀምሮ ከሃገራዊ እውነታ እና ተጨባጭ የህዝብ ፍላጎት ጋር የማይጣጣሙ የፖለቲካ አስተሳሰቦች እና የማህበረሰብ እድገት ሞዴሎችን በጅምላ እና በጭፍን ተቀብሎ ማህበራዊ መሰረቱን ግምት ውስጥ ሳያስገቡ ለማራመድ እና ለመተግበር መሞከር የፖለቲካችን ዋነኛው መለያ ሊሆን ችሏል። እንዲህ ዓይነቱ አመለካከትም ከ1960ዎቹ ጀምሮ በሃገራችን ለተፈጠሩት የፖለቲካ ምስቅልቅሎች ታላቁን ድርሻ እንዳበረከተ ይታመናል።

vii. የዘመናዊው ፖለቲካ አራማጅ ሆኖ የተነሳው የ1960ዎቹ (የእኔ) ትውልድ በሃገሪቱ ከነበሩት የዘመናት ሃገራዊ የአስተዳደር እና የፖለቲካ ልምዶች ጠቃሚውን ከመውሰድ ይልቅ በሚያሳዝን ሁኔታ የባላባታዊው ፖለቲካ ባህል እስረኛ መሆኑ ሌላው አሳዛኝ ዕውነታ ነው። ይህም በመሆኑ፣ አብዛኞቹ አንጋፋ የፖለቲካ ድርጅቶች በተሟላ ነፃነት ላይ ከተመረኮዘ ፖለቲካዊ አካሄድ ይልቅ ፖለቲካዊ ጭሰኝነትን (political serfdom) የሚያራምድ የፖለቲካ አካሄድ ሲተገብሩ ኖረዋል።

viii. ባላፉት ጥቂት ዓመታት የሚወጡ የፖለቲካ ትንተናዎች እና ጥናቶች ባብዛኛው በተናጠል ሁነቶች እና ሂደቶች ላይ በሚያተኩር የተቀነበበ ትንተና ላይ የተመረኮዙ በመሆናቸው የፖለቲካውን ግለት ከማፋፋም ያለፈ አስተዋጽኦ

ሊያረጉ አልቻሉም። በዚህ ረገድ የሃገሪቱ ምሁራን እና የሚዲያ ሰዎች ባንድ አቅጣጫ የተቀነበበ ትንተና (linear thinking) ላይ የተመረኮዘ ፖለቲካዊ ትንተናዎች ከመስጠት መታረም እና ዙሪያ መለስ እይታ ሊሰጥ በሚችለው ምህዳራዊ አስተሳሰብ ለመታነጽ ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል።

ix. ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን አበይት ህመሞች እና ሌሎችንም በጥልቀት ፈትሾ መድሃኒት መሻት የሀገሪቱን ፖለቲካ ወደበሰለ እና የተረጋጋ የፖለቲካ ሥርዓት ለማሸጋገር የመጀመሪያው አስፈላጊ እርምጃ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሂደት ለፖለቲካ መሪዎች ብቻ የሚተው ሳይሆን ሁሉም ባለድርሻ አካላት በእውቀት እና አስተውሎት ላይ ለተመረኮዘ ውይይት እና መግባባት የየበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

x. በምህዳራዊ አስተሳሰብ መሰረት፣ ማንኛውም ምህዳር በአንድ ተመሳሳይ ወቅት በራሱ ምሉእ (whole) ሆኖ የሚቆም ሲሆን በተመሳሳይ ወቅት የሌላ ከፍ ያለ ምህዳር ደግሞ ክፋይ አካል (part) ነው። በዚህ መሰረት ክፋዮች የማንኛውም ምሉእነት መሰረቶች ሲሆኑ እነኚህ ምሉዕነቶች ግን ከክፋዮቹ ተደማሪነት በላይ የሆነ ህልውና ይኖራቸዋል። በክፋይነት እና ምሉዕነት መርህ መሰረት፣ እንደኢትዮጵያ ባሉ የበርካታ ብሔረሰቦች ሃገር ውስጥ አካታች እና ውጤታማ የሆነ ሥርዓተ መንግስት ለመገንባት የእያንዳንዱን ብሔረሰብ ምሉዕነት ከሀገራዊው ልዕልና ጋር የሚያጣጥም የፖለቲካ ሥርዓት መገንባት የግድ ይሆናል።

xi. ሌላው የምህዳራዊ አስተሳሰብ መርህ፣ ሁሉም እውነቶች አንጻራዊ እንደሆኑ እና አንድ እውነታ (reality) ከአንድ በላይ በሆኑ (multivalent) እውነቶች ሊገለጽ እንደሚችል ያመላክታል። የሃገራችን ፖለቲካ አንዱ ልዩ መገለጫ፣ አብዛኞቹ ፖለቲከኞቻችን ሌላው ወገን አለኝ የሚለውን እውነት ለማዳመጥ ዝግጁ አለመሆን ብቻ ሳይሆን የራሳቸውን 'እውነት' በሌላው ላይ በኃይል ለመጫን በሚሄዱበት ርቀትም ነው። ከዚህ በሽታ ለመላቀቅ ብዙዎቹ ፖለቲከኞቻችን በከፍተኛ ደረጃ ከተጠናወታቸው 'የእኔ ብቻ እውነት' ከሚለው አመለካከት ነጽተው የሌላውንም ወገን 'እውነት' ለመስማት ዝግጁ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

xii. ከሃገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ጋር በጥብቅ የሚተሳሰረው ሌላው ዓብይ መርህ በብዝሃነት እና ምህዳራዊ መረጋጋት (stability) መካከል ያለውን ግንኙነት ይመለከታል። በዚህ መርህ መሰረት፣ በማንኛውም ምህዳር ውስጥ የሚኖረው ብዝሃነት ወደ ተሻለ ሥርዐት ለመሻገር የሚያስችል መወራረስ እና መዳቀል ከማሳለጡም በላይ ምህዳራዊ መረጋጋትን እና ሚዛናዊነትን ለማረጋጋጥ ያግዛል። ከዚህ አኳያ፣ በሃገራችን የሚገኘው የሥነ-ምህዳር፣የቋንቋ፣ የባህል፣ እና የሃይማኖት ብዝሃነት ለሃገሪቱ ቀጣይ እና ዘላቂ እድገት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው መሰረት ሊሆን እንደሚችል መረዳት ያስፈልጋል። ይህ ግን ሊሆን የሚችለው የነኚህን ብዝሃነት ጠቀሜታ ባግባቡ ተረድቶ የእርስ በርስ ተደጋጋፊነታቸውን እና ተወራራሽነታቸውን በሚያጠናክር ህገ መንግስታዊ ሥርዓት ሲደገፉ ብቻ ነው።

xiii. የማንኛውም ምህዳር ውጤታማነት እና ዘላቂነት የሚወሰነው በክፋዮቹ መካከል ለሚኖረው ትብብር እና ፉክክር በሚኖረው አያያዝ ውጤታማነት መሆኑ ሌላው የምህዳራዊ አስተሳሰብ ዓበይ መርህ ነው። በክፋዮቹ አካላት መካከል የሚኖረው ትብብር የምህዳሩን አሰራር ውጤታማነት እና መረጋጋት (efficiency and stability) የሚወስን መሰረታዊ ጉዳይ ሲሆን በነኚሁ ክፋዮች መካከል የሚኖረው ፉክክር እና ውድድር ደግሞ ለምህዳሩ ቀጣይ እድገት አስፈላጊ ለሆነው ፈጠራ (innovation) ዋነኛ መሰረት ነው።

xiv. በዚህ መሰረት፣ በአንድ ሃገር ውስጥ የሚኖረው የፖለቲካ ምህዳር ጤናማነት የሚወሰነው በፓርቲዎች መካከል ሊኖር በሚገባው የመተባበሪያ ማእቀፍ (ህገ መንግስት እና ህገ መንግስታዊ ሥርዓት) ጥንካሬ እና በመወዳደሪያ ሜዳው አካታችነት ይሆናል። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የፖለቲካ ምስቅልቅል አንደኛው ምንጭ ይህንን ሃገራዊ የመተባበሪያ ማዕቀፍ ከፓርቲዎች የመወዳደርያ ፕሮግራም ጋር ከማደበላለቅ የሚመነጭ ነው።

xv. በተመከሮአዊ መማማር (adaptive learning) መርህ መሰረት፣ ውጤታማ ተመከሮአዊ የመማማር ስርአት ያለው ምህዳር ያልተቋረጠ እና ቀጣይነት ያለው ሽግግር ለማረጋገጥ ከፍተኛ አቅም ይኖረዋል። ይህም ማለት፣ ጠቃሚ መረጃዎችን በሥርዓት የሚያደራጅ፣ የሚያጠራቅም እና ካንድ ትውልድ ወደ ሌላው ትውልድ የሚያሸጋግር ምህዳር ላለተቋረጠ እና ቀጣይ ለሆነ ሽግግር ጥሩ መሰረት ይኖረዋል። በዚህ ረገድ፣ ከሃገር በቀል የእውቀት ሥርአቶች ልንወስዳቸው የምንችላቸውን ጠቃሚ ትምህርቶች እና ከዘመናዊው ፖለቲካችን የምናገኛቸውን በጎም ሆነ ክፉ ተመክሮዎች በቅንነት በመማር ወጣቱ ትውልድ በበጎው ተመክሮ ላይ በመገንባት ጎጂ ታሪካችንን ላለመድገም ብርቱ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል።

xvi. እስከ አሁን ድረስ ለኢትዮጵያ የፖለቲካ ችግሮች የሚጠቆሙ መፍትሄዎች በአብዛኛው ወይ በአንድ ክፍል ወገናዊነት ላይ የተመረኮዙ ምሉዕነት የጎደላቸው ይሆናሉ ወይም ሁሉንም ዝርዝር ጥያቄዎች በአንድ ጊዜ ለመመለስ በሚያደርጉት ጥረት መያዣ መጨበጫው የጠፋበት የመፍትሄ ሃሳብ ሆነው ይገኛሉ። ከዚህ ይልቅ፣ ላለንበት ውስብስብ ሁኔታ ሁለንተናዊ መፍትሔ ለማግኘት ከተናጠል ሁነቶች (events) እና ድግግሞሽ (patterns) ባሻገር በመመልከት የአመለካከት እና መዋቅራዊ ችግሮችን መመርመር በርካታ ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያስችሉ ልዩ ቋጠሮዎችን (dynamic knots) መፍታት ይቻላል።

xvii. በዚህ ክፍል ውስጥ የተጠቀሱትን ያስተሳሰብ ለውጦች በማምጣት እና ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የምህዳራዊ አስተሳሰብ መርሆዎችን በተቀናጀ መልኩ ተግባራዊ በማድረግ አብዛኞቹን መሰረታዊ የፖለቲካ ህመሞቻችንን ማከም እና የወደፊቱን የሃገራችንን የፖለቲካ ምህዳር በጤናማ መሰረት ላይ ለመገንባት ይቻላል። በዚህ ሂደት ውስጥ፣ አንድን ውስብስብ ሁኔታ ለመፍታት ካንድ በላይ የመፍትሔ መንገዶች ሊኖሩ እንደሚችሉ መገንዘብም ይገባል።

# 3. መዋቅራዊ ችግሮቻችን ከምህዳራዊ እይታ አኳያ

ቀደም ባለው ክፍል፣ የኢትዮጵያን የፖለቲካ ህመሞች ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ የተመለከትን ሲሆን እነኚህን ህመሞች በአግባቡ ለመረዳት እና መፍትሄ ለመሻት ሊያግዙ የሚችሉትን መሰረታዊ የምህዳራዊ አስተሳሰብ መርሆዎችም ዳሥናል። በዚህም፣ በፖለቲካችን ውስጥ ሊኖረን የሚገባንን ዋነኛ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት የሚያስችሉንን መሰረት ለማስጨበጥ ተሞክሯል። በዚህ ክፍል ውስጥ ከፖለቲካችን ዋና ዋና መዋቅራዊ ችግሮች ጥቂቶቹን ቀደም ሲል ከቀረቡት የምህዳራዊ አስተሳሰብ መርሆዎች አኳያ ለመመልከት እንሞክራለን።

## 3.1 የፖለቲካችን መዋቅራዊ ችግሮች[14]

የመጀመሪያው፣ በሃገራችን ታሪክ ላይ ያለው ሁለት ጽንፍ የያዘ አመለካከት ነው። ባንደኛው ጽንፍ፣ ኢትዮጵያ ቀደምት እና እጅግ አኩሪ የሆነ ታሪክ ያላት አገር ናት በማለት ባንዳንድ የታሪክ አጋጣሚ የተፈጠሩ አሳዛኝ እና አሳፋሪ የታሪክ ክስተቶች አልነበሩም፤ ቢኖሩም በሌሎችም ሃገሮች ምስረታ የታዩ በመሆናቸው የተለየ ትኩረት አይገባቸውም ብሎ ያምናል። በሌላኛው ጫፍ ደግሞ፣ ኢትዮጵያ የምትባለው ሃገር ከአንድ መቶ ሃያ ወይም ሰላሳ ዓመት ወዲህ በነበሩ ወረራዎች የተፈጠረች እና ታሪኳም የህዝቦች ጭቆና እና ግፍ ታሪክ ነው የሚል ነው። ስለሆነም ይህ ታሪክ ከመሰረቱ መቀየር አለበት ይላል። በበርካታ የሥነ ህንጻ እና የቅሪተ አካላት ጥናቶች እንደተረጋገጠው፣ ሃገራችን ኢትዮጵያ በአፍሪካም ሆነ በዓለም ልዩ ስፍራ የሚያሰጣት ቅድመ ታሪክም ሆነ ታሪክ እንዳላት ብዙም የሚያከራክር አይደለም። ያም ሆኖ ግን፣ እንደሌሎች ማንኛቸውም ሃገሮች ኢትዮጵያም አሳፋሪ የታሪክ ምዕራፍ አሳልፋለች። በመሆኑም፣ ያለን ብቸኛው እና ጠቃሚው መንገድ የታሪካችንን መንትያ ገጽታዎች በመረዳት በአኩሪ እና ጠቃሚው ላይ መገንባት እና አሳፋሪው እና ጎጂው እንዳይደገም ለማድረግ መጣር ነው። እንዲህ ዓይነቱ አቀራረብ የምንፈልገውን የፖለቲካ ሥርዓት በብሔራዊ መግባባት ላይ ለመገንባት ክፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ በልጅነት አእምሮዬ ተቀርጾ የቀረን አንድ እውነተኛ ገጠመኝ ማካፈል እፈልጋለሁ። በአስራዎቹ የመጀመሪያ እድሜ በነበርኩበት ወቅት ካወኳቸው ሰዎች አንዷ ሲከፉ የምትባል ሴት ነበረች። ይህች ሴት በደቡባዊው የሃገራችን ክፍል ከሚገኝ እንድ ብሔረሰብ የመጣች ስትሆን፣ አብረን አንድ አካባቢ እስከኖርንበት ጊዜ ድረስ ውሎዋም ሆነ አዳርዋ በማዕድ ቤት ውስጥ ነበር። ይህች ሴት በወቅቱ ወደ አርባዎቹ የተጠጋ እድሜ የነበራት ስትሆን በተደጋጋሚ በእመቤት ተብዬዋ ስትደብደብ እና ስታለቅስ እያየሁ ሃዘን ይሰማኝ ነበር። መከፋቷ ሁሌም በፊቷ ላይ ይታይ ስለነበር፣ ሲከፉ የሚለው ስሟ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የወጣላት ይመስለኝ ነበር። አጋጣሚ ባገኘሁ ቁጥር ላጫውታት

[14] የዚህ ክፍል አብዛኛው፣ ሐምሌ 25 ቀን 2012 በወጣው አዲስ አድማስ ጋዜጣ የተነበበ ነው።

እሞክር ስለነበር፣ አንድ ቀን ለምን ሲከፉ እንደተባለች ጠየኳት። እርሷም ስትመልስልኝ፣ መጀመሪያ የተሰጣት ስም 'ሲከፉ መቻል' እንደነበረ እና ቀደም ሲል በዚህ ስሟ ስትጠራ 'ለአምላክ ይመቻል' ብላ መመለስ እንደሚጠበቅባት ነገረችኝ። ከጊዜ በኋላ ይኸው ስሟ አጥሮ ሲከፉ እንደሆነ ነገረችኝ። ይህንን ከሰማሁ በኋላ ሌላ በቅርብ የማውቀው በተመሳሳይ አገልጋይነት ውስጥ የነበረ ሰጠኝ የሚባል ሰው ስለነበር እርሱንም ለምን ሰጠኝ እንደተባለ ጠየኩት። እርሱም ሲመልስልኝ፣ ቀደም ሲል የወጣለት ስም 'ሰጠኝ መርቆ' እንደነበር እና ይህ ስሙ በሚጠራበት ጊዜ እርሱም 'ልፋቴን አውቆ' ብሎ መመለስ ይጠበቅበት እንደነበር አጫወተኝ። ይህ ታሪክ የሚያሳየው፣ በቅርብ ጊዜ ታሪካችን እንኳን ከቡር የሆነውን የሰው ልጅ እንደ ዕቃ የሚመለከት ሥርዓት ብቻ ሳይሆን ይህንን አሳፋሪ ሥርዓት በመለኮታዊ አባባል ለማጽዳት (sanitize) ጥረት ይደረግ እንደነበር ነው።

ሁለተኛው መዋቅራዊ ችግር የዲሞክራሲ ሥርዓቱን የሚመለከት ሲሆን፣ ባንዱ ጫፍ ያሉ ወገኖች የኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ሥርዓት አሁን ሰፍኖ ካለው በአብዮታዊ ዲሞክራሲ ከተቃኘው የብሔር ፖለቲካ ተቀይሮ በሊበራል ዲሞክራሲ ቅኝት ወደሚመራው በግለሰብ ነፃነት ላይ ወደ ተመረኮዘ የዜግነት ፖለቲካ በአስቸኳይ ካልተሸጋገረ ሃገሪቱ በማያባራ የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ትቀጥላለች ብለው ያምናሉ። በሌላ በኩል ደግሞ፣ የብሔር ጥያቄ የሀገሪቱ ዋነኛ የፖለቲካ ጥያቄ በመሆኑ፣ የሀገሪቱ የፖለቲካ ሥርዓትም በዚሁ ዙሪያ ከመዋቀር ውጭ ሌላ አማራጭ የለውም ብለው የሚያምኑ ወገኖች አሉ። በተጨባጭ ካለው አለም አቀፍ ተመክሮ እንደምንረዳው በፍጹማዊ የግለሰቦች ነፃነት ላይ የተመረኮዘ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ገንብተናል ብለው የሚኩራሩ በርካታ የበለፀጉ ሀገሮች በተለያየ ወቅት በሚነሱ የቡድን ጥያቄዎች ሲፈተኑ ኖረዋል ወደፊትም ይፈተናሉ።

በቅርቡ በአሜሪካ የተነሳው የጥቁር ህዝቦች በህይወት የመኖር መብት ጥያቄ በግለሰቦች መብት መጠበቅ ሽፋን፣ ስር ለሰደዱ የቡድን መብት ጥያቄዎች ተገቢውን ትኩረት ካለመስጠት ጋር የተያያዘ ነው። በኢትዮጵያም ሁኔታ ለረጅም ዘመናት የነበረውን የብሔረሰቦች መብት ጥያቄን መመለስ አንዳንዶች እንደሚያስቡት ወደጎን ሊባል የሚችል ጉዳይ አይደለም። ነገር ግን፣ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ የሚወሰዱ እርምጃዎች በምንም አይነት አገባብ የዜጎችን ወይም የግለሰቦችን በህይወት የመኖር፣ የመሳተፍ እና የመበልፀግ መብቶችን የሚገድቡ ሊሆኑ አይገባም። ስለሆነም የብሔረሰቦችን መብት ከዜጎች መሰረታዊ መብት ጋር ማጣጣም የወደፊቱ የፖለቲካ ሥርዓታችን ዋነኛ መገለጫ ሊሆን ይገባዋል።

ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ፣ በግለሰብ መብት እና ቡድን መብት መካከል ጥብቅ የሆነ መተሳሰር ከመኖሩም በላይ ባንዱ ላይ ብቻ የተመረኮዘ የፖለቲካ ሥርዓት የተሟላ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይሆናል ተብሎ አይታመንም። ባላፉት ጥቂት ዓስርተ ዓመታት ውስጥ፣ የአብዮታዊ እና ሊበራል ዲምክራሲ ዲቃላነት ባህርይ ያላቸው 'የልማት መንግሥታት' (developmental states)፣ ኢትዮጵያን ጨምሮ በተለያዩ ሃገሮች እንደ አማራጭ ተራምደዋል። ሆኖም ግን፣ በሃገራችን እንደታየው፣ እነኚህ መንግሥታዊ

ሥርዓቶች ካንዱ ወይንም ከሌላው ከወረሱት በሽታዎች ነጻ ሊሆኑ አልቻሉም። ከዚህ በተጨማሪም፣ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ይዞት ከመጣው በርካታ ፈተናዎች እና እድሎች አኳያ አብዮታዊ ዲሞክራሲም ሆነ ሊበራል ዲሞክራሲ ዘመኑን የማይመጥኑ መሆናቸው ይነገራል። ለምሳሌም ያህል፣ የመረጃ እና ተግባቦት ቴክኖሎጂ በፈጠረው አመቺነት ላይ በመመርኮዝ ህዝቦች በመንግስታዊ ፖሊሲ ውሳኔዎች ላይ የሚኖራቸው ቀጥተኛ ተሳታፊነት (e-Governance) እያደገ እንደሚሄድ ይጠበቃል። ከዚህም በላይ፣ አካታች እና ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ ከምንጊዜውም የበለጠ አሳታፊ (participatory) እና በሰፊ መግባባት (consensus) ላይ የተመረኮዘ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት አጅግ አስፈላጊ ይሆናል። ይህ እንዳለ ሆኖ፣ ከሁለቱም የዲሞክራሲ ሥርዓቶች ሊወሰዱ የሚችሉ ጠቃሚ ተሞክሮዎች ይኖራሉ።

ሶስተኛው መዋቅራዊ ፈተና፣ አሁን በስራ ላይ ካለው ህገ መንግስት ጋር የተያያዘ ነው። ይህን በተመለከተ፣ ባንድ በኩል አሁን ያለው ህገመንግስት በመሰረታዊ ባህሪው ኢዴሞክራሲያዊ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ማስወገድ እና በሌላ አዲስ ህገ መንግስት መተካት አለበት ብለው የሚያምኑ ወገኖች አሉ። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ይህ ህገ መንግስት የብሔረሰቦችን መብት ያስከበረ በመሆኑ እርሱን ለመቀየር መሞከር ሃገሪቱን ወደ መበታተን ሊወስዳት ይችላል የሚሉ ወገኖች አሉ። ከበርካታ የተረጋጋ መንግሥታዊ ሥርዓት ባለቤት ከሆኑ ሃገሮች ታሪክ እንደምንማረው፣ የእነዚህ ሃገሮች ህገ መንግስት ከጅምሩ 'ሙሉ በኩለሄ' ሆኖ የተፈጠረ ሳይሆን በየወቅቱ እየተሻሻለ እና እየበለፀገ የሚሄድ ህልው (organic) ሰነድ ነው። ከዚህ አኳያ፣ በስራ ላይ ያለውን ህገመንግስት አውጥተን እንጣለው የሚለው አቋም አሻጋሪ የመሆን እድሉ ውሱን ከመሆኑም ባሻገር እንደከዚህ ቀደሙ አፍርሶ የመገንባት ቅኝት ያለው በመሆኑ ትርጉም ያለው ለውጥ የሚያመጣ ሆኖ አይታይም። ከዚህ በተጨማሪ፣ በስራ ላይ ያለው ህገመንግስት ምንም እንኳን አንዳንድ ጉድለቶች እና ድክመቶች ያሉበት ቢሆንም፣ በርካታ ጠቃሚ እና አሻጋሪ የሆኑ የህግ አንቀጾችን ይዟል። በመሆኑም፣ የጊዜው ትኩረት መሆን ያለበት ባለው ህገመንግስት ውስጥ ያሉትን ድክመቶች እና ጉድለቶች ህዝብን አካታች እና አሳታፊ በሆነ ሂደት እያሻሻሉ ጠቃሚውን እያጠናከሩ መሄድ ነው። ይህን በተመለከተ፣ በከፍል ስድስት እንመለስበታለን።

አራተኛው ፈተና፣ በስራ ላይ ካለው ህግመንግስት ጋር በተያያዘ ሃገሪቱ ሊኖራት የሚገባው የፌዴራል አወቃቀርን ይመለከታል። ባንድ በኩል፣ አሁን በስራ ላይ ያለው በብሔር ላይ የተመረኮዘ የፌዴራል መዋቅር የሃገሪቱን አንድነት የሚፈታተን እና ወደመበታተን የሚያመራ ስለሆነ ሙሉ በሙሉ መቀየር አለበት ብለው የሚያምኑ ወገኖች አሉ። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ያለው የፌዴራል አወቃቀር ለብሔሮች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ያጎናጸፈ በመሆኑ እርሱን ለመቀየር መሞከር ሀገሪቱን ወደ ብጥብጥ እና መበታተን ሊወስዳት ይችላል የሚሉ ወገኖች አሉ። መልካሙ ነገር፣ ሁለቱም ወገኖች ለሃገሪቱ ሀገረ-መንግሥት፣ ፌደራል የመንግስት አደረጃጀት ብቸኛው አማራጭ መሆኑ ላይ ይስማማሉ። አገራችን ባሁኑ ሰዓት ከተጋፈጠቻቸው ዋና ዋና ፖለቲካዊ ፈተናዎች አኳያ፣

የፌደራላዊ ሥርዓቱ ውጤታማነት ሊለካ የሚገባው፣ ማንኛውም ሰው በሰውነቱ ሊኖረው የሚገባውን መሰረታዊ የመኖር እና በአካልም በመንፈስም የመበልፀግ ህገ መንግሥታዊ መብቶች ከቡድናዊ መብቶች መከበር ጋር አጣጥሞ መተግበር በመቻል አቅሙ ነው።

በዚህ ረገድ፣ አሁን ያለው የፌዴራል አወቃቀር ለብሔሮች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት መከበር መሰረት የጣለ ቢሆንም በህገመንግስቱ ውስጥ የተደነገጉትን መሰረታዊ ሰብዓዊ መብት ለሚጥስ አተገባበር እድል የሚሰጥ ሆኖ በመቀረጹ ለበርካታ የሰብዓዊ መብት ጥሰት እና የመልካም አስተዳደር ጉድለት ምንጭ ሆኗል። ከዚህም በተጨማሪ ያንዳንድ ክልሎች አከላለል ውጤታማ የልማት አስተዳደርን ለመተግበር አመቺ አለመሆንም ይታያል። ስለዚህም፣ የተሻለው አማራጭ ያለው የፌዴራል አወቃቀር ያሉበትን የአካታችነት እና ልማታዊ ውጤታማነት ውሱንነት በሂደት በማሟላት ለዘለቄታው የሀገሪቱ ልማት እና የህዝቦች ብልጽግና እንዲያገለግል ማድረግ ይሆናል። ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት መሰረታዊ መዋቅራዊ ችግሮች አንዱ ከሌላው በእጅጉ የተሳሰሩ በመሆናቸው አንደኛውን በተናጠል ለመፍታት በመሞከር ወደ ዘላቂ መፍትሔ ማምራት እጅግ አስቸጋሪ ይሆናል።

በቀዳሚው ክፍል እንደተጠቀሰው በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ ዋነኛ ተዋንያን ነን የሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች የአጠቃላይ የሃገሪቱ የፖለቲካ ምህዳር አካል ናቸው። ይህም ማለት፣ አንዱ ፓርቲ ከሌላው ፓርቲ ጋር የሚኖረው መስተጋብር ባጠቃላይ የምህዳሩን ጤናማነት ይወስነዋል። በመሆኑም በማንኛውም ወቅት ለሚፈጠር የፖለቲካ ቀውስ፣ (የድርሻ ማነስ ወይም መብዛት ካልሆነ በስተቀር) የትኛውም ፓርቲ ከደሙ ንጹህ ነኝ ማለት አይችልም። ከዚህ አኳያ፣ ለህዝቦች መብት እና ዘላቂ የልማት ፍላጎት መሟላት ቆመናል የሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቀዳሚ ተግባር መሆን ያለበት ለህዝቦች ልዕልና ተገዢ በመሆን፤ ዋነኛ የሆኑት መዋቅራዊ የፖለቲካ ችግሮችን እውቀት ላይ በተመረኮዘ ሂደት ሊፈቱ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር እና በተግባር ላይ ማዋል ነው።

## 3.2 ዳሩን መሃል የማድረግ ፖለቲካ[15]

በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ጉልህ ድርሻ ሊኖራቸው ይችላሉ ተብለው የሚገመቱ የፖለቲካ ቡድኖች እና የህብረተሰብ ክፍሎች በተወከሉበት እና በ 2011 በተካሄደ አንድ ዓውደ ርእይ ላይ በአስተባባሪነት የመሳተፍ እድል አጋጥሞኝ ነበር። በዚህ ወቅት ከተካሄዱ የቡድን ውይይቶች በአንደኛው፣ አንድ ተሳታፊ 'የኢትዮጵያ ፖለቲካ ዋነኛው ችግር በአማራው፣ በኦሮሞው እና በትግራይ የፖለቲካ ልሂቃን (elites) መካከል ያለው የበላይነት ፉክክር ነው' የሚል አስተያየት ይሰጣሉ። ይህን በማስከተል፣ በምስራቃዊው የሃገራችን ክፍል የሚገኝ አንድ የፖለቲካ ድርጅትን ወክለው የመጡ ሌላ ተሳታፊ 'ችግሩ ይህ መሆኑን ከተረዳችሁ ለምን ለተወሰኑ ዓመታት ሥልጣኑን ለእኛ ለቃችሁልን ሃገር እንዴት እንደሚመራ አናሳያችሁም' የሚል ምላሽ ይሰጣሉ። በወቅቱ፣ እነኝህ አስተያየቶች ብዙም ትኩረት ሳይሰጣቸው እና ቀጣይ ውይይት ሳይካሄድባቸው ታልፈዋል። በዚህ ፀሃፊ እምነት፣ እነኚህ አስተያየቶች በሃገራችን ፖለቲካ ውስጥ ካሉት እና ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገቡ ዋነኛ መዋቅራዊ ችግሮች አንዱ የሆነውን የመሃል እና ዳር (centre-periphery) ፖለቲካን የሚያመላክቱ ናቸው። በዚህ ክፍል፣ ከላይ የተጠቀሱት አባባሎች ያላቸውን መልእክት ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ በመተንተን ዳሩን ማዕከል የሚያደርግ ፖለቲካ ለኢትዮጵያ የወደፊት እጣ ፈንታ የሚኖረውን በጎ አስተዋጽኦ ለማመላከት ይሞከራል።

ወደ ወቅቱ የሃገራችን ፖለቲካ ከመግባታችን በፊት ግን ይህ የዳር እና መሃል ፖለቲካ ከዚህ ቀደም በነበሩ የፖለቲካ ሥርዓቶች እንዴት ይታይ እንደነበር በአጭሩ እንመለከታለን። ከዘመነ መሳፍንት በኋላ የነበረውን የሃገር ምስረታ ታሪክ ስንመለከት፣ የሌሎች ማህበረሰቦች አስተዋጽኦ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከአማራ፣ ከትግራይ እና ከኦሮሞው የወጡ ነገስታቶች እና የጦር አበጋዞች የመሪነቱን ድርሻ ይወስዳሉ። ወደ አጼ ኃይለሥላሴ ዘመን ስንመጣ፣ የንጉሳዊው አገዛዝ መንግስታዊ መዋቅር በአብዛኛው ከላይ በተጠቀሱት የአማራ፣ ኦሮሞ እና ትግራይ መኳንንቶች እና ልሂቃን የተሞላ እንደነበር የታሪክ መዛግብት ያረጋግጣሉ። ከዚህ በተጨማሪም፣ ከሰሜናዊው እና ከመሃከላዊው የሃገራችን ክፍል ውጪ ያለው አብዛኛው የሃገራችን ክፍል ዳር ሃገር በሚል አጠራር ውስጥ የሚጠቃለል ነበር። በነዚህ የሃገሪቱ ክፍሎች የሚመደቡ ገዢዎችም፣ በአንዳንድ አካባቢዎች የነበሩትን ባላባታዊ አስተዳደሮች ከማቆየት ውጭ፣ በአብዛኛው ከነኚሁ ሶስት ብሄረሰቦች በተለይም ከአማራው ወገን እንደነበሩ ይታወቃል።

ከዚህም አልፎ፣ ንጉሡ ስልጣናቸውን በመቀናቀን ወይም ለመጋፋት በመሞከር የሚጠረጥሯቸውን መኳንንት እና ልሂቃን በሹመት ስም ወደ እነኚህ የሃገሪቱ ክፍሎች ይመድቡ እንደነበር የሚነገሩ ትርከቶችም ነበሩ። ከልሂቃኖቹ ሹመቶች መካከል የ1953 መፈንቅለ መንግስት ጠንሳሽ እንደሆኑ የሚነገርላቸው የአቶ ገርማሜ ንዋይ የወላይታ እና የጅግጅጋ ሹመት እና በተመሳሳይ መልኩ ፍጹማዊ የንጉሥ አገዛዝ በመተቸት የታወቁት

[15] የዚህ ክፍል አብዛኛው፣ ነሐሴ 16 ቀን 2012 በወጣው አዲስ አድማስ ጋዜጣ ታትሟል።

የፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም አውራጃ ገዢነት ሹመቶች ይጠቀሳሉ። ስለሆነም፣ በዚህ ዘመን ወደ ዳር ሃገር መሸም ማለት ንጉሣዊ ግዞተኝነት ተደርጎ ይወሰድ ነበር።

የ1966 ህዝባዊ ንቅናቄን ተከትሎ የነበረውን ፖለቲካ በሁለት ዘርፍ መመልከት ይቻላል። አንደኛው ገጽታ፣ ሃገሪቱን የመምራት ስልጣንን ጠቅልሎ የወሰደው ወታደራዊው ደርግ የነበረው ያስተዳደር እና አመራር ብሄረሰባዊ ተዋጽኦ ሲሆን፤ ሌላው በወቅቱ የሃገሪቱ ፖለቲካ ውስጥ ቀዳሚ የነበሩት የፖለቲካ ድርጅቶች የነበራቸው የአመራር ስብጥር ነው። የወታደራዊው ደርግን ስብጥር ስንመለከት፣ ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል መልኩ ከነጂሁ ሶስት ዋነኛ ብሄረሰቦች የተውጣጡ መሆናቸው ግልጽ ነው። ይህ ሁኔታ በወቅቱ የነበረው የሃገሪቱ የመከላከያ ሰራዊት ስብጥር በአብዛኛው ከነጂሁ ብሄረሰቦች የተገኘ ከመሆኑ አኳያ ሲታይ ብዙም የሚያስገርም አይሆንም።

በጊዜው የነበሩትን የፖለቲካ ድርጅቶችንም ስንመለከት፣ የሌሎች አናሳ ብሄረሰቦችን ትግል ለማስተባበር በሚል ከተመሰረተው የኢትዮጵያ ጭቁኖች አብዮታዊ ትግል (ኢጭአት[16]) ከሚባለው ድርጅት በስተቀር ያብዛኛዎቹ ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች አመራሮች ከነዚሁ ሶስት ብሄረሰቦች የወጡ መሆናቸው ይታወቃል። ከዚህም አልፎ አንዳንዶቹ ላንዱ ወይም ለሌላው ወገን በማድላት ሲታሙም ነበር። ለምሳሌ፣ የመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) የሚባለው ድርጅት ለኦሮሞው በማድላት ሲታማ፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ፓርቲ (ኢህአፓ) አመራርም በአማራ እና በትግራይ ልጆች ተጽእኖ ስር ነው ይባል ነበር። ምንም እንኳን፣ የመኢሶንም ሆነ የኢህአፓ መሪዎች ላንዱ ወይንም ለሌላው ብሔረሰብ በተናጠል ለማድላታቸው ቀጥተኛ ማረጋገጫ ባይኖርም፣ ከላይ የቀረበው አጭር ትንታኔ የሚያሳየው በንጉሱም ሆነ በደርግ ዘመን በነበረው የሃገሪቱ ፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ፣ ከላይ ከተጠቀሱት ሶስት ማህበረሰቦች የወጡ ልሂቃን ወሳኙን ድርሻ ይዘው እንደነበር ነው።

ይህ የዳር-መሀል ሃገር ፖለቲካ በዘመነ ኢህአዴግ ለየት ያለ መልክ ይዞ ቀጥሏል። በአንድ በኩል፣ ሁሉም ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተድድሩበት እና የራሳቸውን እድል በራሳቸው የሚወስኑበት ህገ መንግስታዊ ሥርዓት በመመስረት ህዝቦች በእኩልነት የሚሳተፉበት ሥርዓተ መንግስት እንደተተገበረ ሲነገር ቆይቷል። በሌላ በኩል ግን፣ በፌደራል ደረጃ ወሳኝ የሆነውን የፓርቲም ሆነ መንግስታዊ ስልጣን በሚመለከት በቀድሞው አጠራር ዳር ሃገር፣ በኢህአዴግ አጠራር ታዳጊ ክልሎች የሚባሉትን የአፋር፣ የሱማሌ፣ የጋምቤላ እና የቤኒሻንጉል ህዝቦችን በአግባቡ ያላካተተ እንደነበር ይታወቃል። ከዚህ አለፍ በማለትም፣ በእነኚህ ክልሎች የነበረው ውስጣዊ አስተዳደርም እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ከማዕከል በሚመደቡ ሞግዚቶች ይወሰን እንደነበር ተነግሯል። በጥቅሉ፣ በኢህአዴግ ዘመን የነበረው መንግስታዊ አስተዳደርም በሶስቱ ብሄረሰቦች ዋነኛ የፖለቲካ

[16] የዚህ ድርጅት መሪ ከነበሩት ፖለቲከኞች መካከል በጽኑ ኢትዮጵያዊነቱ የሚታወቀው አቶ አሰፋ ጫቦ በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳል።

ተዋናይነት ከቀድሞው የዳር መሃል ሃገር ፖለቲካ የቀጠለ መሆኑ ግልጽ ነው። በመሆኑም፣ ለበርካታ ዓመታት በኢህአዴግ ውስጥ ሰፍኖ የነበረው የትግራይ ህዝቦች ነፃ አውጭ ግንባር (ህወሃት) የበላይነት፣ በዋነኝነት፣ በኦሮሞ እና በአማራ (ኦሮማራ) የፖለቲካ ሃይሎች ጥምረት ሊፈርስ ችሏል። ይህም የሚያመላክተው፣ በቅርቡ በነበረው የፖለቲካ ዘመናችንም ቢሆን ከእነኚህ ሶስት ወገኖች በሚወጡ የፖለቲካ ልሂቃኖች መካከል ያለው መስተጋብር የሃገሪቱን የፖለቲካ አቅጣጫ በመወሰን ረገድ ትልቅ ድርሻ እንደነበረው ነው።

ይህ የዳር እና የመሃል ሃገር ፖለቲካ፣ ከ2010 የመንግስት አመራር ለውጥ ወዲህ እየተሻሻለ መምጣቱን የሚያመላክቱ አንዳንድ በጎ እርምጃዎች መታየት መጀመራቸው ግልጽ ነው። ያም ሆኖ፣ የሃገሪቱን የወደፊት ፖለቲካ እጣ ፈንታ በመወሰኑ ረገድ በአማራው፣ በኦሮሞው እና በትግራይ የፖለቲካ ልሂቃን መካከል የሚካሄደው የፖለቲካ መስተጋብር አሁንም ወሳኝ ድርሻ እንደሚኖረው የሚያምኑ ወገኖች በርካታ ናቸው። ከላይ የተጠቀሱት ታሪካዊ ሁኔታዎች የሚያመላክቱት በመግቢያው ላይ የተጠቀሰውን የሃገሪቱን የፖለቲካ ችግሮች በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ አብይ ድርሻ ከነበራቸው የሶስቱ ብሄረሰቦች ልሂቃን ጋር ያያዘው አስተያየት በቂ መነሻ መሰረት እንደነበረው ነው። በመሆኑም፣ በየትኛውም የሃገሪቱ ዘመን ለነበረው የፖለቲካ ቀውስ ከእነኚህ ሶስት ብሔረሰቦች የወጡ የፖለቲካ መሪዎች እና ልሂቃን የጋራ ተወቃሽነት አለባቸው ማለት ይቻላል።

የእነኚህ ሶስት ብሔረሰቦች ህዝቦች በሀገሪቱ የታሪክ፣ ኢኮኖሚ እና መልከዓምድራዊ ይዞታ ውስጥ ካላቸው ጉልህ ድርሻ አኳያ፣ በሃገሪቱ የፖለቲካ ህይወት ውስጥ የነላ ድርሻ መያዝ በራሱ የችግር ምንጭ ሊሆን አይገባውም። ይልቁንም፣ እነኚህ ህዝቦች ለሃገሪቱ የረጅም ዘመን ታሪክ ከነበራቸው ጉልህ አስተዋጽኦ እና ካከማቹት ከፍተኛ ማህበራዊ ንዋይ (social capital) አኳያ በጣም ጠቃሚ የሆነ የአካታችነት (inclusivity) እና የአረጋጊነት (stability) ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። ይህንን ሆኖ ለመገኘት ግን፣ ከዚህ ቀጥሎ ከተጠቀሱት ህመሞች ራሳቸውን ማንጻት ይጠበቅባቸዋል።

የመጀመሪያው፣ የፖለቲካ ልሂቃኖቹ ለዘመናት ተብትቦ ከያዛቸው በሴራ እና እርስ በርስ በመጠፋፋት ላይ ከተመረኮዘ ባላባታዊ ፖለቲካ ራሳቸውን በማንጻት የዳር ሃገር ህዝቦችን እኩል ተሳታፊነት እና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል። በሁለተኛ ደረጃ፣ በሃሳብ ልዕልና ላይ ከተመረኮዘ መንግስታዊ ሥርዓት ይልቅ፣ ባላቸው የህዝብ ቁጥር ትልቅነት ላይ ወደተመረኮዘ ጨቋኝ አገዛዝ (tyranny of numbers) የሚወስድ ዝንባሌን በጥብቅ ሊታገሉ ይገባቸዋል። በአሁኑ ወቅት፣ እንዲህ አይነቱ የፖለቲካ ዝንባሌ በዲሞክራሲ ሽፋን በአንዳንድ የብሄር ፖለቲካ ልሂቃን እና መሪዎች አካባቢ እየተቀነቀነ በመሆኑ በቶሎ ሊታረም ይገባዋል።

በሶስተኛ ደረጃ፣ ምንም እንኳን በስፋት ባይነገርላቸውም፣ በጠረፍ አካባቢ የሚኖሩ ህዝቦች ለኢትዮጵያ ዳር ድንበር መከበር የነበራቸውን ቁልፍ ድርሻ በመገንዘብ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች የዳር-መሃል የሚባለውን ፖለቲካዊ ዘይቤ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ከኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ ማስወገድ ይኖርባቸዋል። ይህ ሊሆን የሚችለው፣ የዳርቻው አካባቢ ማህበረሰቦች ሃገሪቱን ወደ መሃል የሚያሰባስበው ሃይል (centripetal force) አካል ሆነው መሃሉ በብዙ መልኩ ዳሩንም መምሰል ሲጀምር ነው። ያለ ዳሩ መሃል የሚባል ነገር እንደማይኖር መረዳትም ለዚህ ሂደት ይጠቅማል።

ይህ ዳሩን ወደ ማዕከል የማምጣት ፖለቲካ ለዘመናት የነበረውን የሙበት መዛባት ከማስተካከልም በላይ ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ ለሃገራችን የፖለቲካ ሽግግር ልዩ አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችላል። የዚህ ዋነኛው ምክንያት፣ በነኚህ አካባቢዎች የሚኖሩ አብዛኛዎቹ ማህበረሰቦች የሌሎቹን ያህል በሃገራችን ፖለቲካ መሰረታዊ ህመሞች ያልተተበተቡ ከመሆናቸውም በላይ የፖለቲካ ልሂቃኖቻቸውም ከሃገር በቀል እውቀቶች እና ሥርዓቶቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት በሚመለከት እንደ አብዛኞቻችን ጠቅልለው ያልተፋቱ መሆናቸው ነው። ለዚህም ማረጋጋጫ የሚሆኑን፣ ከቦረና እስከ አፋር፣ ኪጋሞ እስከ ሶማሊ ያሉ ማህበረሰቦች ያላቸው የተሻለ የማድመጥ እና የመደማመጥ ባህል፣ ውጤታማ የሆኑ የግጭት አፈታት ዘዴዎቻቸው፣ እና ማህበራዊ ርትዕን የሚያሰፍኑበት የዳኝነት ሥርዓቶቻቸው ናቸው።

እነኚህ ማህበራዊ ክህሎቶች እና እሴቶች በጥርጣሬ እና በበላይነት ስሜት የተተበተበውን የመሃል ሃገር ፖለቲካ በመጠኑም ቢሆን ለማለዘብ እና ለማስከን እንደሚያግዙ የሚያመላክቱ ወጣት የፖለቲካ መሪዎችም ከነኚሁ አካባቢ ወጥተው ማየት ጀምረናል። እዚህ ላይ፣ እነኚህ ሃገር በቀል እውቀቶች እና ሥርዓቶች በዘመኑ የፖለቲካ ህመም የተነሳ ለመሸርሸር አደጋ እየተጋለጡ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል። ስለዚህም፣ ጊዜው ሳይረፍድ ከእነኚህ ሃገር በቀል እውቀቶች እና ሥርዓቶች ሊወሰዱ የሚችሉ ጠቃሚ ልምዶችን በተቀናጀ እና በተደራጀ መልኩ አጥንቶ የፖለቲካ ባህላችን እና ሥርዓታችን አካል እንዲሆኑ ማድረግ ለሃገራዊው የፖለቲካ ሽግግር ጤናማነት ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይታመናል። በዚህ ረገድ፣ በሃገሪቱ የሚገኙ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ የማህበራዊ ሳይንስ ምሁራን እና በዚህ መስክ የሚንቀሳቀሱ ሃገር በቀል ድርጅቶች ጉልህ ድርሻ ሊኖራቸው እንደሚችል ይታመናል።

በአጠቃላይ፣ ከምህዳራዊ አስተሳሰብ መርሆዎች አኳያ፣ በማንኛውም ምህዳር ውስጥ የሚገኙ ክፋዮች ምንም ያህል አናሳ ቢሆኑ፣ እንደ ምሉዕነታቸው ለአጠቃላዩ ምህዳር ጤናማነት እና ዘላቂነት የራሳቸው የሆነ ድርሻ አላቸው። የተፈጥሮ ምህዳሮቻችንን ብንመለከት፣ ከትንሿቷ ህዋስ አንስቶ አስከ ታላቁ ሰው የየራሳቸው ወሳኝ ድርሻ እንዳላቸው ነው የምናየው። በተመሳሳይም፣ በሃገራችን ውስጥ ያሉ ማህበረሰቦች፣ ምንም ያህል አናሳ ቢሆኑ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚኖረው የፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ምህዳር ጤናማነት እና ዘላቂነት የራሳቸው የሆነ ድርሻ እንደሚኖራቸው መገንዘብ ይገባል።

ባለፉት ሁለት የሽግግር ዓመታት ውስጥ፣ በአፋር እና በሶማሊ ክልሎች የታየው አንጻራዊ መረጋጋት እና ሰላም ለሃገሪቱ ቀጣይነት የነበረው አስተዋጽኦ ለዚህ አንድ ማረጋገጫ ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪ፣ የአንድ የፖለቲካ ሥርዓት ዴሞክራሲያዊነት ከሚመዘንበት ዋነኛ የመልካም አስተዳደር መስፈርቶች አንዱ ለአናሳ የማህበረሰብ ክፍሎች በሚሰጠው የመብት ጥበቃ መሆኑን የፖለቲካ መሪዎቻችን ተረድተው ዳሩን ከመሃሉ ለሚያስተሳስር ፖለቲካ መትጋት ይኖርባቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ፣ በእነኚህ ክልሎችም የሚገኙ ወጣት የፖለቲካ መሪዎች እየተካሄደ ላለው ሽግግር ልዩ እና ጠቃሚ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉበት ታሪካዊ ወቅት ላይ መሆናቸውን ተገንዝበው ለሃገራዊው አንድነት ምስረታ ድርሻቸውን አጠናክረው ማበርከት ይጠበቅባቸዋል።

## የክፍል ሶስት ቁልፍ ሐሳቦች

i. ከመዋቅራዊ ችግሮቻችን የመጀመሪያው፣ በሃገራችን ታሪክ ላይ ያለው ሁለት ጽንፍ የያዘ አመለካከት ነው። ባንደኛው ጽንፍ፣ ኢትዮጵያ ቀደምት እና እጅግ አኩሪ የሆነ ታሪክ ያላት አገር ናት በማለት ሲያምን በሌላኛው ጫፍ ደግሞ፣ ኢትዮጵያ የምትባለው ሃገር ከአንድ መቶ ሃያ ወይም ሰላሳ ዓመት ወዲህ በነበሩ ወረራዎች የተፈጠረች እና ታሪኳም የህዝቦች ጭቆና እና ግፍ ታሪክ ነው የሚል ነው። ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ፣ እንደብዙዎቹ ሃገሮች ኢትዮጵያም አንፀባራቂ እና አሳፋሪ የታሪክ ምዕራፍ አሳልፋለች። በመሆኑም፣ ያለን ብቸኛው እና ጠቃሚው መንገድ ከዚህ የታሪክ ዕውነታ በመማር በአኩሪ እና ጠቃሚው ላይ መገንባት እና አሳፋሪው እና ጎጂው እንዳይደገም መጣር ነው።

ii. ሁለተኛው መዋቅራዊ ችግር የዴሞክራሲ ሥርዓቱን የሚመለከት ሲሆን፣ ባንዱ ጫፍ ያሉ ወገኖች የኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ሥርዓት አሁን ሰፍኖ ካለው የብሔር ፖለቲካ ተቀይሮ በግለሰብ ነፃነት ላይ ወደ ተመረኮዘ የዜግነት ፖለቲካ በአስቸኳይ ካልተሸጋገረ ሃገሪቱ በማያባራ የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ትቀጥላለች ብለው ያምናሉ። በሌላ በኩል ደግሞ፣ የብሔር ጥያቄ የሀገሪቱ ዋነኛ የፖለቲካ ጥያቄ በመሆኑ የሀገሪቱ የፖለቲካ ሥርዓትም በዚሁ ዙሪያ ከመዋቀር ውጭ ሌላ አማራጭ የለውም ብለው የሚያምኑ ወገኖች አሉ። ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ፣ በግለሰብ መብት እና ቡድን መብት መካከል ጥብቅ የሆነ መተሳሰር ከመኖሩም በላይ ባንዱ ላይ ብቻ የተመረኮዘ የፖለቲካ ሥርዓት የተሟላ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይሆናል ተብሎ አይታመንም።

iii. ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ይዞት ከመጣው በርካታ ፈተናዎች እና እድሎች አኳያ አብዮታዊ ዲሞክራሲም ሆነ ሊበራል ዲሞክራሲ ዘመኑን የማይመጥኑ መሆናቸው ይነገራል። ለምሳሌም ያህል፣ የመረጃ እና ግንኙነት ቴክኖሎጂ በፈጠረው አመቺነት ላይ በመመርኮዝ ህዝቦች በመንግስታዊ ፖሊሲ ውሳኔዎች ላይ የሚኖራቸው ቀጥተኛ ተሳታፊነት (e-Governance) እያደገ እንደሚሄድ ይጠበቃል። ከዚህም በላይ፣ አካታች እና ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ ከምንጊዜውም የበለጠ አሳታፊ (participatory) እና በሰፊ መግባባት

(consensus) ላይ የተመረኮዘ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት አጅግ አስፈላጊ ይሆናል።

iv. ሶስተኛው መዋቅራዊ ፈተና፣ አሁን በስራ ላይ ካለው ህገመንግስት ጋር የተያያዘ ነው። ይህን በተመለከተ፣ ባንድ በኩል አሁን ያለው ህገመንግስት በመሰረታዊ ባህሪው ኢዴሞክራሲያዊ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ ማስወገድ እና በሌላ አዲስ ህገመንግስት መተካት አለበት ብለው የሚያምኑ ወገኖች አሉ። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ይህ ህገመንግስት የብሔረሰቦችን መብት ያስከበረ በመሆኑ እርሱን ለመቀየር መሞከር ሃገሪቱን ወደ መበታተን ሊወስዳት ይችላል የሚሉ ወገኖች አሉ። ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ፣ የትኛውም ህገመንግስት ከጅምሩ ሙሉ በኩለሄ ሆኖ የሚፈጠር ሳይሆን በየወቅቱ እየተሻሻለ እና እየበለፀገ የሚሄድ ህልው (organic) ሰነድ ነው።

v. አራተኛው ፈተና፣ በስራ ላይ ካለው ህገመንግስት ጋር በተያያዘ ሃገሪቱ ሊኖራት የሚገባው የፌዴራል አወቃቀርን ይመለከታል። ባንድ በኩል፣ አሁን በስራ ላይ ያለው በብሔር ላይ የተመረኮዘ የፌደራል መዋቅር የሃገሪቱን አንድነት የሚፈታተን እና ወደመበታተን የሚያመራ ስለሆነ ሙሉ በሙሉ መቀየር አለበት ብለው የሚያምኑ ወገኖች አሉ። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ያለው የፌደራል አወቃቀር ለብሔሮች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ያጎናጸፈ በመሆኑ እርሱን ለመቀየር መሞከር ሀገሪቱን ወደ ብጥብጥ እና መበታተን ሊወስዳት ይችላል የሚሉ ወገኖች አሉ። ከምህዳራዊው አስተሳሰብ አኳያ፣ የማንኛውም ፌደራላዊ ሥርዓት ውጤታማነት የሚለካው ማንኛውም ሰው በሰውነቱ ሊኖረው የሚገባውን መሰረታዊ የመኖር እና በአካልም በመንፈስም የመበልፀግ መብቶች ከቡድናዊ መብቶች ጋር አጣጥሞ መተግበር ሲችል ነው።

vi. በኢትዮጵያ የፖለቲካ ስርዓት ውስጥ ዋነኛ ተዋንያን ነን የሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች የአጠቃላይ የሃገሪቱ የፖለቲካ ምህዳር አካል ናቸው። ይህም ማለት፣ አንዱ ፓርቲ ከሌላው ፓርቲ ጋር የሚኖረው መስተጋብር ባጠቃላይ የምህዳሩን ጤናማነት ይወስነዋል። በመሆኑም በማንኛውም ወቅት ለሚፈጠር የፖለቲካ ቀውስ፣ (የድርሻ ማነስ ወይም መብዛት ካልሆነ በስተቀር) የትኛውም ፓርቲ ከደሙ ንጹህ ነኝ ማለት አይችልም። ከዚህ አኳያ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቀዳሚ ተግባር መሆን ያለበት ለህዝቦች ልዕልና ተገዢ በመሆን፤ ዋነኛ የሆኑት መዋቅራዊ የፖለቲካ ችግሮችን እውቀት ላይ በተመረኮዘ አካሄድ በሂደት ሊፈቱ የሚችሉበትን መንገድ ማዘጋጀት እና መተግበር ነው።

vii. በርካታ ኢትዮጵያውያን 'የኢትዮጵያ ፖለቲካ ዋነኛው ችግር በአማራው፣ በኦሮሞው እና በትግራይ የፖለቲካ ልሂቃን (elites) መካከል ያለው የበላይነት ፉክክር ነው' የሚል እምነት አላቸው። እነኚህ አስተያየቶች በሃገራችን ፖለቲካ ውስጥ ካሉት እና ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገቡ ዋነኛ መዋቅራዊ ችግሮች አንዱ የሆነውን የመሃል እና ዳር (centre-periphery) ፖለቲካን የሚያመላክቱ ናቸው። ይህ የዳር እና የመሃል ፖለቲካ በረጅሙ የመሳፍንት ዘመን መሰረቱን

የጣለ ቢሆንም በተከታታይ የነበሩ መንግስታትም መልኩን በመጠኑ ከመቀየር ባለፈ መሰረታዊ ይዘቱን አልቀየሩትም።

viii. ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ በዘመነ ኢህአዴግ በአንድ በኩል ሁሉም ህዝቦች ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩበት እና የራሳቸውን እድል በራሳቸው የሚወስኑበት ህገ መንግስታዊ ሥርዓት በመመስረት ህዝቦች በእኩልነት የሚሳተፉበት ሥርዓተ መንግስት እንደተተገበረ ሲነገር ቆይቷል። በሌላ በኩል ግን፣ በፌደራል ደረጃ ወሳኝ የሆነውን የፓርቲም ሆነ መንግስታዊ ስልጣን በሚመለከት በቀድሞው አጠራር ዳር ሃገር፣ በኢህአዴግ አጠራር ታዳጊ ክልሎች የሚባሉትን ህዝቦችን በአግባቡ ያላካተተ እንደነበር ይታወቃል።

ix. ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ፣ የአማራ፣ የኦሮሞ እና የትግራይ ህዝቦች በሀገሪቱ የፖለቲካ ህይወት ጉልህ ድርሻ መያዝ በራሱ የችግር ምንጭ ሊሆን አይገባውም። ይልቁንም፣ እነኚህ ህዝቦች ለሃገሪቱ የረጅም ዘመን ታሪክ ከነበራቸው ጉልህ አስተዋጽኦ እና ካበለጸጉት ከፍተኛ ማህበራዊ ንዋይ (social capital) አኳያ በጣም ጠቃሚ የሆነ የአካታችነት (inclusivity) እና የአረጋጊነት (stability) ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። ይህንን ሆኖ ለመገኘት ግን፣ ከዚህ ቀጥሎ ከተጠቀሱት ህመሞች ራሳቸውን ማንጻት ይጠበቅባቸዋል።

x. የመጀመሪያው፣ የፖለቲካ ልሂቃኖቹ ለዘመናት ተብትቦ ከያዛቸው በሴራ እና እርስ በርስ በመጠፋፋት ላይ ከተመረኮዘ ባላባታዊ ፖለቲካ ራሳቸውን ማንጻት ይኖርባቸዋል። በሁለተኛ ደረጃ፣ በሃሳብ ልዕልና ላይ ከተመረኮዘ መንግስታዊ ሥርዓት ይልቅ ባላቸው የህዝብ ቁጥር ትልቅነት ላይ ወደተመረኮዘ ጨቋኝ አገዛዝ (tyranny of numbers) የሚወስድ ዝንባሌን በጥብቅ ሊታገሉ ይገባቸዋል። በሶስተኛ ደረጃ፣ በጠረፍ አካባቢ የሚኖሩ ህዝቦች ለኢትዮጵያ ዳር ድንበር መከበር እና ለሃገራዊ እሴት ግንባታ ቁልፍ አስተዋጽ ማበርከታቸውን መረዳት ነው።

## 4. ማንነት እና የዳያስፖራው ፖለቲካ

ከማንነት ጋር የተያያዙ የፖለቲካ ጥያቄዎች በ1960ዎቹ የተማሪዎች ንቅናቄ መቀንቀን ከጀመሩበት ጊዜ አንስቶ የፖለቲካ ውዝግብ ምንጮች ነበሩ። ከ1983 የመንግስት ለውጥ በኃላ፣ የማንነት ጥያቄ የተለየ ተቋማዊ ቅርጽ እና ይዘት ይዞ በመምጣቱ የሃገሪቱ ፖለቲካ ምስቅልቅል ዋነኛ ምንጭ ሊሆን ችሏል። አንዳንዶች በየዋህነት እንደሚያስቡት፣ የማንነት ጥያቄ እንዲህ በቀላሉ ገሸሽ (write-off) የሚደረግ ሳይሆን ባግባቡ ልንመለከተው እና ልንወያይበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ይህም፣ በሃገራችን ውስጥ ያሉ መሰረታዊ የማንነት ቀውስ ምንጮችን መመርመር እና ተገቢውን ምላሽ መስጠት ይጠይቃል።

### 4.1 የማንነት ቀውስ እና የኢትዮጵያ ፖለቲካ[17]

በህዝቦች መካከል ለበርካታ ምዕተ ዓመታት በተለያየ ደረጃ የነበሩት መስተጋብሮች እና መተሳሰሮች የአሸበራቂው የኢትዮጵያ ታሪክ ዋነኛ መሰረቶች መሆናቸው እሙን ነው። ይህ የህዝቦች መተሳሰር ባለፉት ጥቂት ዓስርተ ዓመታት በሃገሪቱ የተከሰቱትን ከፍተኛ የፖለቲካ ምስቅልቅሎች ለመሻገር ዓብይ ድርሻ የነበረው እና ወደፊትም የሚኖረው መሆኑ አያጠያይቅም። ነገር ግን፣ ይህ በህዝቦች መካካል ለዘመናት የቆየው መተሳሰር በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ የሃገረ መንግስት ምስረታ ሂደት ውስጥ ከፉኛ ተፈትኗል፣ በመፈተንም ላይ ይገኛል። የዚህም ፈተና ዋነኛው አስኳል በሁለት ልዩ ታሪካዊ ወቅቶች በተግባር ላይ ከዋሉ የአሃዳዊነት ሥርዓቶች ጋር በተያያዘ የተፈጠሩ የማንነት ቀውሶች (Identity crisis) ናቸው።

የመጀመሪያው፣ የኢትዮጵያን ሃገረ መንግስት በአንድ ወጥ አሃዳዊነት (Monocultural unitarianism) ላይ በተመረኮዘ ማንነት ለመገንባት ከተደረገው ጥረት ጋር የሚያያዝ ሲሆን፤ ሁለተኛው፤ ቀደም ሲል በአሃዳዊነት ዘመን የደረሰውን በደል ለማከም በሚል በተወሰዱ መንግስታዊ እርምጃዎች የተፈጠረው ብሔረሰባዊ አሃዳዊነት (Ethnicised unitarianism) ናቸው። የኢትዮጵያን ፖለቲካ ለማከም የሚደረገው ጥረት፣ የእነኚህን የማንነት ቀውሶች ምንጭ ባግባቡ በመረዳት መፍትሄ መሻትን ይጠይቃል። የዚህ ክፍል ዋነኛ ትኩረት እነኚህን አበይት የማንነት ቀውሶች ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ በመመርመር የመፍትሄ ሃሳቦችን መጠቆም ነው።

ከዘመነ መሳፍንት በኃላ ኢትዮጵያን እንደገና ለማጠናከር እና ዘመናዊ ፊር ለማስያዝ በዓጼ ቴዎድሮስ የተጀመረው እና በተከታታይ ነገሥታት የቀጠለው ሂደት በሃገሪቱ ታሪክ ውስጥ ለዘመናዊቷ ኢትዮጵያ መመስረት እንደ አዲስ ፊር ቀዳጅ ተደርጎ ይወሰዳል። ይህ የአገዛዝ ሽግግር፣ ለጥቁር ህዝቦች የነፃነት ተምሳሌት የሆነውን የዓድዋን ድል ለማስገኘት እና ሃገሪቱንም ከቅኝ ተገዢነት ለመከላከል ያስቻለውን ታላቅ ማህበራዊ

[17] የዚህ ክፍል አብዛኛው፣ ነሐሴ 2 ቀን 2012 በወጣው አዲስ አድማስ ጋዜጣ ታትሟል።

መሰረት ማበርከቱ አያጠያይቅም። ይሁን እንጂ፣ በተከታታይ ነገሥታት የተከናወኑት የሃገረ መንግሥት ግንባታ ሂደቶች በኢኮኖሚያዊ ትስስር እና ልማት ላይ የተመረኮዘ ሃገራዊ አንድነት ላይ ከማተኮር ይልቅ አንድ ወጥ አሃዳዊነትን በሚያጠናክሩ ተቋማዊ እርምጃዎች እና ተጽእኖዎች ላይ በማተኮሩ ለበርካታ የማንነት ቀውሶች ምንጭ ሊሆኑ ችለዋል።

ለዚህም፣ ቋንቋና ሃይማኖቶች እንደ ዋነኛ መሳሪያ ማገልገላቸውን የሚያመላክቱ በርካታ የታሪክ መረጃዎች አሉ። ይህም ለዘመናት፣ በተለይም በአማርኛ እና በኦሮምኛ እንዲሁም በክርስትና እና በእስልምና መካከል የነበረውን መገፋፋት እና መወራረስ መመልከት ይቻላል። በዘመነ ዓጼ ኃይለ ሥላሴ ይህ የአሃዳዊነት ሂደት ከፍተኛ ተቋሟዊ ቅርጽ እየያዘ ለመምጣቱ በርካታ ማሳያዎች ማቅረብ ይቻላል። ለምሳሌም ያህል፣ ለበርካታ ዓመታት በሀገሪቱ ብቸኛ በሆነው የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ ለመማር የአማርኛ ፈተናን ማለፍ ግዴታ ነበር። አንድን ቋንቋ እንደሃገራዊ የመግባቢያ ቋንቋ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ድረስ ማስተማሩ አስፈላጊ መሆኑ ባይካድም፣ በዩኒቨርሲቲ የማስተማር ሂደት ውስጥ ምንም አይነት አስተዋጽኦ የማይኖረውን እና ለብዙዎች ሁለተኛ ቋንቋ የሆነውን ካላለፍክ ብሎ የአንድን ዜጋ የመማር መብት መከልከል የሚፈጥረው የተጎጂነት ስሜት ቀላል አይደለም።

ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ በርካታ ኢትዮጵያውያን ገና ወደ ትምህርት ቤት ሲመጡም ሆነ ስራ በሚቀጠሩበት ጊዜ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የተሰጣቸውን መጠሪያ ስም እንዲቀይሩ ይገደዱ እንደነበር የሚነገሩ ትርክቶችም አሉ። እዚህ ላይ፣ ታላቁ የአማርኛ ሥነጽሁፍ ሊቅ እና ባለቅኔው አቦ ፀጋዬ ገብረመድህን የዚሁ ተጽእኖ ሰለባ እንደነበር መግለጹ በቂ ነው። ይህና ሌሎች ከቋንቋ ጋር የተያያዙ ተቋሟዊ ጭቆናዎች በአፍሪካ ውስጥ ብቸኛ የሆነ የራሱ የጽሁፍ ሥርዓት ባለው የአማርኛ ቋንቋችን መኩራት ሲገባን በርካቶች እንደመጨቆኛ መሳሪያ እንዲመለከቱት አድርጓቸዋል። ለአስተዋይነታቸው ምስጋና ይግባው እና፣ አቦ ፀጋዬን እና ጋሽ ስብሐትን የመሰሉ በርካታ የሥነ ጽሁፍ ሰዎች እንደዘመኑ አንዳንድ ፖለቲከኞች አማርኛን አትናገሩ ከማለት በተቃራኒው ቋንቋውን ይበልጥ አበልጽገውት እና አዳብረውት አልፈዋል።

ወደ ሃይማኖቱ ስንመጣ፣ ሃገራችን ኢትዮጵያ ከመካ ውጭ ሁለተኛዋ እስልምና የተሰበከባት እና የተመለከባት ሃገር ብቻ ሳትሆን ያለ እርሷ ከለላ እና ድጋፍ ምናልባትም እስልምና ዛሬ ለደረሰበት ደረጃም ላይደርስ ይችል ነበር ተብሎ ይነገራል። ይህም በመሆኑ፣ በነጂህ ሁለት ታላላቅ ሃይማኖቶች መካከል አልፎ አልፎ የመገፋፋት ግጭት ቢኖርም በአብዛኛው ለዘመናት የዘለቀ መወራረስ እና መተሳሰርን ፈጥሯል። ይህ ሁኔታ በአብዛኛው ማህበረሰባችን ውስጥ የሚታይ ሲሆን በተለይም በቀድሞው የወሎ ክፍለ ሃገር ውስጥ እጅግ በሚያስገርም ሁኔታ ጎልቶ ይገኛል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ተከታታይ ነገሥታት ከክርስትና እምነት ጋር ከነበራቸው ጥብቅ ትስስር የተነሳ የእስልምና ዕምነት ተከታዮች የተለያዩ የኢድሎአዊነት በደሎችን ሲያስተናግዱ ኖረዋል። ይህ አድሎአዊነት በመጨረሻዎቹ ነገሥታት ዘመን ይበልጥ ተቋማዊ ቅርጽ ሊይዝ ችሏል።

ከዚህ ውስጥ አንዱ መገለጫ፣ በርካታ የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ ተማሪዎች ባሉበት ትምህርት ቤት ውስጥ በየዕለቱ ጠዋት ትምህርት ከመጀመሩ በፊት የክርስትያኑን ፀሎት ሁሉም እንዲጸልዩ ማስገደድ ነበር[18]። ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ በልጅነት አእምሮዬ ከሚያሳዝኑኝ ትውስታዎቼ አንዱ የተወሰኑ አብሮ አደግ ጓደኞቼ በረመዳን ጾም ወቅት ይህንን የግዴታ ፀሎት ላለመጸለይ ሲሉ ዘግይተው ወደ ትምህርት ቤት በመምጣት ወደ ክፍል ከመግባታቸው በፊት የሚደርስባቸው ቅጣት ነበር። ከላይ የቀረቡት ምሳሌዎች በእኛው ዘመን ከነበረው ታሪካችን እንደማሳያ የቀረቡ ሲሆኑ ከዚህም የከፉ በርካታ የአሃዳዊነት መገለጫዎች ተቋማዊ በሆነ ደረጃ ይራመዱ እንደነበር መካድ ራስን መሸንገል ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ በርካታ ወገኖቻችን በተለያየ መልክ ለሚገለጹ የማንነት ቀውሶች እንዲጋለጡ እና አንዳንድ ወገኖቻንም ኢትዮጵያዊነታቸውን እስከመጠራጠር እንዲደርሱ አድርጓቸዋል።

የዘመናዊ ትምህርት በሃገሪቱ እየተስፋፋ መምጣቱ እና ከፊውዳላዊው ሥርዓት ጋር ተያይዞ ከነበረው መጠነ ሰፊ ጭቆና ጋር መጣጣም አለመቻሉ ለተማሪው እንቅስቃሴ መጀመር ዋነኛ ምክንያት ነበር። ከዚህ በተጨማሪ፣ ከላይ በተጠቀሰው አሃዳዊ አገዛዝ ምክንያት ተፈጥሮ የነበረው የማንነት ቀውስ የተለያዩ የማንነት ሙብት ጥያቄዎች እንዲነሱ አድርጓል። በመሆኑም፣ በርካታው ተማሪ መሰረታዊ የሆኑ ሃገራዊ እና ሰብአዊ የሙብት ጥያቄዎችን እንደሃገራዊ ዋነኛ የለውጥ መታገያ ሲያነሳ፣ የተወሰኑት ደግሞ የብሄረሰቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ሙብት እንደዋነኛ መታገያ ሊያነሱ ችለዋል። የተማሪው ንቅናቄ ድርጅታዊ ቅርጽ እየያዘ ሲመጣም፣ የመጀመሪያዎቹ ወደ ህብረ ብሄራዊ የፖለቲካ ድርጅትነት ሲቀየሩ ሁለተኞቹ ደግሞ ወደ ብሔረሰብ ነፃ አውጪ ድርጅትነት ተሸጋገሩ።

የየካቲት 1966 የህዝብ ንቅናቄን ተከትሎ፣ ወታደራዊው ደርግ አንዳንድ የጭቆና መገለጫዎችን ለማስወገድ የሚያስችሉ እርምጃዎችን የወሰደ ቢሆንም፣ መሰረታዊ ሃገራዊ አንድነትን ለማምጣት የሚያስችሉ መብቶችን ሊያከብር አልቻለም። ከዚህ ይልቅ፣ በወቅቱ የነበሩት የፖለቲካ ድርጅቶች የነበረባቸውን ድክመት በመጠቀም የራሱን አምባገነናዊ አገዛዝ ለማጠናከር በወሰደው እርምጃ ለበርካታ ብርቅዬ ዜጎች መሰዋት ምክንያት ሆኗል። በዚህ እርምጃው፣ ወታደራዊው ደርግ በቀዳሚነት ለማጥፋት ቆርጦ የተነሳው በፍጹም የሃገር እና የህዝብ መውደድ ስሜት በተለያዩ ህብረ ብሄራዊ የፖለቲካ ድርጅቶች ስር ተሰባስበው ይታገሉ የነበሩትን መሆኑ የሃገሪቱን ቀጣይ ዘመን እጅግ ፈታኝ አድርጎታል። ይህ ሁኔታም፣ በዋነኝነት የብሔር ጭቆናን ለመታገል በሚል የተደራጁት የብሔር ነጻ አውጪ ድርጅቶች ይበልጥ እንዲጠናከሩ እና ሰፊ ማህበራዊ መሰረት እንዲያገኙ አግዟቸዋል። የኢትዮጵያ ህዝብ አብዮታዊ ሠራዊት (ኢህአሠ) መበተን እና የህወሃት ተጠናክሮ መውጣት ከዚህ ሁኔታ ጋር የተያያዘ እንደነበር ይነገራል።

[18] ይህ ሁኔታ፣ በወቅቱ እንደወሎ እና ሐረርጌ ክፍለ ሃገር ከነበሩ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች በስተቀር በአብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች የነበረ እውነታ ነው።

ከዚህ ተከትሎ የመጣው የኢህአዴግ መንግስት፣ በተማሪዎች እንቅስቃሴ ውስጥ ያቆጠቆጠውን የብሔረሰቦችን ራስን በራስ የማስተዳደር መብቶችን ለመተግበር የሚያስችሉ ማእቀፎችን ለመመስረት ሙከራ አድርጓል። የህዝቦች ቋንቋ እና ባህል የሚከበርበት እና ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩበት መንግስታዊ ሥርዓት መፍጠር እንደ ኢትዮጵያ ላሉ የበርካታ የብሔረሰቦች ሃገር ዘላቂ ልማት እና እድገት አስፈላጊ መሆኑ ሊያከራክር አይገባም። ነገር ግን፣ ኢህአዴግ የተከተለው መስመር የትናትናውን በደል ለመካስ በሚመስል መልኩ፣ የሌሎችን ዜጎች በየትኛውም የሃገሪቱ ክልል በነፃነት የመኖር መብት ለመጣስ መጠቀሚያ በመሆኑ ቀደም ሲል የነበረውን አንድ ወጥ አሃዳዊነት በርከት ወዳለ ብሔረሰባዊ አሃዳዊነት (Ethnicised Unitarianism) እንዲያመራ አድርጎታል።

በመሆኑም፣ በተለያዩ ክልሎች የሚኖሩ በርካታ የሃገሪቱ ዜጎች ኢትዮጵያዊነታቸውን ለሚያጠራጥር አዲስ አይነት የማንነት ቀውስ ተዳርገዋል። ይህ ባንዳንድ የአፍሪካ ፖለቲካ ተንታኞች አደገኛ ተብሎ የሚጠቀስ ሙከራ ለሃገራዊ አንድነት መጠናከር የሚጠቅሙ እሴቶችን ለመሸርሸር የሄደበት አሳፋሪ መንገድም ሃገሪቱን ዛሬ ላለችበት የፖለቲካ ቀውስ እና ራሱንም ለታሪክ ተወቃሽነት አብቅቷል። በጥቅሉ፣ የማንነት ጥያቄ ባለፉት ሰላሳ ዓመታት በተግባር ላይ ከዋለው የፌደራል አወቃቀር ጋር በተያያዘም ይበልጥ አወዛጋቢ ከሆኑ የፖለቲካ ጥያቄዎች አንዱ እና ዋነኛው እንዲሆን አድርጎታል። ከዚያም አልፎ፣ ለበርካታ ወገኖች እልቂት እና በብዙ መቶ ሺህ ለሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን መፈናቀል ምክንያት ሆኗል።

ባለፉት ስልሳ አመታት የማንነትን ጥያቄ በተመለከተ የሚሰጡ ትንታኔዎች በአብዛኛው በፖለቲካው መስክ ከሚታየው የተቀነበበ ትንተና ድክመቶች የነጻ ሊሆኑ አልቻሉም። ይህም፣ ባንድ በኩል በሃገሪቱ ምንም አይነት የብሔር ጭቆና አልነበረም ከሚለው እና ገሃድ የነበረውን የማንነት በደሎች በሃገራዊ አንድነት ለመሸፈን ከሚደረግ ሰጎናዊ አቋም አንስቶ፣ ፍትሃዊ የሆነውን የብሔሮችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ድረስ በሚለጥጠው ተስፈንጣሪ የግራ ዘመም አቋም ይገለጻል። ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ፣ የማንኛውም ሰው ማንነት የበርካታ ጥምር መለያዎች መስተጋብር እንጂ በአንድ የተናጠል ባህርይ የሚገለጽ አይደለም። በዚህም መሰረት፣ የማንኛውም ሰው ማንነት በመሰረታዊነት በሚከተሉት ሶስት ዋነኛ የማንነት ጥምር መስተጋብር የሚገለጽ ይሆናል።

የመጀመሪያው ዓብይ ማንነት፣ የተፈጥሮ ማንነት (natural identity) ሲሆን ይህም የሰው ልጅ ከእንስሳቱ ዓለም የሚለየውን ሰብዓዊ ባህርይ የሚያጎናጽፈው ተፈጥሮዋዊው የዘረ መልእ ማንነቱ ነው። በዚህም ማንነቱ የተነሳ ሁሉም የሰው ልጅ በሰውነቱ የሚጎናጸፈው መሰረታዊ ባህሪያት እና መብቶች ይኖሩታል። ይህ የተፈጥሮ ማንነት የማናቸውም ማንነት መነሻ መሰረት በመሆኑ የሉላዊነት (universality) ባህሪ አለው። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማግስት፣ በተባበሩት መንግስታት የጸደቀው ሉላዊ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌ (Universal Declaration of Human Rights) በዚሁ የሰው ልጆች ሰብዓዊ ማንነት እና ተያያዥ መብቶቻቸው ላይ የተመሰረተ ነው። በመሆኑም፣ ለበርካታ አባል ሃገራት ህገ መንግስት እንደመነሻ ግብዓት በማገልገል ላይ ይገኛል። በጥቅል

አነጋገር፣ ሰብዓዊነትን በምሉዕነቱ የማይቀበል ማንነት ለሌሎች ማንኛቸውም የማንነት መብቶች መከበር የመቆም የሞራል ብቃት ሊኖረው አይችልም። መነሻ መሰረቱን አልያዘምና።

ሁለተኛው ዓብይ ማንነት፣ ማህበራዊ ማንነት (social identity) ሲሆን ይህም ማንነት የሰው ልጆች ታሪክ መመዝገብ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በተለያየ ማህበራዊ እድገት ውስጥ ያለፈ ማንነት ነው። የማህበራዊ ማንነት ዋነኛ መሰረቱ ቤተሰብ እና ያደጉበት ማህበረሰብ ሲሆን፣ የማንኛችንም ማህበራዊ ማንነት ከቤተሰብ እና ከማህበረሰብ በሚተላለፉ የቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ትምህርት፣ ባህል፣ እና፣ ልማዳዊ ውርሶች የሚወሰን ይሆናል። ስለዚህም፣ ማህበራዊ ማንነት ከከባቢ መንደር (neighbourhood) አንስቶ እስከ ጎሳ፣ነገድ፣ እና የብሔረሰብ ደረጃ ሊኖረው ይችላል። በዚህ ማህበራዊ ማንነት ውስጥ፣ ከቤተሰብ እና ከመንደር ጋር የተያያዘው ማንነት ከሌሎቹ ማህበራዊ ማንነቶች የጠበቀ ቁርኝት ይኖራቸዋል። በመሆኑም፣ ማንኛውም ሰብዓዊ ማንነትን ማእከል አድርጎ ያልተደራጀ የብሔረሰብ ነፃ አውጪ ድርጅት በመንደርተኝነት መፈተኑ የማይቀር ይሆናል። እንዲህ አይነቱ ፈተና፣ ባሁኑ ወቅት በሃገራችን በሚገኙም ብዙዎቹ የብሔረሰብ ድርጅቶች ውስጥ የሚታይ ችግር ነው[19]።

ሶስተኛው አቢይ ማንነት፣ ፖለቲካዊ ማንነት (political identity) ሲሆን ይህም ማንነት ከሃገረ-መንግሥት ምስረታ ታሪክ ጋር የተያያዘ የዜግነት ማንነት ነው። የዜግነት ማንነት፣ ባንድ ሃገረ መንግስት ወይም ምድራዊ ክልል ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች በሚጋሯቸው የጋራ ፖለቲካዊ እና ታሪካዊ እሳቤዎች የሚቀረጽ ይሆናል። በመሆኑም፣ ዛሬ ባለው ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ አንድ ሰው ካንድ በላይ የሆነ ዜግነት ሊኖረው ይችላል። ለምሳሌም ያህል፣ በአንዳንድ ሃገሮች ካለው የጥምር ዜግነት በተጨማሪ፣ በበርካታ ሃገራት የመስራት እና የመኖር እድል ያገኘ ወይም ራሱን ከበርካታ ሃገራት በሚገኙ ዕውቀቶች ያበለጸገ ሰው ራሱን ከኢትዮጵያዊነቱ ባሻገር አፍሪካዊ (Pan African) እና ዓለም አቀፋዊ ዜጋ (Global citizen) ነኝ ብሎ ሊያምን ይችላል። እንዲህ አይነቱ የዜግነት ልህቀት ለማንኛቸውም ማህበራዊ ማንነት ተገቢውን እውቅና እና አክብሮት የሚሰጥ ከመሆኑም በላይ በመጀመሪያ ደረጃ ካነሳነው ሰብዓዊ ማንነት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ይሆናል። በመሆኑም፣ የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የዜግነት መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል።

ለዘመናት በሃገራችን ሲራመድ የኖረው አሃዳዊ ሥርዓት ከፈጠረው የማንነት ቀውስ ጋር በተያያዘ የተለያዩ ቡድኖች በማህበራዊ ማንነት ላይ የተመረኮዙ የፖለቲካ ድርጅቶች መስርተው ለመታገል መነሳታቸው እንደ ሃጢያት ሊቆጠር አይገባውም። በዚህ ረገድ፣ አንዳንድ የፖለቲካ መሪዎች እና ተንታኞች በብሔር ለሚደራጁ ወገኖች የተለያዩ

[19] የኦሮሞ ነፃ አውጭ ግንባር ለረጅም ዘመን በወለጋ ኦሮሞዎች በተለይም በሆሮ ጉዱሩ ተወላጆች ተጽእኖ ስር ወድቋል ሲባል፤ የትግራይ ህዝቦች ነፃ አውጭ ግንባርም በአድዋ ተወላጆች ተጽእኖ ስር እንደነበር መነገሩ፣ በብሔር ማንነት ላይ የተመረኮዘ የፖለቲካ ንቅናቄ በሰብዕአዊ ማነነት እና በዜግነት አስተሳሰብ ካልተቃኘ ወደ መንደርተኝነት ለመውረዱ ማሳያ ነው።

አፍራሽ ቅጥያዎች በመለጠፍ በህግ እንዲታገዱ ከመጠየቃቸው በፊት የሀገሪቱን ታሪካዊ እና ተጨባጭ እውነታ በጥሞና መመርመሩ ይጠቅማቸዋል። በብሔር የመደራጀት ዋነኛው ችግር የሚመነጨው፣ ማህበራዊ ማንነትን እንደ ብቸኛው የማንነት መገለጫ ከማድረግ እና ይህንንም ለሃገረ መንግስት ምስረታ እንደ ዋነኛ መነሻ መሰረት አድርጎ ከመውሰዱ ላይ ነው። እነኚህ በማህበራዊ ማንነት ላይ የተመረኮዙ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ከተፈለገ ሰብዓዊ ማንነትን በሚያከብር እና ለዘመኑ በሚመጥን የዜግነት አመለካከት ሊቃኙ ይገባቸዋል። ይህ ካልሆነ፣ በብዙዎቹ አንጋፋ የብሔር ድርጅቶች ውስጥ ባሁኑ ስዓት እንደሚታየው ጠባብ ወደሆነ የመንደር እና የቤተሰብ መጠቀሚያነት መሸጋገራቸው እና የግጭት እና ውድቀት ምንጭ መሆናቸው የማይቀር ይሆናል።

የሃገራችንን ፖለቲካ አካታች እና ፍትሃዊ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት ለዘመናት የተጠራቀሙትን የማንነት ቀውሶች በሃገራዊ አንድነት ማከም በጣም አስፈላጊ ያደርገዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ ባለፉት ሰላሳ ዓመታት ባጠቃላይ፣ ላለፉት ጥቂት ዓመታት በተለይ በሃገሪቱ ገኖ የታየውን 'የብሔር ፖለቲካ' በሃገራዊ አንድነት መቃኘት ያሰፈልጋል። ይህ እንዲሆን፣ በማህበራዊ ማንነት ላይ የተመረኮዘ ሃቀኛ ፖለቲካ የሚያራምዱ ቡድኖች ጥያቄዎቻቸው በተሟላ ሁኔታ ሊመለሱ የሚችሉት ሰብዓዊ ማንነትን እና የዜግነት መብትን በሚያካትት ማዕቀፍ ውስጥ ብቻ መሆኑን መረዳት እና ይህንኑም ማክበር እና ማስከበር ይኖርባቸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ፣ ህብረብሔራዊ ወይንም የዜግነት ፖለቲካ እናራምዳለን የሚሉ የፖለቲካ ቡድኖችም፣ በዘመናት ውስጥ የተፈጠረውን የማንነት ቀውስ እና ከዚህ ጋር ተያይዞ ያለውን የመንፈስ መጎዳት በመረዳት ይህንን ለመፈወስ የሚያስችሉ መፍትሔዎችን ከብሔር ፖለቲካ አራማጆች ጋር በጋራ መሻት እና ለተግባራዊነቱም አብሮ መስራት ይጠበቅባቸዋል። ይህንንም በማድረግ፣ ይበልጥ አሰባሳቢ እና አካታች ወደሆነ የፖለቲካ ሥርዓት መሸጋገር ይቻላል።

## 4.2 ዳያስፖራው እና የኢትዮጵያ ፖለቲካ[20]

በአንድ ወቅት፣ ካንድ ወዳጄ ጋር ኢትዮጵያውያኖች ከሃገራችን ውጪ ስንኖር ከኢትዮጵያዊነታችን ጋር ያለንን ማህበራዊ ትስስር ለማቆየት የምንሄድበትን ርቀት ከሌሎች የአፍሪካ ሃገራት ዜጎች ጋር እያወዳደርን በመገረም ተወያይተን ነበር። በዚህ ውይይት የደረስንበት ማጠቃለያ፣ በርግጥም እንደሚባለው 'ኢትዮጵያዊውን በአካል ከኢትዮጵያ ታወጣው እንደሆነ እንጂ ኢትዮጵያን ከኢትዮጵያዊው ውስጥ ማውጣት እንደማይቻል ነበር'። ይህም፣ የሃገሪቱ ህዝቦች ካሏቸው ጥልቅ ማህበራዊ እና ታሪካዊ መሰረት ጋር የተያያዘ መሆኑ አያጠያይቅም። ከዚሁ ጥብቅ ትስስር ጋር በተያያዘ፣ ከሃገር ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በተለያየ ወቅት በሃገሪቱ በተከሰቱ አበይት የፖለቲካ ሁነቶችም ንቁ ተሳታፊ እንደነበሩ ይታወቃል። ስለሆነም፣ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሲነሳ፣ በውጭ ሃገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የነበራቸውን ጠቃሚም ሆነ ጎጂ አስተዋጽኦዎች አለማንሳት አይቻልም። ከሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳዎቹ ወዲህ ያለውን የኢትዮጵያውያን ዳያስፖራ የፖለቲካ ተሳትፎ በምንመለከትበት ጊዜ በዋነኝነት በሚከተሉት ሶስት የዳያስፖራ ፖለቲካ ዘመኖች የሚካተቱ ይሆናል።

የመጀመርያው፣ ከ1966 የህዝብ ንቅናቄ ጋር በተያያዘ ከንቅናቄው በፊት እና በኋላ በነበሩ በርካታ ከስተቶች ውስጥ ከሃገራችን ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ምሁራን እና ተማሪዎች የነበራቸው የመሪነት እና ተሳታፊነት ሚና ነው። የየካቲት ስልሳ ስድስቱ የህዝብ ንቅናቄ በተማሪው እንቅስቃሴ ውስጥ ተጸንሶ በመምህራኑ፣ በታክሲ ነጂው፣ በእስልምና እምነት ተከታዩ፣ እና በመለዮ ለባሹ የመብት ጥያቄዎች በመታገዝ ህዝባዊ ንቅናቄ ለመሆን የበቃ ነበር[21]። ለንቅናቄው መከሰት አብይ ድርሻ ከነበረው የሃገር ውስጥ የተማሪ ንቅናቄ በተጨማሪ በሰሜን አሜሪካ እና በአውሮፓ የነበረው የኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ማህበር የኢትዮጵያን ቀጣይ እጣ ፋንታ በመወሰን ረገድ ጉልህ ድርሻ ነበረው። ይህ በውጭ ሃገር በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ይካሄድ የነበረ እንቅስቃሴ በፍጹም የሃገር እና ህዝብ የመውደድ ስሜት ላይ የተመረኮዘ ቢሆንም፣ ገና ከጅምሩ ትግሉ ሊከተለው በሚገባው አቅጣጫ ላይ የተወሰነ የአካሄድ ልዩነት ነበረው። ይህንን የአካሄድ ልዩነት ለማስታረቅ እና ለማስማማት የሚያስችል የርዕዮተ ዓለም እና የግብ መመሳሰል ቢኖርም፤ ጥቂት መሪዎች ባሳዩት የ'አልሸነፍም ባይነት' አመለካከት የተነሳ አንዱ የሌላውን ሃሳብ ለማዳመጥ እና ለማስተናገድ ዝግጁ ባለመሆኑ ከፍተቱ እየሰፋ መጠላለፉም እየባሰበት ሊሄድ ችሏል።

[20] የዚህ ክፍል አብዛኛው፣ ነሐሴ 9 ቀን 2012 በወጣው አዲስ አድማስ ጋዜጣ ታትሟል።

[21] ከዚህ ቀደም ሲል፣ በጎጃም፣ በባሌ እና በትግራይ የተነሱ የገበሬዎች እንቅስቃሴዎች ቢኖሩም በተወሰደባቸው ወታደራዊ እርምጃ ለህዝባዊ ንቅናቄነት ሳይበቁ ቀርተዋል።

እነኚህ ወገኖች በመሃከላቸው የነበረውን ልዩነት እንደያዙ ወደ ሃገር ውስጥ በመግባታቸው፣ በሃገር ቤት የነበረው ወጣትም በሁለት ጎራ እንዲሰለፍ አድርጎታል። ይህ ልዩነት፣ በለውጡ የመጀመሪያዎቹ ዓመታት በተወሰዱ የገጠር መሬትን የህዝብ ያደረገውን አዋጅ በመሳሰሉ ስር ነቀል እርምጃዎች ምክንያት ይበልጥ እየሰፋ በመሄድ ላንድ ትውልድ የርስ በርስ መተላለቅ የራሱን አሳዛኝ ድርሻ ሊያበረክት ችሏል። በመሆኑም፣ የመጀመሪያው ትውልድ ዳያስፖራ የ1966 ንቅናቄ ይዞት ለመጣው ሃገራዊ የሽግግር እድል መምጣትም ሆነ በአጭር መጨናገፍ የራሱን አስተዋጽ አድርጓል ማለት ይቻላል።

የ1966 የህዝብ ንቅናቄን ተከትሎ ወደ ስልጣን የመጣው ወታደራዊ መንግስት ስልጣኑን ለማጠናከር የወሰዳቸው ፖለቲካዊ እርምጃዎች በህዝባዊው ንቅናቄ ግንባር ቀደም ተሳታፊ የነበረውን የተማረ የሰው ኃይል በእጅጉ ሊያመናምነው ችሏል። ይህንን ተከትሎ፣ እስከ 1983 ድረስ በነበረው ከፍተኛ የፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ቀውስ የተነሳ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ሃገር ጥለው ለመሰደድ ተገደዋል። ይህም፣ ቀደም ሲል በአብዛኛው ለትምህርት በወጣው እና አነስተኛ ቁጥር ባለው ኢትዮጵያዊ የሚታወቀውን የመጀመሪያውን የዳያስፖራ የፖለቲካ ዘመን ገድታ ቀይሮታል። ከዚህ ከሁለተኛው የዳያስፖራ የፖለቲካ ዘመን ኢትዮጵያውያን አብዛኞቹ በሁለተኛ ዜግነታቸው የሚደርስባቸውን በርካታ ፈተናዎች በመቋቋም ኑሮአቸውን ማሸነፍ ላይ ቢያተኩሩም፣ የተወሰኑት ከኑሮው ትግል በተጨማሪ በሃገሪቱ የወደፊት የፖለቲካ እጣ ፋንታ ላይ መንቀሳቀሱን ቀጥለው ነበር።

ይህንን መሰረት በማድረግም ቁጥራቸው ከበፊቱ በዛ ያለ የፖለቲካ ቡድኖች ተደራጅተው የተለያየ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ቆይተዋል። ይህም፣ ቀደም ሲል በሃገር ውስጥ ለመንቀሳቀስ የሞከሩትን ህብረ ብሔራዊ ድርጅቶችን ጨምሮ አዳዲስ የፖለቲካ ድርጅቶች እና ሃገር ውስጥ በትጥቅ ትግል ይንቀሳቀሱ የነበሩ 'ነጻ አውጭ ድርጅቶች' ደጋፊ ቡድኖችን ያካትታል። የነኚህን ድርጅቶች የተናጠል እንቅስቃሴዎች ለማቀናጀት የተለያዩ ጥረቶች ቢደረጉም አካታች ለሆነ የፖለቲካ ሥርዓት ባለው አናሳ አእምሮአዊ ዝግጁነት የተነሳ ውጤታማ ሊሆን አልቻለም። በዚህ አይነቱ፣ ሁሉም በየራሱ ጎጆ ተደራጅቶ እርስ በርሱ በሚራኮትበት ሁኔታ እራሳቸውን በትጥቅ ትግል ያደራጁ 'የነጻ አውጭ ድርጅቶች'[22] ተሳክቶላቸው ሃገሪቱን ሙሉ ለሙሉ ሊቆጣጠሩ ችለዋል። ኢህአዴግም፣ ከጅምሩ በህብረ ብሔራዊ የፖለቲካ ድርጅቶች ላይ በነበረው የጠላትነት ስሜት የተነሳ እንዲህ አይነቶቹ ድርጅቶች ወደ ሃገር ውስጥ እንዳይገቡ ከገቡም ትርጉም ያለው እንቅስቃሴ እንዳያደርጉ

[22] እነኚህ ድርጅቶች ለትጥቅ ትግሉ የነበራቸው ጽኑ እምነት እና የከፈሉት መስዋዕትነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በገዢው ሥርዓት ውስጥ የነበረው መፍረክረክ እና በዓመታት ውስጥ የተጠናከረው የህዝብ ድጋፍ እጦት ለ 1983 ለውጥ መምጣት ከፍተኛውን ድርሻ አበርክቷል ተብሎ ይታመናል።

ከፍተኛ ጫና አድርጓል።በመሆኑም፣ ሁለተኛው የዳያስፖራ ትውልድ በ1983 በነበረው የሽግግር ኢጋጣሚ ትርጉም ያለው ድርሻ ለማበርከት ሳይችል ቀርቷል።

ሶስተኛው የዳያስፖራ የፖለቲካ ዘመን ከአንደኛው እና ከሁለተኛው የዳያስፖራ የፖለቲካ ዘመን ከተሸጋገረው በተጨማሪ በዘመነ ኢህአዴግ ከሃገር ተሰዶ የወጣውን እና በተለያየ ህጋዊ የቪዛ ፕሮግራሞች የሄደውን ኢትዮጵያዊ ያካትታል። ይህ ጊዜ ከ1983 እስከ 2010 የነበረውን የኢህአዴግ ዘመን የሚሸፍን ሲሆን ምናልባትም ቀደም ሲል ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ጽንፈኝነት የበረታበት የፖለቲካ አመለካከት ገኖ የወጣበት ዘመን ነው። ለዚህ ሁኔታ መፈጠር፣ በሁሉም ዘመን ከነበሩት መሰረታዊ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ህመሞች በተጨማሪ የሚከተሉት ሁኔታዎች አስተዋጽኦ እንዳደረጉ ይገመታል። የመጀመሪያው እና ምናልባትም ዋነኛው ምክንያት፣ ተረኛ ጨቋኝነት (reverse repression) በሚመስል መልኩ በኢህአዴግ ተግባራዊ የተደረገው በብሔረሰባዊ አሃዳዊነት (Ethnicised unitarianism) ላይ የተመረኮዘው ፌደራላዊ ሥርዓት ያስከተለው የሰብዓዊ መብት ጥሰት እና ከዚህ ጋር ተያይዞ የተፈጠረው ጥልቅ የተጠቂነት ስሜት ነው።

ሁለተኛው አቢይ ችግር፣ ጭፍን በሆነ የተጠቃሚነት ስሜት ፖለቲካውን በቀጥታ ራስን እና የራስን ቡድን ለማበልጸጊያ ለመጠቀም የተዘጋጁ ግለሰቦች እና የተደራጁ ቡድኖች እየበረከቱ መምጣታቸው ነው። የእነኚህ የፖለቲካ ነጋዴዎች (political entrepreneurs) ህልውና የሀገሪቱ ፖለቲካ የተረጋጋ ካለመሆኑ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ጽንፍ የያዙ የፖለቲካ አመለካከቶችን ማራገብ ዋነኛ መገለጫቸው ሊሆን ችሏል። ሶስተኛው፣ ባግባቡ ያልተብላላ እና ያልበሰለ መረጃን ለማሰራጨት ማህበራዊ ሚዲያ የፈጠረው አመቺነት እና ከዚህ ጋር በተያያዘ እየገነነ የመጣው ዋልታ ረገጥነት ነው። በይነ መረብ (internet) እና ማህበራዊ ሚዲያ[23] ማንኛውንም መረጃ በእኩልነት ለሁሉም ማዳረስ ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ሰው መረጃን የማመንጨት አቅምንም ፈጥሮለታል። በዚህም የተነሳ፣ ማህበራዊ ሚዲያ አንድን ማህበረሰብ ከፍ ወዳለ እድገት ለማሻገር የሚያስችል የመሆኑን ያህል ለከፍተኛ ጥፋትም ሊዳርግ ይችላል። በዚህ ረገድ፣ የበይነ መረብን አመቺ ሁኔታ ለህዝብ እና ለሃገር ጥቅም በሚጠቅም መልኩ የሚጠቀሙ በርካቶች የመኖራቸውን ያህል ጥቂቶች በህዝቦች መካከል መቃቃር እና ግጭት ለመፍጠር የሚያደርጉት አሳዛኝ እና አሳፋሪ ጥረት ለሃገሪቱ ፖለቲካ መረጋጋት ከባድ ፈተና እየሆነ መጥቷል። ይህ ሁኔታ፣ በጋዜጠኝነት፣ ማህበራዊ አንቂነት እና በፖለቲከኛነት መካከል ባለው የሚና መጠላለፍና የሥነምግባር ጉድለት ይበልጥ እየተወሳሰበ ይገኛል።

[23] አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፣ የብዙዎቹ ገበያ ተኮር ማህበራዊ ሚዲያዎች መሰረታዊ አደረጃጀት (architecture) ከመጠን ያለፈ ራስ ወዳድነትን (egocentrism) የሚያበረታቱ በመሆናቸው፣ ማህበራዊ ደህንነትን እና ትብብርን አደጋ ላይ የመጣል እድላቸው ከፍተኛ ሊሆን ይችላል። ይህ ሁኔታ፣ በማደግ ላይ ላሉ ሃገሮች ብቻ ሳይሆን በቅርቡ በአሜሪካ እንደታየው፣ ለበለጸጉት ሃገሮችም ፈታኝ በመሆን ላይ ይገኛል።

ይህ እንዳለ ሆኖ፣ ሶስተኛው የዳያስፖራ የፖለቲካ ዘመን በመሰረታዊ ባህሪያቸው የሚለያዩ ሁለት አበይት ክፍሎች እንዳሉት መገንዘብ ያስፈልጋል። የመጀመሪያው፣ አብዛኛውን ዳያስፖራ ኢትዮጵያዊ የሚወክለው እና የሃገሪቱን ሰላም እና እድገት በጽኑ የሚመኘው ዝምተኛው ብዙኃን (the silent majority) ሲሆን፣ እነኚህ ወገኖች ለሃገሪቱ እና ለህዝቡ ይጠቅማሉ ለሚባሉ ጥሪዎች ሁሉ ያለብዙ ጫጫታ ጊዜያቸውን፣ ገንዘባቸውን፣ እና ዕውቀታቸውን የሚያበረክቱ ናቸው። ከዚህ በተቃራኒው የሚገኙት ጥቂት ጫጫሂዎች (the noisy minorities) ጽንፈኛ በሆነ የፖለቲካ አመለካከት እና ስሜታዊ በሆኑ የፖለቲካ ጥያቄዎች እያደናገሩ የራሳቸውን እና የቡድናቸውን ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ አላማዎች ለማሳካት የሚሯሯጡ ናቸው።

ምንም እንኳን፣ በዘመነ ኢህአዴግ የነበረው የዳያስፖራ ፖለቲካ ጽንፈኝነት የበረታበት ቢሆንም ብዙዎቹ ለኢህአዴግ ከነበራቸው ጥልቅ ተቃውሞ የተነሳ ቀጥተኛ ያልሆነ ተደጋጋፊነትም ነበራቸው። ይህም በመሆኑ፣ በ2010 በሃገሪቱ ለተከሰተው ሃገራዊ ለውጥ የየራሳቸውን አስተዋጽኦ አድርገዋል። የ2010 ለውጥንም ተከትሎ፣ ጥቂት የዳያስፖራ ፖለቲካ አቀንቃኞች በሃገሪቱ ፖለቲካ ውስጥ በቀጥታ ለመሳተፍ የተደረገውን ጥሪ በመቀበል ወደ ሃገር ውስጥ ሊገቡ ችለዋል። ይህ እድል የ1966 ህዝባዊ ንቅናቄን ተከትሎ ከተከሰቱ የፖለቲካ እድሎች ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን ለተመሳሳይ ውድቀት ሊያጋልጡት የሚያስችሉ ምልክቶችም በመታየት ላይ ይገኛሉ። አሁን የተፈጠረው መልካም የለውጥ አጋጣሚ እንደ ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ስድስቱ የለውጥ አጋጣሚ እንዳያመልጠን ከዚህ በታች የተመለከቱትን ከዳያስፖራው ፖለቲካ ጋር የተያያዙ መሰረተ ቢስ እምነቶችን (myths) ማከም ይገባል።

አንደኛው እና ምናልባትም ዋነኛው፣ ጥቂት የ2010 የዳያስፖራ የፖለቲካ ዘመን ጽንፈኛ መሪዎች እና አቀንቃኞች ለተፈጠረው የለውጥ ሂደት ያበረከቱትን አስተዋጽኦ እጅግ አግዝፈው ማየታቸው ነው። ከዚህም የተነሳ፣ በሃገር ውስጥ የነበረው የብዙሃኑን የለውጥ ታጋይ ድርሻ አሳንሶ ከመመልከትም ባሻገር ለውጡ ያለ እነሱ አመራር የትም ሊደርስ አይችልም ብለው እስከማመን ይደርሳሉ። በምህዳራዊ አስተሳሰብ መሰረት፣ በማንኛውም ምህዳር ውስጥ ሊመጣ የሚችል ለውጥ ዋነኛው መሰረቱ (foundation) በዚያው ምህዳር ውስጥ ያለው ውስጣዊ መስተጋብር (internal dynamics) ሲሆን የውጫዊ ሁኔታዎች ድርሻ የዚህን የለውጥ ፍጥነት ከማፋጠን ወይም ከማዘግየት ያለፈ አይሆንም። በመሆኑም፣ ለ2010 ለውጥ መምጣት የዳያስፖራው የአጋዥነት ድርሻ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ዋነኛው ድርሻ ሊሰጥ የሚገባው በቀዳሚነት በሃገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ለነበረው የህዝቦች ትግል እና የወጣቶች ንቅናቄ ሊሆን ይገባዋል። ከዚህ በተጨማሪ፣ ለለውጡ አንጻራዊ ሰላማዊነት የወሳኝነቱን ሚና (determining factor) የሚወስደው በራሱ በኢህአዴግ ውስጥ የተፈጠረው የለውጥ አመራር እና ከዚህ ጋር ተያይዞ የተፈጠረው የኦሮሞ እና የአማራ ህዝቦች (ኦሮማራ) ጥምረት መሆኑ ብዙም አካራካሪ ሊሆን አይገባም።

በዚህ ረገድ፣ የዛሬዎቹም ሆኑ የወደፊቶቹ የዳያስፖራ ፖለቲካ አራማጆች እና አቀንቃኞች ለራሳቸው ከሚሰጡት የገዘፈ የመሪነት ማማ (pedestal) ወርደው ሃገራዊ ለውጡን ወደፊት ለማራመድ በሚያስችሉ ድጋፎች ላይ ቢያተኩሩ የሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳ ስድስቱ የዳያስፖራ ትውልድ ፖለቲካ መሪዎች ካጋጠማቸው የታሪክ ተወቃሽነት ሊድኑ ይችላሉ።

ሁለተኛው፣ ለሃገሪቱ ለውጥ ታላቅ ድጋፍ እና አበርክቶት ሊያረግ የሚችለው ዝምተኛው ብዙሃን በጋራም ሆነ በተናጠል እራሱ ሊኖረው የሚችለውን ሚና አሳንሶ ማየቱ ነው። በዚህም የተነሳ፣ የበርካታው ዳያስፖራ ኢትዮጵያዊ በጎ ፈቃድ የጥቂት ብልጣብልጥ ፖለቲከኞች እና የማህበራዊ ሚድያው[24] አርበኞች መጠቀሚያ ሲሆን ይታያል። እንደሚታውቀው፣ 'በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ እጅግ አሳዛኝ እና አሳፋሪ ሁነቶች በዋነኝነት የተከሰቱት እኩይ አመለካከት ባላቸው ጥቂቶች ጥንካሬ ሳይሆን መልካም አስተሳሰብ ባላቸው ብዙሃኖች ዝምታ ነው' ይባላል። በቅርቡ በሃገራችን ለደረሰው እና እየደረሰ ላለው አሳዛኝ እና አሳፋሪ ኢሰብዓዊ ወንጀል የባላባታዊ ሴራ ፖለቲካ አራማጆች እና ጥቂት ጽንፈኛ አመለካከት ያላቸው የማህበራዊ ሚዲያ አርበኞች ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስዱ ቢሆንም የእነኚህን አጥፊ ወገኖችን ተግባር በዝምታ ያስተናገድነው ብዙሃንም የራሳችን ድርሻ አለን። በዚህ ረገድ፣ እነኚህ የጥፋት መልእክተኞች ያላቸውን መልካም ኢጋጣሚ እና ዕድል በመጠቀም በህዝቦች መካከል መቃቃር እና ግጭትን ለመፍጠር የሚችሉበትን ሁኔታ ማጥበብ እና ማስወገድ ያስፈልጋል።

የሃገራችን ፖለቲካ ለረጅም ጊዜ በጥቂት ጫፍዎች ሲታመስ ቆይቶ ዛሬ ያለንበት አሳዛኝም ተስፋ ሰጪም ሁኔታ ላይ ደርሷል። በተለያዩ አገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች የተነሳ፣ አሁን ሃገሪቱ ያለችበት ሁኔታ ከዚህ ቀደም ከነበሩት የሽግግር ወቅቶች እጅግ የተለየ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። በዚህ ጸሃፊ እምነት፣ በሚመጡት ጥቂት ዓመታት በሀገሪቱ የሚከሰቱት የፖለቲካ ሁኔታዎች ይህች ሃገራችንን ወይ ወደ ከፍተኛ የልማት እና እድገት አቅጣጫ ይወስዳታል አለበለዚያ እንደ ሃገር የማትቀጥልበት ሁኔታ ውስጥ ይከታታል። ስለሆነም፣ የዚህች ሃገር የነገ እጣ ፋንታ የሚያስጨንቀን ወገኖች ዝምታችንን ሰብረን ባለን እውቀት እና አቅም እየተካሄደ ያለው ለውጥ ሁሉንም አካታች ወደሆነ እና የዜጎችን ሁለንተናዊ የዲሞክራሲ እና የልማት ፍላጎቶችን ሊያሟላ ወደሚችል ሥርዓት እንዲሸጋገር ማገዝ ይኖርብናል።

[24] በአሁኑ ወቅት፣ ማህበራዊ ሚዲያው በዓለም ዙሪያ ህዝበኝነት (populist) ለሚያጠቃቸው ፖለቲከኞች እና ቡድኖች መጠቀሚያ ከመሆን ባሻገር ከፍተኛ ጥፋት ሊያስከትሉ የሚችሉ አክራሪ ብሔርተኞች (ultra nationalist) እንዲፈለፈሉ አመቺ ሁኔታ በመፍጠር ላይ ይገኛል።

## የክፍል አራት ቁልፍ ሐሳቦች

i. በህዝቦች መካከል ለበርካታ ምዕተ ዓመታት በተለያየ ደረጃ የነበሩት መስተጋብሮች እና መተሳሰሮች የአሸብራቂው የኢትዮጵያ ታሪክ ዋነኛ መሰረቶች መሆናቸው እሙን ነው። ይህ የህዝቦች መተሳሰር ባለፉት ጥቂት ዓስርተ ዓመታት በሃገሪቱ የተከሰቱትን ከፍተኛ የፖለቲካ ምስቅልቅሎች ለመሻገር ዓብይ ድርሻ የነበረው እና ወደፊትም የሚኖረው መሆኑ አያጠያይቅም። ነገር ግን፣ ይህ በህዝቦች መካካል ለዘመናት የቆየው መተሳሰር በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ የሃገረ መንግስት ምስረታ ሂደት ውስጥ ከፉኛ ተፈትኗል፣ በመፈተንም ላይ ይገኛል። የዚህም ፈተና ዋነኛው አስኳል በሁለት ልዩ ታሪካዊ ወቅቶች በተግባር ላይ ከዋሉ የአሃዳዊነት ሥርዓቶች ጋር በተያያዘ የተፈጠሩ የማንነት ቀውሶች (Identity crises) ናቸው።

ii. የመጀመሪያው፣ የኢትዮጵያን ሃገረ መንግስት በአንድ ወጥ አሃዳዊነት (Monocultural unitarianism) ላይ በተመረኮዘ ማንነት ለመገንባት ከተደረገው ጥረት ጋር የሚያያዝ ሲሆን፤ ሁለተኛው፤ ቀደም ሲል በአሃዳዊነት ዘመን የደረሰውን በደል ለማከም በሚል በተወሰዱ መንግስታዊ እርምጃዎች የተፈጠረው ብሔረሰባዊ አሃዳዊነት (Ethnicised unitarianism) ናቸው። የኢትዮጵያን ፖለቲካ ለማከም የሚደረገው ጥረት፣ የእነኚህን የማንነት ቀውሶች ምንጭ ባግባቡ በመረዳት መፍትሄ መሻትን ይጠይቃል።

iii. የዘመናዊ ትምህርት በሃገሪቱ እየተስፋፋ መምጣት እና ከፊውዳላዊው ሥርዓት ጋር ተያይዞ ከነበረው መጠነ ሰፊ ጭቆና ጋር መጣጣም አለመቻል ለተማሪው እንቅስቃሴ መጀመር ዋነኛ ምክንያት ነበር። ከዚህ በተጨማሪ፣ ከላይ በተጠቀሰው አሃዳዊ አገዛዝ ምክንያት ተፈጥሮ የነበረው የማንነት ቀውስ የተለያዩ የማንነት መብት ጥያቄዎች እንዲነሱ አድርጓል። በመሆኑም፣ በርካታው ተማሪ መሰረታዊ የሆኑ ሃገራዊ እና ሰብአዊ የመብት ጥያቄዎችን እንደሃገራዊ ዋነኛ የለውጥ መታገያ ሲያነሳ፣ የተወሰኑት ደግሞ የብሄረሰቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እንደዋነኛ መታገያ ሊያነሱ ችለዋል።

iv. ባለፉት ስልሳ አመታት የማንነትን ጥያቄ በተመለከተ የሚሰጡ ትንታኔዎች በአብዛኛው በፖለቲካው መስክ ከሚታየው የተቀነበበ ትንተና ድክመቶች የነጹ ሊሆኑ አልቻሉም። ይህም፣ ባንድ በኩል በሃገሪቱ ምንም አይነት የብሔር ጭቆና አልነበረም ከሚለው እና ገሃድ የነበረውን የማንነት በደሎች በሃገራዊ አንድነት ለመሸፈን ከሚደረግ ሰነናዊ አቋም አንስቶ ፍትሃዊ የሆነውን የብሔሮችን የራስን በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል ድረስ በሚለጥጠው ተስፈንጣሪ የግራ ዘመም አቋም ይገለጻል።

v. ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ፣ የማንኛውም ሰው ማንነት የበርካታ ጥምር መለያዎች መስተጋብር እንጂ በአንድ የተናጠል ባህርይ የሚገለጽ አይደለም። ከዚህም የመጀመሪያው ማንነት፣ የተፈጥሮ ማንነት ሲሆን ይህም የሰው ልጅ ከእንስሳቱ ዓለም የሚለየውን ሰብዓዊ ባህርይ የሚያንጸባርቀው ተፈጥሮዋዊው

የዘረ መልእ ማንነቱ ነው። ሁለተኛው ማንነት፣ ማህበራዊ ማንነት ሲሆን የማንኛችንም ማህበራዊ ማንነት ከቤተሰብ በሚተላለፉ የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የባህል፣ እና፣ የልማዳዊ ሁነት ውርሶች የሚወሰን ይሆናል። ሶስተኛው ማንነት፣ ፖለቲካዊ ማንነት ሲሆን ይህም ከሃገረ መንግስት ምስረታ ታሪክ ጋር የተያያዘ የዜግነት ማንነት ነው።

vi. በማህበራዊ ማንነት ላይ የተመረኮዙ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ከተፈለገ ሰብዓዊ ማንነትን በሚያከብር እና ለዘመኑ በሚመጥን የዜግነት አመለካከት ሊቃኙ ይገባቸዋል። ይህ ካልሆነ፣ በብዙዎቹ አንጋፋ የብሔር ድርጅቶች ውስጥ ባሁኑ ስዓት እንደሚታየው ጠባብ ወደሆነ የመንደር እና የቤተሰብ መጠቀሚያነት መሸጋገራቸው እና የግጭት እና ውዝግብ ምንጭ መሆናቸው የማይቀር ይሆናል።

vii. 'አትዮጵያዊውን በአካል ከኢትዮጵያ ታወጣው እንደሆነ እንጂ ኢትዮጵያን ከኢትዮጵያዊው ውስጥ ማውጣት አይቻልም' የሚል አባባል አለ። ይህም፣ የሃገሪቱ ህዝቦች ካሏቸው ጥልቅ ማህበራዊ እና ታሪካዊ መሰረት ጋር የተያያዘ መሆኑ አያጠያይቅም። ከዚሁ ጥብቅ ትስስር ጋር በተያያዘ፣ ከሃገር ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በተለያየ ወቅት በሃገሪቱ በተከሰቱ አበይት የፖለቲካ ሁነቶችም ንቁ ተሳታፊ እንደነበሩ ይታወቃል። ስለሆነም፣ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሲነሳ፣ በውጭ ሃገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የነበራቸውን ጠቃሚም ሆነ ጎጂ አስተዋጽኦዎች አለማንሳት አይቻልም።

viii. ከሺህ ዘጠኝ መዶ ስልሳዎቹ ወዲህ ያለውን የኢትዮጵያውያን ዳያስፖራ የፖለቲካ ተሳትፎ በምንመለከትበት ጊዜ በዋነኝነት ሶስት የዳያስፖራ ፖለቲካ ዘመኖች እንዳሉ እናያለን። እነኚህም፣ በሃገሪቱ የቅርብ ዘመን የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ታላላቅ የለውጥ አጋጣሚዎችን ከሚወክሉት የ1966፣ የ1983 እና የ2010 የለውጥ አጋጣሚዎች ጋር የተያያዙ ሆነው እናገኛቸዋለን። በእነዚህ የለውጥ አጋጣሚዎች ዳያስፖራው ጠቃሚም ጎጂም አበርክቶት እንደነበረው ይነገራል።

ix. ዳያስፖራው ሊያበረክት የሚችለውን በጎ አስተዋጽኦ ለማጠናከር፣ በእንቅስቃሴው ውስጥ የሚታዩ አንዳንድ መሰረተ ቢስ እምነቶችን (myths) ማከም ይገባል። የመጀመሪያው፣ አንዳንድ የዳያስፖራ የፖለቲካ ዘመን መሪዎች እና አቀኝቃኞች ለተፈጠረው የለውጥ ሂደት ያበረከቱትን አስተዋጽኦ እጅግ አግዝፈው ማየታቸው ነው። ከዚህም የተነሳ፣ ለውጡ ያለ እነሱ አመራር የትም ሊደርስ አይችልም ብለው እስከማመን ይደርሳሉ።

x. በማንኛውም ምህዳር ውስጥ ሊመጣ የሚችል ለውጥ ዋነኛው መሰረቱ በዚያው ምህዳር ውስጥ ያለው ውስጣዊ መስተጋብር (internal dynamics) ሲሆን የውጫዊ ሁኔታዎች ድርሻ የዚህን የለውጥ ፍጥነት ከማሳለጥ ወይም ከማዘግየት ያለፈ አይሆንም።

xi. ሁለተኛው፣ ለሃገሪቱ ለውጥ ታላቅ ድጋፍ እና አበርክቶት ሊያረግ የሚችለው ዝምተኛው ብዙሃን ዳያስፖራ በጋራም ሆነ በተናጠል እራሱ ሊኖረው የሚችለውን ሚና አሳንሶ ማየቱ ነው። በዚህም የተነሳ፣ የበርካታው ዳያስፖራ ኢትዮጵያዊ በጎ ፈቃድ የጥቂት ብልጣብልጥ ፖለቲከኞች እና የማህበራዊ ሚድያው አርበኞች መጠቀሚያ ሲሆን ይታያል።

xii. ስለሆነም፣ የዚህች ሃገር የነገ እጣ ፋንታ የሚያስጨንቀን ወገኖች ዝምታችንን ሰብረን ባለን እውቀት እና አቅም እየተካሄደ ያለው ለውጥ ሁሉንም አካታች ወደሆነ እና የዜጎችን ሁለንተናዊ የዲሞክራሲ እና የልማት ፍላጎቶችን ሊያሟላ ወደሚችል ሥርዓት እንዲሸጋገር ማገዝ ይኖርብናል።

# 5. ሴታዊነት፣ ለኢትዮጵያ ፖለቲካ ጤናማነት

የዓለማችን የሃገረ መንግስት ምስረታ በአጠቃላይ የወንዶች የበላይነት የሰፈነበት ነው ማለት ይቻላል። ያም ሆኖ፣ በሃገራችን ኢትዮጵያ የሃገረ መንግስት ታሪክ ውስጥ ታላቅ ስፍራ የነበራቸው ሴት ነገሥታቶች ነበሩ። የ1966 አብዮትን ተከትሎ በመላ ሃገሪቱ ይሰሙ ከነበሩ ፖለቲካዊ መፈክሮች አንዱ 'ያለ ሴቶች ተሳትፎ አብዮቱ ግቡን አይመታም' የሚለው ሶሻሊስታዊ መፈክር እንደነበር ይታወቃል። ምንም እንኳን በዓለም አቀፍ ደረጃ ባለፉት መቶ ዓመታት ሴቶች ባንድ ማህበረሰብ እድገት ውስጥ ያላቸው ሁለንተናዊ ድርሻ ይበልጥ እውቅና እያገኘ የመጣ ቢሆንም፣ በተግባራዊነቱ ላይ ግን ገና ብዙ ርቀት መጓዝ ያስፈልጋል። ለዚህም የመጀመሪያው እርምጃ፣ ሴታዊነት ለማንኛውም ማህበረሰብ ዘላቂ ልማት ሊያበረክታቸው የሚችላቸውን ልዩ አስተዋጽኦ በበቂ ሁኔታ መረዳት ነው።

## 5.1 ሴታዊነት እና የኢትዮጵያ ፖለቲካ[25]

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዓቢይ አህመድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተወደሱበት አበይት እርምጃዎች አንዱ በርካታ ሴት አመራሮችን በመንግስታቸው ውስጥ ማካተታቸው እና በዘመናዊው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ታሪክ ውስጥ የመጀመርያ የሆኑትን የሃገሪቱ ሴት ርዕሰ ብሔር እንዲሾሙ ማድረጋቸው ነው። እንዲህ ዓይነቱ እርምጃ፣ የሃገራችን ሴቶች በሃገሪቱ የወደፊት እጣ ፈንታ ሊኖራቸው የሚችለውን በጎ አስተዋጽኦ ለማበረታት ጉልህ ድርሻ እንደሚኖረው ይታመናል። ከዚህ እርምጃ ቀደም ሲል፣ ባላፉት ጥቂት አስርተ ዓመታት ውስጥ ሴቶችን በሚመለከት በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉትን የተዛቡ አመለካከቶች በማጋለጥ እና በመታገል የሴቶችን ሁለንተናዊ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለማሳደግ የሚጥሩ ሃገር በቀል ተቋማት እየበዙ መምጣታቸውም አበረታች የለውጥ ምልክት ነው።

እነኝህ እርምጃዎች፣ በተባባሩት መንግስታት እና በአፍሪካ ሕብረት ከተወሰኑት የሴቶችን የእኩልነት መብት የማረጋገጥ ውሳኔዎች ጋር የተጣጣሙ ከመሆኑም ባሻገር ለሃገራዊው ፖለቲካ ጤናማነት ከፍተኛ ድርሻ ሊያበረክቱ ይችላሉ። ነገር ግን፣ እነኝህ በፖለቲካ ድርጅቶችም ሆነ መንግስታዊ ባልሆኑ የህዝብ ተቋማት የተጀመሩ ቀና እርምጃዎች ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆኑ ከተፈለገ ሴታዊነት (Feminism) ባንድ ምህዳር ውስጥ ያለውን ምሉዕ ድርሻ በመረዳት ላይ የተመረኮዙ ሊሆኑ ይገባቸዋል። በዚህ ክፍል፣ ሴታዊነት ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ እንዴት ሊታይ እንደሚገባው እና በኢትዮጵያ ሁኔታ ሊኖረን የሚገባውን አጠቃላይ አካሄድ ለማመላከት ይሞከራል።

[25] የዚህ ክፍል አብዛኛው፣ ነሐሴ 23 ቀን 2012 በወጣው አዲስ አድማስ ጋዜጣ ታትሟል።

ተደጋግሞ እንደሚነገረው፣ የማንኛቸውም ማህበረሰብ አወቃቀር መሰረቱ ቤተሰብ ነው። ስለሆነም፣ ከሴታዊነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ባግባቡ ለመረዳት የቤተሰብ አመሰራረት ያለፈበትን ሂደት በጥቅሉ መመልከት ይጠቅማል። የቅድመ ታሪክ ቤተሰብ አመሰራረት በአብዛኛው ሴቶችን ማዕከል ባደረገ የእማዊነት (matriarchal) ሥርዓት ላይ የተመረኮዘ እንደነበር ይጠቀሳል። ይህ ሁኔታ በሂደት እየተቀየረ መጥቶ ቀስ በቀስ ወንዶች ይበልጥ ወሳኝ ወደሆኑበት አባዊ (patriarchal) የቤተሰብ ሥርዓት ተሸጋግሯል። በዚህ ሽግግር ምክንያት የተፈጠረው የወንዶች የበላይነት በተለያዩ የኢኮኖሚ ሥርዓት እያደገ ከመጣው የግል ሃብት ክምችት ጋር ይበልጥ እየተጠናከረ ሊመጣ እንደቻለ ይታወቃል። የሰው ልጅ አደረጃጀት ከቤተሰብ ወደ ማህበረሰብ ከዚያም ወደ ሃገር እያደገ ሲመጣ የወንዶችን የበላይነት የሚያጠናክረው የአባዊነት አመለካከት ይበልጥ ተቋማዊ መሰረት እየያዘ ሊመጣ ችሏል።

በዚህም የተነሳ፣ በመላው ዓለም ባሉ ማህበረሰቦች ውስጥ ሴቶች ሊኖራቸው የሚገባውን ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ስፍራ አሳጥቷቸው ቆይቷል። ይህ በመሆኑም፣ በሴቶች ላይ ከደረሱ በርካታ የሙብት ጥሰቶች ባሻገር ባጠቃላይ የሰው ልጆች ከሴቶች ቀጥተኛ ተሳታፊነት ሊያገኙ የሚችሉትን ጠቀሜታዎች እንዲያጡ አድርጎታል። ለዚህም አንዱ ማሳያው ከአባዊነቱ ዘመን እየተጠናከረ መምጣት ጋር ተያይዞ እየተበራከተ የመጣው ግጭት እና ጦርነት ከዚያም ጋር ተያይዞ የተፈጠሩት በርካታ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ቀውሶች ናቸው። ከኢንዱስትሪ አብዮት መምጣት ጋር ተያይዞ ሃገሮች በይበልጥ ወደ ህገ መንግስታዊ ሥርዓት እየተሸጋገሩ ሲመጡ የሴቶች የሙብት ጥያቄዎችም በልዩ ልዩ መልክ መገለጽ እና መነሳት ጀመሩ።

ዘመናዊውን የተደራጀ የሴቶች የሙብት እንቅስቃሴ (Feminist movement) አነሳስን ስንመለከት አሜሪካዊቷ የሴኔካ ፏፏቴ መግለጫ (Seneca Falls Declaration, 1848) አዘጋጅ ወይዘሮ ኤልሳቤጥ ስታንተን እና ጀርመናዊቷ ሶሻሊስታዊ የሴቶች ሙብት አቀንቃኝ ወይዘሮ ክላራ ዜትኪን (1857-1933) በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ። በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ አካባቢ የተጀመረው የአሜሪካው የሴቶች ሙብት እንቅስቃሴ በቀዳሚነት ያተኮረው የሃገሪቱ ሴቶች ተነፍገውት የነበረውን መሰረታዊ የመምረጥ እና የመመረጥ ሙብት ማስከበር ላይ ነበር። ይህ እንቅስቃሴ፣ ከሰባ ዓመታት ያላቋረጠ ትግል በኋላ የዛሬ ሙዳ ዓመት አካባቢ የአሜሪካ ሴቶች መሪዎቻቸውን ለመጀመሪያ ጊዜ ለመምረጥ አስችሏቸዋል።

በአንጻሩ፣ ሶሻሊስታዊው የሴቶች ሙብት እንቅስቃሴ የአሜሪካውን የሴቶች ሙብት እንቅስቃሴ የጥቂት ከበርቴዎች እና ንዑስ ከበርቴዎች ስልጣን የመካፈል ጥረት አድርጎ በመፈረጅ ትኩረቱን የብዙኃን ሴት ገበሬዎች እና ሰራተኞች ሙብትን ማስከበር ላይ ያደርጋል። እዚህ ላይ፣ የ1960ዎቹ ሴት እህቶቻችን በሶሻሊስታዊ ርእዮት ታንጸው በወቅቱ የሃገራችን ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች ያበረከቱት የመሪነት አስተዋጽኦ እና የከፈሉት መስዋዕትነት ሊዘከር ይገባዋል። ምንም እንኳን ገና በርካታ ተግባራት የሚቀሩ ቢሆንም፣

የሁለቱም ዓለም የሴቶች እንቅስቃሴዎች፣ የሴቶችን የእኩልነት መብት በማረጋገጥ ረገድ ባለፈው አንድ ምዕተ ዓመት ሊታዩ አበይት ለውጦች የየራሳቸውን ድርሻ አበርክተዋል።

ሆኖም፣ አሜሪካንን ጨምሮ በበርካታ ምዕራባዊያን ሃገራት የሚገኙ ሴቶች በፖለቲካም ሆነ በንግዱ አለም ተጭኖባቸው ያለውን ወንዴ-ሰራሽ የሥልጣን ገደብ (glass ceiling) ሰብሮ ለመውጣት ያለባቸውን ፈተና ለተመለከተ፣ ሶሻሊስታዊ ቅኝት ያላቸው ሃገሮች ሁሉን አቀፍ የሴቶች የእኩልነት መብት መከበርን በተመለከተ በተሻለ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ መረዳት ይቻላል። ለዚህም እንደማሳያ፣ በተለይ ስዊድንን በመሰሉ ስካንዲኔቪያን ሃገሮች ያለውን ሰፊ የሴቶች መብት ጥበቃ እና የአመራር ተሳትፎ መጥቀስ ይቻላል።

ወደሃገራችን ሁኔታ ስንመጣ፣ እህቶቻችን እና እናቶቻችን እንደየትኛውም የዓለማችን ማህበረሰብ በተመሳሳይ የአባዊነት ሥርዓት ለሚፈጠሩ የመብት ንፍገቶች እና ጥሰቶች የተጋለጡ ነበሩ፤ ዛሬም ናቸው። ከዚህም በላይ፣ ከተለያዩ አካባቢያዊ ልማዶች እና እምነቶች ጋር ለተያያዙ ተጨማሪ አድሎዎች እና ጥቃቶች ሲጋለጡ ኖረዋል። ያም ሆኖ ግን፣ በሃገሪቱ የረጂም ዘመን ታሪክ ውስጥ እጅግ ከፍተኛ ድርሻ የነበራቸው ንግሥቶች፤ እንስት የጦር አበጋዞች እና የማህበረሰብ መሪዎች እንደነበሩም ተመዝግቧል። ከዚህም ባሻገር፣ በሃገራችን ታሪክ ውስጥ ጉልህ ስፍራ ከሚሰጣቸው ነገሥታት እና የማህበረሰብ መሪዎች በስተጀርባ ብርቱ ሴቶች እንደነበሩ የሚያመላክቱ መረጃዎችም አሉ። በዚህ ረገድ፣ በታሪክ ቀደምት ከሚባሉት በርካታ ሃገሮች በተሻለ የሃገራችን ሴቶች በሃገሪቱ የፖለቲካ ህይወት ውስጥ የራሳቸውን አሻራ እንዳሳረፉ መረዳት ተገቢ ይሆናል።

ከዚህ በተጨማሪም፣ በአንዳንድ ማህበረሰቦች ውስጥ አንዲት ሴት በትዳር ህይወቷ የሚያጋጥሟትን ጥቃቶች፣ ሴቶች ተሰባስበው በጋራ ለመከላከል የሚያስችሏቸው ሥርዓቶች እንዳሏቸው ይነገራል። የኦሮሞ ሴቶች የሲቄ ሥርዓት ለዚህ አንድ ምሳሌ ነው።። ከዚህም አልፎ፣ ቀደም ካሉ ዘመናት ጀምሮ ለሴቶች መብት በግንባር ቀደምትነት በመቆም በየዘመኑ ተንሰራፍተው የነበሩ ኢፍትሃዊ አሰራሮችን ማስቀየር የቻሉ ቀደምት የሴቶች መብት አቀንቃኞች እንደነበሩ የሚነገሩ ተረኮችም አሉ። ለዚህም እንደማሳያ፣ በ1870ዎቹ በጉራጌ ማህበረሰብ ውስጥ ተነስተው የነበሩትን የሴቶች መብት አቀንቃኝ ወይዘሮ ቃቄ ወርድወትን መጥቀስ ይቻላል። ይህም የሚያሳየው፣ ባሁኑ ሰዓት ባንዳንድ ወገኖች ከምዕራባዊያን ሃገሮች እንደተኮረጀ ተደርጎ የሚነገርለት የሴቶች የመብት እንቅስቃሴ በሃገራችንም ቀደም ብሎ የተጀመረ እንደነበር ነው።

በምህዳራዊ አስተሳሰብ መሰረት፣ ሴታዊነት ለማንኛቸውም ተፈጥሮአዊ እና ማህበራዊ ምህዳር ቀጣይነት ዋነኛው መሰረት ነው። ይህም በአበይትነት ለሴቶች በተሰጣቸው የእናትነት ምግባር የሚገለጽ ከመሆኑም በላይ ሌሎችም መሰረታዊ የሆኑ እና ከወንዶች በበለጠ ለሴቶች የተሰጧቸው ባህርያት አሉ። ከነዚህም ውስጥ አንዱ፣ የሌላ ሰውን ችግር እንደራስ ሆኖ ለመረዳት እና ለመካፈል (empathy) ያላቸው ዝግጁነት ከብዙ ወንዶች

የበለጠ መሆኑ ነው። ሌላው፣ ኑሮን ለማሸነፍ በሚደረገው ትግል ውስጥ ካላቸው ቁልፍ ድርሻ ጋር በተያያዘ ፈታኝ ሁኔታዎችን ለመሻገር ያላቸው የስሜት (survival instinct) ዝግጁነት ነው። ይህም ባብዛኛው፣ የራሳቸውን መንፈሳዊም ሆነ ቁሳዊ ፍላጎት በመጫን እና አሳልፎ በመስጠትም ጭምር የሚገለጽ ይሆናል።

ሶስተኛው፣ ተፈጥሮአዊው ዐደትን ለማስቀጠል ካላቸው ልዩ ኃላፊነት እና ድርሻ ጋር በተያያዘ ከተፈጥሮአዊው ምህዳር ጋር ያላቸው ቅርበት እና ተዛማጅነት (ecological sensibility) ነው። አራተኛው እና ምናልባትም በሰፊው ካለብን የፖለቲካ ህመም ለመፈወስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊኖረው የሚችለው ባህሪ፣ ኃይልን መሰረት ካዳረገ (hard power) አመራር እና የግጭት አፈታት ይልቅ ስሜትን በማለስለስ እና በማሳመን (soft power) ላይ ለተመረኮዘ መፍትሄ ያላቸው ብልህነት ነው። እነኚህ እና እነኚህን የመሳሰሉ በርካታ የሴታዊነት ባህርያት እስከዛሬ ድረስ በነበሩ መንግስታዊ ሥርዓቶች ውስጥ በአግባቡ ባለመካተታቸው የተነሳ የሰው ልጆች ተነግረው ለማያልቁ ጥፋቶች እና እልቂቶች ሊዳረጉ በቅተዋል። ይህንን ሁኔታ መቀየር፣ ባሁኑ ሰዓት ዓለማችንም ሆነ ሃገራችን ተጋፍጠውት ያለውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊ፣ እና ፖለቲካዊ ፈተናዎች ለማለፍ አቢይ ድርሻ እንደሚኖረው ይታመናል።

ወደ ኢትዮጵያ ሁኔታም ስንመጣ፣ ያሉብንን ዙሪያ መለስ ፈተናዎች ባግባቡ ለመወጣት የሴታዊነት ግብአትን በሁሉም መስኮች እያጠናከርን መሄድ ይኖርብናል። ይህንን በምናደርግበት ጊዜም፣ ጥረቶቻችንን የይምሰል ሊያስመስሉ ከሚችሉ እና ውጤታማነታቸውን ከሚያሳንሱ (sub-optimal) አስተሳሰቦች ራሳችንን ማጽዳት ይጠበቅብናል። ከዚህ ውስጥ የመጀመሪያው፣ የሴቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ ለማጠናከር የምንወስዳቸው እርምጃዎች የየትኛውንም ውጫዊ አካል ቅቡልነት ለማግኘት ብለን ሳይሆን መሰረታዊ ከሆነው የሴታዊነት ባህርያት ልናገኛቸው የሚገቡንን ማህበራዊ እና ተፈጥሮአዊ እሴቶች ባግባቡ ለመጠቀም በማሰብ መሆኑን ማመን ነው። በዚህ ላይ በመመስረት፣ ሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ የማጠናከሩ ተግባር የቁጥርን ኮታ ለማሟላት ከሚደረግ ጥረት ባሻገር አመራሩ እና አደረጃጀቱ ከሴታዊነት ባህርያት የሚመነጩትን ጠቃሚ እሴቶች እንደ ግብዓት ለመጠቀም የሚያስችል መሆን ይኖርበታል።

ከሁሉም በላይ ግን፣ በማንኛውም መንገድ የአመራር ቦታ የሚይዙ እህቶቻችን ወንዳዊ ሃይለኝነትን (machismo) እንዲላበሱ የሚያስገድዱ ሁኔታዎችን መከላከል እና በሴታዊነት ልዩ ባህሪያቸው ላይ በመመርኮዝ ሊያበረክቱ የሚችሉት አስተዋጽኦ ላይ ማተኮር ይኖርባቸዋል። ይህ ፈተና፣ በወንዳዊ አስተሳሰብ ከተቃኘው ተቋማዊ ባህላችን አኳያ ሲታይ በእጅጉ ፈታኝ ሊመስል ይችላል። ነገር ግን፣ እንደምሳሌ ሊወሰዱ የሚችሉ

የሴታዊነት መሰረታቸውን የጠበቁ ጠንካራ ሴት አመራሮች[26] እያየን በመሆኑ የእነርሱን አርአያነት ማበራከት ያስፈልጋል። ባጭር አነጋገር፣ በአሁኑ ወቅት ከሴቶቻችን በእጅጉ የሚያስፈልገን በሴታዊነት የተቃኘ አመራራቸው እንጂ ወንዳዊነትን የተላበሰ መሪነታቸው አይደለም።

ከላይ የተዘረዘሩትን አካሄዶች በዘላቂነት ተግባራዊ ለማድረግ ሴታዊነትን ከመሰረቱ ሊያጠናክሩ የሚያስችሉ ተቋማዊ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል። ከዚህ ውስጥ የመጀመሪያው፣ በቤተሰብ ደረጃ ሴታዊነት ያለውን በርካታ ማህበራዊ ጠቀሜታ በተመለከተ ያለውን ግንዛቤ ማሳደግ እና ከዚህ በተቃራኒው ያሉ ልማዳዊ አስተሳሰቦችን ማስወገድ ነው። ከዚህ በተጨማሪ፣ የትምህርት ሥርዓት አደረጃጀትም ሆነ አሰጣጥ ለሴታዊነት አመለካከት መጠናከር በሚያስችል መልኩ እና በሁለቱ ጾታዎች ማህበራዊ ባህሪያት መካከል ያሉትን በርካታ ተደጋጋፊነት እና ተመጋጋቢነት በሚያጠናክር መልኩ መቃኘት ይኖርበታል።ለእነኚህ ተቋማዊ እርምጃዎች ትኩረት እንዲሰጥ በማድረግ ረገድ፣ በሴቶች ሁለንተናዊ የመብት ጥበቃ ላይ የሚሰሩ ሃገር በቀል ድርጅቶች ግንባር ቀደም ድርሻ ይኖራቸዋል። በአጠቃላይ፣ ሁለንተናዊ የሴታዊነት ድርሻን ማጠናከር ለረጂም ዘመናት በውጥረት የታጀበውን ፖለቲካችንን ወደ ተረጋጋ እና የሰከነ ፖለቲካ ለማሸጋገር ከማገዙም በላይ አካታች እና ዘላቂ ልማትን በማረጋገጡም በኩል የራሱ ከፍተኛ ድርሻ ይኖረዋል።

[26] ለዚህም እንደምሳሌ፣ ለበርካታ ዓመታት በቅርበት እማውቃቸውን ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ ዘውዴን እና ከ2010 ለውጥ በኋላ ሥራቸውን በመከታተል ያወኳቸውን ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚልን መጥቀስ ይቻላል።

## 5.2 ኢትዮጵያ፣ ብዙ ሙፈሪያቶች ያስፈልጓታል[27]

ከዚህ በላይ በቀረበው ጽሁፍ፣ የወንዳዊነት አስተሳሰብ ጎልቶ በሚታይበት የሃገራችን ፖለቲካ ውስጥ ያለውን ውስብስብ ችግር ለመፍታት በሚደረገው ጥረት የፖለቲካችንን ሴታዊነት ባህርይ ማጠናከር ሊኖረው የሚችለውን ጉልህ ድርሻ ለማመላከት ተሞክሮአል። በተጨማሪም፣ እንደ ምሳሌ ሊወሰዱ የሚችሉ የሴታዊነት መሰረታቸውን የጠበቁ ሴት አመራሮች እያየን በመሆኑ የእነርሱን አርአያነት ማበራከት እንደሚያስፈልግ ተወስቷል።። በህዳር ወር 2013፣ ከነዚህ ተምሳሌታዊ ሴት አመራሮች አንዷ የሆኑት የሰላም ሚኒስትር ወ/ሮ ሙፈሪያት ካሚል ተናገሩት የተባለው መልዕክት በመደበኛ እና ማህበራዊ ሚዲያው ላይ ከፍተኛ መወያያ ሆኖ ነበር። ባለሥልጣኖቻችን የሚናገሩትን ከልዩ ልዩ አቅጣጫ መመርመር እና ተጠያቂነትን ማስፈን ተገቢ ቢሆንም፣ ሴት አመራሮቻችንን 'እንዴት ተደርጎ' በሚል የወንዳዊነት መንፈስ ለመዳኘት መሞከር ሃገራዊ ጉዳት የሚያስከትል ይሆናል።

ከሁሉም በላይ፣ ከብዙዎች በተሻለ ደረጃ ሚዛናዊ ናቸው ብዬ የምገምታቸው ፖለቲከኞች፣ የፖለቲካ ተንታኞች እና ጦማሪዎችም የዚሁ ዘመቻ አካል የሚያስመስላቸው ሃሳብ ሲሰጡ ተሰምተዋል። ይህ አዝማሚያ፣ በቅርቡ በተለያየ መስክ መታየት የጀመረውን አበረታች የሴት አመራር ተሳትፎ ሊያቀጭጭ የሚችል በመሆኑ አጠቃላይ ማህበረሰቡ በትኩረት ሊመለከተው ይገባል። በዚህ ክፍል፣ እነዚህ ወገኖች የሚያራምዱትን ጎጂ አስተሳሰብ ቀደም ሲል ከቀረበው የሴታዊነት እሳቤ አስፈላጊነት ጋር በማያያዝ ለመተንተን ተሞክሯል።

በቅድሚያ ይህ ወ/ሮ ሙፈሪያት የተናገሩት እና ከየአቅጫው እንዲዘመትባቸው ያደረገው ሃሳብ ምንድን ነው የሚለውን እንመልከት። ምንም እንኳን ንግግራቸውን እንደወረደ (verbatim) የመስማት እድል ባይኖረኝም፣ በተለያዩ ሚዲያዎች እንደቀረበው ከሆነ የሚከተሉት አንኳር ነጥቦች ይገኙበታል። አንደኛ፣ የፌዴራሉም ሆነ የክልሉ መንግስታት ከራሳቸው ጥቅም ይልቅ የህዝቡን እና የሃገሪቱን ጥቅም ማስቀደም አለባቸው። ሁለተኛ፣ ፖለቲከኞቻችን በሃሳብ ተለያየን ብለው አይንህን ለአፈር መባባላቸው ነውር ነው። ሶስተኛ፣ መርዝን ከሚረጩ ጥቂት ፖለቲከኞች ባሻገር ህዝብ እና ሃገር የሚባሉ ታላቅ ጉዳዮች አሉ። አራተኛ፣ በር ዘግቶ እንኪያ ስላንቲያ ከመግጠም ይልቅ ወደ ጠረጴዛ ዙሪያ መጥተን መወያየት ይኖርብናል። አምስተኛ፣ ያለብንን የፖለቲካ ችግሮች በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት አሁንም እድሉ አለን። ነገር ግን ይህ ዕውን እንዲሆን በሁለቱም ወገኖች ያሉ የፖለቲካ መሪዎች ሰከን ሊሉ ይገባል የሚሉ ነበሩ።

[27] የዚህ ክፍል አብዛኛው፣ ጥቅምት 6 ቀን 2013 በወጣው አዲስ አድማስ ጋዜጣ ታትሟል።

ከዚህ በላይ በአጭሩ የተጠቀሱት ሃሳቦች እንደሃሳብ እንኸን ሊወጣላቸው የማይችል ከመሆናቸውም ባሻገር፣ በወቅቱ በፌደራል እና በትግራይ ክልል መንግሥታት መካከል ከነበረው ውጥረት አኳያ፣ እኔን ጨምሮ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን የሚጋሯቸው ጭንቀቶች እና ሃሶቦች ይመስሉኛል። ለዚህም ታላቅ ከበሬታ እና አድናቆት ሊቸራቸው ይገባል። ይህ እንዳለ ሆኖ፣ የተለያዩ ወገኖች ወ/ሮ ሙፈሪያትን ከልዩ ልዩ አቅጣጫ ሲወቅሱ ተሰምተዋል። ከዚህ በመቀጠል የነዚህን ወገኖች ዋና ዋና መከራከሪያዎች ለመመልከት እንሞክራለን።

በቀዳሚነት በብዙዎቹ የተነሳው፣ እነኚህን ከብልፅግና ፓርቲ የተለዩ የሚመስሉ ሃሳቦችን አደባባይ ላይ እንዲወጣ ማድረጋቸው ከፓርቲው መስመር ማፈንገጣቸውን ከማመልከቱም በላይ በፓርቲው ከፍተኛ አመራሮች መካከል መከፋፈል እንዳለ ያሳያል የሚለው ነው። እንዲህ አይነቱ አመለካከት ለረጂም ዘመናት ተቆራኝቶን ከቆየው የዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት አስተሳሰብ ጋር የተያያዘ እና የውስጠ ፓርቲ ዲሞክራሲ አስፈላጊነትን ካለመረዳት የመነጨ ሊሆን ይችላል። ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ፣ ባንድ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ውስጥ በመሰረታዊ የፖለቲካ ዓላማዎች እና ግቦች የጋራ አመለካከት መኖር አስፈላጊ የመሆኑን ያህል ወደነዚህ ግቦች ለመድረስ በሚያስችሉ መንገዶች ላይ የተለያዩ አማራጮች መኖር ለፓርቲው ጤናማነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

ይህን መግለጫ እስከሰጡበት ጊዜ ድረስ፣ ብልፅግና ፓርቲ እንደ ፓርቲ በወቅቱ በፌዴራል መንግስቱ እና በትግራይ ክልል መንግስት መካከል እየሰፋ የነበረውን የአመለካከት እና የአስተዳደር ልዩነት ከጦርነት እና ግጭት በመለስ መፈታት እንደሚገባው ይገልጽ ነበር። በርግጥ፣ ከብልፅግና ውጭ ያሉ አንዳንድ ፖለቲካኞች እና ተንታኞች የትግራይ ክልልን በመምራት ላይ የነበረው ህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ (ህወሃት) በማናቸውም መንገድ ከስልጣን እንዲወገድ የሚሹ እንደነበር አይካድም። በብልፅግና ፓርቲ ውስጥም ይህንን አማራጭ የሚደግፉ ወገኖች እንደነበሩ ይገመታል። ይህ እንዳለ ሆኖ፣ ችግሮችን በልዩ ልዩ አማራጮች የመፈተሽ እና የማንሸራሸር ባህል ለሃገሪቱ ፖለቲካ ጤናማነት የሚበጅ እንጂ ጎጂ ተደርጎ መወሰድ አልነበረበትም። በመሆኑም፣ ብልፅግናም ሆነ ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ለየት ያሉ ሃሳቦችን ወደ አደባባይ ማውጣት ሊያበረታቱት የሚገባ ልማድ ነው። ከሁሉም በላይ ግን ሊታመን የሚገባው፣ የፖለቲካ ልዩነቶችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት የምንጊዜውም ተመራጭ መንገድ መሆኑን ነው።

በሁለተኛ ደረጃ የሚነሳው፣ እንዴት በማናቸውም መንገድ ከኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥርዓት መወገድ ከሚገባው ህወሃት[28] ጋር ባንድ ጠረጴዛ ዙሪያ ቁጭ ብለን እንወያይ ይላሉ የሚል ነበር። እነኚህ ወገኖች፣ ባብዛኛው በህወሃት የበላይነት ይመራ በነበረው ዘመነ

[28] የዚህ መጽሃፍ ዝግጅት እየተጠናቀቀ ባለበት ወቅት፣ የትግራይ ህዝብ ነፃአውጭ ግንባር ከህጋዊ ድርጅትነት መሰረዙን ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ያስታወቀ ቢሆንም ተመሳሳይ ስህተቶች ወደፊት እንዳይደገሙ ከነበረው ሁኔታ መማር ጠቃሚ ነው።

ኢህአዴግ (ኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር) ባደረሰው የፖለቲካ እና አስተዳደር በደል የተጎዱ እና የቆሰሉ ወገኖች ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን፣ ዴሞክራሲያዊ ባህልን ከመገንባት አኳያ፣ የእንዲህ አይነት ወገኖች ትኩረት እና ጥረት መሆን ያለበት የተሻሉ አማራጮችን በማቅረብ የመሰል ድርጅቶችን እጣ ፈንታ በህዝብ ድምጽ እንዲወሰን ማድረግ ነው መሆን የነበረበት። ከዚህ በተቃራኒው፣ ማንኛውንም የፖለቲካ ድርጅት በማናቸውም መንገድ መወገድ እና መጥፋት አለበት ብሎ መናገር የዲምክራሲያዊነት ዋነኛ መሰረት የሆነውን የህዝብን የመጨረሻ ወሳኝነት ሙቦት መንጠቅ ይሆናል። ስለሆነም፣ በወቅቱ በህጋዊነት ተመዝግቦ የነበረን የፖለቲካ ድርጅት ለውይይት መጋበዝ የፖለቲካ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ባህልን ለማዳበር የሚደረግ ጥረት አካል ተደርጎ መወሰድ ነበረበት።

በሶስተኛ ደረጃ የሚነሳው፣ ወ/ሮ ሙፈሪያት በሃገሪቱ ውስጥ ህግ እና ሰላምን ለማስከበር ከፍተኛ ሃላፊነት የተሰጣቸውን ዋና ዋና መስሪያ ቤቶችን የሚመራውን የሚኒስቴር መስሪያ ቤት በበላይነት የሚመሩ በመሆናቸው ባለፉት ሁለት የለውጥ ዓመታት በሃገሪቱ ለደረሰው የጸጥታ መናጋት እና ህዝቦች መፈናቀል ዋነኛ ተጠያቂ መሆናቸውን ይገልጻሉ። በወቅቱ የሰጡትን መግለጫም የማይመለከታቸውን የድርድር ጉዳይ በማንሳት ድክመታቸውን ለመሸፈን የተደረገ ጥረት እንደሆነ ያመለክታሉ። እንዲህ አይነቱ፣ ሃገሪቱ ያለባትን የሰላም እና ጸጥታ ችግር ከአንድ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ወይንም ከተወሰነ የፖለቲካ ቡድን ጋር የማያያዝ ዝንባሌ የፖለቲካ ችግሩን ውስብስብነት አለመረዳት ነው።

ከዚህ በተጨማሪ፣ የሰላም ሚኒስትርን መሠረታዊ አላማ እና ተግባራት ካለመረዳት እና የሚኒስትር መስሪያ ቤቱ ከዚህ ቀደም በተለያዩ ወገኖች ተነሳሽነት ለተካሄዱ ውይይቶች እና ድርድሮች ይሰጥ የነበረውን ድጋፍ ካለመገንዘብ የመነጨ ሊሆን ይችላል። የአንድ የሽግግር ወቅት መንግስት ውጤታማነት የሚወሰነው በእጁ ውስጥ ያለውን የኃይል እና የማሳመን አቅም (hard and soft power) በሚዛናዊነት ለመጠቀም ባለው ብቃት ነው። እንዲህ አይነቱ ተግባርም ባንድ የሚኒስትር መስሪያ ቤት የሚከናወን ሳይሆን አጠቃላዩ የመንግስት መዋቅር የሚረባረብበት ተግባር ነው። በዚህ ረገድ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተጠናክሮ የተጀመረውን ህግን የማስከበር ተግባር ከውጤታማ የብሔራዊ መግባባት ውይይት ጋር ማቀናጀት እጅግ አስፈላጊ ነው። በወቅቱ፣ ወ/ሮ ሙፈሪያት የተናገሩት ነገርም ይህንን ሚዛን ለመጠበቅ የተደረገ መልካም ጥረት ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል።

በአራተኛ ደረጃ፣ አንዳንድ ወገኖች ሚኒስትሯ የተናገሩትን ሃሳብ ለህወሃት ነበራቸው ከሚባለው ስስ ስሜት (sympathy) ጋር በማያያዝ እየተካሄደ ላለው ለውጥ ያላቸውን ታማኝነት ጥያቄ ውስጥ ለማስገባት ሞክረዋል። ጥቂቶቹም፣ ካሉበት ኃላፊነት መነሳት አለባቸው ብለዋል። ይህ አሳዛኝ አመለካከት፣ ለረጂም ዘመን ተጠናውቶን የቆየው ሃሳብን በሃሳብ ከመሞገት ይልቅ ወደ ስም ማጥፋት እና ማጠልሸት (character assassination) የመሄድ አሳፋሪ የፖለቲካ ቅሪትን ያመላክታል። እንዲህ አይነቱን አዝማሚያ ሁሉም በሃገራችን ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሰፍን የሚሹ ወገኖች

ሊያወግዙት እና በጽኑ ሊታገሉት ይገባል። በተለይም፣ በአብዛኛው ማህበረሰብ እንደ አቅጣጫ አመላካች (opinion makers) ተደርገው የሚገመቱ ወገኖች ከእንዲህ አይነቱ ስህተት ሊጠበቁ ይገባል። ይህም ሲባል፣ ማንኛውም ባለሥልጣን ለሚፈጽማቸው ጥፋቶች ሙሉ ኃላፊነት እና ተጠያቂነት ሊኖረው እንደሚገባ በማመን ነው።

በአምስተኛ ደረጃ የተነሳው፣ እንዴት የፌዴራሉን እና የክልሉን መንግስት በእኩልነት በማስቀመጥ ሁለቱንም ወገኖች 'ሰከን በሉ' ብለው ይናገራሉ የሚል ነበር። በመጀመሪያ ደረጃ፣ እኔ እንደተረዳሁት ወ/ሮ ሙፈሪያት ሰከን በሉ ያሉት በሁለቱም ወገኖች ያሉ አንዳንድ ፖለቲከኞችን እንጂ መንግስታቱን አይደለም። በርግጥም፣ በሁለቱም ወገኖች ያሉ አንዳንድ የፖለቲካ መሪዎች በተለያየ ወቅት እየወጡ የተናገሩት ነገር ውጥረቱን ይበልጥ የሚያከሩ እንጂ ወደ መፍትሔ ለመሄድ የሚያግዙ አልነበሩም። ይህም፣ በስተመጨረሻ ለምን ዓይነት ጥፋት እና ውድመት እንደዳረገን ታይቷል። ከሌሎች ሃገሮች ተመክሮ እንደታየው፣ ለሰላማዊ መፍትሄ የሚደረግ ማንኛውም ጥረት የመጀመሪያው እርምጃ ሁሉም ወገኖች ውጥረትን ከሚያባብሱ አባባሎች (rhetoric) መታቀብ ይሆናል። በወቅቱ፣ በፌዴራል መንግስቱ እና በትግራይ ክልል መንግስት መካከል የነበረውን መካረር ለማርገብ እና ለመፍታት ከሁሉም ወገኖች በተለይም ከፌዴራል መንግስቱ ከምንም ጊዜ በላይ ከፍተኛ ሆደ ሰፊነት (magnanimity) እና ታጋሽነት የሚጠበቅበት ወቅት ነበር። ይህንን ማድረግ ለሃገር እና ለህዝብ ታላቅ አክብሮት በማሳየት መከበርን የሚያስገኝ እንጂ በደካማነት የሚያስፈርጅ አልነበረም።

በአጠቃላይ፣ ወ/ሮ ሙፈሪያት ተናገሩት የተባሉት ነጥቦች ለሌሎች መሰል የሃገራችን የፖለቲካ ችግሮች መፈታት አይነተኛ አስተዋጽኦ ሊያድርጉ የሚችሉ በመሆናቸው ወደፊትም ይበልጥ ሊበረታቱ እና ሊደገፉ ይገባል። ይህ ንግግራቸው፣ በወንዳዊነት መንፈስ የተጫነብንን 'የሃይ ዘራፍ' ፖለቲካ ለማከም የሴታዊነት አመለካከት ሊኖረው የሚችለውን ጉልህ አስተዋጽኦ በተጨባጭ የሚያሳይ በመሆኑ በድጋሚ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ብዙ ሙፈሪያቶች ያስፈልገዋል እንላለን። በዚሁ አጋጣሚ፣ በማናቸውም ወቅት ብሔራዊ መግባባትን ለማጠናከር በየደረጃው የሚካሄዱ ውይይቶች የሴታዊነት ልዩ ባህርያት ሊያበረክት የሚችለውን ጠቃሚ አስተዋጽ ግምት ውስጥ ማስገባት እና በተገቢው መንገድ መጠቀም ይኖርባቸዋል። ታላቁ የሳይንስ ምሁር አልበርት አይንሽታይን እንዳሉት 'የዛሬውን ችግራችንን በትናንትናው መንገድ ለመፍታት መሞከር ከንቱ ድካም ነው'። ስለዚህም፣ ፖለቲካችንን 'ከወንዳዊነት' ባህሪው ቀስ በቀስ በማላቀቅ ጊዜው በሚጠይቀው አስተሳሰብ ልንቃኘው ይገባል።

## የክፍል አምስት ቁልፍ ሐሳቦች

i. ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዓብይ አህመድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተወደሱበት አበይት እርምጃዎች አንዱ በርካታ ሴት አመራሮችን በመንግስታቸው ውስጥ ማካተታቸው እና በዘመናዊው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ታሪክ ውስጥ የመጀመርያ የሆኑትን የሃገሪቱ ሴት ርዕሰ ብሔር እንዲሾሙ ማድረጋቸው ነው። ይህ እና በሌሎችም የፖለቲካ ድርጅቶች ሆነ መንግስታዊ ባልሆኑ የህዝብ ተቋማት የተጀመሩ ቀና እርምጃዎች ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆኑ ከተፈለገ ሴታዊነት (Feminism) ባንድ ምህዳር ውስጥ ያለውን ምሉዕ ድርሻ በመረዳት ላይ የተመረኮዙ ሊሆኑ ይገባቸዋል።

ii. ዘመናዊውን የተደራጀ የሴቶች የመብት እንቅስቃሴ አነሳስን ስንመለከት በ 19ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩት አሜሪካዊቷ የሴኔካ ፏፏቴ መግለጫ አዘጋጅ ወይዘሮ ኤልሳቤጥ ስታንተን እና ጀርመናዊቷ ሶሻሊስታዊ የሴቶች መብት አቀንቃኝ ወይዘሮ ክላራ ዜትኪን በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ።

iii. በሃገራችንም፣ በተመሳሳይ ወቅት በጉራጌ ማህበረሰብ ውስጥ ተነስተው የነበሩትን የሴቶች መብት አቀንቃኝ ወይዘሮ ቃቄ ወርድወትን መጥቀስ ይቻላል። ይህም የሚያሳየው፣ ባሁኑ ሰዓት ባንዳንድ ወገኖች ከምዕራባዊያን ሃገሮች እንደተኮረጀ ተደርጎ የሚነገርለት የሴቶች የመብት እንቅስቃሴ በሃገራችንም ቀደም ብሎ የተጀመረ እንደነበር ነው።

iv. በምህዳራዊ አስተሳሰብ መሰረት፣ ሴታዊነት ለማንኛቸውም ተፈጥሮአዊ እና ማህበራዊ ምህዳር ቀጣይነት ዋነኛው መሰረት ነው። ይህም በአበይትነት ለሴቶች በተሰጣቸው የእናትነት ምግባር የሚገለጽ ሲሆን ሌሎችም መስረታዊ የሆኑ እና ከወንዶች በበለጠ ለሴቶች የተሰጧቸው ባህርያት አሉ።

v. ከነዚህም ውስጥ አንዱ፣ የሌላ ሰውን ችግር እንደራስ ሆኖ ለመረዳት እና ለመካፈል (empathy) ያላቸው ዝግጁነት ከብዙ ወንዶች የበለጠ መሆኑ ነው። ሌላው፣ ኑሮን ለማሸነፍ በሚደረገው ትግል ውስጥ ካላቸው ቁልፍ ድርሻ ጋር በተያያዘ ፈታኝ ሁኔታዎችን ለመሻገር ያላቸው የስሜት (survival instinct) ዝግጁነት ነው።

vi. ከዚህ በተጨማሪ፣ ተፈጥሮአዊው ዑደትን ለማስቀጠል ካላቸው ልዩ ኃላፊነት እና ድርሻ ጋር በተያያዘ ከተፈጥሮአዊው ምህዳር ጋር ያላቸው ቅርበት እና ተዛማጅነት (ecological sensibility) ነው። ከሁሉም በላይ በሰፊው ካለብን የፖለቲካ ህመም ለመፈወስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊኖረው የሚችለው ባህሪ፣ ኃይልን መሰረት ካደረገ (hard power) አመራር እና የግጭት አፈታት ይልቅ ስሜትን በማለስለስ እና በማሳመን (soft power) ላይ ለተመረኮዘ መፍትሄ ያላቸው ብልህነት ነው።

vii. እነኚህ እና እነኚህን የመሳሰሉ በርካታ የሴታዊነት ባህርያትን በውጤታማነት ለመጠቀም የአመራር ቦታ የሚይዙ እህቶቻችን ወንዳዊ ሃይለኝነትን (machismo) እንዲላበሱ የሚያስገድዱ ሁኔታዎችን መከላከል እና በሴታዊነት

ልዩ ባህሪያቸው ላይ በመመርኮዝ ሊያበረክቱ የሚችሉት አስተዋጽኦ ላይ ማተኮር ይኖርባቸዋል። ይህ ፈተና፣ በወንዳዊ አስተሳሰብ ከተቃኘው ተቋማዊ ባህላችን አኳያ ሲታይ በእጅጉ ፈታኝ ሊመስል ይችላል። ነገር ግን፣ እንደምሳሌ ሊወሰዱ የሚችሉ የሴታዊነት መሰረታቸውን የጠበቁ ሴት አመራሮች እያየን በመሆኑ የእነርሱን አርአያነት ማበራከት ያስፈልጋል።

viii. ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ የሴቶችን የአመራር እና የፖለቲካ ተሳትፎ የሚያበረታቱ እርምጃዎች በመወሰድ ላይ ይገኛሉ። ይህ እንዳለ ሆኖ፣ ለረጂም ዘመናት በሁሉም ተቋማዊ አደረጃጀቶች እና በአብዛኛው ህብረተሰብ ውስጥ ተንሰራፍቶ የኖረው የወንዳዊነት አመለካከት ለብዙዎቹ ሴት አመራሮች ታላቅ ፈተና እንደሚሆኑባቸው ይገመታል።

ix. ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፣ አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች እና አቀንቃኞች በሴት አመራሮች ላይ ግልጽ ዘመቻ የጀመሩ ይመስላል። ማንኛውም የመንግስት አመራር ለሚሰራው ስራ ተጠያቂነት ያለበት መሆኑ ባይካድም፣ በተዛባ አመለካከት ላይ ተመርኩዞ በሴት አመራሮቻችን ላይ ብያኔ ማሳለፍ የተጀመረውን መልካም ጥረት ስለሚያዳክም ሊታረም ይገባዋል።

x. በፌዴራል መንግሥቱ እና በትግራይ ክልል መንግሥት መካካል የነበረው ውጥረት ከፍተኛ ደረጃ በደረሰበት ወቅት የሠላም ሚኒስትር የሆኑት ወይዘሮ ሙፈሪያት ካሚል በድፍረት ወጥተው የተናገሩት ሃሳብ በማህበራዊ ሚዲያው ዘርፍ ውዝግብ አስነስቶ ከርሞ ነበር።

xi. ይህ፣ ከውጥረት ይልቅ ስክነትን፣ ከወታደራዊ ፍጥጫ ይልቅ በጠረጴዛ ዙሪያ ቀርቦ መነጋገርን የሚያሳስብ ንግግር የ 'ቁረጠው ፍለጠው ሃይ ዘራፍ ፖለቲካ' አራማጆችን ያስቆጣበት ዋነኛው ምክንያት ቀደም ሲል የቀረበውን የሴታዊነት ልዩ ባህርያት እና ጠቀሜታ ባለመረዳታቸው መሆኑ ግልጽ ነው።

xii. ወ/ሮ ሙፈሪያት ተናገሩት የተባሉት ነጥቦች ለሌሎች መሰል የሃገራችን የፖለቲካ ችግሮች መፈታት አይነተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ በመሆናቸው ወደፊትም ይበልጥ ሊበረታቱ እና ሊደገፉ ይገባል። ይህ ንግግራቸው፣ በወንዳዊነት መንፈስ የተጫነብንን 'የሃይ ዘራፍ' ፖለቲካ ለማከም የሴታዊነት አመለካከት ሊኖረው የሚችለውን ጉልህ አስተዋጽኦ በተጨባጭ የሚያሳይ በመሆኑ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ብዙ ሙፈሪያቶች እንደሚያስፈልገው አበክረን መግለጽ እንፈልጋለን።

xiii. በመሆኑም፣ በማናቸውም ወቅት ብሔራዊ መግባባትን ለማጠናከር በየደረጃው የሚካሄዱ ውይይቶች የሴታዊነት ልዩ ባህርያት ሊያበረክቱ የሚችሉትን ጠቃሚ አስተዋጽ ግምት ውስጥ ማስገባት እና በተገቢው መንገድ መጠቀም ይኖርባቸዋል። ታላቁ የሳይንስ ምሁር አልበርት አይንሽታይን እንዳሉት 'የዛሬውን ችግራችንን በትናንትናው መንገድ ለመፍታት መሞከር ከንቱ ድካም ነው'።

## 6. ተረኮች[29] እና ብሔራዊ መግባባት

በማናቸውም ማህበረሰብ ወይም ሃገር ውስጥ የተለያዩ ማህበራዊ ተረኮች መኖር የሚጠበቅ ሲሆን እነኚህ ተረኮች ግን ለግጭቶች መነሻ የሚሆኑት እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በማደግ ላይ ባሉ ሃገሮች ውስጥ ብቻ ነው። የዚህም ዋነኛው ምክንያት፣ በተለያዩ ተረኮች መካከል የሚኖሩ አለመጣጣሞችን ሲቻል ለማስታረቅ ያም ካልተቻለ ደግም ለመዳኘት የሚያስችሉ ተቋማዊ አደረጃጀቶች እና ሥርዓቶች ደካማ መሆናቸው ነው። በእንዲህ ዐይነት ሁኔታ ውስጥ ያሉ ሃገሮች ለወደፊት እጣ ፈንታቸው ወሳኝ ከሆነ የሽግግር ወቅት ጋር በሚፋጠጡበት ጊዜ የብሔራዊ መግባባት ውይይት ማካሄድን እንደ አንድ ዓብይ መፍትሔ ይጠቀሙበታል። ባለፉት ሰላሳ ዓመታትም፣ የብሔራዊ መግባባት አስፈላጊነት በበርካታ የፖለቲካ መሪዎች እና ልሂቃን በተደጋጋሚ መነሳቱም ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው። የብሔራዊ መግባባት ውይይት ዋነኛ ግቡ በተለያዩ ተረኮች (narratives) መሃል ያሉ ከአነስተኛ ልዩነቶች እስከ ከፍተኛ ተቃርኖዎች የሚደርሱ የግጭት ምንጮችን ማቀራረብ እና ማቻቻል ነው። ይህንንም በአግባቡ ለማከናወን፣ የተረኮችን መሰረታዊ ባህርይ መረዳት እና ምህዳራዊ መፍትሔዎቻቸውን መሻት ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ የመጀመሪያው ዓብይ ነጥብ፣ ጥልቅ መሰረት ባላቸው ማህበረሰባዊ ተረኮች እና በተቋማዊ ተረኮች መካከል ያለውን አይነታዊ ልዩነት መረዳት ነው።

ማህበረሰባዊ ተረክ (social narrative)፣ አንድ ማህበረሰብ የመጣበትን፣ ያለበትን እና የሚሄድበትን ማህበራዊ ፍኖት የሚረዳበት እና የሚገልጽበት (collective sensemaking) ሲሆን የዚያን ማህበረሰብ አባላት አመለካከት  በመወሰን ረገድ ታላቅ አቅም አለው። ማንኛውም ማህበረሰባዊ ተረክ የዚያ ማህበረሰብ የእምነት ስርዓቶች እና ዕሴቶች (value systems) ምናባዊ ማከማቻም ናቸው። ስለሆነም አንድን ማህበረሰባዊ ተረክ ባግባቡ ለመረዳት የዚያን ማህበረሰብ የዕሴት መሰረቶችን በጥልቅ መመርመር እና መረዳት ያስፈልጋል። ይህን በሚያደርጉበት ጊዜም፣ ማንኛውም ማህበረሰባዊ ተረክ በጊዜ ሂደት በሚከሰት ዝግመታዊ ለውጥ ሊቀረጽም ሆነ ሊለወጥ ይችላል ብሎ ከማሰብ ውጭ የተሳሳተ የሚባል ማህበራዊ ተረክ እንደማይኖር በመገንዘብ መሆን አለበት። በዚህ መሰረት በሃገራችን በኢትዮጵያ ያሉትን ማህበረሰባዊ ተረኮች ብንመረምር፣ ሁሉም ማህበረሰባዊ ተረኮች በጋራነት የሚጋሯቸው በርካታ ማህበረሰባዊ ዕሴቶች እናገኛለን። ከእነዚህም አንዱ እና ዋነኛው፣ አንዱ ለብዙው፣ ብዙው ለአንዱ የሚተሳሰብበት (collective solidarity) ዕሴት ነው።  እነኚህ በዘመናት የመተሳሰር እና የመወራረስ ሂደቶች ውስጥ የዳበሩ የጋራ ማህበራዊ ዕሴቶች የማንኛውም ብሔራዊ መግባባት ውይይቶች ዋነኛ መሰረቶች ናቸው።

[29] በትርክቶች (anecdotes)፣ ተረክ (narratives) እና ታሪክ (history) መካከል ያለው መደበላለቅ ሌላው ሊጠራ የሚገባው አመለካከት ነው።

ከዚህ በተቃራኒው፣ ተቋማዊ ተረኮች አንድን የተወሰነ የማህበረሰብ ክፍል ወይም ቡድን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ዓላማዎች በሚጠቅም መልኩ የሚቀረጹ ናቸው። ተቋማዊ ተረኮች፣ ከአካታችነት (power with) ይልቅ ገዢነት (power over)፣ ከመደጋገፍ ይልቅ መቃቃር፣ ከጋራ እድገት ይልቅ ራስ ወድነት (egoism) ጎልቶ የሚታይባቸው ናቸው[30]።እንዲህ ዐይነት ተረኮች በህብረተሰቡ ውስጥ የሚኖራቸውን ተቀባይነት ለማጠናከር ሲሉ፣ ሰፋ ያለ ተቀባይነት ያለውን ማህበረሰባዊ ተረክ በመጥለፍ ለራሳቸው ውሱን ዓላማ በሚጠቅም መልኩ ሲያራምዱት ይስተዋላል። ይህንን ለማሳካትም፣ በነባር ማህበረሰባዊ ተረኮች ውስጥ ስሜታዊ ምላሽ የሚያጭሩ ጉዳዮችን (emotive issues) በማግነን ይታወቃሉ። በመሆኑም፣ ለአብዛኞቹ በዓለማችንም ሆነ በሀገራችን ለተከሰቱት ጦርነቶች እና የእርስ በእርስ ግጭቶች ዋነኛ መነሻዎች ናቸው። የተቋማዊ ተረኮች ልዩ ባህርያት፣ በአብዛኛው ለራስ አገልጋይ (self-serving) በሆኑ ተጠቃሚዎች ከተጠለፈው ማህበራዊ ሚዲያ ጋር ባለው ተጣጣሚነት የተነሳ ባሁኑ ወቅት የብዙ ሃገሮች ፈተና በመሆን ላይ ይገኛል። ይህንን ፈተና ለመሻገር አይነተኛው መፍትሔ፣ ዓይነታዊ የለውጥ ተረኮችን ለማበልጸግ ጥረት ማድረግ ይሆናል።

## 6.1 ችግሩን ከስሩ ለመንቀል፣ መዋቅራዊ ምንጩን ማድረቅ[31]

በምህዳራዊ አስተሳሰብ መሰረት፣ በልዩ ልዩ መልኩ የሚከሰቱ የተፈጥሮ አደጋዎች በተፈጥሮአዊው ምህዳር ውስጥ ያሉ ከመጠን ያለፉ ከባቢያዊ መዛባቶችን ለማስተካከል የሚከሰቱ ተፈጥሮአዊ ሁነቶች ናቸው። ዛሬ በዓለም ዙሪያ በተጠናከረ ሁኔታ እየተከሰተ ያለው ድርቅ፣ ጎርፍ፣ አውሎ ነፋስ (tornedo)፤ ሰደድ እሳት እና የባህር ማእበል (hurricane) ሁሉ ተፈጥሮአዊው ምህዳር የሚደርስበትን ከባቢያዊ መዛባት ለማስተካከል የሚጠቀምባቸውን ሂደቶች የሚያመላክቱ ናቸው። በተመሳሳይ መልኩ፣ ግጭቶችና ጦርነቶች ባንድ ማህበረሰብ ውስጥ ወይም በሀገሮች መካከል ያሉ እና ጥልቅ የሆኑ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ቅራኔዎች መገለጫ ናቸው። በዕውቀትና አስተውሎት ላይ በተመረኮዙ አስተሳሰቦችና አካሄዶች በመጠቀም ባንድ ሁኔታ ውስጥ የተፈጠሩ መዛባቶችንና ግጭቶችን መፍታትና፣ ሚዛናዊ የሆነ አካሄድን በመከተል አብዛኛዎቹን ከባቢያዊም ሆነ ፖለቲካዊ ቀውሶች ወደ ከፋ ጉዳት እንዳያመሩ ማድረግ ይቻላል።

ወደ ሃገራችን ሁኔታ ስንመጣ፣ ለእንዲህ አይነቱ ጤናማ አካሄድ ያለው ዝግጁነት ደካማ በመሆኑ ብዙዎቹ ልዩነቶች በኃይል እና በግጭት ሲቋጩ ኖረዋል። በቅርቡም፣ ከትግራይ ክልል መሪዎች በኩል ለሰላማዊ መፍትሔ የነበረው ዝግጁነት ይበልጥ አናሳ በመሆኑ የብዙዎቹን ህይወት ላጠፋ እና የሚሊዮኖችን ኑሮ ላመሰቃቀለ አሳዛኝ ጦርነት ተዳርገናል። አንዳንድ ፖለቲከኞችና ተንታኞች ይህ ጦርነት ህወሓትን በመደምሰስ

[30] እንዲህ ዓይነት ተቋማዊ ተረኮች ብዙውን ጊዜ ህዝበኝነት (populism) ለተጠናወታቸው የፖለቲካ መሪዎች እና ቡድኖች ዋነኛ መጠቀሚያ ናቸው።

[31] የዚህ ክፍል አብዛኛው፣ ህዳር ፲፩ 2013 በወጣው አዲስ አድማስ ጋዜጣ ታትሟል።

በኢትዮጵያ ያለውን መሰረታዊ የፖለቲካ ችግር ከስሩ ለመንቀል መልካም አጋጣሚ እንደሆነ ሲናገሩ ይደመጣል። በእርግጥም፣ እንዲህ ዓይነት ጦርነቶችና ግጭቶች ወደፊት አላራምድ ያሉ ሁኔታዎችን  በመለወጥ ረገድ የራሳቸውን ጉልህ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ እንደሚችሉ ይታመናል።

ይህ ሊሳካ የሚችለው ግን፣ ጦርነቱ የሚፈጥረውን አጋጣሚ፣ ለምህዳሩ ጤናማነት አስቸጋሪ የሆኑ በጥባጮችን (rogue elements) ከማስወገድ ባሻገር ለእንዲህ አይነት ሁኔታዎች መፈጠር ምንጭ የሆኑትን መዋቅራዊ ሁኔታዎች መፍታት ሲቻል ነው። ይህ ደግሞ፣ ከወታደራዊ ዘመቻው ጎን ለጎን፣ የሰከነ እና የበሰለ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ መፍትሄዎችንም ማፈላለግ ይጠይቃል። እንዲህ አይነት ሁሉን አቀፍ የመፍትሄ አቅጣጫን መከተል ወታደራዊ መፍትሄ የሚጠይቀውን መስዋእትነት ከመቀነሱም በላይ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ችግር የሚፈጠርበትንም ሁኔታ ይቀንሰዋል። ይህ ክፍል፣ ይህንን ለማድረግ የሚያስፈልጉንን የአመለካከት ለውጦችና ሊተኮርባቸው የሚገቡ አበይት መዋቅራዊ ጉዳዮችን ይጠቁማል።

በአሁኑ ወቅት፣ ሃገራችን ኢትዮጵያ በታሪኳ አጋጥሟት የማያውቅ እጅግ ፈታኝ የሆነ ሁኔታ ውስጥ ትገኛለች። ይህንን አስቸጋሪ ሁኔታ ለመወጣት በሰሜኑ የሃገራችን ክፍል እና በሌሎችም አካባቢዎች የሚከፈለው መስዋእትነት ትርጉም የሚኖረው ለዘመናት ተጣብቶን የኖረውን የፖለቲካ ምስቅልቅል ከምንጩ ለማድረቅ ወደሚያስችል ዕድል መቀየር ከቻልን ብቻ ነው። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ከሁሉ በማስቀደም፣ እንዴት ዛሬ ላለንበት አሳዛኝና አሳፋሪ የፖለቲካ ምስቅልቅልና ጦርነት ልንደርስ እንደ በቃን ሁሉም የፖለቲካ ተዋንያኖች እና ልሂቃን በሃቀኝነት የነፍሲያ ፍተሻ (soul searching) ሊያደርጉ ይገባል። እዚህ ላይ፣ ባሁኑ ሰዓት በሰሜኑ የሃገራችን ክፍል ላለው አሳዛኝ ሁኔታ በዋነኝነት የህወሃት አመራር ባለፉት የሽግግር ዓመታት ውስጥ የተከተለው ግትርና ለውይይትና ሽምግልና ያስቸገረ አካሄድ ከፍተኛውን ድርሻ እንደሚወስድ አያጠያይቅም። በመሆኑም፣ በዚህ ግጭትና ጦርነት ለተፈጠረው ሰብዓዊና ቁሳዊ ውድመት ቀዳሚ ተጠያቂነት ይኖርበታል።

ይህ እንዳለ ሆኖ፣ በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ከሚመራው የፖለቲካ ፓርቲ ጀምሮ ሁሉም የፖለቲካ ተዋንያን ወይ መደረግ የማይገባውን ወቅት ሳይጠብቁ በማድረግ፣ አለበለዚያ ማድረግ የሚገባቸውን በወቅቱ ባለማድረግ (acts of commission or omission) ለሁኔታዎች መባባስ የየራሳቸውን ድርሻ እንዳበረከቱ መረዳት ይጠበቅባቸዋል። ይህንን እውነታ አለመቀበልና ችግሩን በሙሉ ‘ከሰይጣናዊው’ የህወሃት አመራር ጋር በማያያዝ ሁሉም ፈተና ይህንን ድርጅት በማስወገድ ሊጠፋ እንደሚችል አድርጎ ማሰብ ሃገሪቱን ለሌላ ተመሳሳይ ችግርና ጥፋት ለማጋለጥ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል። ይህ እንዳይሆን፣ ሰፊውን የትግራይ ማህበረሰብና አጠቃላዩን የኢትዮጵያ ህዝብ ባሳተፈ መልኩ ለመሰል ችግሮች መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮችን መመርመርና መፍትሄ መሻት ይጠቅማል።

እስከዛሬ ለነበሩትና አሁን ላለንበት ውስብስብና አስቸጋሪ ሁኔታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካደረጉ አበይት ችግሮች አንደኛው በህገ መንግስታዊ ሥርዓትና በፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም መካከል ያለው የጽንሰ ሃሳብና የተግባር መደበላለቅ ነው። ባለፉት ሁለት ዓመታት የትግራይ ክልል መስተዳድር በፌዴራል መንግስቱ ላይ ካሰማቸው ክሶች አስገራሚው የፌዴራል መንግስቱ ህገ መንግስታዊ ሥርዓቱን ጥሷል የሚለው ውንጀላ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚወጡ በርካታ ትንተናዎች አንድ መሰረታዊ ችግር ይታይባቸዋል። ይህም ህገ መንግስታዊ ሥርዓትን ካንዱ ወይም ከሌላው ዓይነት የፖለቲካ ርዕዮት ዓለም ጋር አዛምዶ የመመልከት ችግር ነው። ይህ ችግር በዋነኝነት በህወሃት እና መሰል የፖለቲካ ድርጅቶች አመራር ውስጥ ገኖ የሚታይ ችግር ነው። በመሆኑም፣ ለህወሃት አመራር ህገ መንግስታዊ ሥርዓት ማለት በአብዮታዊ ዲምክራሲ የፖለቲካ አስተሳሰብ የተቃኘ መንግስታዊ ሥርዓት ብቻ አድርጎ በመውሰድ፣ ከዚህ የተለየ አካሄድ መከተል ኢ-ህገ መንግስታዊነት አድርጎ ይደመድማል።

እንዲህ አይነቱ አመለካከት ባንድ ሃገር ውስጥ ያለን የፖለቲካ ምህዳር አረዳድ የተዛባ ከማድረጉም በላይ የፖለቲካ ድርጅቱ የራሱን ድምጽ የሚያዳምጥበት ሳጥን (echo chamber) ውስጥ ታጥሮ ከገሃዱ እውነታ ጋር እንዲጣላና ወደ አምባገነናዊነት ወይም ወደ ውድቀት እንዲያመራ ያደርገዋል። ይህን መሰል ሁኔታ ዛሬ በህወሃት ብቻ የተከሰተ ሳይሆን፣ ከዚህ ቀደም በነበሩት የፖለቲካ ሥርዓቶች ላይም የታየ እና ወደፊትም በሌሎች ላይ ሊታይ የሚችል ችግር ነው። ስለዚህም፣ እንዲህ አይነቱን መደበላለቅ የፈጠሩ እና ወደፊትም ሊፈጥሩ የሚችሉ ሁኔታዎችን ከመሰረቱ መረዳትና መፍትሄውንም መሻት አሁን ኢጋጥሞን ያለውን አይነት ፈተናዎች ለመቀነስ አይነተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። ለዚህም፣ ሁሉም የፖለቲካ ቡድኖች ሊገነዘቡት የሚገባው ቁም ነገር፣ ያንድ ሃገር ህገ መንግሥት ዴሞክራሲያዊ ሊባል የሚችለው በተለያየ ርዕዮት ዓለም የተቃኙ የፖለቲካ መስመሮች በህዝብ የመጨረሻ ውሳኔ ሊስተናገዱ የሚችሉበትን ማዕቀፍ ሲፈጥር ብቻ መሆኑን ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ በአበይትነት ሊነሳ የሚችለው መዋቅራዊ ጥያቄ ባሁኑ ወቅት በስራ ላይ ያለው ህገ መንግስት ጉዳይ ነው። የማናቸውም ህገ መንግስታዊ ሥርዓት ዋነኛው መሰረቱ ህገ መንግስቱ እንደመሆኑ መጠን በዚህ ላይ ልዩ ትኩረት ማድረጉ ተገቢ ነው። ነገር ግን፣ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚካሄዱ ትንተናዎች በህገ መንግሥት እና በህገ መንግሥታዊ ሥርዓት መካከል ያለውን አንድነት እና ልዩነት ሲያደበላልቁት ይስተዋላል። ከምህዳራዊ ትንተና አኳያ፣ ህገ መንግሥት ያንድ ሃገር የፖለቲካ ሥርዓት የሚመሰረትበት ዋነኛው የህግ ሰነድ ሲሆን፤ ያንድ ሃገር ህገ መንግሥታዊ ሥርዓት በህገ መንግሥቱ ላይ ተመርኩዘው የሚወጡ ዝርዝር ህጎችን እና ህገ መንግሥቱን ለማስፈጸም የሚደራጁ ተቋማትን ያካትታል።

ባሁኑ ሰዓት በስራ ላይ ያለው የፌዴራሉ ህገ መንግስት ለማንኛውም ጤናማ ህገ መንግስታዊ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ የዜጎችንና የማህበረሰቦችን መብቶች የሚያስከብሩ በርካታ መሰረታዊ የህግ አንቀጾችን የያዘ መሆኑ ይታወቃል። ነገር ግን፣ ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው መደበላለቅ ጋር በተያያዘ ህገ መንግስቱን የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ቅኝት የሚሰጡ አንዳንድ አንቀጾችም አሉት። ይህ ይዘትም ህገ መንግስቱን ባንዳንድ ሁኔታዎች እርስ በርሱ የሚጣረስ አድርጎታል። እንዲህ አይነቱ የግጭት ይዘት በተለይም የህገ መንግሥታዊው ሥርዓት ዋነኛ አካል የሆኑት የከልል መስተዳድሮች ባጸደቋቸው ህገ መንግስቶች ውስጥ እጅግ ገንነው ይታያሉ።

ከዚህ በተጨማሪም፣ ህገ መንግሥቱን ለማስፈጸም የተቋቋሙ ተቋማትንም የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ቅኝት እንዲይዙ በመደረጉ በህገ መንግሥቱ ውስጥ ያሉ በርካታ ጠቃሚ ሃሳቦች እንዲኮላሹ አድርጓቸዋል። ይህንን ችግር ለማስወገድ፣ በፌዴራል ህገ መንግስቱ ውስጥ ያሉ የተቃርኖ ምንጮችን መለየትና የከልሎች ህገ መንግስቶችን ከፈዴራሉ ህገ መንግስት ጋር የማጣጣም ስራ መስራት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ነው። በተለይም በፈዴራሉ ህገ መንግስት የተከበረውንና ኢትዮጵያ ዓለም አቀፋዊ ግዴታ የገባችባቸውን የዜጎችን በየትኛውም የሃገሪቱ ክፍል በህይወት የመኖር፣ የመስራት፣ ሃብት የማፍራት፣ የመምረጥና የመመረጥ መብቶቻቸውን ማረጋገጥ ከሁሉም ቀዳሚው ተግባር መሆን ይኖርበታል። እነኝህ መሰረታዊ መብቶች በሚጣሱበት ወቅትም የማንኛውንም ክልል ግብጉም ሆነ ፈቃድ ሳይጠብቅ ህገ መግስቱን ማስከበር የፈዴራሉ መንግስት ግዴታ ሊሆን ይገባል። እነኚህን መሰረታዊ መብቶች ማስከበር በምንም አይነት ሁኔታ በፈዴራል ህገ መንግስቱ የተረጋገጡ የቡድን መብቶችን ሊሸራርፍ ወይንም የሚሸራርፍ ተደርጎ ሊወሰድም አይገባውም።

ሌላው ህገ መንግስታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣለው ተቋማዊ ችግር፣ በህግ አውጭው፣ በህግ ተርጓሚውና በህግ አስፈጻሚው መካከል ያለው ቅጥ የለሽ መደበላለቅ ነው። ይህ ሁኔታ፣ በእነኚህ ሶስት ቁልፍ ህገ መንግስታዊ ተቋሞች መካከል ሊኖር የሚገባውን የትብብርና የቁጥጥር ሥርዓቶች ከማመንመኑም በላይ በህገ መንግስቱ የተከበሩ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ከፉኛ እንዲሸረሸሩ ከፍተኛውን አስተዋጽኦ አድርጓል። ባለፉት ጥቂት የሽግግር ዓመታት ውስጥ፣ በተለይ የህግ ተርጓሚውን ነጻነት ለማረጋገጥ በፈዴራል ደረጃ የተወሰዱ አንዳንድ እርምጃዎች መኖራቸው ይታወቃል። ነገር ግን፣ አጠቃላይ የሽግግር ሂደቱን ቀደም ሲል ከነበረው ከፍተኛ መዋቅራዊ መደበላለቅ ለማላቀቅ እጅግ በርካታ ስራዎች እንደሚቀሩ የሚያመላክቱ በርካታ ሁነቶች ዛሬም ይታያሉ።

በዚህ፣ መዋቅራዊ መደበላለቅን መስመር ለማስያዝ በሚወሰደው እርምጃ ውስጥ ሊካተት የሚገባው ሌላው አቢይ ጉዳይ የህዝብ አስተዳደር (civil service) መዋቅሩን ከፖለቲካዊ መዋቅሩ የመለየት ጉዳይ ነው። ምንም እንኳን በምርጫ አሸናፊ የሆነ የፖለቲካ ድርጅት አሸናፊ ያደረጉትን ፖሊሲዎቹን የሚያስፈጽሙለትን መሪዎች በበላይ ሃላፊነት መመደቡ ተገቢ ቢሆንም፣ አጠቃላይ የህዝብ አስተዳደር መዋቅሩን

ፖለቲካዊ ቅኝት መስጠት ተጠያቂነትን የሚቀንስ ከመሆኑም በላይ የአገልግሎት ውጤታማነትንና መልካም አስተዳደርን የሚያዳክም ይሆናል። ከሁሉም በላይ፣ እንዲህ አይነቱ መደበላለቅ በቅርቡ በሰሜናዊው የሃገራችን ክፍል ጎልቶ እንደወጣው፣ አጠቃላይ መንግስታዊ ተቋማትን የጥቂት አምባገነን ቡድኖች እስረኛና መጠቀሚያ (captive) እንዲሆን ያደርገዋል። በዚህ ረገድ፣ በስልጣን ላይ ያለው ፓርቲም ሆነ ተፎካካሪ ፓርቲዎች መንግስታዊ ያስተዳደር ተቋማትን ከዚህ አይነቱ ፈተና ነጻ እንዲሆኑ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

በቅርቡ በሃገራችን ከተከሰተው አስቸጋሪ ሁኔታ ጋር በጥብቅ የሚተሳሰረው ሌላው መዋቅራዊ ችግር ለዘመናት ሰፍኖ የኖረው የሀገሪቱን የመከላከያ ሰራዊት በየወቅቱ ላሉ የአገዛዝ ሥርዓቶች ጠባቂና አገልጋይ የማድረግ ዝንባሌ ነው። አሁን በስራ ላይ ያለው የፌዴራል ህገ መንግስት፣ የመከላከያ ሰራዊቱ ከማናቸውም ፖለቲካዊ ወገናዊነት ነጻ ሆኖ የሀገሪቱን ሉዓላዊነትና ህገ መንግስታዊ ሥርዓቱን ከጥቃት ይጠብቃል ይላል። ይህ ድንጋጌ በአንድ ሃገር ውስጥ የተረጋጋ ህገ መንግስታዊ ሥርዓት እንዲኖር ከሚያደርጉ ቁልፍ ድንጋጌዎች መካከል ዋነኛው ነው። ያም ሆኖ፣ ለሃያ ሰባት ዓመታት በሀገሪቱ ሰፍኖ የቆየው የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ቅኝት ወደ ሰራዊቱ ዘልቆ በመግባት አብዛኛውን የሰራዊቱን አደረጃጀትና አመራር ፖለቲካዊ ይዘት እንዲኖረው አድርጎት ቆይቷል።

ባለፉት ሁለት የሽግግር ዓመታት፣ ይህንን ሁኔታ ለመቀየርና ሰራዊቱን ከማናቸውም ፖለቲካዊ አደረጃጀት ነጻ ለማድረግ በርካታ የአስተሳሰብ (indoctrination) እና መዋቅራዊ ለውጥ ስራ እንደተሰራ ተነግሯል። ነገር ግን፣ በቅርቡ በሰሜን እዝና በመከላከያ ሰራዊት መዋቅር ውስጥ የተፈጠረው አሳዛኝ ክስተት በዚህ ረገድ ገና ብዙ ቀሪ ስራ እንደሚኖር አመላክቷል። ስለሆነም፣ መንግስትና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የፖለቲካ ቡድኖች ይህንን ለማስተካከል ጥቅል ከሆነ ነቀፌታ እና ምልከታ በጸዳ መልኩ ሁኔታውን ለማጥራት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል። ከዚህ በተጨማሪም፣ የሃገር ህልውናን እስከ መፈታተን የደረሰውን የከልሎች የልዩ ኃይል አደረጃጀት ወደ ህገ መንግስታዊ የአደረጃጀት ሥርዓት ማስገባት ሌላው አቢይ ተግባር ነው።

በመጨረሻም፣ ከዚህ ቀደም በተፈጠሩ ሃገራዊ ጥቃቶች ወቅት እንደታየው፣ በሰሜኑ እዝ የመከላከያ ሰራዊት ላይ የተፈጸመው ጥቃት ከፍተኛ የሆነ ሀገራዊ የአንድነት ስሜት ፈጥሯል። ይህ ከሚያጎናጽፈው መልካም አጋጣሚዎች አንዱ ሃገራዊ መግባባትን ለማጠናከር የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠሩ ነው። ይህንን መልካም አጋጣሚ በቅጡ በመረዳት የብልፅግና ፓርቲም ሆነ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ሃገሪቱን ወደፊት ሊያሻግሩ በሚያስችሉ አበይት ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ በመወያየት ቀጣዩን ምርጫ ነፃና ተዓማኒ ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

የዛሬ መሪዎቻቸን ከዚህ ቀደም በእንዲህ አይነት ሁኔታ ተፈጥረው የነበሩ መሰል መልካም አጋጣሚዎችን ባለመጠቀማችን ከገባንበት ቀውስ ተምረዋል ወይም ይማራሉ የሚል እምነት አለን። ይህ ወቅት፣ የሁሉም ፖለቲካ መሪዎች አስተዋይነትና አርቆ አሳቢነት የሚለካበት ወቅት እንደመሆኑ፤ ሃገራዊ አንድነቱ የፈጠረውን መልካም አጋጣሚ ለህዝቦች ዘላቂ ሰላም፣ እድገትና ልማት ማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ አለመጠቀም ከፍተኛ የታሪክ ተወቃሽነት የሚያስከትል ይሆናል። ከእንዲህ ዓይነቱ ተወቃሽነት ለመዳን፣ በአንድ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ከታጠረ የተዐብዮ ተረክ በመውጣት ዓይነታዊ የለውጥ ተረኮችን በትብብራዊ አስተሳሰብ ለማበልጸግ ዝግጁ መሆንን ይጠይቃል።

## 6.2 ከተዓብዮ ወደ ዓይነታዊ የለውጥ ተረክ ለመሻገር

ከላይ እንደተጠቀሰው፣ በማናቸውም ሃገረ መንግስት ታሪክ ውስጥ፣ የተለያየ ይዘት ያላቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ተረኮች (narratives) መኖር የሚጠበቅ ሲሆን ይህ በራሱ ለግጭት የሚያበቃ አይደለም። ተረኮች ወደ ግጭት የሚያመሩት አንደኛው ወገን በራሱ ተረክ በመታበይ የእኔ የሚለውን ተረክ በሌላው ላይ በኃይል ለመጫን በሚሞክርበት ወቅት ነው። ከ1950ዎቹ ጀምሮ፣ በሃገራችን ለተከሰቱት የፖለቲካ ግጭቶች እና የርስ በርስ ጦርነቶች ዋነኛው መነሻም በእንደዚህ አይነት መታበይ የአንድ ወገን ተረክን በሌላው ላይ ለመጫን ከሚደረግ ጥረት ጋር የተያያዘ ነው።

በምህዳራዊ አስተሳሰብ መሰረት፣ በማናቸውም ህብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ ተቃራኒ ተረኮችን (conflicting narratives) ወደ ዐይነታዊ የለውጥ ተረክ (transformational narratives) ማምጣት ያንን ማህበረሰብ በዘላቂነት ወደፊት ለማሻገር ቁልፍ እና አይነተኛ እርምጃ ነው። ይህ በሰላማዊ ሂደት መሆን በማይችልበት ጊዜ፣ የምህዳሩ በከፍተኛ ቀውስ መናጥ ሌላኛው ነባሪ አማራጭ (default option) ይሆናል። አብዛኞቹ ግጭቶች እና ጦርነቶች የአንዲህ ዓይነት አማራጮች ውጤቶች ናቸው። ይህንን ተከትሎም ቀውሱን ለመሻገር የሚያስችል የስክነት እና አስተውሎት ተዋናዮች መኖር እጅግ አስፈላጊ ይሆናል። ባለፉት ሶስት ዓመታት፣ በህወሃት እና በለውጡ ኃይል መካከል መሰረታዊ የሆነ ሃገራዊ የፖለቲካ ተረክ ልዩነት የነበረ መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው። በመጨረሻም፣ የህወሃት ተዓብዮ ከልኬቱ አልፎ በሃገር መከላከያ ሰራዊት ላይ በወሰደው አሳፋሪ እርምጃ ሀገሪቱን አሳዛኝ ለሆነ የጦርነት ፍዳ ሊዳርጋት በቅቷል።

በሰሜኑ የሃገራችን ክፍል የተካሄደው ህግ የማስከበር ዘመቻ መጠናቀቁን ተከትሎ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዓብይ አህመድ ለተወካዮች ምክር ቤት ያቀረቡት ማብራሪያ ሃገራችን የምትገኝበትን ልዩ የታሪክ አጋጣሚ ያመላከተ ነበር። የገባንበት ቀውስ ለሁላችንም ግልጽ ስለሆነ፣ በዚህ ክፍል የተጋፈጥነው ቀውስ የፈጠራቸውን መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀም እንዴት ለዘላቂ ሃገራዊ ልማት ወደሚጠቅም ዓይነታዊ የለውጥ ተረክ መሸጋገር እንደሚቻል ለመጠቆም ይሞክራል።

ዓይነታዊ የለውጥ ተረኮችን ለማበልጸግ በስራ ላይ ከሚውሉት መርሆዎች አንዱ እና ዋነኛው፣ በልዩ ልዩ ምክንያት አወዛጋቢ እና አጨቃጫቂ የሆኑ ጉዳዮችን ለቀጣይ ሂደት በማቆየት፣ አብዛኛውን ወገኖች ሊያግባቡ በሚችሉ ዋና ዋና ሰበዞች ላይ ተመርኩዞ የጋራ ሃገራዊ ራዕይ መሰረቶችን ማጠናከር ነው። ይህንን በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ ከማብራራት ይልቅ ከአንዳንድ ስሞናዊ ሁነቶች ጋር በማያያዝ መመልከት ይቻላል።

ከነዚህም የመጀመሪያው፣ የሃገር መካላከያ ሰራዊቱ እና ክልላዊ ሃይሎች በሃገሪቱ አጠቃላይ ህልውና ላይ የተጋረጠውን አደጋ ለመመከት ያደረጉት ተጋድሎ እና የትግራይ ህዝብን ጨምሮ መላው የሃገሪቱ ህዝብ ያሳየው የሰላም እና ሃገር ወዳድነት ስሜት ተጠቃሽ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ ጦርነቱን ተከትሎ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለተወካዮች ምክር ቤት

ካቀረቡት ማብራሪያ ውስጥ አንደኛው ነጥብ የሃገር መከላከያ ሰራዊት የብሔራዊ አንድነታችን እና ሉዓላዊነታችን መገለጫ መሆኑን በማስመር ይህንን የሃገር አንድነት ኃይል ከማናቸውም የፖለቲካ ቡድን ተጽእኖ ነጻ ማድረግ እንደሚገባ ነው።

በዚህ ረገድ፣ በህብረተሰቡ ውስጥ ሊሰራ ከሚገባው የማስተማር እና ማሳወቅ ተግባር ባሻገር፣ መንግስት እና የፖለቲካ ቡድኖችም ከእንግዲህ ወዲያ የሃገር መከላከያ ሠራዊትን በምንም አይነት ሁኔታ ለፖለቲካ ዓላማቸው መጠቀሚያ ከማድረግ መቆጠብን እንደ መሰረታዊ አገራዊ መርህ መቀበል እና ማክበር ይኖርባቸዋል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ፣ በክልል መስተዳድሮች የሚደራጁት ልዩ ኃይሎች የሃገርን ልዕልና በማፍረስም ይሁን በማስከበር ሊኖራቸው የሚችለውን ድርሻ በሰሜኑ የሃገራችን ክፍል የተፈጠረው ወታደራዊ ቀውስ በግልጽ አሳይቶናል። እንዲህ ዓይነት ኃይሎች በሃገር ህልውና ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ጥፋት ለመቀነስ የክልል ልዩ ኃይሎች አደረጃጀትን ከህገ መንግሥታዊ ሥርዓቱ አኳያ መመርመር እና ማስተካከል ያስፈልጋል።

ሌላው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያ ላይ የተጠቀሰው አቢይ ነጥብ፣ የተመዘገበውን ወታደራዊ ድል በተመለከተ የትኛውም ወገን በድል አድራጊነት ስሜት ወደ መታበይ እንዳይሄድ የሰጡት ማሳሰቢያ ነው። ይህ አባባል እንደ ማንኛውም አባባል በግርጌ ማስታወሻነት (footnote) የሚታለፍ ሳይሆን፣ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ፋይዳ ያለው ቁምነገር ነው። የወቅቱን የመንግስት ስልጣን ጠቅልሎ በያዘ ድርጅት መሪም መነገሩ ታላቅ ተስፋ የሚሰጥ ነው። ይህንን ለመረዳት፣ ሩቅ ሳንሄድ የደርግ መንግስት የሶማሊያውን ድል ከተቀዳጀ በኃላ እና የኢህአዴግ መንግስት ከኤርትራው ድል በኃላ በምን ያህል ፍጥነት ወደ ለየለት አምባገነናዊነት እንደተቀየሩ ማስታወሱ በቂ ይሆናል።

በህወሃት ላይ የተገኘውን ድል ተከትሎም፣ እንዲህ አይነቱ አዝማሚያ በአንዳንድ ፖለቲካ ሹመኞች አካባቢ መታየት ጀምሯል። በሚያስገርም ሁኔታ፣ እነኚህ አዝማሚያዎች በስልጣን ላይ ካለው ፓርቲ በበለጠ ተቃዋሚ ተረክ በሚያራምዱ ፖለቲካኞች እና ተንታኞች አካባቢ ጎልቶ ታይቷል። ይህም፣ በጦርነቱ የተገኘውን ድል በማስታከክ አስቀድሞም ተናግረን ነበር አሁንም መሆን ያለበት እንደዚህ ነው በማለት የአንድን ወገን ፖለቲካዊ ተረኮች የበላይነት ለማስረጽ በሚደረጉ ጥረቶች ይገለጻሉ። እንዲህ አይነት አመለካከቶች በጦርነቱ የተፈጠረውን የሃገራዊ አንድነት ስሜት የሚሸረሽሩ ከመሆናቸውም በላይ ለዓመታት ሲብላሉ በቆዩት ተቃራኒ ተረኮች መካከል ያለውን ግጭት እንዲባባስ ሊያደርገው ይችላል። ከዚህ ይልቅ፣ ከየትኛውም ወገን ሊመጣ የሚችልን የመታበይ ስሜት በመቋቋም እና ለሌላ የተወሳሰበ ችግር ሊዳርጉ ከሚችሉ ያንድ ወገን ተረኮች በመቆጠብ መጪውን ሃገራዊ ምርጫ ነጻ፣ ፍትሃዊ እና ተዓማኒ ማድረጉ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራቱ ተገቢ ይሆናል።

ባላፉት ጥቂት ዓመታት ከሚያወዛግቡ አንዳንዴም የግጭቶች መነሻ ከሆኑ ጉዳዮች አንዱ የሰንደቅ ዓላማ ጉዳይ ነው። ይህ ችግር ኢህአዴግ ሁሉንም ጉዳይ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ቅኝት ለመስጠት ካለው አምባገነናዊ አባዜ ጋር ተያይዞ በሀገራዊ ሰንደቅ ዓላማ እና መንግስታዊ አርማ መካከል ከፈጠረው መደበላለቅ ጋር የተያያዘ ነው። የቅርብ ጊዜ ታሪካችንን ብንመለከት፣ በንጉሡ ዘመን የሞኅ እንበሳ አርማ ያለበት ሰንደቅ ዓላማ ንጉሱ በሚኖሩበት እና በሚገኙበት ስፍራ ብቻ የሚውለበለብ ሲሆን በደርግ ጊዜም የወታደራዊው ደርግ ዓርማ ያለበት ባንዲራ በቤተ መንግስት እና በዋና ዋና መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ሲውለበለብ ኖሯል። ከዚህ ውጭ፣ አጠቃላዩ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያውቀውም ሆነ በየቤቱ ደጃፍ የሚያውለበልበው ሰንደቅ ዐላማ ለዘመናት የዘለቀው ባለ ሶስት ቀለሙን ሰንደቅ ዓላማ ነው።

በመሰረቱ፣ ማንኛውም ዜጋ እንኳንስ ሃገራዊ ሰንደቅ ዓላማን አይደለም፣ ሃሳቡን እና እምነቱን ይወክላል የሚለውን ማንኛውንም አርማ ይዞ መዘዋወር ሃሳቡን በነጻነት የመግለጽ ህገ መንግስታዊ መብቱ አካል ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል። በዚሁ አገባብ፣ መንግስታዊ ተቋማት መንግስታዊ አርማ ያለበትን ሰንደቅ ዓላማ ማውለብለብ የሚጠበቅባቸው ሲሆን ሌሎች ዜጎች ግን እንደምርጫቸው ባለዓርማውንም ሆነ መደበኛውን ሰንደቅ ዓላማ የመያዝ እና የመጠቀም ነጻነታቸው ሊጠበቅ ይገባል። ይህንን በማድረግም፣ በሰንደቅ ዓላማ ዙሪያ ሊኖር የሚገባውን ሃገራዊ አንድነት ማጠናከር ይቻላል።

በቅርቡ የተከሰተው ሃገራዊ ቀውስ አንድ አቢይ ጠቃሚ ጎኑ በከፍተኛ ደረጃ የፈጠረው ሃገራዊ የአንድነት ስሜት ነው። ይህ ደግሞ፣ አከራካሪ በሆኑ አበይት የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ወደ ዓይነታዊ የለውጥ ተረኮች ሊወስዱ የሚያስችሉ መግባባቶችን ለማዳበር የሚያስችል ሁኔታ ፈጥሯል። ከነዚህ አከራካሪ ጉዳዮች ውስጥ ዋነኛው በስራ ላይ ያለው ህገ መንግስት መነካት የለበትም በሚሉ እና ህገ መንግስቱ ሙሉ በሙሉ መቀየር አለበት በሚሉ ሁለት ተቃራኒ ተረኮች ዙሪያ ይሽከረከራል። ከዓይነታዊ የለውጥ ተረክ አኳያ ለሃገሪቱ ሽግግር እጅግ ጠቃሚ የሚሆነው በእነዚህ ጽንፍ አቋሞች ዙሪያ መነታረክ ሳይሆን በህገ መንግስታዊ ስርዓቱ ውስጥ ያሉትን መሰረታዊ የተቃርኖ ምንጮች ማድረቅ ነው።

ከዚህ ውስጥ ዋነኛው በስራ ላይ ያለው ህገ መንግስት 'የሀገሪቱ ሉዓላዊነት ባለቤት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ናቸው' ብሎ ይደነግጋል። ነገር ግን፣ በዚሁ ህገ መንግስት መሰረት የተቋቋሙት አብዛኞቹ የክልል መንግስታት ህገ መንግስቶች 'ህዝቦች' የሚለውን ቁልፍ ህገ መንግስታዊ ቃል እንደሌለ በመቁጠር ክልሎችን የአንድ ወይንም የተወሰኑ ብሔሮች እና ብሔረሰቦች ብቻ እንደሆኑ አድርገው ደንግገዋል። እንዲህ ዓይነቱ ኢህገመንግስታዊ አካሄድም ለበርካታ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት፣ ህይወት መጥፋት እና ህዝቦች መፈናቀል ዋነኛ መነሻ ሆኗል።

ወደፊት ሊያራምደን የሚችለው ዓይነታዊ የለውጥ ተረክ በስራ ላይ ባለ ህገ መንግስታዊ ሥርዓት ውስጥ ያሉትን ነጂ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ይዘቶች እና ተቃርኖዎች በሂደት በመንቀስ ለሁሉም ህዝቦች መሰረታዊ መብት መከበር መስራት ነው። ለዚህም አብዩ የአጭር ጊዜ መፈተሻ፣ በመጪው ሃገራዊ ምርጫ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በየትኛውም የሚኖርበት ክልል በነጻነት መምረጥ እና መመረጥ የሚችልበትን ሁኔታ ማስከበር እና በየትኛውም የሃገሪቱ ክፍል የሚኖሩ ህዝቦች በነጻነት በመረጧቸው መሪዎቻቸው የመተዳደር መብታቸውን ማክበር ይሆናል።

ከህገ መንግስቱ ጋር የተያያዘ ሌላው አከራካሪ ጉዳይ የፌዴራል አወቃቀር ሥርዓቱ ነው። አንደኛው ተረክ፣ 'ዛሬ ያለው የክልል አወቃቀር የብሔር ብሔረሰቦችን ራስን በራስ የማስተዳደር መብት ያስከበረ በመሆኑ ሊነካ አይገባም' ሲል፣ የዚህ ተቃራኒው ተረክ ደግሞ 'አሁን ያለው የክልል አወቃቀር ሃገሪቱን ለማያባራ የህዝቦች ግጭት የዳረገ በመሆኑ ሊፈርስ እና በሌላ አደረጃጀት ሊተካ ይገባዋል' ይላል። በዚህ ፀሃፊ ዕምነት፣ የወቅቱ ዋነኛ የፖለቲካ ችግር በስራ ላይ ያለው የክልል አከላለል ሳይሆን የፌዴራል ሥርዓቱ ዲምክራሲያዊ አለመሆን ነው። ስለዚህም፣ የዓይነታዊ ለውጥ ትርክቱ ትኩረት መሆን ያለበት እንዴት አሁን ያለውን የፌዴራል አከላለል ዴሞክራሲያዊ እናድርገው መሆን የኖርበታል።

ለዚህም አብዩ የአጭር ጊዜ መፈተሻ፣ አንደኛ፣ በሃገሪቱ ህገ መንግስት አንቀጽ ስምንት መሰረት ባሁኑ ሰዓት በሃገሪቱ የሚገኙ ክልሎች ባለቤቶች በየክልሉ ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች በሙሉ እንጂ የአንድ ወይንም የተወሰኑ ብሔረሰቦች ብቻ አለመሆናቸውን አምኖ መቀበል፤ ሁለተኛ፣ በክልሎች መካከል የሚገኘው መለያ አስተዳደራዊ ወሰን እንጂ ሃገራዊ ድንበር አለመሆኑን መረዳት እና እንዳስፈላጊነቱ በግጭት ሳይሆን በህዝቦች ቀጥተኛ ተሳትፎ እና ውሳኔ ሊቀየሩ የሚችሉ መሆናቸውን መቀበል፤ እና ሶስተኛ፣ የፌዴራላዊው አስተዳደር መሰረት የሆኑት የወረዳ አስተዳደሮች የህዝቦች ራስን በራስ የማስተዳደር ተግባራዊነት ዋነኛ መገለጫዎች መሆናቸውን አምኖ በክልሎች የተማከለውን አስተዳደር ወደ ህዝቡ ማቅረብ ይሆናል። ይህንን በማድረግም፣ አሁን ያለውን የፌዴራል ሥርዓትን ዴሞክራሲያዊነት በተግባር ማጠናከር ይቻላል።

በመጨረሻም፣ ከዚህ በላይ ከተመለከትናቸው የህገ መንግስት እና ፌዴራል አወቃቀር ጋር የተያያዘ ሌላው አከራካሪ ጉዳይ የቋንቋ ጉዳይ ነው። በዚህ ረገድ፣ ከህዝቦች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት መከበር አኳያ፣ እያንዳንዱ ክልል በክልሉ ውስጥ የሚገኘው አብዛኛው ህዝብ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የሆነውን የክልሉ ዋነኛ የስራ ቋንቋ ማድረጉ ያለው ጠቀሜታ የሚያከራክር አይሆንም። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በህዝቦች አንድነት ላይ የተመረኮዘ ፌዴራላዊ ሥርዓት እንዲኖረን ከተፈለገ ለሃገራዊ መግባባት የሚያገለግል ቋንቋ መኖር አስፈላጊነትን መገንዘብ ያስፈልጋል። ከዚህ አኳያ፣ በህገ መንግስቱ የፌዴራል መንግስቱ የስራ ቋንቋ የሆነው በክልሎች አስተዳደር መስሪያ ቤቶች እንደ ሁለተኛ ቋንቋ አለመስራቱ ሥርዓቱን ከፌዴራላዊ ይልቅ የኮንፌዴራላዊ ሥርዓት አስመስሎታል።

ይህ በአብዛኛው፣ አንድን ቋንቋ ከመግባቢያ መሳሪያነት ይልቅ በመጨቆኛ መሳሪያነት ከሚያቀርበው የአብዮታዊ ዲሞክራሲ የፖለቲካ በሽታ ጋር የተያያዘ ነው። በሌላ በኩል ግን፣ እንደ ኢትዮጵያ ባለ በርካታ ቋንቋዎች በሚነገርበት ሃገር የፌዴራሉ የስራ ቋንቋ ባንድ ብቻ ተወስኖ እንዲቀር መጠበቅም አይቻልም። ስለሆነም፣ በበርካታ የሃገሪቱ ህዝቦች የሚነገሩ የተወሰኑ ቋንቋዎችን በፌዴራል ቋንቋነት መቀበል አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ እነኝህን ቋንቋዎች እንደየሰዉ ምርጫ ለመማር የሚያስችል ሁኔታን በየትኛውም ክልል ማመቻቸትም ያስፈልጋል።

በዚህ ሂደት ውስጥ፣ ተማሪዎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ከማጠናቀቃቸው በፊት፣ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በተጨማሪ ቢያንስ አንድ የፌዴራል ቋንቋን እንዲማሩ ማበረታታት የፌዴራል ሥርዓቱን ማህበራዊ መሰረት በማጠናከር ረገድ ታላቅ ድርሻ ይኖረዋል። ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን እርምጃዎች በመውሰድ፣ ቋንቋዎቻችን የግጭቶች ምንጭ ከመሆናቸው ይልቅ የሃገራዊ ልማት እና አንድነት መሳሪያዎቻችን ልናደርጋቸው እንችላለን። እዚህ ላይ፣ ለረጂም ጊዜ የነበረውን ተቋማዊ አድልኦን ጨምሮ፣ በበርካታ ምክንያቶች የተነሳ መጀመሪያው ላይ አንደኛው ቋንቋ ከሌላው የተሻለ ተቀባይነት ሊኖረው ይችላል[32]። ይህን ሁኔታ ግን፣ ሌሎች አስገዳጅ ተቋማዊ ሁኔታዎችን በመጫን ሳይሆን፣ ማናቸውም ተቋማዊ አድሎዎችን በማስወገድ እና በግለሰቦች ፈቃድ ላይ የተመረኮዘ የቋንቋ ትምህርቶችን በማስፋፋት ማጣጣም ይቻላል።

[32] እንዲህ ዓይነት ሁኔታ በማንኛውም ከአንድ በላይ የፌዴራል ቋንቋ ባላቸው ሃገሮች የሚያጋጥም እንጂ ለኢትዮጵያ ብቻ የተለየ አይደለም። እንደምሳሌም፣ በእንግሊዝኛ እና በፈረንሳይኛ መካከል በካናዳ፣በፈረንሳይኛ እና በፍሌሚሽ መካከል በቤልጂየም፣ እንዲሁም በፈረንሳይኛ፣ በጀርመንኛ እና በጣሊያንኛ መካከል በስዊዘርላንድ ያለውን ሁኔታ መመልከት ይቻላል።

## 6.3 ለብሔራዊ መግባባት ውይይት ውጤታማነት[33]

ላለፉት በርካታ ዓመታት በሃገራችን በኢትዮጵያ ያለውን የፖለቲካ መመሰቃቀል ለመረዳት እና መፍትሄ ለመሻት የብሔራዊ መግባባት አስፈላጊነት በተደጋጋሚ ሲነሳ እና ሲጠየቅ እንደነበር ይታወቃል። ይህንንም እውን ለማድረግ በተለያዩ ዜጎች እና የበጎ ፍቃድ ቡድኖች ልዩ ልዩ ጥረት ሲደረግ ቆይቷል። ነገር ግን፣ ከእነኚህ ጥረቶች አብዛኞቹ ወይ በጅምር ከሽፈዋል አለበለዚያም በውሱን ውጤታማነት ተጠናቀዋል። ለዚህም በርካታ ምክንያቶች ሊጠቀሱ የሚችሉ ቢሆንም የሂደቶቹ አካታች አለመሆን እና በስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ለሂደቶቹ የነበረው ፈቃደኝነት ውሱን መሆን በዋነኝነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። በቅርቡ በሠላም ሚኒስቴር እና በኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አማካኝነት ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያካተተ የብሔራዊ መግባባት ውይይት ለማካሄድ የተደረሰው ስምምነት እና ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግ በፖለቲካ ፓርቲዎች መሃል እየተካሄደ የሚገኘው ውይይት ከላይ የተጠቀሱትን መሰረታዊ ችግሮች በማስወገድ ረገድ የተሻለ እድል ይኖረዋል ተብሎ ይገመታል። በመሆኑም፣ ሁሉም የዚህች ሃገር የወደፊት እጣ ፈንታ የሚያስጨንቀው ወገን ሊያበረታታው እና ህዝባዊ እና ሙያዊ ድጋፍ ሊቸረው ይገባል። ይህንን ለሃገሪቱ መጻኢ ዕድል ወሳኝ የሆነ ሂደት የሚመሩ እና የሚያስተባብሩ ወገኖችም ሂደቱ ውጤታማ እንዲሆን፣ ካለፉ መሰል ጥረቶች መማር እና ለችግሩ ውስብስብነት በሚመጥን የአተናተን ዘዴ (methodology) ሂደቱን መምራት ይጠበቅባቸዋል።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ከተደረጉ መሰል ጥረቶች መካከል በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችለው የምንፈልጋት ኢትዮጵያ (Destiny Ethiopia) በሚል ስያሜ እየተነቃነቀ የሚገኘው ሃገር በቀል ተነሳሽነት ነው። ይህ ሂደት በተከተለው ልዩ ስልታዊ አካሄድ የተነሳ፣ ምናልባትም በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ የተሻለ ውጤታማነት የታየበት ሂደት ነበር ማለት ይቻላል። የዚህ ሂደት የመጀመሪያው ግብ፣ በፖለቲካ ልሂቃኖቹ መሃከል ለዘመናት ተኮትኩቶ የተገነባውን አእምሮአዊ አጥር (Mental barriers) ማፈራረስ ነበር። ይህንን ግብ፣ በግለሰብ፣ በቡድን እና በስብስብ ደረጃ በተካሄዱ በርካታ ውይይቶች እና የተግባር ልምምዶች አማካኝነት በአብዛኛው ለማሳካት እንደቻለ መመስከር ይቻላል። ከዚህ በመቀጠል የነበረው ግብ የሀገሪቱን መሰረታዊ የፖለቲካ ችግሮች ሊፈታ የሚያስችል አሻጋሪ ቢሆንሶችን (transformational scenarios) መለየት ነበር። ይህንንም ለማድረግ ከተናጠል ሁነቶች እና ሂደቶች አሻግሮ በመመልከት መዋቅራዊ ምክንያቶችን እና አእምሮአዊ ምስሎችን (models) መፈተሽ አስፈላጊ ነበር።

[33] የዚህ ክፍል አብዛኛው፣ መስከረም 30 ቀን 2013 በወጣው አዲስ አድማስ ጋዜጣ ታትሟል።

በዚህም መሰረት፣ የሂደቱ ተሳታፊዎች በሃገራችን ፖለቲካ ውስጥ ያሉትን መዋቅራዊ አይገመቴዎች (structural uncertainties) በሚገባ መለየት ችለው ነበር። ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ፣ መዋቅራዊ አይገመቴዎችን ከለዩ በኋላ መሰረታዊ ምንጮቻቸውን መረዳት እና እነርሱም የሚያስከትሉትን የተለያዩ እንደምታዎች መተንተን ወደ አሻጋሪ ቢሆኑላቹ የሚወስድ መሰረታዊ ሂደት ነው። የምንፈልጋት ኢትዮጵያ ሂደት ይህንን መሰረታዊ የትንተና ደረጃ በመዝለል ከመዋቅራዊ አይገመቴዎች በቀጥታ ቢሆንሶቹን ወደ መግለጽ ውስጥ ገብቷል። የዚህም ውጤት በአብዛኛው ህብረተሰብ ሊገመቱ የሚችሉ አንድ የተስፋ እና ሶስት የስጋት ቢሆንሶችን ከማውጣት ሊዘል አልቻለም።

እዚህ ላይ፣ ይህንን ሂደት ከሃሳብ ማመንጨት እስከ መጨረሻው ተግባራዊነት የነበረውን አድካሚ ስራ በማስተባበር የመሩት ኢትዮጵያዊያን እና በሂደቱ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ያደረጉት የምንፈልጋት ኢትዮጵያ ቡድን አባላት አድናቆት ሊቸራቸው ይገባል። ይህ ሂደት ለሃገሪቱ የፖለቲካ ችግሮች መፍትሄ ለመሻት ያደረገው አስተዋጽኦ ቢኖርም፣ በሂደቱ የመጨረሻ ክፍል የታየው መሰረታዊ ያካሄድ ግድፈት[34] በተገኘው የመግባባት መንፈስ ላይ በመገንባት ለሃገሪቱ የፖለቲካ ችግር አመላካች የሆኑ መፍትሄዎችን ለማመንጨት የሚያስችለውን እድል እንዲያመልጠው አድርጎታል።

አሁንም ሆነ ወደፊት ሊካሄዱ የሚችሉ የብሔራዊ መግባባት ውይይቶች ከምንፈልጋት ኢትዮጵያ ሂደት ሊማሩ የሚችላቸው በርካታ ቁምነገሮች ሲኖሩ፣ የሚከተሉትን በዓበይትነት መጥቀስ ይቻላል። የመጀመሪያው፣ ምንም እንኳን በአሁኑ ሰዓት በሃገሪቱ የሚገኙ የፖለቲካ ድርጅቶች እጅግ የተለያየ አንዳንዴም የማይታረቅ የሚመስል አቋም ያላቸው ቢመስልም በጽሞና ለመደማመጥ በሚያስችል ሁኔታ ከተወያዩ መግባባት የሚችሉበት አጋጣሚ ከፍተኛ መሆኑን ነው። ሁለተኛው፤ የብሔራዊ መግባባት ውይይቱ የተሳካ እንዲሆን የሃገሪቱን ውስብስብ ሁኔታ በሚመጥን እና በብዙ መሰል ውስብስብ ሂደቶች ላይ በተፈተነው የዓይነታዊ ለውጥ አስተሳሰብ (transformational thinking) ዘዴ እና ዕውቀት ሊደገፍ ይገባል። ይህንን ዕውቀት ለመሻትም ባህር አቋርጦ ወደ ውጭ መመልከት የሚያስፈልግ ሳይሆን በሃገራችን የሚገኙ ሃገር በቀል የውይይት እና መደማመጥ ሥርዓቶችን፣ ውስብስብ ችግሮችን ለመፍታት ከሚያስችሉ የዘመኑ ዕውቀት እና ዘዴዎች ጋር በማሰናሰል መጠቀም ይቻላል። ይህንን መሰረት በማድረግ፣ ከምህዳራዊ አስተሳሰብ አኳያ በአሁኑ ሰዓት እየተካሄደ ያለውን እና ወደፊትም የሚካሄደውን የብሔራዊ መግባባት ውይይት ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ አንዳንድ መሰረታዊ ነጥቦችን ከዚህ በመቀጠል ተመልክተዋል።

[34] የዚህ ግድፈት ዋነኛው ምክንያት፣ ለዚህ ሂደት በዓለም አቀፍ አማካሪነት የተመረጠው ቡድን በምህዳራዊ አስተሳሰብ ላይ ስለተመረኮዙ ዓይነታዊ የለውጥ ቢሆንሶች (Transformational scenrios) ያለው ዕውቀት ውሱን መሆን ነበረ።

ከላይ እንደተጠቀሰው፣ ባሁኑ ስዓት በተለያየ ደረጃ እየተካሄደ ያለው የብሔራዊ መግባባት ውይይት በቅርብ ጊዜው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው መልካም አጋጣሚ ነው ማለት ይቻላል። ይህንን አጋጣሚ ውጤታማ ለማድረግ ቁልፉ መለኪያ አጠቃላይ ሂደቱ ትብብራዊ አስተሳሰብን (collaborative thinking) በሚያጠናክር መልኩ እንዲዋቀር ማድረጉ ላይ ነው። የሚፈለገውን የአስተሳሰብ ሽግግር ለማምጣት እና ወደ መፍትሔዎቹ ለማምራት የምህዳራዊ አስተሳሰብ ዋና ዋና መርሆዎችን መሰረት በማድረግ ሶስት ምዕራፍ ባለው ትብብራዊ የአስተሳሰብ (Collaborative thinking) ሂደት ውስጥ ማለፍን ይጠይቃል። የመጀመሪያው፣ በሀገሪቱ መሰረታዊ የፖለቲካ ጥያቄዎች ላይ የሚነሱ የተለያዩ ሃሳቦች እና አቋሞች የሚጠበቁ መሆኑን ተገንዝቦ፣ ምንም ያህል የተቃረኑ (divergent) ቢመስሉም፣ ከልብ ለመስማት እና ለመደማመጥ የሚያስችል ዝግጁነት መፍጠር እና ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው።

ምስል ሶስት፡ ትብብራዊ የአስተሳሰብ ሂደት (Collaborative thinking process)

ከዚህ በመቀጠል፣ ለተቃራኒ አመለካከቶች መነሻ የሆኑ ተጨባጭ እና ግምታዊ ስጋቶችን ለመረዳት መጣር ያስፈልጋል። ይህን ለማድረግም፣ ሌሎች ወገኖች የሚያነሷቸውን ጥያቄዎች እና ሃሳቦች ተገቢውን አክብሮት መስጠት እና ሥረ-መሰረቱን በእነርሱ ቦታ ሆኖ ለመረዳት መሞከርን ይጠይቃል። ከዚህ በተጨማሪ፣ በተገኘው የሃሳብ መግባባት ላይ በመመርኮዝ ያሉትን ስጋቶች እና ቅሬታዎች ሲቻል ለመፈወስ ይህም ባይቻል ድጋሚ እንዳይከሰቱ ለማድረግ የሚያስችል አዲስ እይታ እንዲመነጭ (emergence) ማድረግ

ይሆናል። የመጨረሻው ደረጃ፣ ከላይ በተጠቀሱት ሁለት ሂደቶች በተፈጠረው መደማመጥ እና መተማመን ላይ ተመርኩዞ እንዲኖረን ለምንፈልገው የፖለቲካ ሥርዓት አስፈላጊ በሆኑ ዋና ዋና መዋቅራዊ መሰረቶች ላይ መግባባትን (convergence) መፍጠር ይሆናል። እንዲህ ዓይነቱ የትብብራዊ አስተሳሰብ ሂደት፣ ከቤተሰብ እስከ ሃገረ መንግሥት፣ ከአነስተኛ ድርጅት እስከ ዓለም አቀፋዊ ኩባንያ ሊሰራ የሚችል ያስተሳሰብ ሂደት መሆኑ የተረጋገጠ በመሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ቢያዳብረው ይጠቅማል።

ከዚህ በተጨማሪ፣ ከመወያያ ርዕስ መረጣ እስከ ጽሁፍ ዝግጅት፣ አቀራረብ እና የውይይት አደረጃጀት ድረስ ያሉትን ሂደቶች በጥንቃቄ መንደፍ እና ማዘጋጀትን ይጠይቃል። የመወያያ ርዕስ መረጣን በሚመለከት ለብሔራዊ መግባባት ውይይት የሚመረጡ ርዕሶች የዲምክራሲያዊ መፎካከሪያ ምህዳሩን ጤናማነት ለማጠናከር አስፈላጊ የሆኑ የመተባበሪያ ርዕሶች ሊሆኑ ይገባቸዋል። የዚህ ዋነኛው ምክንያት፣ የመፎካከሪያ ርዕሶችን ለውይይት መምረጡ ከመግባባት ይልቅ መቋጠሪያ ወደሌለው ንትርክ የሚያስገባ በመሆኑ ነው። ይህንን በምሳሌ ለማስረዳት፣ ለሁለተኛው ዙር የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ውይይት ከተመረጡት ርዕሶች አንደኛው ከፓርቲዎች ሙብዛት ጋር በተያያዘ የፓርቲዎች አደረጃጀትን የሚመለከት ጥናታዊ ጽሁፍ እንዲሆን መወሰኑን በሚድያ ሲነገር ተሰምቷል። ዛሬ ሃገሪቱ ካሉባት በርካታ የፖለቲካ አጣብቂኞች አኳያ ይህ ርዕስ በምንም አይነት መመዘኛ ለብሔራዊ መግባባት የሚመጥን ካለመሆኑም በላይ፣ አወዛጋቢ የመሆን እድሉም ከፍተኛ ይሆናል።

በመሰረቱ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን አደረጃጀት እና ብዛት በእንደዚህ አይነት ስብሰባ ለመወሰን መሞከር የኢዴሞክራሲያዊነት ዝንባሌም ያለው ይመስላል። ይህንን ሁኔታ ባግባቡ ለማስተናገድ ማንኛውም ፓርቲ እንደፓርቲ ለመመዝገብ እና ከምርጫም በኋላ በሚያገኘው የህዝብ ድምጽ ላይ ተመርኩዞ ሊኖረው የሚችለውን ፖለቲካዊ ሙበት በምርጫ ህጉ ውስጥ በአግባቡ እንዲካተት ማድረግ ተገቢ ነው። ነገር ግን፣ ይህንን ሂደት አካታች በሆነ ሂደት በባለቤትነት መምራት ያለበት ገለልተኛ እንዲሆን የሚጠበቀው የምርጫ ቦርድ እንጂ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አይደለም።

የብሔራዊ መግባባት ውይይት አንደኛው መሰረታዊ ግቡ፣ በፖለቲካ ተዋንያኖች መካከል ሊኖር የሚገባውን ትብብራዊ አስተሳሰብ ማጠናከር ነው። በዚህ ረገድ፣ ለውይይት መነሻ የሚሆኑ ጽሁፎች የሚዘጋጁበት እና የሚቀርቡበት መንገድ ወደዚህ ግብ የሚደረገውን ጉዞ ከሚወስኑት አካሄዶች አንዱ እና ዋነኛው ነው። እስካሁን በተካሄዱት ውይይቶች በተመረጡት ርዕሶች ላይ የመወያያ ጽሁፎች የማቅረቡ ሃላፊነት የተሰጠው ከፓርቲዎች ውስጥ ለተመረጡ ግለሰቦች በተናጠል ነው። እንዲህ አይነቱ አካሄድ፣ በአቅራቢው በኩል ጽሁፉን ምንም ያህል ሚዛናዊ ለማድረግ ቢሞክር፣ በፓርቲው መስመር ለመጠለፍ ወይንም በፓርቲ ወገናዊነት ለመኮነን አደጋ መጋለጡ የበዛ ነው።

ከትብብራዊ አስተሳሰብ አኳያ ተመራጩ መንገድ፣ ባንድ ርዕስ ላይ የሚቀርብን የመወያያ ጽሁፍ ከሶስት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተወከሉ ግለሰቦች በጋራ እንዲያዘጋጁ እና እንዲያቀርቡ ማድረግ ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ፣ አዘጋጆቹ የሚጠበቅባቸው በተሰጣቸው ርዕስ ላይ የሚግባቡባቸውን እና የሚለያዩባቸውን አንኳር ነጥቦች ለይተው በማቅረብ በሚግባቡባቸው ነጥቦች ላይ እንዴት አብሮ መስራት እንደሚቻል እና የሚለያዩባቸውን ነጥቦች እንዴት ሊስተናገዱ እንደሚችሉ ማመላከት ይሆናል። ይህንን አካሄድ በመጠቀምም፣ የጋራ ሃላፊነት በተሰጣቸው ግለሰቦች መካከል የተሻለ የሃሳብ ግንኙነት እና መረዳት ከመፍጠር ባሻገር ለብሔራዊ መግባባት መፈጠር የሚያግዙ መሰረታዊ ጡቦችን (building blocks) ደረጃ በደረጃ ለማስቀመጥ የሚያስችል ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል።

ከርዕስ መረጣ እና የመወያያ ጽሁፍ አዘገጃጀት ባልተናነሰ ቁልፍ ድርሻ ያለው ሶስተኛው አካሄድ፣ በጽሁፎቹ ላይ የሚካሄዱ ውይይቶች አደረጃጀት ይሆናል። በሚድያ ሲተላለፍ እንደታየው ከሆነ፣ እስካሁን በተደረጉት ስብሰባዎች ላይ ጽሁፎቹ ከቀረቡ በኋላ ሁሉም ተሳታፊዎች ባሉበት ምልዐተ ስብሰባ (plenary) ላይ ውይይቱ ይቀጥላል። እንዲህ አይነቱ አካሄድ፣ ሃሳባቸውን ለማካፈል የሚፈልጉ ተሳታፊዎች የሚኖራቸውን እድል የሚያጠብ ከመሆኑም በላይ በዋነኛ ነጥቦች ላይ ትኩረት ያደረገ እና ውጤታማ የሆነ ውይይት ለማካሄድ የሚኖረውን እድል እጅግ ፈታኝ ያደርገዋል። ከዚህ ይልቅ ተመራጩ እና ውጤታማው መንገድ፣ የመወያያ ጽሁፎቹ ከቀረቡ እና በጽሁፎቹ ላይ ለሚነሱ የማብራሪያ ጥያቄዎች መልስ ከተሰጡ በኋላ ያሉትን ተሳታፊዎች በአነስተኛ ቡድኖች በመከፋፈል በቀረቡት ጽሁፎች ላይ ተወያይተው የሚደርሱበትን ማጠቃለያ ለምልዐተ ስብሰባው ለውይይት እንዲያቀርቡ ማድረግ ነው።

እንዲህ ዓይነቱ የምልዐተ ስብሰባ እና የቡድኖች ውይይት ቅይጥ አካሄድ ሃሳቦች በደንብ የሚብላሉበትን ሁኔታ ከመፍጠሩም ባሻገር በተሳታፊዎቹ መካከል ሊፈጠር የሚገባውን ግለሰባዊም ሆነ ቡድናዊ መስተጋብር ይበልጥ ስኬታማ እና ጤናማ እየሆነ እንዲሄድ ያደርገዋል። ይህም፣ ፓርቲዎቹ ይበልጥ እየተሰባሰቡ እንዲሄዱ ሊያግዛቸው ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ፣ የብዙ መሰል ጉባኤዎች ልምድ እንደሚያመላክተው፣ እንዲህ አይነት ስብሰባዎች ላይ ቢያንስ በቡድን ተከፋፍለው የሚደረጉ ውይይቶችን ከሚድያ እይታ ውጭ እንዲካሄዱ ማድረግ ይመከራል። ይህም፣ ተሳታፊዎች በፍጹም ነጻነት ሃሳባቸውን እንዲገልጹ ከማበረታታቱም ባሻገር በደንብ ያልተብላሉ ሃሳቦችን በሚዲያ በማሰራጨት ሊፈጠሩ ከሚችሉ ብዥታዎች ህብረተሰቡን መጠበቅ ያስችላል።

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የአካሄድ መርሆች ባሻገር፣ እንዲህ ዓይነት ጉባዔ ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ፣ ሁሉም ተሳታፊዎች በተናጠልም ሆነ በጋራ ሊያከብሯቸው የሚገቡ መሰረታዊ የሥነምግባር መመሪያዎች ይኖራሉ። ከዚህ ውስጥ የመጀመሪያው እና ዋነኛው ሁሉም ተሳታፊዎች ለሀገራቸው እድገት እና ለህዝባቸው ኑሮ መሻሻል ቀና አስተሳሰብ ይዘው የተነሱ ናቸው የሚል ቀና ግምት (benefit of the doubt) መስጠት ይሆናል። እንዲህ አይነቱ እምነት፣ በህዝቦች ዳኝነት ከማመን ጋር በጥብቅ የተሳሰረ

በመሆኑ ፖለቲከኞቻችን የየትኛውንም የፖለቲካ ድርጅት ወይንም ፖለቲከኛ የመጨረሻውን ዳኝነት በነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ለሚወስነው ህዝብ ሊተዉለት ይገባል።

ከዚህ በተጨማሪ፣ በእንዲህ አይነት መድረክ የሚቀርቡ ማናቸውንም ሃሳቦች በሃሳብ መሞገት እንጂ ለምን እንዲህ ተባለ ብሎ፣ ከዚህ በፊት በተካሄዱ አንዳንድ ውይይቶች ላይ እንደታየው፣ ፖለቲካዊ ፍረጃ እና ቅጥያ (Political labelling) ለመስጠት መሞከር አይገባም። ይህ ፖለቲካዊ ቅጥያ የመስጠት ዝንባሌ ከተማሪው እንቅስቃሴ ጀምሮ ፖለቲካችንን የተጠናወተ በሽታ በመሆኑ በዚህ ዘመን ልናስወግደው ይገባል። ከዚህ በተጨማሪ፣ ለብሔራዊ መግባባት የሚደረግ ውይይት ዘላቂ፣ ሃገራዊ እና ህዝባዊ ሰላም እና ልማት ለማረጋገጥ የሚደረግ ውይይት እንጂ ለምርጫ መፎካከሪያ የሚሆን የፖለቲካ ነጥብ ማስቆጠሪያ እንዳልሆነ ሁሉም ተሳታፊዎች ሊገነዘቡት ይገባል። በመጨረሻም የአህጉራችን ታላቅ ሰው የሆኑት ኔልሰን ማንዴላ እንደተናገሩት ውስብስብ የፖለቲካ ፈተና ውስጥ ለሚገኙ ሃገራት ብሔራዊ መግባባት፣ ተግባራዊ ሆኖ እስከሚገኝ ድረስ በጭራሽ የማይቻል መስሎ ይታያል። ነገር ግን ይቻላል፤ ተችሏልም።

## የከፍል ስድስት ቁልፍ ሐሳቦች

i. በማናቸውም ማህበረሰብ ወይም ሃገር ውስጥ የተለያዩ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና የልማት ተረኮች መኖር የሚጠበቅ ሲሆን እነኚህ ተረኮች ግን ለተለያዩ ግጭቶች መነሻ የሚሆኑት እንደ ኢትዮጵያ ባሉ በማደግ ላይ ባሉ ሃገሮች ውስጥ ብቻ ነው። የዚህም ዋነኛው ምክንያት፣ በተለያዩ ተረኮች መካከል የሚኖሩ አለመጣጣሞችን ሲቻል ለማስታረቅ ያም ካልተቻለ ደግሞ ለመዳኘት የሚያስችሉ ተቋማዊ አደረጃጀቶች እና ሥርዓቶች ደካማ ሆነው መገኘታቸው ነው።

ii. በእንዲህ ዐይነት ሁኔታ ውስጥ ያሉ ሃገሮች ለወደፊት እጣ ፈንታቸው ወሳኝ ከሆኑ የሽግግር ወቅት ጋር በሚፋጠጡበት ጊዜ የብሔራዊ መግባባት ውይይት ማካሄድን እንደ አንድ ዓብይ መፍትሔ ይጠቀሙበታል። ለዚህም መሳካት የመጀመሪያው አስፈላጊ ነጥብ፣ በማህበራዊ ተረክ እና በተቋማዊ ተረክ መካከል ያለውን አይነታዊ ልዩነት መረዳት ነው።

iii. ማህበረሰባዊ ተረክ (social narrative)፣ አንድ ማህበረሰባዊ ቡድን የመጣበትን፣ ያለበትን እና የሚሄድበትን ማህበራዊ ፍኖት የሚረዳበት እና የሚገልጽበት (collective sensemaking) ሲሆን የዚያን ማህበረሰብ አባላት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ በመወሰን ረገድ ታላቅ ጉልበት አለው።

iv. በንግግር እና በተግባር ካሉት መገለጫዎች ባሻገር፣ ማንኛውም ማህበረሰባዊ ተረክ የዚያ ማህበረሰብ የእምነት ስርዓቶች እና ዕሴቶች (value systems) ምናባዊ ማከማቻም ነው። ስለሆነም አንድን ማህበረሰባዊ ተረክ ባግባቡ ለመረዳት የዚያን ማህበረሰብ የዕሴት መስረቶችን በጥልቅ መመርመር እና መረዳት ያስፈልጋል።

v. ከዚህ በተቃራኒው፣ ተቋማዊ ተረኮች አንድን የተወሰነ የማህበረሰብ ክፍል ወይም ቡድን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ዓላማዎች በሚጠቅም መልኩ የሚቀረጹ ናቸው። ተቋማዊ ተረኮች፣ ከአሳታፊነት (power with) ይልቅ ገዢነት (power over)፣ ከመደጋገፍ ይልቅ መቃቃር፣ ከጋራ እድገት ይልቅ ራስ ወዳድነት (egoism) ጎልቶ የሚታይባቸው ናቸው።

vi. እንዲህ ዐይነት ተረኮች በህብረተሰቡ ውስጥ የሚኖራቸውን ተቀባይነት ለማጠናከር ሲሉ፣ ሰፋ ያለ ተቀባይነት ያለውን ማህበረሰባዊ ተረክ በመጥለፍ ለራሳቸው ውሱን ዓላማ በሚጠቅም መልኩ ሲያራምዱት ይስተዋላል።

vii. ተረኮች ወደ ግጭት ከሚያመሩበት ዋነኛ ምክንያቶች አንዱ፣ አንደኛው ወገን በራሱ ተረክ በመታበይ የእኔ የሚለውን ተረክ በሌላው ላይ በኃይል ለመጫን በሚሞክርበት ወቅት ነው። ከ1950ዎቹ ጀምሮ፣ በሃገራችን ለተከሰቱት የፖለቲካ ግጭቶች እና የርስ በርስ ጦርነቶች ዋነኛው መነሻም በእንደዚህ አይነት መታበይ የአንድ ወገን ተረክን በሌላው ላይ ለመጫን ከሚደረግ ጥረት ጋር የተያያዘ ነው።

viii. እንዲህ አይነቱን ሁኔታ በሰላማዊ ሂደት መፍታት በማይቻልበት ጊዜ፣ የምህዳሩ በከፍተኛ ቀውስ መናጥ እና ይህንን ተከትሎም ቀውሱን ለመሻገር የሚያስችል የስክነት እና አስተውሎት ተዋናዮች መኖር ሌላኛው አማራጭ (default option) ይሆናል።

ix. በምህዳራዊ አስተሳሰብ መሰረት፣ በማናቸውም ህብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ ተቃራኒ ተረኮችን (conflicting narratives) ወደ ዐይነታዊ የለውጥ ተረክ (transformational narratives) ማምጣት ያንን ማህበረሰብ በዘላቂነት ወደፊት ለማሻገር ቁልፍ እና አይነተኛ እርምጃ ነው።

x. ዓይነታዊ የለውጥ ተረኮችን ለማበልጸግ በስራ ላይ ከሚውሉት መርሆዎች አንዱ እና ዋነኛው፣ በልዩ ልዩ ምክንያት አወዛጋቢ እና አጨቃጫቂ የሆኑ ጉዳዮችን ለቀጣይ ሂደት በማቆየት፣ አብዛኛውን ወገኖች ሊያግባቡ በሚችሉ ዋና ዋና ሰበዞች ላይ ተመርኩዞ የጋራ ሃገራዊ ራዕይ መስረቶችን ማጠናከር ነው።

xi. የብሔራዊ መግባባት ውይይትን ውጤታማ ለማድረግ ቁልፉ መለኪያ አጠቃላይ ሂደቱ ትብብራዊ አስተሳሰብን (collaborative thinking) በሚያጠናክር መልኩ እንዲዋቀር ማድረጉ ላይ ነው። ይህም ሶስት ምዕራፍ ባለው ሂደት ውስጥ ማለፍን ይጠይቃል።

xii. እነኚህም፣ የተለያዩ ሃሳቦችን እና አቋሞችን ምንም ያህል የተቃረኑ (divergent) ቢመስሉም ከልብ ለመስማት እና ለመደማመጥ የሚያስችል ዝግጁነት መፍጠርን፣ ለተቃራኒ አመለካከቶች መነሻ የሆኑ ተጨባጭ እና ግምታዊ ሲጋቶችን ለመረዳት መጣር እና አዲስ እይታ እንዲፈልቅ (emergence) ማድረግ፣ እና በመጨረሻም ለምንፈልገው የፖለቲካ ሥርዓት አስፈላጊ በሆኑ ዋና ዋና መዋቅራዊ መሰረቶች ላይ መግባባትን (convergence) መፍጠር ይሆናል።

xiii. ከዚህ በተጨማሪም፣ ከመወያያ ርዕስ መረጣ እስከ ጽሁፍ ዝግጅት፣ አቀራረብ እና የውይይት አደረጃጀት ድረስ ያሉትን ሂደቶች በጥንቃቄ መተለም እና ማዘጋጀትን ይጠይቃል። የመወያያ ርዕስ መረጣን በሚመለከት ለብሔራዊ መግባባት ውይይት የሚመረጡ ርዕሶች የዲምክራሲያዊ መፎካከሪያ ምህዳሩን ጤናማነት ለማጠናከር አስፈላጊ የሆኑ የመተባበሪያ ርዕሶች ሊሆኑ ይገባቸዋል።

xiv. ከዚህ በተጨማሪ፣ ለብሔራዊ መግባባት ውይይት የሚቀርቡ ጽሁፎች በአንድ ባለሙያ ወይም የፖለቲካ ድርጅት ከሚዘጋጁ ይልቅ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተወከሉ ግለሰቦች በጋራ እንዲያዘጋጁ እና እንዲያቀርቡ ማድረግ ነው። ይህም፣ የተለያየ አመለካከት ባላቸው ወገኖች ሊኖር የሚገባውን የመደማመጥ እና የመተባበር ባህል ያዳብራል።

xv. የመወያያ ጽሁፎቹ ከቀረቡ እና በጽሁፎቹ ላይ ለሚነሱ የማብራሪያ ጥያቄዎች መልስ ከተሰጡ በኋላ የምልዐተ ስብሰባ እና የቡድኖች ውይይት ቅይጥ አካሄድ መከተል ሃሳቦች በደንብ የሚብላሉበትን ሁኔታ ከመፍጠሩም ባሻገር በተሳታፊዎቹ መካከል ሊፈጠር የሚገባውን ግለሰባዊም ሆነ ቡድናዊ መስተጋብር ይበልጥ ስኬታማ እና ጤናማ እየሆነ እንዲሄድ ያደርገዋል።

xvi. ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የአካሄድ መርሆች ባሻገር፣ እንዲህ ዓይነት ጉባዔ ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ፣ ሁሉም ተሳታፊዎች በተናጠልም ሆነ በጋራ ሊያከብሯቸው የሚገቡ መሰረታዊ የሥነምግባር መመሪያዎች መካከል ዋነኛው ሁሉም ተሳታፊዎች ለሀገራቸው እድገት እና ለህዝባቸው ኑሮ መሻሻል ቀና አስተሳሰብ ይዘው የተነሱ ናቸው የሚል ግምት (benefit of the doubt) መስጠት ነው።

xvii. ከዚህ በተጨማሪ፣ በእንዲህ አይነት መድረክ የሚቀርቡ ማናቸውንም ሃሳቦች በሃሳብ መሞገት እንጂ ለምን እንዲህ ተባለ ብሎ ፖለቲካዊ ፍረጃ እና ቅጥያ (Political labelling) ለመስጠት አለመሞከር፤ እና ለብሔራዊ መግባባት የሚደረግ ውይይት ዘላቂ፣ ሃገራዊ እና ህዝባዊ ሰላም እና ልማት ለማረጋገጥ የሚደረግ ውይይት እንጂ ለምርጫ መፎካከሪያ የሚሆን የፖለቲካ ነጥብ ማስቆጠሪያ እንዳልሆነ መተማመን ነው።

# 7. አካታች እና ዘላቂ ልማት

በአንድ ሃገር የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ሥርዓት መካከል ጥብቅ ትስስር መኖሩ በዘርፉ ቀደምት ነው ከሚባለው ከካርል ማርክስ ጀምሮ የነበሩ ዕውቅ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ምሁራን አበክረው ያስገነዘቡት ጉዳይ ነው። ከዚህም የተነሳ፣ ባንድ ሃገር የፖለቲካ ሁኔታ ላይ የሚደረግ የፖለቲካ ምልከታ ኢኖሚውን ሳያካትት የተሟላ ሊሆን አይችልም። በ 1950ዎቹ የተጀመረው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ የተሟላ የፖለቲካ ንቅናቄ መሆን የቻለውም የባላባታዊው ሥርዓት መሰረት የነበረውን የመሬት ለአራሹ ጥያቄ ካነሳበት ጊዜ ጀምሮ ነው። የ1967 የመሬት አዋጅ ይህንን መሰረታዊ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ጥያቄ ከመለሰ ወዲህ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ እጅግ ገኖ የሚታየው የዲሞክራሲ እና የስልጣን ጥያቄ ሆኖ ቆይቷል። ይህም፣ ከነበረው የገዘፈ የዲሞክራሲ ረሃብ እና የመብት ጥሰት አኳያ ተገቢ ነበር ማለት ይቻላል። ያም ሆኖ፣ በተከታታይ መንግሥታት ይወጡ የነበሩ የኢኮኖሚ ልማት ፖሊሲዎች እና እቅዶች በየወቅቱ ለነበረው የፖለቲካ ችግር መባባስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጋቸው አይካድም። በቅርቡ የነበረውን የኢህአዴግ ዘመን የኢኮኖሚ ፖሊሲ እንኳን ብንመለከት በዋነኝነት በስልጣን ላይ ያለው ቡድን የፖለቲካ ዓላማ አገልጋይ እንዲሆን ተደርጎ በመቀረጹ እና በመተግበሩ የሥርዓቱን ተጠቃሚዎች ይበልጥ ሲያበለጽግ የአብዛኛውን ህዝብ የኑሮ መከራ አባብሶታል። በዚህም የተነሳ፣ የበርካታ ሚሊዮን ህዝቦች ህይወት ከመመሰቃቀሉም ባሻገር ፖለቲካዊ መስተጋብሩንም ይበልጥ ሲያወሳስበው ታይቷል። በመሆኑም፣ ኢትዮጵያን ለማሻገር የሚደረገው ጥረት ፖለቲካውን ከኢኮኖሚው ጋር አስተሳስሮ መመልከት ይጠይቃል።

የማንኛውም ዴሞክራሲያዊ መንግስት ታላቁ ፈተና የህዝቦቻቸውን መሰረታዊ ፍላጎት ለማሟላት እና ዘላቂ ደህንነታቸውን (wellbeing) ለማረጋገጥ የሚያስችል የኢኮኖሚ ሥርዓት መገንባት ነው። እንዳለመታደል ሆኖ፣ ኢትዮጵያን ጨምሮ አብዛኞቹ የአፍሪካ ሀገራት ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓትም ሆነ መሰረታዊ የህዝቦችን ፍላጎት የሚያሟላ የኢኮኖሚ ሥርዓት መፍጠር ተቸግረው ኖረዋል። እስካሁን ድረስ ለዘለቀው ኋላ ቀርነታችን ምንጮች እና ለተደረጉ የልማት ጥረቶች ሁሉ መክሸፍ ዋነኛ ምክንያቶችን በተመለከተ፣ በርካታ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ አጥኚዎች እና ተንታኞች የየራሳቸውን ምክንያቶች እና መላ ምቶች ሲሰነዝሩ ኖረዋል። የዚህ ክፍል ዋና ዓላማ፣ ዛሬ ሃገራችን ከምትገኝበት አሳፋሪ የድህነት ደረጃ ለመውጣት እንዴት አካታች እና ዘላቂ ልማት ለማምጣት እንችላለን የሚለውን ለማመላከት ነው። በሃገራችን ውስጥ ልናየው የምንሻውን የኢኮኖሚ ልማት እና እድገት ለማምጣት፣ በዓለም አቀፋዊውም ሆነ በሃገራችን ደረጃ ያሉብንን ዋና ዋና ፈተናዎችን እና እድሎችን በጥልቀት መረዳት የመጀመሪያው ተግባር መሆን ይኖርበታል። በዚህ ላይ ተመርኩዞም በፈተናዎቹ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት መቀነስ ወይንም ማስቀረት እና እድሎቹንም በተቻለ መጠን ለመጠቀም የሚያስችሉ ፖሊሲዊችን መንደፍ እና መተግበር ይጠይቃል።

## 7.1 አጠቃላይ የልማት እና ዕድገት ፈተናዎች

ዛሬ ባለው እጅግ የተሳሰረ የኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ፣ ያንድን ሃገር የልማት እና ዕድገት ፈተናዎች ከዓለም አቀፋዊው ሁኔታ ነጥሎ ማየት የማይቻል ነው። በመሆኑም፣ አብዛኞቹ በማደግ ላይ ያሉ ሃገሮች ዋነኛ የልማት እና ዕድገት ፈተናዎቻቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚታዩ አበይት ፈተናዎች ጋር በጥብቅ የተሳሰሩ ናቸው። ስለዚህም፣ በቀዳሚነት አሁን በምንገኝበት ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን በማንኛውም ሃገር የኢኮኖሚ እድገት እና ልማት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖዎች ሊያሳድሩ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱትን ዓለም አቀፋዊ ወሳኝ ክስተቶች ከሃገራችን ልዩ ሁኔታ ጋር አዛምደን በመመልከት እንጀምራለን። በዚህ ረገድ፣ ምንም እንኳን በርካታ ጉዳዮች ሊነሱ ቢችሉም፣ በዚህ ፀሃፊ እምነት አካታች እና ዘላቂ ልማትን ሊያደናቅፉ ከሚችሉ ፈተናዎች መካከል የሚከተሉት ዋነኞቹ ናቸው።

***የዓለም ሙቀት መጨመር*** (Global warming)፡ በሃያኛው ክፍለ ዘመን ለተመዘገበው እጅግ ፈጣን ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካደረጉት የቴክኖሎጂ ለውጦች አንዱ ታዳሽ ባልሆኑ የኃይል ምንጮች አጠቃቀም ላይ የታየው ከፍተኛ እድገት ነው። ከዚህ ውስጥ ዋነኛው የቸግር ምንጭ፣ ከፋብሪካዎች እና የመጓጓዣ አገልግሎት መስፋፋት ጋር ተያይዞ ፍጆታው በከፍተኛ ደረጃ የጨመረው የቅሪተ አካላት ነዳጅ (fossil fuels) አጠቃቀም ነው። ይህም፣ በከባቢ አየር ውስጥ ሊኖር የሚገባውን የካርቦን ጭስ መጠን በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምር በማድረጉ የተነሳ የዓለማችንን የሙቀት መጠን መጨመርን አስከትሏል። በዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ የሳይንቲስቶች (International Panel on Climate Change) ቡድን ጥናት መሰረት፣ የዓለማችን ሙቀት መጠን በቅድመ ኢንዱስትሪ አብዮት ከነበረው በሁለት ዲግሪ ሴንቲግሬድ ከጨመረ ተመልሶ ሊተካ የማይችል (irreversible) ከፍተኛ የተፈጥሮ አካባቢ ውድመት ሊያደርስ እንደሚችል ተረጋግጧል። በ2008 በፓሪስ ከተማ በተደረገው ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ((climate change) ስምምነት አማካኝነት፣ በአሁኑ ወቅት፣ መላው የዓለም ህብረተሰብ እንዲህ አይነቱ ጥፋት እንዳይከሰት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል። ይህ ጥረት እንዳለ ሆኖ፣ እስካሁን ድረስ በተፈጠረው የዓለም የከባቢ አየር ሙቀት መጨመር የተነሳ ሃገራችንን ጨምሮ በርካታ ሃገሮች ተለዋዋጭ ለሆነ የከባቢ አየር ሁኔታ መለዋወጥ (climate variability) በመጋለጥ ላይ ይገኛሉ። ለዚህም፣ በቅርቡ በሃገራችን የተከሰቱትን የጎርፍ እና የድርቅ አደጋዎች መመልከቱ በቂ ማረጋገጫ ነው።

የአሜሪካኑን ብሔራዊ የበረራ እና የሕዋ አስተዳደርን (National Aeronautics and Space Administration) ጨምሮ በርካታ የሳይንስ ጥናት ማዕከሎች እንዳመላከቱት ከሆነ፣ በመጪዎቹ አስርተ ዓመታቶች እነኚህ የተፈጥሮ አደጋዎች በድግግሞሽ መጠንም ሆነ በሚያስከትሉት ጉዳት ይበልጥ ጠንካራ እየሆኑ ሊሄዱ እንደሚችሉ ተገምቷል። ምንም እንኳን እስከ ዛሬ ድረስ ላለው የዓለም ሙቀት መጨመር ችግር የነበራቸው አስተዋጽኦ ዝቅተኛ ቢሆንም፣ ይህ ሁኔታ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በማደግ ላይ የሚገኙ ሃገሮችን ይበልጥ የጉዳቱ ተጠቂ ከማድረጉም በላይ የልማት ጥረታቸውንም ይበልጥ ፈታኝ

እንደሚያደርግባቸው ይጠበቃል። በመሆኑም፣ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሃገሮች የሚያወጧቸው ብሔራዊም ሆነ የዘርፍ የልማት ፖሊሲዎች የአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖን መቋቋም የሚችል (climate resilient) እድገት ለማምጣት በሚያስችል መንገድ መቅረጽ እና መተግበራቸው አካታች እና ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ በጣም አስፈላጊ ነው።

***የተፈጥሮ ሃብት መመናመን*** (Natural resource depletion)፡ በዓለም አቀፍ የሳይንቲስቶች የተፈጥሮ ሃብት ጥናት ቡድን (International Respurce Panel) መሰረት፣ በሃያኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ ብቻ ከተፈጥሮ አካባቢያችን የወሰድነው አጠቃላይ የተፈጥሮ ሃብት በስምንት እጥፍ ሲያድግ፣ እ.ኤ.አ. በ1900 ሰባት ቢሊዮን ቶን የነበረው በ2010 ወደ 60 ቢሊዮን ቶን አድጓል። እስከዛሬ በመጣንበት መንገድ ከቀጠልን፣ እ.አ.አ. በ2050 አንድ መቶ አርባ ቢሊዮን ቶን እንደሚደርስ ይገመታል። ከዚህ ጋር ተያይዞ በደረሰው የተፈጥሮ ሃብት መመናመን የተነሳ፣ ከ1970 እስከ 2010 በነበሩት አርባ ዓመታት ውስጥ ብቻ የዓለማችን የብዝሃ ህይወት መለኪያ (Living planet index) በሃምሳ ሁለት በመቶ ቀንሷል። ይህ ከዚህ በላይ የተጠቀሰው የተፈጥሮ ሃብት መመናመን፣ የምድራችን ውሃን ጨምሮ፣ እያደገ የሚሄደውን የዓለም ህዝብ የተፈጥሮ ሃብት ፍላጎት ማሟላት ወደ ማይችልበት ደረጃ አድርሷታል። ከዚህ በተጨማሪ፣ ይኸው የተፈጥሮ ሃብት መመናመን ባሁኑ ሰዓት ዓለማችንን ከዳር እስከዳር ያንበረከከው የኮሮና ወረርሽኝ ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላፍበትን ሁኔታም አመቻችቷል።

ሁኔታዎች በመሰረታዊነት ካልተቀየሩ፣ እንዲህ ላይነቱ አደጋ በመጪዎቹ ዐስርተ ዓመታት እየጨመረ ሊሄድ እንደሚችል ተገምቷል። የተፈጥሮ ሃብት መመናመንም ሆነ የወረርሽኝ በሽታዎች መከሰት እንደ ኢትዮጵያ ላሉ በማደግ ላይ ላሉ እና ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር እድገት ለሚታይባቸው ሃገሮች በጣም ፈታኝ እንደሚሆንባቸው ይጠበቃል። የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም ባወጣው የ2020 የሰብዓዊ ልማት ዕድገት ሪፖርት መሰረት ኢትዮጵያ ባሁኑ ወቅት አላት ተብሎ ከሚገመተው ታዳሽ የተፈጥሮ ሃብት አቅም (bio-capacity) 99.7% በመጠቀም ላይ ትገኛለች። ይህ የሚያመላክተው የሃገሪቱ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃላይ የመሸከም አቅምን (carrying capacity) ሙሉ ለሙሉ በመጠቀማችን፣ ተጨማሪ ጫና ለማስተናገድ ያለን ቀሪ አቅም ዜሮ መሆኑን ነው። ስለዚህም፣ ሃገሪቱ የምትተገብራቸው የልማት እቅዶች በሙሉ፣ የሃገሪቱን የተፈጥሮ ሃብት መሰረት (ecological foundation) ይበልጥ የሚያጠናክሩ፣ ምርታማ የሆነ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምን (resource efficiency) የሚያረጋግጡ፣ እና የሃገሪቱን ብዝሐ ህይወት የሚያበራክቱ ሊሆኑ ይገባል።

***የህዝብ ብዛት ጫና*** (Population pressure): በህዝብ ብዛት እና በተፈጥሮ አካባቢ መካከል ያለው ያልተቋረጠ መስተጋብር ዓለማችን ዛሬ ያለውን ገጽታ እንዲይዝ በማደረጉ በኩል ከፍተኛውን አስተዋጽኦ እንዳደረገ ይታመናል። ይህም፣ ሁለት አበይት ምዕራፎችን የያዘ ነው። የመጀመሪያው፣ በርካታ ሺዎች ዓመታትን የሚሸፍነው የቅድመ ታሪክ ዘመን ሲሆን የዚህም ዋነኛው መለያ በአንድ አካባቢ ያለው የተፈጥሮ ሃብት ሲመናመን ወደ አልተነካ ለም አካባቢ (green pasture) መነቃነቅ ነው። ይህ ከተራቆተ

ወደ ለም አካባቢ መነቃነቅ (mobility) ዛሬም ቢሆን ከተፈጥሮ አካባቢ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ባላቸው ማህበረሰቦች የሚተገበር ዑደት ነው። ይህ ዑደት፣ ዛሬ ያለውን የዓለማችንን የህዝቦች አሰፋፈር ገጽታ ሊሰጠን ችሏል።

የሁለተኛው ምዕራፍ ዋነኛው መለያ፣ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ከመነቃነቅ ይልቅ በዕውቀት ላይ የተመረኮዙ ግብአቶችን (intensification) በመጠቀም ከአንድ የተፈጥሮ ምህዳር ሊገኝ የሚችለውን ምርት ማሳደግ እና እጥረትን እና መመናመንን መቋቋም ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞም የተገኘው የተሻለ ምርት እና የአኗኗር ዘይቤ መቀየር ለመጀሪያው ዙር የህዝብ ብዛት እድገት አስተዋጽኦ አድርጓል። ከኢንዱስትሪ አብዮት ጋር ተያይዞም የዓለማችን የህዝብ ብዛት በከፍተኛ መጠን አድጓል። በተለይም ከሃያኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አንስቶ የዓለማችን የህዝብ ብዛት በብዙ እጥፍ አድጎ እ.አ.አ. በ2019 7.7 ቢሊዮን ሲደርስ፣ ይኸው ቁጥር እ.ኤ.አ. በ2030 8.5 ቢሊዮን እንዲሁም እ.አ.አ. በ2050 ወደ 9.7 ቢሊዮን እንደሚደርስ ተገምቷል። በተመሳሳዩ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት እ.አ.አ. በ 2017፣ 105 ሚሊዮን እንደነበረ የሚገመት ሲሆን፣ ይህ ቁጥር እ.ኤ.አ. በ 2050 190 ሚሊዮን እና እ.አ.አ. በ 2100 ደግሞ 250 ሚሊዮን እንደሚደርስ ተገምቷል። ይህንን ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር እድገት ግምት ውስጥ ያስገባ የልማት ራዕይ ማበልጸግ የሃገሪቱን ልማት ዘላቂነት ለማረጋገጥ ወሳኝ ነው።

***አራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት*** (Fourth industrial revolution-4IR)፦ የሰው ልጅ የመጀመሪያውን የእደን መሳሪያ ከፈጠረበት ጊዜ አንስቶ የተለያዩ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን በመፍጠር የራሱን ህይወት እና አካባቢውን ሲቀይር መጥቷል። በተለይም፣ የመጀመሪያው የኢንዱስትሪ አብዮት መሰረት የሆነው የእንፋሎት ሞተር (steam engine) ከተፈጠረበት ጊዜ አንስቶ ዐለማችንን በተለያዩ ሁለት ተከታታይ የኢንዱስትሪ አብዮቶች ውስጥ ያሳለፉ ቁልፍ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ነበሩ። አሳዛኙ እውነታ፣ ሃገራችን ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ በማደግ ላይ የሚገኙ ሃገሮች ያለፉት ሶስት የኢንዱስትሪ አብዮቶች በተሳታፊነት ሳይሆን በበዪ ተመልካችነት ማሳለፋቸው ነው።

በአሁኑ ወቅት ዓለማችን የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ዋነኛ መለያ ወደሆነው አራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት በመገስገስ ላይ ይገኛል። የዚህም ዋነኛው መሪ ኃይል በመረጃ እና ተግባቦት (information and communication) ዘርፍ እየተካሄደ ያለው እጅግ ፈጣን የቴክኖሎጂ እድገት ነው። ይህ ፈጣን እድገት እስካሁን ድረስ የነበረውን የአመራረት እና የፍጆታ (production and consumption) አደረጃጀት በመሰረታዊ መልኩ ሊቀይረው እንደሚችል ይገመታል። ከዚህ ጋር ተያይዞም፣ ለሁሉም ሃገሮች በርካታ ፈተናዎች እና እድሎችን ይዞ እንደሚመጣ ይጠበቃል። ከመልካም ገጽታዎቹ አንዱ፣ አራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ባለው ልዩ መረጃን እና ዕውቀትን ለሁሉም ተደራሽ (democratize) የማድረግ አቅሙ የተነሳ ቀደም ሲል ከነበሩት የኢንዱስትሪ አብዮቶች በተለየ መልኩ ለሁሉም ሃገሮች የተሻለ ተጠቃሚነት በር መክፈቱ ነው።

ስለሆነም፣ ሃገራችን ኢትዮጵያ ከዚህ የኢንዱስትሪ አብዮት የበዩ ተመካችነት እንድትድን ከተፈለገ የትኛውንም የኢኮኖሚ ዘርፍ ለማሳደግ የሚወጡ ፖሊሲዎች እና ስልቶች፣ የአራተኛውን የኢንዱስትሪ አብዮት ፈተናዎችን በሚቀንስ እና እድሎቹን በሚያሰፋ መልኩ ሊቀረጹ እና ሊተገበሩ ይገባል።

***ሉላዊነት*** (Globalization)**፦** ዛሬ ባለንበት ሁኔታ ስለሉላዊነት በምንነጋገርበት ጊዜ፣ በሚከተሉት ሁለት አይነት ሉላዊነት መሃል ያለውን ልዩነት እና አንድነት መረዳት ይጠቅማል። የመጀመሪያው እና በሃያኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ከታዩት ዓለም አቀፋዊ ክስተቶች አንዱ እና ዋነኛው፣ በዓለም አቀፍ የገንዘብ፣ የፋይናንስ እና የንግድ ተቋማት አማካኝነት የተራመደው የኢኮኖሚ ሉላዊነት ነው። ይህ በነጻ ገበያ የኢኮኖሚ አስተሳሰብ የተቃኘው ሉላዊነት በአብዛኛው የበለጸጉ ሃገሮችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን በሚያረጋግጥ መልኩ ተቀርጾ የተተገበረ ነው። ለዚህም፣ እ.ኤ.አ. ከ 1970ዎቹ መጨረሻ አንስቶ በመላው ዓለም የሚገኙ በማደግ ላይ ያሉ ሃገሮች በግዴታ እንዲተገብሯቸው የተደረጉትን የመዋቅራዊ ማሻሻያ ፕሮግራሞችን (structural adjustment programmes) እና ያስከተሏቸውን መጠነ ሰፊ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ እና አካባቢያዊ ቀውሶች መመልከቱ በቂ ነው። ይህ አካሄድ አሁንም ሰወር ባለ (subtle) መልኩ የቀጠለ በመሆኑ፣ እንደኢትዮጵያ ያሉ ሃገሮች ተገቢውን የፖሊሲ ጥንቃቄ ሊያደርጉ ይገባል።

ሁለተኛው ሉላዊነት፣ ከመረጃ እና ተግባቦት ቴክኖሎጂ እድገት ጋር ተያይዞ የመጣው የዕውቀት እና መረጃ ሉላዊነት ነው። ምንም እንኳን ይህ ዓይነቱ ሉላዊነት፣ በመሰረታዊ ባህሪው ዕውቀት እና መረጃ ለሁሉም ሊዳረስ የሚችልበትን ሁኔታ የሚፈጥር ቢሆንም፣ የመረጃውንም ሆነ የዕውቀቱን ፍሰት በመቆጣጠር የግል ብልጽግናቸውን ወይም ያላቸውን የበላይነት ለማስጠበቅ በሚሹ ወገኖች የመጠለፍ እድሉ ከፍተኛ ነው። ስለዚህም፣ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሃገሮች ከዕውቀት እና መረጃ ሉላዊነት የሚገኘውን መልካም እድሎች ለሃገሮቻቸው አካታች እና ዘላቂ ልማት እንዲያገለግሉ የሚስችሉ በብልህነት ላይ የተመሰረቱ ፖሊሲዎችን (smart policies) መቅረጽና መተግበር ይኖርባቸዋል።

## 7.2 ብሔራዊ ፈተናዎቻችን እና መፍትሄዎቻቸው

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ዓለም አቀፋዊ ቅርጽ እና ይዘት ካላቸው ፈተናዎች በተጨማሪ፣ ከሀገራዊው ልዩ ሁኔታዎች ጋር የሚያያዙ ፈተናዎች አሉ። እነኚህን ፈተናዎች በአግባቡ ለይቶ መረዳት እና መፍትሄ መሻት ከዓለም አቀፋዊው ፈተናዎች ሊደርሱ የሚችሉ ተጽእኖዎችን ለመቋቋምም ሆነ ወደ አካታች እና ዘላቂ ልማት የሚደረገውን ግስጋሴ ለማፋጠን አቢይ ድርሻ ይኖረዋል። በዚህ ረገድ ሊነሱ ከሚችሉ በርካታ ፈተናዎች እና መፍትሄዎቻቸው መካከል የሚከተሉትን በአበይትነት መጥቀስ ይቻላል።

***የሁለንተናዊ ደህንነት ኢኮኖሚ*** (Wellbeing Economy) ***ፖሊሲ***፡ አትዮጵያን ጨምሮ አብዛኞቹ የአፍሪካ ሃገሮች ባላፉት በርካታ ዐስርተ ዓመታት የተገበሯቸው የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች በተሳሳቱ (misguided) ቅኝቶች ላይ የተመረኮዙ በመሆናቸው የህዝቦቻቸውን ኑሮ ከዕለት ወደ ዕለት ለባሰ ድህነት እና ጉስቁልና እያጋለጡ በመሄድ ላይ ይገኛሉ። በዓለም አቀፍ ደረጃ ከነበረው የኢኮኖሚም ሆነ የፖለቲካ የኃይል አሰላላፍ አኳያ የእነኚህ ሃገሮች ፖሊሲዎች በምዕራባውያን ሃገሮች ሲራመድ በነበረው የነጻ ገበያ የኢኮኖሚ ሥርዓት እና በሶሻሊስቱ ዓለም በተራመደው የተማከለ የኢኮኖሚ ሥርዓት መሃል መዋዠቁ ብዙም የሚያስገርም ላይሆን ይችላል። ትልቁ ችግር የሚመነጨው የቀረበላቸውን የኢኮኖሚ ፖሊሲ አማራጭ ከሃገራዊው ልዩ ፍላጎት እና ጥቅም ጋር ሳያጣጥሙ በጅምላ ወስደው ለመተግበር መሞከራቸው ነው።

ከዚህ በተጨማሪም፣ የፖሊሲ አማራጮቹ የሚመዘኑበት ዋነኛው መለኪያ የህዝቦችን የኑሮ ሁለንተናዊ ደህንነት (wellbeing) ለማሻሻል በሚኖራቸው አስተዋጽኦ ሳይሆን በስልጣን ላይ ላለው ቡድን ፖለቲካዊ ዓላማዎች መሳካት በሚያበረክቱት ድርሻ መሆኑ ነው። በዚህም የተነሳ፣ በአንድ ታዋቂ ፓን አፍሪካዊ ምሁር እንደተባለው፣ ብዙዎቹ የአፍሪካ ሃገሮች የሚያራምዷቸው የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች በምትሃታዊ የኢኮኖሚ ፍልስፍና (Voodoo economics) የተቃኙ አስመስሏቸዋል[35]። ከዚህ አይነት አዙሪት ለመውጣት፣ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሃገሮች የህዝቦችን መሰረታዊ የኑሮ ዋስትና የሚያረጋግጡ እና ሃገራዊ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ የሁለንተናዊ ደህንነት ኢኮኖሚ (Wellebing economy) ፖሊሲዎችን ለመቅረጽና ለመተግበር መጣር ይኖርባቸዋል። የዚህም አንዱ እና ዋነኛው መገለጫ፣ ከውጭ ቀጥተኛ መዋዕለ ንዋይ (Foreign direct investment) በበለጠ፣ ሀገራዊውን የተፈጥሮ ሃብት (natural resource) እና የሰው ኃይል (human capital) እንደ ዋነኛው የአካታች እና ዘላቂ ልማት አንቀሳቃሽ አድርጎ መውሰድ እና ይህንን በዘመኑ የዕውቀት እና የቴክኖሎጂ ግብአቶች ማበልፀግ እና ጥቅም ላይ ማዋል ነው።

[35] በዚህ ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት https://teifaiq.com/2020/09/07/from-voodoo-economics-to-a-well-being-economy-africas-choice/ ይጎብኙ።

***የሸመና[36] እቅድ*** (discusiive planning)፡ ከላይ ለተጠቀሰው ‘ምትሃታዊ የኢኮኖሚ ፖሊሲ’ አንዱ መገለጫው ተግባራዊነታቸው በአብዛኛው አጠያያቂ የሆኑ ዓመታዊ፣ የአምስት ዐመት እና አንዳንድ ጊዜም የአስር ዓመት እቅድ የሚመስሉ ‘ያልታቀዱ እቅዶችን’ (unplanned planning) ማውጣታቸው ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ፣ የብዙ የአፍሪካ ሃገሮች ከፍተኛ የልማት ፈተና አብዛኛውን የሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ በእርዳታ የሚገኝ ሃብት ባግባቡ ባልታቀዱ ‘የልማት’ እቅዶች አማካይነት ስራ ላይ በማዋል የሚፈጥሩት የሃብት ብክነት ነው። ለዚህም፣ በሥልጣን ላይ ያለው ቡድን አስቦበት የተወሰኑ የፖለቲካ ቡድን አባሎችን እና ደጋፊ ወገኖችን ለመጥቀም ከሚፈጽማቸው ተግባራት ባሻገር የሚከተሉት ሁለት ችግሮች በአበይት ምክንያትነት ይጠቀሳሉ። የመጀመሪያው፣ መሬት ላይ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታም ሆነ የህዝብን መሰረታዊ ፍላጎት ባላካተተ መልኩ ከላይ ወደ ታች በሚወርድ እቅድ (top-down planning) አማካይነት ልማትን ለማምጣት መሞከር ነው። ለዚህም፣ እዚሁ በሃገራችን በርካታ መከነው የቀሩ ወይንም የሚፈለገውን ያህል ውጤት ያላመጡ የልማት ፕሮጀክቶችን መዘርዘር ይቻላል።

ሁለተኛው ያልታቀደ ዕቅድ ችግር የሚመነጨው በተለያዩ የዘርፍ መስሪያ ቤቶች በሚወጡ እርስ በእርስ ባልተናበቡ እና ባልተቀናጁ (fragmented) የልማት እቅዶች ምክንያት የሚፈጠር የሀብት ብክነት እና ውድመት ችግር ነው። ይህ፣ በተለይም የከተሞችን እና የኢንዱስትሪ መሠረተ ልማት ለመገንባት በሚወጡ እቅዶች ላይ ጎልቶ የሚታይ ችግር ነው። እነኚህን ችግሮች ለማወስገድ፣ ከላይ ወደ ታች የሚወርድ አመላካች ዕቅድን (indicative planning) ከታች ወደላይ ከሚመነብ እና ህዝብን ካካተተ የአፈጻጸም ዕቅድ (operational planning) ጋር ማዋሃድ አካታች እና ዘላቂ የሆነ ልማት ለማውጣት እጅግ አስፈላጊ ነው። እንዲህ ዓይነቱ የዕቅድ አወጣጥ እና አፈጻጸም ‘የሸመና እቅድ’ (discusrive planning) ተብሎ ይታወቃል።

***ዘላቂ የልማት አስተዳደር*** (sustainable development governance): አጠቃላይ የመልካም አስተዳደር (good governance) እጦት፣ ኢትዮጵያን ጨምሮ፣ የብዙዎቹ በማደግ ላይ ያሉ ሃገሮች ችግር መሆኑ ተደጋግሞ የተነገረ ነው። ይህንን የመልካም አስተዳደር ችግር ለመፍታትም፣ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓት መገንባት እና የህግ የበላይነትን ማስከበር እንደ ዋነኛ የመፍትሔ አቅጣጫዎች ተደርገው ይጠቆማሉ። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አካታች እና ዘላቂ ልማትን ለማምጣት ተጨማሪ የልማት መልካም አስተዳደር እርምጃዎችን መመልከት ተገቢ ይሆናል። ለዚህም የመጀመሪያው መነሻ፣ የሃገሪቱ የልማት ጥረት መሰረታዊ ግብ፣ ጥቅል ሃገራዊ ምርትን (Gross Doemstic Product (GDP)) እና የነፍስ ወከፍ ገቢን (per capita income) ከማሳደግ ባሻገር፣ የህዝቦችን ሁለንተናዊ የኑሮ ሁለንተናዊ ደህንነት (wellbeing) ማረጋገጥ ሊሆን ይገባዋል።

[36] የሸመና ስራ ድር እና ማጉን አንዴ ወደ ላይ ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደታች በሚደረግ የማያቋርጥ እንቅስቃሴ ሂደት ውስጥ በማስተሳሰር ያማረ ሸማ ወይንም ጥበብ እንደሚያወጣው ሁሉ discusrive ለሚለው የእግሊዝኛ ቃል የሚመጥን ሆኖ ተገኝቷል።

ከዚህ በተጨማሪም፣ በአንድ ሃገር ህዝብ ውስጥ ያለውን የማህበራዊ ንዋይ (social capital) መሰረት በጥልቀት መረዳት እና ይህንንም ባግባቡ ለማነቃነቅ እና ለመጠቀም መቻል እንደዋነኛ የልማት አካሄድ መተግበር ያስፈልጋል። ይህንን ለማድረግም፣ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚገኙ የሃገር በቀል እውቀቶችን እና የስውሩ ኢኮኖሚ (informal economy) አሰራሮችን ከነተያያዥ መረቦቻቸው (networks) መረዳት እና ለልማት ማነቃነቅ ይጠይቃል።

እንዲህ ዓይነቱ የልማት አስተዳደር፣ በተወሰኑ ከተሞች አካባቢ ከሚከማቹ የኢንዱስትሪ እና ልማት ማዕከሎች ባሻገር ለበርካቶች የስራ ዕድል እና የኑሮ ዋስትና ሊሰጡ የሚችሉ እና ከየአካባቢው የተፈጥሮ ሃብት እና መሰረታዊ ፍላጎት ጋር የተስማሙ፣ ያልተከማቹ፣ ነገር ግን እርስ በእርስ የተሳሰሩ የኢኮኖሚ መረቦች (distributed economy networks) እንዲስፋፉ ያደርጋል። ይህንን በማድረግም፣ ፍትሃዊ የሆነ የልማት ተደራሽነትን ከማረጋገጥም በላይ በየአካባቢው ባለ የተፈጥሮ ሃብት ላይ የሚደርሱ የልማት ተጽእኖዎችን ባካባቢው የተፈጥሮ ሃብት የመሸከም እና የማዋሃድ አቅም (carrying and assimilation capacity) ክልል እንዲስተናገድ ማድረግ ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪም፣ በበርካታ የአፍሪካ ሀገሮች እንደሚታየው፣ በከፍተኛ የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ተገንብተው ከአካባቢያዊም (local) ሆነ ከብሔራዊ ኢኮኖሚ ጋር በጣም ዝቅተኛ ትስስር ያላቸው የውጭ ኢንቬስተር ግዛቶች (enclaves) ሊያደርሱት የሚችሉትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና አካባቢያዊ ጉዳቶች መቀነስ ያስችላል።

***ዘመነኛ ክህሎት (skill-sets) ማዳበር:*** ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ኢኮኖሚ ዋነኛው መለያ ከምንጊዜውም በላይ በዕውቀት እና መረጃ የበላይነት የሚወሰን መሆኑ ነው። በእንዲህ ዓይነት ኢኮኖሚ ውስጥ አሸናፊ ሆኖ ለመገኘት ለዘመኑ የሚመጥን ክህሎትን ያለማቋረጥ ማዳበር እና ማበልጸግ ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ፣ የሚከተሉትን አበይት ነጥቦች መስረት በማድረግ የኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት በእጅጉ ሊፈተሽ እና ሊሻሻል ይገባዋል። የመጀመሪያው፣ ከአፀደ ህፃናት እስከ ሁለተኛ ደረጃ ባሉ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያልፉ ተማሪዎች አካባቢያቸውን በደንብ እንዲረዱ እና የምክንያታዊነት አስተሳሰብን (critical thinking) እንዲያዳብሩ የሚያስችል የትምህርት አሰጣጥ ሥርዓትን መተግበር ነው። ይህንን ተመርኩዞም፣ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ውስብስብ ችግሮችን በልዕለ-ዘርፍ ሳይንስ ዘዴ (transdisciplinary methodlogy) ተንትኖ ለመረዳት እና በምህዳራዊ አስተሳሰብ (systems thinking) ላይ የተመረኮዙ መፍትሔዎችን ለማፍለቅ የሚያስችላቸውን ክህሎት እንዲያዳብሩ ማድረግ ተገቢ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም፣ በአራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት አማካኝነት የሚፈጠሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በደንብ ተረድቶ ለአካታች እና ዘላቂ ልማት ማዋል የሚያስችለውን የሙያ እና የቴክኒክ ክህሎት ማዳበር ያስፈልጋል። ይህንን በማድረግ ሂደት ውስጥ፣ ከሀገር በቀል ዕውቀት ሊወሰዱ የሚችሉ ጠቃሚ አስተሳሰቦች እና ሂደቶች ለመማር እና ይህንንም ከዘመናዊው የዕውቀት መስኮች ጋር በማጣጣም ሃገራዊ እና አካባቢያዊ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ መፍትሔዎች ማመንጨት እና መተግበር ሊበረታታ ይገባዋል። በጥቅሉ፣ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመንን በአሸናፊነት ለመሻገር ሉላዊ የሆነውን የዕውቀት እና የመረጃ ፍሰት ሃገራዊ ከሆነው ልዩ ሁኔታ እና ፍላጎት ጋር በማዋሃድ ለመጠቀም እና ለመተግበር መዘጋጀት እጅግ አስፈላጊ ነው።

## *7.3 የዘላቂ ልማት ዕድሎቻችን*

ቀደም ሲል በነበረው ክፍል ለማሳየት እንደተሞከረው፣ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ ዓለማችን በርካታ ውስብስብ እና ተደራራቢ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊ እና ፖለቲካዊ ፈተናዎች በመጋፈጥ ላይ ትገኛለች። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በማደግ ላይ የሚገኙ ሃገሮች፣ የእነኚህ ዓለም አቀፍ ፈተናዎች ዋነኛ ገፈት ቀማሾች እንደሚሆኑ ይገመታል። በሌላ በኩል ግን፣ ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ የአፍሪካ ሃገሮች ያሉበትን ልዩ አስቸጋሪ ሁኔታ ወደ መልካም አጋጣሚዎች እና ዕድሎች (opportunities) ለመቀየር የሚችሉበት ሁኔታ አሏቸው። በዚህ ክፍል ውስጥ፣ ከነዚህ መልካም አጋጣሚዎች በተለይ ለአካታች እና ዘላቂ ልማት አጋዥ ሊሆኑ የሚችሉትን ዋና ዋናዎቹን ለመመልከት እንሞክራለን።

***ተፈጥሮአዊ የማገገም አቅም*** (natural resilience)፦ በ2020 የተባበሩት መንግሥታት ሰብዓዊ ልማት ሪፖርት እንደተመለከተው፣ ሃገራችን ኢትዮጵያ ያላትን ህያው የተፈጥሮ ሃብት አቅም (bio capacity) ሙሉ በሙሉ የተጠቀመችበት ደረጃ ላይ ደርሳለች። ይህም፣ እስከዛሬ በመጣንበት የአመራረት እና የፍጆታ (production and consumption) ሥርዓት ከቀጠልን ዋናውን የተፈጥሮ ሃብት ካፒታላችንን እያመናመን የራሳችንንም ሆነ የተተኪውን ትውልድ የኑሮ ዋስትና እናወድማለን ማለት ነው[37]። በሌላ በኩል ግን፣ ኢትዮጵያ ሃገራችን በዓለም ውስጥ ከሚገኙ በጣም ጥቂት ከፍተኛ የተፈጥሮአዊ ምህዳር፣ የእንስሳት እና የዕፅዋት ሃብት ብዝሃነት ከሚታይባቸው ሃገሮች ውስጥ ትመደባለች። እንዲህ ዓይነቱ ዘርፈ ብዙ የሆነ የብዝሃነት ሃብት የሃገሪቱ የተፈጥሮ ሃብት መሰረት ከፍተኛ የማገገም አቅም (resilience) እንዲኖረው ያደርገዋል። ለዚህም ማረጋገጫው፣ ከዚህ በፊት ሙሉ ለሙሉ ጠፍተው ወይንም ተራቁተው የነበሩ የተፈጥሮ ምህዳሮች ተገቢው ትኩረት ሲሰጣቸው እና እንክብካቤ ሲደረግላቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ ተመልሰው የቀድሞ ገጽታቸውን መያዛቸው ነው።

ስለዚህም፣ የማናቸውም የልማት ፍላጎታችን መሟላት ዋነኛ መሰረት የሆነውን የተፈጥሮ አካባቢያችንን መንከባከብ እና ማልማት ከህጻንነት ጀምሮ የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ባህል እንዲሆን ማድረግ የሁሉንም ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ አካታች እና ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ ዋነኛው ዋስትናችን ነው። ይህንን በማድረግም፣ ቁጥሩ እጅግ እያደገ የሚሄደውን ህዝብ የምግብ ዋስትና ከማረጋገጥም በላይ፣ በተለይ በገጠር ተንሰራፍቶ ያለውን ድህነት ለመቀነስ ከፍተኛ መሰረት ይሆናል።

[37] በሌላ አገላለጽ፣ ቋሚ ንብረት ላይ እና ባንክ ውስጥ ቆጥበን ያስቀመጥነው ካፒታል በሚሰጠን ትርፍ እና ወለድ ከመኖር ይልቅ ዋናውን ካፒታል እየበላን የኑሮ ዋስትናችንን እናጣለን ማለት ነው።

**ዓይነታዊ እመርታ** (Transformational leapfrogging)፡ ኢትዮጵያን ጨምሮ፣ ያብዛኞቹ የአፍሪካ ሃገሮች ፈተና ከምዕራባዊው ዓለም የሚጫንባቸውን ማንኛቸውም አስተሳሰቦች፣ ልማዶች፣ እና ቴክኖሎጂዎችን ያለአንዳች ሃገራዊ ምልከታ እና ለውጥ (adaptation) እንዳሉ መቀበላቸው እና ለመጠቀም መሞከራቸው ነው። እንዲህ አይነቱ አካሄድ ከሚፈጥረው የአስተሳሰብ ጥገኝነት ባሻገር ሃገሮቹን ጊዜው ያለፈባቸው ቴክኖሎጂዎች ማራገፊያ በማድረግ ከፍተኛ ሃገራዊ ጉዳት ያስከትላል። ለምሳሌም ያህል፣ እንደ እ.አ.አ ከ1990ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ ውጤታማ ያልሆነውን እና ኋላቀር ተደርጎ የተወሰደውን ቆሻሻን በማቃጠል (incineration) ሃይል የማመንጨት ቴክኖሎጂ በቅርቡ ወደሃገራችን በማስገባት እንደ አዲስ እና ንጹህ ቴክኖሎጂ ለማቅረብ የተደረገው ሙከራ ሊጠቀስ ይቻላል[38]።

ከዚህ በተጨማሪ፣ ከ65000 ሜጋዋት በላይ የሆነ የኤሌክትሪክ ኃይልን ከታዳሽ የኃይል ምንጮች ማመንጨት የምትችል ሃገራችን የኑክሊየር የኃይል ማመንጫ መገንባት የሚያስችል ስምምነት መፈራረሟ መሰማቱ የሚያስገርም ብቻ ሳይሆን የሚያስደነግጥም ነው ። በአራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ዘመን እንዲህ አይነት የተዛቡ የቴክኖሎጂ መረጣ እና ሽግግር ውሳኔዎች ከፍተኛ ዋጋ ከማስከፈላቸውም በላይ የሃገሪቱን ዘላቂ ልማት እድሎች ሊያጠቡ ይችላሉ። ይህን መሰል አደጋዎች ለመቀነስ እና ለማስወገድ፣ ወደ እኛ የሚጎርፉ ማንኛውንም የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በጭፍን የአጋጣሚ እመርታ (incidental leapfrogging) ተቀብሎ ከማስተናገድ ይልቅ በዕውቀት ላይ በተመረኮዘ የዓይነታዊ እመርታ መርሆዎች መሰረት ማንኛውንም ቴክኖሎጂን ለሃገሪቱ ልዩ ሁኔታ እና ዘላቂ ልማት ግቦች በሚስማማ መልኩ በትኖ መፈተሽ (unpack) እና አስማምቶ ስራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል።

***የሰነ ህዝብ ትሩፋት*** (demographic dividend)፡ ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ በማደግ ላይ የሚገኙ ሃገሮች በከፍተኛ የህዝብ ብዛት እድገት የመፈተናቸውን ያክል፣ ልዩ ተጠቃሚነት ሊሰጣቸው የሚችል እድልም አላቸው። የዚህም ዋነኛ ምክንያት፣ ካደጉት ሃገሮች በተቃራኒው፣ የህዝባቸው አብዛኛው ክፍል አምራች በሆነው የእድሜ ክልል ውስጥ መገኘቱ ነው። ለምሳሌም ያህል፣ በሃገራችን ውስጥ እ.አ.አ በ2018 ከነበረው አጠቃላይ የህዝብ ብዛት ውስጥ ወደ 39 ሚሊዮን የሚጠጋው ከ15 እስከ 34 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ይኸው ቁጥር እ.አ.አ በ2037 ወደ ሃምሳ ሚሊዮን ከፍ ይላል።

በተለያዩ ሃገራዊ እና አህጉራዊ የልማት ሰነዶች እንደተጠቀሰው፣ ለዚህ በከፍተኛ ቁጥር እያደገ ለሚሄድ የህብረተሰብ ክፍል የሥራ ዕድል መፍጠር የሁሉም የአፍሪካ ሃገሮች ዓብይ ፈተና እንደሚሆን ይታመናል። በሌላ በኩል ግን፣ ይህንን ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ወጣት እና አምራች የህብረተሰብ ክፍል በአግባቡ በማበልፀግ ወደ ምርታማ የሰው ሃይልነት መቀየር ከተቻለ ሃገሪቱን ወደ ከፍተኛ እድገት ለማሸጋገር ታላቅ አጋዥ ኃይል

[38] በዚህ ላይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት https://teifaiq.com/2020/09/07/repi-waste-to-energy-plant-sunk-misguided/ ይግቡ።

ሊሆን እንደሚችል ይታመናል። ለዚህም፣ ወጣቱን ትውልድ ዘመኑ ከሚፈጥረው ዕውቀት እና ቴክኖሎጂ ጋር ከመደበኛው ትምህርቱ ጎን ለጎን አንዲተዋወቅ ማድረግ እና የመፍትሔ ፈጣሪነት ክህሎቱን ማዳበር ያስፈልጋል። ይህንን በማድረግ፣ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በማደግ ላይ ያሉ ሃገሮች ከፈጣን የህዝብ ብዛት እድገት ጋር ሊመጣ የሚችለውን ፈተና ከፍተኛ ትሩፋት ሊፈጥሩ ወደሚችሉ እድሎች መቀየር ይችላሉ።

***ዓይነታዊ የለውጥ መሠረተ ልማት*** (Transformational infrastructure)፡ የአፍሪካ ሃገሮች ኢኮኖሚ ላይ የተካሄዱ በርካታ ጥናቶች እንደሚያመላክቱት፣ በአብዛኞቹ የአፍሪካ ሃገሮች ውስጥ ጎልቶ የሚታየው የመሠረተ ልማት ክፍተት ለብዙዎቹ የኢኮኖሚ ዕድገት ደካማነት ዋነኛ ምክንያት ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ባላፉት ጥቂት ዓስርተ ዓመታት እጅግ ፈጣን በሆነ ሁኔታ እየበለፀገ ከመጣው የዘላቂ መሠረተ ልማት ግንባታ ዕውቀት እና ቴክኖሎጂ አኳያ ሲታይ፣ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሃገሮች ወደ ኋላ መቅረት እንደ መልካም አጋጣሚ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ምክንያቱም እነኚህ ሃገሮች የሚያስፈልጓቸውን ማናቸውም መሠረተ ልማቶች ልማዳዊ (conventional) በሆነው እና ሃብት አባካኝ እና ኢዘላቂ (unsustainable) በሆነ የግንባታ መንገድ ከማልማት ይልቅ፣ የረጂም ዘመን አዋጪነታቸው እና ዘላቂነታቸው በተረጋገጠ እውቀት እና ቴክኖሎጂ ላይ በመገንባት አካታች እና ዘላቂ ልማትን ማሳካት ይችላሉ።

ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ከሚያስችሉ የዕውቀት መሳሪያዎች አንዱ እና ዋነኛው የማንኛውንም መሠረተ ልማት ሙሉ የህልውና ዑደት የሚሸፍን እቅድ አወጣጥ እና ሥራ አመራር (life-cycle management) መርህን መተግበር ይሆናል። ዓይነታዊ የለውጥ መሰረተ ልማት ግንባታ፣ ሃገሮች በመሰረተ ልማት ላይ ከሚያውሉት መዋዕለ ንዋይ ማግኘት የሚገባቸውን ሁለንተናዊ የኢኮኖሚ ጥቅም ከማረጋገጡም በላይ የልማቱን አካታችነትም ያረጋግጣል። በተለያዩ ጥናቶች እና በተግባርም እንደተረጋገጠው፣ ማንኛውም የመሰረተ ልማት ከዕቅድ ነደፋው ጀምሮ አስከ ግንባታው ፍፃሜ ድረስ የሚጠቀመው ዘዴ መሰረተ ልማቱ ተግባር ላይ ሲውል የሚኖረውን አካታችነትም ይወስነዋል። ከዚህም በተጨማሪ፣ ዓይነታዊ የመሰረተ ልማት ግንባታ መርሆዎችን መከተል እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሃገሮች የሚኖርዋቸውን በኪሳራ የታጠሩ ንብረቶች (stranded assets) ቁጥር ለመቀነስ ያስችላቸዋል።

## የከፍል ሰባት ቁልፍ ሐሳቦች

i. በአንድ ሃገር የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ሥርዓት መካከል ጥብቅ ትስስር መኖሩ በዘርፉ ቀደምት ከሚባለው ከካርል ማርክስ ጀምሮ የነበሩ ዕውቅ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ምሁራን አበክረው ያስገነዘቡት ጉዳይ ነው። ከዚህም የተነሳ፣ ባንድ ሃገር የፖለቲካ ሁኔታ ላይ የሚደረግ የፖለቲካ ምልከታ ኢኮኖሚውን ሳያካትት የተሟላ ሊሆን አይችልም። ኢትዮጵያን ለማሻገር የሚደረገው ጥረትም ፖለቲካውን ከኢኮኖሚው ጋር አስተሳስሮ መመልከት ይጠይቃል።

ii. ዛሬ ባለው እጅግ የተሳሰረ የኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ፣ ያንድን ሃገር የልማት እና ዕድገት ፈተናዎች ከዓለም አቀፋዊው ሁኔታ ነጥሎ ማየት የማይቻል ነው። በመሆኑም፣ አብዛኞቹ በማደግ ላይ ያሉ ሃገሮች ዋነኛ የልማት እና ዕድገት ፈተናዎቻቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚታዩ አበይት ፈተናዎች ጋር በጥብቅ የተሳሰሩ ናቸው። ስለዚህም፣ በቀዳሚነት አሁን በምንገኝበት ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን በማንኛውም ሃገር የኢኮኖሚ እድገት እና ልማት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖዎች ሊያሳድሩ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱትን ዓለም አቀፋዊ ወሳኝ ክስተቶች ከሃገራችን ልዩ ሁኔታ ጋር አዛምዶ መመልከት ያስፈልጋል።

iii. በዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ የሳይንቲስቶች (International Panel on Climate Change) ቡድን ጥናት መሰረት፣ የዓለማችን ሙቀት መጠን እ.አ.አ. በ1900 ከነበረበት በሁለት ዲግሪ ሴንቲግሬድ ከጨመረ ተመልሶ ሊተካ የማይችል (irreversible) ከፍተኛ የተፈጥሮ አካባቢ ውድመት ሊያደርስ እንደሚችል ተረጋግጧል።

iv. እስካሁን ድረስ በተፈጠረው የዓለም የከባቢ አየር ሙቀት መጨመር የተነሳ ሃገራችንን ጨምሮ በርካታ ሃገሮች ተለዋዋጭ ለሆነ የከባቢ አየር ሁኔታ መለዋወጥ (climate variability) በመጋለጥ ላይ ይገኛሉ። በመሆኑም፣ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሃገሮች የሚያወጧቸው ብሔራዊም ሆነ የዘርፍ የልማት ፖሊሲዎች ለአየር ንብረት ለውጥ ተስማሚ (climate resilient) የሆነ እድገት ለማምጣት በሚያስችል መንገድ መቀረጽ እና መተግበራቸው አካታች እና ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ በጣም አስፈላጊ ነው።

v. የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም ባወጣው የ2020 የሰብዓዊ ልማት ዕድገት ሪፖርት መሰረት ኢትዮጵያ ባሁኑ ወቅት አላት ተብሎ ከሚገመተው ታዳሽ የተፈጥሮ ሃብት አቅም (bio-capacity) 99.7% በመጠቀም ላይ ትገኛለች። ይህ የሚያመላክተው የሃገሪቱ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃላይ የመሸከም አቅምን ሙሉ ለሙሉ በመጠቀማችን፣ ተጨማሪ ጫና ለማስተናገድ ያለ ቀሪ አቅም ዜሮ መሆኑን ነው።

vi. ስለዚህም፣ ሃገሪቱ የምትተገብራቸው የልማት እቅዶች በሙሉ፣ የሃገሪቱን የተፈጥሮ ሃብት መሰረት (ecological foundation) ይበልጥ የሚያጠናክሩ፣ ምርታማ የሆነ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምን (resource efficiency) የሚያረጋግጡ፣ እና የሃገሪቱን ብዝሐ ህይወት የሚያበራክቱ ሊሆኑ ይገባል።

vii. ከሃያኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አንስቶ የዓለማችን የህዝብ ብዛት በብዙ እጥፍ አድጎ እ.ኤ.አ. በ2019 7.7 ቢሊዮን ሲደርስ፣ ይኸው ቁጥር እ.አ.አ. በ2030 8.5 ቢሊዮን እንዲሁም እ.ኤ.አ. በ2050 ወደ 9.7 ቢሊዮን እንደሚደርስ ተገምቷል። በተመሳሳዩ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛት እ.አ.አ. በ 2017፣ 105 ሚሊዮን እንደነበረ የሚገመት ሲሆን፣ ይህ ቁጥር እ.አ.አ. በ 2050 190 ሚሊዮን እና እ.ኤ.አ. በ 2100 ደግሞ 250 ሚሊዮን እንደሚደርስ ተገምቷል። ይህንን ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር እድገት ግምት ውስጥ ያስገባ የልማት ራዕይ ማበልጸግ የሃገሪቱን ልማት ዘላቂነት ለማረጋገጥ ወሳኝ ነው።

viii. ሃገራችን ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ በማደግ ላይ የሚገኙ ሃገሮች ያለፉት ሶስት የኢንዱስትሪ አብዮቶች በተሳታፊነት ሳይሆን በበዪ ተመልካችነት አሳልፈውታል። በአሁኑ ወቅት ዓለማችን የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ዋነኛ መለያ ወደሆነው አራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት በመገስገስ ላይ ይገኛል።

ix. ሃገራችን ኢትዮጵያ ከዚህ ኢንዱስትሪ አብዮት በዪ ተመልካችነት እንድትድን ከተፈለገ የትኛውንም የኢኮኖሚ ዘርፍ ለማሳደግ የሚወጡ ፖሊሲዎች እና ስልቶች፣ የአራተኛውን የኢንዱስትሪ አብዮት ፈተናዎችን በሚቀንስ እና እድሎቹን በሚያሰፋ መልኩ ሊቀረጹ እና ሊተገበሩ ይገባል።

x. በዓለም አቀፍ የገንዘብ፣ የፋይናንስ እና የንግድ ተቋማት አማካኝነት የተራመደው የኢኮኖሚ ሉላዊነት በአብዛኛው የበለጸጉ ሃገሮችን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ ተቀርጾ የተተገበረ በመሆኑ በማደግ ላይ የሚገኙ ሃገሮችን ለከፍተኛ ቀውስ ዳርጓቸዋል። ይህ አካሄድ አሁንም ሰወር ባለ (subtle) መልኩ የቀጠለ ሲሆን ከመረጃ እና ተግባቦት ቴክኖሎጂ እድገት ጋር ተያይዞ የመጣው የዕውቀት እና መረጃ ሉላዊነትም ተጨምሮበታል።

xi. እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሃገሮች የኢኮኖሚ ሉላዊነት ሊያስከትል የሚችለውን ጎጂ ተጽእኖ ከመቋቋም ባሻገር ከዕውቀት እና መረጃ ሉላዊነት የሚገኘውን መልካም እድሎች ለሃገሮቻቸው አካታች እና ዘላቂ ልማት እንዲያገለግሉ የሚያስችሉ ብልህነት ላይ የተመሰረቱ ፖሊሲዎችን (smart policies) መተግበር ይኖርባቸዋል።

xii. በአንድ ታዋቂ ፓን አፍሪካዊ ምሁር እንደተባለው፣ ብዙዎቹ የአፍሪካ ሃገሮች የሚያራምዷቸው የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ከሃገራዊ እውነታ እና ፍላጎት ጋር ያልተጣጣሙ በመሆናቸው በምትሃታዊ የኢኮኖሚ ፍልስፍና (Voodoo economics) የተቃኙ አስመስሏቸዋል ። ከዚህ አይነት አዙሪት ለመውጣት፣ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሃገሮች፣ ሃገራዊውን ፍላጎቶች እና ሃብቶች ከዓለም አቀፋዊው እድሎች እና ፈተናዎች ጋር በማጣጣም የህዝቦችን መሰረታዊ የኑሮ

ዋስትና የሚያረጋግጡ የሁለንተናዊ ደህንነት ኢኮኖሚ (Wellebing economy) ፖሊሲዎችን ለመቅረጽና ለመተግበር መጣር ይኖርባቸዋል።

xiii. የ ‘ምትሃታዊ የኢኮኖሚ ፖሊሲ’ ሌላው መገለጫው ተግባራዊነታቸው በአብዛኛው አጠያያቂ የሆኑ ዓመታዊ፣ የአምስት ዐመት እና አንዳንድ ጊዜም የአስር ዓመት እቅድ የሚመስሉ ‘ያልታቀዱ እቅዶችን’ (unplanned planning) ማውጣታቸው ነው። ይህም፣ ከፍተኛ ለሆነ የሃብት ብክነት እንዲጋለጡ አድርጓቸዋል።

xiv. እነኚህን ችግሮች ለማወስገድ፣ ከላይ ወደ ታች የሚወርድ አመላካች ዕቅድን (indicative planning) ከታች ወደላይ ከሚመጣብ እና ህዝብን ካካተተ የአፈጻጸም ዕቅድ (operational planning) ጋር ማዋሃድ አካታች እና ዘላቂ የሆነ ልማት ለማምጣት እጅግ አስፈላጊ ነው። እንዲህ ዓይነቱ የዕቅድ አወጣጥ እና አፈጻጸም ‘የሸመና እቅድ’ (discursive planning) ተብሎ ይታወቃል።

xv. አጠቃላይ የመልካም አስተዳደር (good governance) እጦት፣ ኢትዮጵያን ጨምሮ፣ የብዙዎቹ በማደግ ላይ ያሉ ሃገሮች ችግር መሆኑ ተደጋግሞ የተነገረ ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አካታች እና ዘላቂ ልማትን ለማምጣት ተጨማሪ የልማት መልካም አስተዳደር እርምጃዎችን መመልከት ተገቢ ይሆናል።

xvi. ለዚህም የመጀመሪያው መነሻ፣ የሃገሪቱ የልማት ጥረት መሰረታዊ ግብ፣ ጥቅል ሃገራዊ ምርትን (Gross Doemstic Product (GDP)) እና የነፍስ ወከፍ ገቢን (per capita income) ከማሳደግ ባሻገር፣ የህዝቦችን ሁለንተናዊ የኑሮ ደህንነት (wellbeing) ማረጋገጥ ሊሆን ይገባዋል።

xvii. እንዲህ ዓይነቱ የልማት አስተዳደር፣ በተወሰኑ ከተሞች አካባቢ ከሚከማቹ የኢንዱስትሪ እና ልማት ማዕከሎች ባሻገር ለበርካቶች የስራ ዕድል እና የኑሮ ዋስትና ሊሰጡ የሚችሉ እና ከየአካባቢው የተፈጥሮ ሃብት እና መሰረታዊ ፍላጎት ጋር የተስማሙ፣ ያልተከማቹ፣ ነገር ግን እርስ በእርስ የተሳሰሩ የኢኮኖሚ መረቦች (distributed economy networks) እንዲስፋፉ ያደርጋል።

xviii. ይህንን በማድረግም፣ ፍትሃዊ የሆነ የልማት ተደራሽነትን ከማረጋገጥም በላይ በየአካባቢው ባለ የተፈጥሮ ሃብት ላይ የሚደርሱ የልማት ተጽእኖዎችን ባካባቢው የተፈጥሮ ሃብት የመሸከም እና የማዋሃድ አቅም (carrying and assimilation capacity) ከልል እንዲስተናገድ ማድረግ ይቻላል።

xix. የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ኢኮኖሚ ዋነኛው መለያ ከምንግዜውም በላይ በዕውቀት እና መረጃ የበላይነት የሚወሰን መሆኑ ነው። በእንዲህ ዓይነት ኢኮኖሚ ውስጥ አሸናፊ ሆኖ ለመገኘት ለዘመኑ የሚመጥን ክህሎትን ያለማቋረጥ ማዳበር እና ማበልጸግ ያስፈልጋል። ይህም፣ በመደበኛው ትምህርት የምክንያታዊነት አስተሳሰብን (critical thinking) እንዲያዳብሩ ማድረግ እና በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍም በምህዳራዊ አስተሳሰብ (systems thinking) ላይ የተመረኮዙ መፍትሔዎችን ለማፍለቅ የሚያስችላቸውን ክህሎት እንዲያዳብሩ ማድረግ ተገቢ ነው።

xx. ኢትዮጵያ ሃገራችን በዓለም ውስጥ ከሚገኙ በጣም ጥቂት ከፍተኛ የተፈጥሮአዊ ምህዳር፣ የእንስሳት እና የዕፅዋት ሃብት ብዝሃነት ከሚታይባቸው ሃገሮች ውስጥ ትመደባለች። እንዲህ ዓይነቱ ዘርፈ ብዙ የሆነ የብዝሃነት ሃብት የሃገሪቱ የተፈጥሮ ሃብት መሰረት ከፍተኛ የማገገም አቅም (resilience) እንዲኖረው ያደርገዋል።

xxi. ስለዚህም፣ የማናቸውም የልማት ፍላጎታችን መሟላት ዋነኛ መሰረት የሆነውን የተፈጥሮ አካባቢያችንን መንከባከብ እና ማልማት ከህጻንነት ጀምሮ የማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ባህል እንዲሆን ማድረግ የሁሉንም ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ አካታች እና ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ ዋነኛው ዋስትናችን ነው።

xxii. ኢትዮጵያን ጨምሮ፣ ያብዛኞቹ የአፍሪካ ሃገሮች ፈተና ከምዕራባዊው ዓለም የሚጫንባቸውን ማንኛቸውም አስተሳሰቦች፣ ልማዶች፣ እና ቴክኖሎጂዎችን ያለአንዳች ሃገራዊ ምልከታ እና ለውጥ (adaptation) እንዳሉ መቀበላቸው እና ለመጠቀም መሞከራቸው ነው። በአራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ዘመን የተዛቡ የቴክኖሎጂ መረጣ እና ሽግግር ውሳኔዎች ከፍተኛ ዋጋ ከማስከፈላቸውም በላይ የሃገሪቱን ዘላቂ ልማት እድሎች ሊያጠቡ ይችላሉ።

xxiii. ይህን መሰል አደጋዎች ለመቀነስ እና ለማስወገድ፣ ወደእኛ የሚጎርፉ ማንኛውንም የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በዕውቀት ላይ በተመረኮዘ የዓይነታዊ እመርታ መርሆዎች መሰረት ማንኛውንም ቴክኖሎጂን ለሃገሪቱ ልዩ ሁኔታ እና ዘላቂ ልማት ግቦች በሚስማማ መልኩ በትኖ መፈተሽ (unpack) እና አስማምቶ ስራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል።

xxiv. ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ በማደግ ላይ የሚገኙ ሃገሮች በከፍተኛ የህዝብ ብዛት እድገት የመፈተናቸውን ያክል፣ ልዩ ትሩፋት ሊሰጣቸው የሚያስችል እድልም አላቸው። የዚህም ዋነኛ ምክንያት፣ ካደጉት ሃገሮች በተቃራኒው፣ የህዝባቸው አብዛኛው ክፍል አምራች በሆነው የእድሜ ክልል ውስጥ መገኘቱ ነው። ይህንን ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ወጣት እና አምራች የህብረተሰብ ክፍል በአግባቡ በማበልፀግ ወደ ምርታማ የሰው ሃይልነት መቀየር ከተቻለ ሃገሪቱን ወደ ከፍተኛ እድገት ለማሸጋገር ታላቅ አጋዥ ኃይል ሊሆን እንደሚችል ይታመናል።

xxv. ባላፉት ጥቂት ዓስርተ ዓመታት እጅግ ፈጣን በሆነ ሁኔታ እየበለፀገ ከመጣው የዘላቂ መሠረተ ልማት ግንባታ ዕውቀት እና ቴክኖሎጂ አኳያ ሲታይ፣ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሃገሮች ወደ ኋላ መቅረት እንደ መልካም አጋጣሚ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ምክንያቱም እነኚህ ሃገሮች የሚያስፈልጓቸውን ማናቸውም መሠረተ ልማቶች ልማዳዊ (conventional) በሆነው እና ሃብት አባካኝ እና ኢዘላቂ (unsustainable) በሆነ የግንባታ መንገድ ከማልማት ይልቅ፣ የረጂም ዘመን አዋጪነታቸው እና ዘላቂነታቸው በተረጋገጠ ቴክኖሎጂ ላይ በመገንባት አካታች እና ዘላቂ ልማትን ማሳካት ይችላሉ።

xxvi. ዓይነታዊ የለውጥ መስረተ ልማት ግንባታ፣ ሃገሮች በመሰረተ ልማት ላይ ከሚያውሉት መዋዕለ ንዋይ ማግኘት የሚገባቸውን ሁለንተናዊ የኢኮኖሚ ጥቅም ከማረጋገጡም በላይ የልማቱን አካታችነት በማረጋገጥ ረገድም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በተለያዩ ጥናቶች እና በተግባርም እንደተረጋገጠው፣ ማንኛውም የመስረተ ልማት ከዕቅድ ነደፋው ጀምሮ አስከ ግንባታው ፍፃሜ ድረስ የሚጠቀመው ዘዴ መሰረተ ልማቱ ተግባር ላይ ሲውል የሚኖረውን አካታችነት ይወስነዋል። ከዚህም በተጨማሪ፣ ዓይነታዊ የመሰረተ ልማት ግንባታ መርሆዎችን መከተል እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሃገሮች የሚኖርዋቸውን በኪሳራ የታጠሩ ንብረቶች (stranded assets) ቁጥር ለመቀነስ ያስችላቸዋል።

# ማጠቃለያ

ሃገራችን ኢትዮጵያ፣ የበርካታ ምዕተ ዓመታት የተጻፈ ታሪክ ካላቸው ጥቂት የአፍሪካ ሃገሮች ውስጥ አንዷ መሆና ይነገራል። ለዚህም፣ በበርካታ ግንባር ቀደም ዩኒቨርሲቲዎች እና ዓለም አቀፍ የታሪክ ጥናት ማእከሎች የሚካሄዱ ጥናቶች እና የሚገኙ የታሪክ ሰነዶች እንደ ማረጋገጫ ይቀርባሉ። ይህ እንዳለ ሆኖ፣ በዘመናዊ የሃገረ መንግሥት ምስረታ ሂደት ያላት ታሪክ ነጻነታቸውን በቅርቡ ከተቀዳጁ ሌሎች የአፍሪካ ሃገሮች ብዙም የተለየ አይደለም። በቅርቡ የሃገራችን የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ በለውጥ ቀስቃሽነት የሚጠቀሰው የ1953 መፈንቅለ መንግስት ሙከራ በርካታ የአፍሪካ ሃገሮች ከቅኝ ተገዢነት ነጻ ከወጡበት ዓመት ጋር መገጣጠሙ ከላይ የተጠቀሰውን ምልከታ ያጠናክረዋል። እንዳብዛኞቹ የአፍሪካ ሃገሮች፣ ኢትዮጵያም ባለፉት ስልሳ ዓመታት በተለያዩ የፖለቲካ ሙከራዎች እና ሂደቶች ውስጥ አልፋለች። ነገር ግን፣ እነኚህ ከፍተኛ መስዋእትነት የተከፈለባቸው ሙከራዎች እና ሂደቶች የመላ ህዝቦቻችን ተቀባይነት ወዳለው ሃገረ መንግሥት ምስረታ ሊያሸጋግሯት አልቻሉም። ዛሬ ሃገሪቱ ካሉባት ውስብስብ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ፣ ከባቢያዊ፣ ፖለቲካዊ እና ንፍቀ ከባቢያዊ ፈተናዎች አኳያ ሌላ ያልተሳካ የፖለቲካ ሙከራ የመሻገር እድሏ እጅግ የመነመነ መሆኑን መገመት ይቻላል። ስለሆነም፣ ከፊት ለፊታችን ያለውን የለውጥ እና ሽግግር ዕድል የተሳካ ለማድረግ ሁሉም ወገን የሚቻለውን ርብርብ ማድረግ ይጠበቅበታል።

ይህ ጥረት የተሳካ እንዲሆን፣ የችግሮቻቻን መሰረታዊ ምንጮች ባግባቡ መረዳት እና ባላፉት ስልሳ ዓመታት ካለፍንባቸው የፖለቲካ ምስቅልቅሎች ልንማር የሚገባንን ትምህርት መቅሰም ይኖርብናል። ከዚህ በተጨማሪም፣ የምንገኝበትን የሃያ አንደኛውን ክፍለ ዘመን ውስብስብ ፈተናዎች እና እድሎች ጠንቅቆ መረዳት እና ፈተናዎቹ ሊያስከትሉ የሚችሉትን ጉዳት ለመቀነስ እና እድሎቹን ባግባቡ ለመጠቀም የሚያስችሉንን አቅጣጫዎች መተለም ይገባል። ይህንን ሁሉ ለማድረግ፣ ጊዜውን በሚመጥን እውቀት መታጠቅ እና መመራት አስፈላጊ ነው። በዚህ ረገድ፣ ውስብስብ ችግሮችን ለመተንተን እና መፍትሄ ለመሻት ኢጋዥ በሆነው ምህዳራዊ አስተሳሰብ መመራት ከፍተኛ ጠቀሜታ አንደሚኖረው ይታመናል። በዚህ መጽሃፍ፣ የምህዳራዊ አስተሳሰብ ታሪካዊ አመጣጡን እና መስረታዊ መርሆዎቹን ከማቅረብ ባሻገር የኢትዮጵያን ፖለቲካ መሰረታዊ ህመሞች ከዚሁ አኳያ ለመተንተን እና አመላካች መፍትሄ ለመጠቆም ተሞክሯል። ምንም እንኳን፣ የቀረቡትን ሃሳቦች የተሟላ ለማድረግ ጥረት የተደረገ ቢሆንም፣ ትንተናዎቹም ሆነ የመፍትሄ ሃሳቦቹ ከአመላካችነት የዘለለ ድርሻ እንዳይሰጣቸው ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። በመሆኑም፣ በመጽሃፉ ውስጥ የቀረቡትን ሃሳቦች ይበልጥ መፈተሽ እና ተለዋዋጭ ከሆነው ሃገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ እውነታ ጋር አዛምዶ መተንተን ከሁሉም ወገን የሚጠበቅ ድርሻ ይሆናል።

የፖለቲካችንን ህመሞች ለማከም የምናደርገው ጥረት በኢኮኖሚው መስክ ሊመጣ በሚገባው ለውጥ ካልታገዘ ውጤታማነቱ አጠራጣሪ በመሆኑ፣ የመጽሃፉ የመጨረሻ ክፍል በሃገራችን ውስጥ አካታች እና ዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ መታየት የሚገባቸውን አበይት ነጥቦች ተመልክቷል። ይህም፣ ፖለቲካችንን ጤናማ ከማድረግ ባሻገር በከፍተኛ መጠን እያደገ ላለው ወጣት የሥራ እድል ለመፍጠር እና የአጠቃላዩን ህዝብ ማህበራዊ ሁለንተናዊ ደህንነት ለማረጋገጥ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዝባል። ይህንንም ለማሳካት፣ የአጠቃላይ ህልውናችን ዋነኛው መሰረት የሆነውን የተፈጥሮ አካባቢያችንን መንከባከብ እና የዚህ ምዕተ ዓመት ወሳኝ ገጽታ ከሆነው ከአራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ጋር ተያይዘው የሚመጡ ፈተናዎችን ለመቋቋም እና እድሎቹንም ለመጠቀም ዝግጁ መሆንን ይጠይቃል። በዚህ ረገድ፣ በተለይ ወጣቱ ትውልድ ጊዜው በሚጠይቀው እውቀት እና ክህሎት ራሱን በማስታጠቅ የራሱንም ሆነ የሀገሪቱን የወደፊት እጣ ፈንታ የመወሰን ታላቅ ድርሻ እና ሃላፊነት እንዳለበት መገንዘብ ይኖርበታል። ለዚህም፣ ከምህዳራዊ አስተሳሰብ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን እና ፈጣን በሆነ ሁኔታ እየበለጸጉ በመሄድ ላይ ያሉ አስተሳሰቦችን ከሃገራዊው ፍላጎት እና ሁኔታ ጋር በማጣጣም ለመተግበር መጣር ይኖርበታል።

በመጨረሻም፣ መጪው ሃገራዊ ምርጫ በሃገራችን ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በህዝብ ዘንድ የተሻለ ይሁንታ ያገኘ ዴሞክራሲያዊ የመንግሥት ሥርዓት ለመመስረት የሚያስችል መልካም አጋጣሚ እንደሆነ ይነገራል። ይህ እንዲሆን፣ ሁሉም የሃገራችን የፖለቲካ መሪዎች፣ ልሂቃን፣ ቀስቃሾች እና የሚዲያ ባለሙያዎች ምርጫው ነጻና ፍትሃዊ እንዲሆን ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። የምርጫው ውጤት ምንም ይሁን ምን፣ የዴሞክራሲያዊው ሥርዓት ምስረታ ጅማሮ በመሆኑ በተከታዮቹ ዓመታት በርካታ ቀሪ ስራዎች እንደሚኖሩ መታወቅ ይኖርበታል። በዚህ መጽሃፍ የተነሱት ሃሳቦች በመጪው ዓስርተ አመታቶች የሚጠብቁንን በርካታ የፖለቲካ እና የዘላቂ ልማት ስራዎች ከስሜታዊነት ይልቅ በፋና-ወጊ እና ሩቅ አሳቢ አመለካከት እንድንወጣ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚል እምነት አለኝ።

# ተጨማሪ ንባቦች


1. Bryan, B., Goodman, M., & Schaveling, J. (2006). Systeemdenken (Systems thinking) . Academic Service.
2. Central Statistical Agency. 2012. Population Projections for Ethiopia, 2007-2037. Addis Abeba
3. International Panel on Climate Change (IPCC). 2014. Climate change synthesis report. Geneva: IPCC. https://doi.org/10.1017/CBO9781107415416
4. International Resource Panel. (2019). Global resource outlook: Natural resources for the future we want. Nairobi: United Nations Environment Programme.
5. Koska, Bart. 1994. "Fuzzy Thinking: The New Science of Fuzzy Logic." London: Harper Collins Publishers.
6. Khun, Thomas. 1996. The Strcture of Scientific Revolutions. Chicago: University of Chicago.
7. Lazslo, E. 1991. The New Evolutionary Paradigm. New York: Gordon and Breach Science Publishers
8. Mebratu, D. 2004. Systems concept of sustainability and sustainable development. In G. Mudacumura, D. Mebratu & M.S. Haque (eds.), Sustinable development policy and admisnitration. New York: Taylor and Francis.
9. Mebratu, D. & Swilling, M. (eds). 2019. Transformational Infrastructure for Development of a Wellbeing Economy in Africa. Stellenbosch: African Sun Media.
10. Oxfam. (2016). An economy for 1%: How privilege and power in the economy drive extreme inequality and how this can be stopped. London: Oxfam.
11. Piketty, T. (2014). Capital in the twenty-first century. Cambridge, MA: The Belknap Press of Harvard University Press.
12. Senge, Peter M. 1990. The Fifth Discipline: the art and practice of the learning organization. New York: Currency

United Nations. 2019. World Population Prospects 2019. New York: United Nations.
13. United Nations Development Program (UNDP). 2020. Human Development Report 2020. New York: United Nations
14. Weinberg, Gerald M. 1975. "An Introduction to General Systems Thinking." New York: Wiley-Interscience Publication.

ፕሮፌሰር ደስታ መብራቱ፣ በኬሚካል፣ ኢንዱስትሪ እና አካባቢ ምህንድስና ከፍተኛ ትምህርታቸውን የተከታተሉ ሲሆን በስራው ዓለም፣ ከሰላሳ ሁለት ዓመት በላይ በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ ሰርተዋል። ከዚህ ውስጥ ለአስራ ሶስት አመታት በተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም (UNEP) ውስጥ የድርጅቱ የአፍሪካ ምክትል ዳይሬክተር መሆንን ጨምሮ በልዩ ልዩ ሃላፊነት ሰርተዋል። ፕሮፌሰር ደስታ በተለይ በዘላቂነት ሳይንስ እና ዘላቂ የኢንዱስትሪ ልማት ላይ ያተኮሩ በርካታ የምርምር ስራዎች አሳትመዋል። ከታህሳስ 2009 ጀምሮ፣ ደቡብ አፍሪካ በሚገኘው ስታለንቦሽ ዩኒቨርሲቲ (Stellenbosch University) ፕሮፌሰር ሲሆኑ በአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩትም ያስተምራሉ። ቀደም ሲል በሃገር ውስጥ የሙያ ህይወታቸው ከሰሩባቸው መሥሪያ ቤቶች በተጨማሪ፣ ፕሮፈሰር ደስታ የኢትዮጵያ የኬሚስትሪ ባለሙያዎች ማህበር እና የኢትዮጵያ የኬሚካል መሐንዲሶች ማህበር ፕሬዚዳንት እንዲሁም የለም ኢትዮጵያ የአካባቢ እና ልማት ማህበር መስራች ምክትል ፕሬዚዳንት በመሆን አገልግለዋል። ፕሮፌሰር ደስታ መብራቱ የአፍሪካ ሳይንስ አካዳሚ (African Academy of Sciences) እና በተለያዩ ሃገሮች የሚገኙ ቀደምት የሳይንስ ጥናት ተቋሞች አባል (Fellow) ናቸው።

**ምህዳራዊ አስተሳሰብ፣ ለዘላቂ ሃገራዊ መፍትሔ**

በፕሮፌስር ደስታ መብራቱ የቀረበው መጽሀፍ በአጽንኦት የሚነበብ፣ የሚጠናና፣ መተግበር ያለበት ነዉ ብዬ አስባለሁ። ለዘመናት ተብትቦ የያዘን፣ ነጭ -ጥቁር፤ ግራ-ቀኝ፣ ጠባብ-ትምክህት፣ ላብአደር-ከበርቴ፤ ወዘተ ብዙ ግራጫዎች መኖራቸውን አንዳናይ አውሮን፤ ያሰከፈለንን ዋጋ መገመት ያስቸግራል። የኔ ትውልድ የዚህ ሸፋፋ አመለካከት ሰለባ ነዉ። ምህዳራዊ አስተሳሰብን ተቀብሎ፣ ችግሮችንና ተግዳሮቶችን በሁለንተናዊ መርህ መመርመር፣ ከመዳህ ወደ መራመድ ያሻግራል። ለዚህ ፕሮፌስር ደስታ ባለውለታችን ነው።

**ፕሮፌስር ጌታቸው እንግዳ**፣ ቺንግዋ ዩኒቨርስቲ፣ ቻይና

ወጣቶች፣ ፖለቲከኞች፣ የፖለቲካ ተንታኞች፣ እና በማንኛውም የስልጣንና የሃላፊነት ደረጃ ላይ ያሉ ግለሰቦች ከመጽሐፉ በርካታ ቁምነገሮችን እንደሚያገኙ እገምታለሁ። በተለይ ሃገራችን ባሁኑ ጊዜ ያለችበትን የተወሳሰበ ሁኔታ አቅጣጫ ማስያዝ ሃላፊነቱ ለተጣለባቸው ወገኖች ሁሌ ከስሜትና ከምኞት በመራቅ እና ምህዳራዊ አስተሳሰብን በመጠቀም መፍትሄ እንዲያገኙ የፕሮፌሰር ደስታ መብራቱ መጽሐፍ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

**አቶ ብርሐነ መዋ**፣ ሜሪላንድ፣ አሜሪካ

እውቁ የኢኮኖሚክስ ባለሙያ ዶ/ር እሸቱ ጮሌ በ1984 ባቀረበው አንድ ጥናታዊ ጽሁፍ፣ ሃገሪቱ ሌላ መልካም የለውጥ አጋጣሚ ላይ እንደምትገኝ አውስቶ ይህንን የለውጥ ዕድል ማበላሸት በታሪክ ታላቅ ተወቃሽ እንደሚያደርገን አስጠንቅቆ ነበር። ከሰላሳ ዓመታት በኋላ በሌላ የለውጥ አጋጣሚ ላይ ከተመሳሳይ ሃገራዊ ጥያቄዎች ጋር ተፋጠን እንገኛለን። ይህ መጽሐፍ ፊት ለፊታችን የተድቀኑብንን ፈተናዎች ለመሻገር ከሚኖረው አበርክቶት ባሻገር ለመጪው ትውልድም ታላቅ ትምህርታዊ ፋይዳ ይኖረዋል።

**ዶ/ር ጉልላት ከበደ**፣ ኒው ስኩል፣ አሜሪካ

ይህ መጽሐፍ ከተለመደው ወጣ ያለ ጭብጥ ይዞ መነሳቱ የመፅሀፉ አንዱ ፋና ወጊ ገፅታው ይመስለኛል። የተወሳሰቡና ሙያዊ የሆኑ የምህዳራዊ አስተሳሰብ አላባዊያንና ተግባራዊ አንድምታቸዉን በሃገራዊ ሁነቶች መመንዘሩና ቀላልና ጣፋጭ በሆነ አቀራረብ መቀመሩ ደራሲዉ ብዙ ትጋትን የጠየቁ ሰፊ ማብሰልሰልንና መብሰልሰልን ያካተቱ ረዣዥም የሃሳብና የምጥ ሌሊቶች እንደነበሩት ይጠቁማል።

**ዶ/ር ሰለሞን አበበ**፣ የተባበሩት መንግስታት አቶሚክ ኢነርጂ ተቋም

ይህ መጽሐፍ እጅግ በጣም የሚያሳስበንን የወቅቱን የሃገራችንን ጉዳይ እስከአሁን ድረስ ሲቀርቡ ከነበሩት ፖለቲካዊ አቀራረቦች ወጣ ባለ ሁኔታ አዲስ፣ ሁለንተናዊና ሳይንሳዊ በሆነ የአመለካከት ስልት (ምሕዳራዊ አስተሳሰብ) ትንታኔ የሚያቀርብ ነው። የመፍትሔ አቅጣጫዎቹ የተሳሳቱ አመለካከቶችን በአሳማኝና ሐቀኛ ምክንያቶች በመሞገትና ገንቢና አካታች የሆኑትን በማሳየት የቀረቡ ስለሆኑ ብዙዎችን ሊያግባቡ ይችላሉ የሚል ዕምነት አለኝ።

**በቀለ ባይሳ**፣ የምክር ሥራ ባለሙያ

ISBN 978-99944-3-160-1